መጽሐፈ ነገሥት - አንደኛ

አስተዋፅኦ

I. የሰሎሞን ዘመነ መንግሥት (1፥1—11፥43)
(ሀ) ሰሎሞን ተተኪ ሆኖ የዳዊትን ዙፋን ወረሰ (1፥1—2፥11)
(ለ) ሰሎሞን ዙፋኑን አደላድሎ ያዘ (2፥12-46)
(ሐ) የሰሎሞን ጥበብና አስተዳዳር (3፥1—4፥34)
(መ) የሰሎሞን ስኬታማነትና ዝና (5፥1—10፥29)
1. የመቅደሱ ሥራ ዝግጅት (5፥1-18)
2. የመቅደሱ ግንባታ (6፥1-38)
3. የሰሎሞን ቤተ መንግሥት ግንባታ (7፥1-12)
4. የቤተ መንግሥቱ ዕቃዎች (7፥13-15)
5. የቤተ መቅደሱ ምረቃ (8፥1-66)
6. የዳዊትን ኪዳን ማጽናት (9፥1-9)
7. የሰሎሞን ተግባርና ዝና (9፥10—10፥29)
(ሠ) የሰሎሞን አወዳደቅና ሞት (11፥1-43)
1. የሰሎሞን አሳፋሪ ድርብ ጋብቻና ባዕድ አምልኮ (11፥1-8)
2. እግዚአብሔር አስቀድሞ የተናገረው መከፋፈልን ያመጣው ፍርድ (11፥9-13)
3. እግዚአብሔር በሰሎሞን ላይ ጠላቶችን አስነሣበት (11፥14-28)
4. የአኪያ ትንቢት (11፥29-40)
5. የሰሎሞን ሞት (11፥41-43)

II. የመንግሥቱ መከፋፈል፣ እስራኤልና ይሁዳ (12፥1—22፥53)
(ሀ) የመከፈል ፍርድ ተፈጸመ (12፥1-24)
(ለ) የኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት (እስራኤል) (12፥25—14፥20)
(ሐ) የሮብዓም ዘመነ መንግሥት (ይሁዳ) (14፥21-31)
(መ) የአብያ ዘመነ መንግሥት (ይሁዳ) (15፥1-8)
(ሠ) የአሳ ዘመነ መንግሥት (ይሁዳ) (15፥9-24)
(ረ) የናዳብ ዘመነ መንግሥት (እስራኤል) (15፥25-31)
(ሰ) የባኦስ ዘመነ መንግሥት (እስራኤል) (15፥32—16፥7)
(ሸ) የኤላ ዘመነ መንግሥት (እስራኤል) (16፥8-14)
(ቀ) የዘምሪ ዘመነ መንግሥት (እስራኤል) (16፥15-20)
(በ) የዖምሪ ዘመነ መንግሥት (እስራኤል) (16፥21-28)
(ተ) የአክዓብ ዘመነ መንግሥት (እስራኤል) (16፥29—22፥40)
1. የአክዓብ ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ (16፥29-34)
2. አክዓብና ነቢዩ ኤልያስ (17፥1—19፥21)
3. አክዓብ ከሶርያ (ከአራም) ጋር ጦርነት መግጠሙ (20፥1-43)
4. አክዓብና የናቡቴ የወይን ተክል ቦታ (21፥1-29)
5. አክዓብ ለሞት ያደረሰውን ጦርነት ከሶርያ (ከአራም) ጋር ማድረጉ (22፥1-40)
(ቸ) የኢዮሣፍጥ ዘመነ መንግሥት (ይሁዳ) (22፥41-50)
(ኀ) የአካዝያስ ዘመነ መንግሥት (እስራኤል) (22፥51-53)

ጸሓፊው፤ ስሙ አልተገለጸም

የመጽሐፉ ዋና ሐሳብ፤ የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት

የተጻፈበት ዘመን፤ *ከ560—550 ዓ.ቅ.ክ. አካባቢ*

ታሪካዊ ዳራ

በመጽሐፈ ነገሥት አንደኛና ሁለተኛ የተጻፈው ታሪክ፣ ከመጽሐፈ ሳሙኤል አንደኛና ሁለተኛ ታሪክ የቀጠለ ነው። እነዚህ አራት መጻሕፍት በአንድ ላይ ተደምረው፣ የመላውን የእስራኤልንና የይሁዳን ነገሥታት ታሪክ ብጥር በማድረግ ይዘው ይገኛሉ (1050—586 ዓ.ቅ.ክ. አካባቢ)። መጽሐፈ ነገሥት አንደኛና ሁለተኛ የዘመናትን ቅደም ተከተል በመጠበቅ የዚህኑ ታሪክ አራት ምዕተ ዓመታት ይሸፍናሉ፤ ይኸውም ከንጉሥ ሰሎሞን ዘመን ጀምሮ (970 ዓ.ቅ.ክ.) እስከ የባቢሎን ምርኮ ድረስ ነው (586 ዓ.ቅ.ክ.)። መጽሐፈ ነገሥት አንደኛ ብቻውን 120 ዓመታትን ያካትታል፤ ይኸውም 40 የሰሎሞን ዘመነ መንግሥት (970—930 ዓ.ቅ.ክ.) እና መንግሥቱ ከተከፈለ በኋላ ያለውን 80 ዓመታት ያጠቃልላል (930—852 ዓ.ቅ.ክ. አካባቢ)።

ከመጀመሪያውኑ መጽሐፈ ነገሥት አንደኛና ሁለተኛ በብሉይ ኪዳን የዕብራይስጥ መጻሕፍት እንደ አንድ መጽሐፍ ይቈጠሩ ነበር፣ ስለዚህ ከጻፊው ማንነት አኳያ ሲታይ፣ እነዚህ ሁለቱ መጻሕፍት እንደ አንድ መጽሐፍ ሆነው ይታወቃሉ። በመጨረሻ ሰፍሮ የሚገኘው ታሪካዊ ሁኔታ (2ነገ 25፥27)፣ ንጉሥ ዮአኪን ከባቢሎን እስር ቤት ነጻ መውጣቱ ነው (560 ዓ.ቅ.ክ. አካባቢ)። ስለዚህ መጽሐፈ ነገሥት አንደኛና ሁለተኛ ተጠቃልለው ፍጻሜ ያገኙበት ዐሥርት ዓመት ከ560—550 ዓ.ቅ.ክ. ያለው ነው። የጸሐፊው ማንነት ባይጠቀስም እንኳ የእስራኤልንና የይሁዳን ነገሥታት ታሪክ፣ እግዚአብሔር ከዕብራውያን ጋር ከገባው ኪዳን አኳያ በመመልከት፣ በመንፈስ ተመርቶ የነቢይነትንም ጸጋ ተቀብሎ የተጻፈ የታሪክ ባለሙያ ሥራ መሆኑ ግልጽ ነው። ጸሐፌው በስም የሚታወቁ የተለያዩ የጽሑፍ ማስረጃዎችንም መጠቀሙ ግልጽ ነው፤ (1) "በሰሎሞን የታሪክ መጽሐፍ" (11፥41)፣ (2) "በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ" (ለምሳሌ 14፥19)፣ (3) "በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ (ለምሳሌ 14፥29)። እነዚህ የታሪክ ምንጮች የመንግሥት ታሪክ ጻሓፊ ያሰፈራቸው ሳይሆኑ፣ ነቢያት ራሳቸው የመዘገቧቸው ጽሑፎች ሳይሆኑ አይቀሩም፣ ከዚህም በላይ ይኸው ጸሓፊ ሌሎችን የነቢያት ጽሑፎች፣ ለምሳሌ በመጽሐፍ ዜና መዋዕል አንደኛ 29፥29 ላይ የተመለከቱትን ዐይነት ጽሑፎች ሳይጠቀም አልቀረም። ስለ እስራኤልና ስለ ይሁዳ ነገሥታት ታሪክ እጥር ምጥን ተደርጎ የተካተተውን ለማየት በገጽ 585 ላይ፣ "የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት" በጊዜ ቅደም ተከተል በሚል ርእስ የቀረበውም ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

ዐላማ

መጽሐፈ ነገሥት አንደኛና ሁለተኛ የተጻፉበት ዐላማ በባቢሎን ምርኮ የሚገኙት ዕብራውያን በነቢይነት ዐይን የታተመውን ታሪካቸውን እንዲያስተውሉት ለማድረግ ነው፤ ይኸውም በ930 ዓ.ቅ.ክ. መንግሥቱ ለምን እንደተከፈለ፣ በ722 ዓ.ቅ.ክ. ላይም የሰሜኑ መንግሥት እስራኤል ለምን እንደ ወደቀ፣ እንዲሁም በ586 ዓ.ቅ.ክ. ላይ የዳዊት መንግሥትና ኢየሩሳሌም ለምን እንደ ወደቁ ይረዱ ዘንድ ነው። የእስራኤልና የይሁዳ መከፋፈል፣ ነገሥታቱም ሆኑ በአጠቃላይ ሕዝቡ ጣዖትን ከማምለካቸውና በጽድቅ መንገድ ካለመሄዳቸው ጋር ቀጥታ የሆነ ግንኙነትና ይኸውም ያስከተለውን የማይቀር ውጤት ጸሐፊው በአጽንዖት ገልጾአል። በዚህም መሠረት ጸሐፊው የአንድን ንጉሥ የሥልጣን ዘመን መሳካትና አለመሳካት ለእግዚአብሔርና ለኪዳኑ ታማኝ ሆኖ ከመገኘቱ ወይም ካለመገኘቱ ጋር ያያይዘዋል። ለእግዚአብሔር አንድ ንጉሥ በፖለቲካ ረገድም ሆነ በምጣኔ ሀብት የተሳካለት ቢሆንም እንኳ፣ የእግዚአብሔርን ኪዳን እስካላከበረ ድረስ፣ ዋጋ ቢስ ነው ተብሎ ተፈርዶበታል። በነቢዩ አስተውሎት እንዲህ መቅረቡ ምርኮኞቹ እስከ ዘላለሙ ከጣዖት አምልኮ ተመልሰው፣ የሚመጡት ትውልዶች ሁሉ ልባቸውን ወደ እግዚአብሔር በማቅናት የእርሱን ትእዛዞች እንዲያከብሩ ነው።

ቅኝት

መጽሐፈ ነገሥት አንደኛ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፤ (1) የመጀመሪያው ክፍል የንጉሥ ሰሎሞንን ዘመነ መንግሥት ይገልጻል (ምዕ 1—11)፣ መግቢያ የሆኑት ምዕራፎች ሰሎሞን ንጉሥ የሆነበትን ሁኔታና (ምዕ 1—2)፣ ሕዝቡን ለማስተዳደር ይችል ዘንድ ጥበብን ለማግኘት ያቀረበውን ልመና (ምዕ 3) ያመለክታሉ። የሚቀጥሉት ሰባት ምዕራፎችም ሰሎሞን በዓለም ሁሉ የቱን ያህል ከፍ ከፍ እያለ እንደመጣና እስራኤልም በብልጽግና፣ በሰላም በጎይልና በክብር ምጥቀት ደረጃ ወደላይ እንደ ደረሰች ያመለክታሉ፤ ይህም ሁሉ እውን የሆነው በመጀመሪያዎቹ ሃያ የሰሎሞን የንግሥ ዓመታት ነው። በዚህ ጊዜ ሰሎሞን

በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስን ሠርቶ መረቀው (ምዕ 6፥6)። ምዕ 11 ሁለተኛውን ሃያ የሰሎሞንን የንግሥ ዓመታት የሚገልጽ ሲሆን፣ እነዚህም ዓመታት ሰሎሞን ቅጥ አጥቶ፣ በሚያሳፍር ሁኔታ አያሌ ሚስቶችን ያገባበትና ለጣዖታት የሰገደበት፣ የሕዝቡም መሠረታዊ ቅርስ የፈራረሰበት ዘመናት ናቸው። ሰሎሞን በሚሞትበት ጊዜ መንግሥቱ የሚከፈልበትና የሚወድቅበት ክፉ ዘር ተዘርቶ ነበር።

(2) ሁለተኛው ክፍል በሰሎሞን ልጅ በሮብዓም ዘመን፣ መንግሥቱ መከፈሉንና በሚቀጥሉት ሰማኒያ ዓመታት በሁለቱ መንግሥታት ላይ በየግላቸው በተከታታይ በነገሡት ነገሥታት ዘመን፣ በፖለቲካም ሆነ በመንፈሳዊ ረገድ ሁለቱም መንግሥታት የቱን ያህል እየዘቀጡ እንደመጡ ያመለክታል (ምዕ 12—22)። በዚህ በሁለተኛው የመጽሐፉ አጋማሽ ላይ የታወቁት ነገሥታትና ግለሰቦች በደቡብ መንግሥት ሮብዓም ሲሆን፣ በሰሜኑ መንግሥት ደግሞ ኢዮርብዓም፣ ንጉሥ አክዓብና ጨካኟ ሚስቱ ኤልዛቤል እንዲሁም ነቢዩ ኤልያስ ናቸው።

ልዩ ገጽታ

መጽሐፈ ነገሥት አንደኛን ልዩ የሚያደርጉት አራት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) የእግዚአብሔር ተወካዮች እንዲሁም የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት አፍ ሆነው የሚናገሩትን ነቢያት ያሳያል፤ ለምሳሌ አኪያ (11፥29-40፤14፥5-18)፣ ሳማያ (12፥22-24)፣ ሚክያስ (22፥8-28)፣ በተለይ ደግሞ ኤልያስ (ምዕ 17—19)። (2) በነገሥታቱ ታሪክ ውስጥ በትንቢትና በፍጻሜው ላይ አጽንዖት ያደርጋል። የተነገረው ትንቢትም የተፈጸመ መሆኑ ብዙ ጊዜ ተጽፎ ይገኛል (ለምሳሌ 2ሳሙ 7፥13 እና 1ነገ 8፥20፣ 11፥29-39 እና 12፥15፣ ምዕ 13 እና መጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ 23፥16-18)። (3) አያሌ የታወቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችንም አቅፎ ይገኛል፤ ለምሳሌ የሰሎሞን ጥበብ (ምዕ 3—4) የቤተ መቅደሱ መመረቅ (ምዕ 8)፣ ንግሥት ሳባ በኢየሩሳሌም ያደረገችው ጉብኝት (ምዕ 10) እንዲሁም የኤልያስ አገልግሎት በተለይም በቀርሜሎስ ተራራ በበኣል ካህናት ላይ ያሳየው ፉክክር (ምዕ 18)። (4) አንዳንድ ጊዜ የትረካ ሰንሰለቱን ለማየት አስቸጋሪ የሆነውን የእስራኤልንና የይሁዳን ነገሥታት ታሪክ ቅደም ተከተልን በመጠበቅ፣ ያለውን ታሪክ በስፋት አቅፎ ይገኛል። ይሁን እንጅ ይህን የግዛቶች መደራረብ፣ አባትና ልጅ አንድ ላይ መግዛታቸውንና ነገሥታቱ ዙፋን የሚጨብጠዝበት ዘመን አቈጣጠር የተለያየ ስልት ያለው መሆኑን መገንዘቡ የተደቀነውን ችግር በአጥጋቢ ሁኔታ ይፈታዋል።

መጽሐፈ ነገሥት አንደኛ በአዲስ ኪዳን መፈጸሙ

ጌታ ኢየሱስ በዘመኑ ለነበረው ትውልድ የእርሱ ሕይወትና መንግሥት ከሰሎሞን ጥበብ፣ ሥልጣን፣ ክብርና ሞገስ እንዲሁም ግዛት እንደሚልቅ በመግለጽ "እነሆ፤ ከሰሎሞን የሚልቅ እዚህ አለ" (ማቴ 12፥42) ብሏል። ከዚህም በላይ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሲመረቅ ቤተ መቅደሱን ሞልቶት የነበረው የእግዚአብሔር ክብር፣ የእግዚአብሔር አብ አንድያ ልጅ በሆነው በኢየሱስ በኩል በሰው ዘንድ ወደ ሚገኘው ማደሪያ መጣ (ዮሐ 1፥14)።

መጽሐፈ ነገሥት አንደኛን ለማንበብ

ሙሉውን ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ መጽሐፈ ነገሥት አንደኛን ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በዐሥራ አንድ ቀናት መነበብ ይኖርበታል፣

❑ 1 ❑ 2—3 ❑ 4—6 ❑ 7—8 ❑ 9 ❑ 10—11 ❑ 12—14 ❑ 15—17 ❑ 18—19 ❑ 20—21 ❑ 22

ማስታወሻ

አዶንያስ ለመንገሥ እንደ ፈለገ

1 ንጉሥ ዳዊት እየሸመገለና ዕድሜው በጣም እየገፋ ሲሄድ፣ ልብስ ቢደራርቡለትም እንኳ ሊሞቀው አልቻለም። 2ስለዚህ አገልጋዮቹን፣ "ንጉሡን የምትንከባከብና የምታገለግል ወጣት ድንግል እንፈልግ፤ እርሷም ጌታችን ንጉሥ እንዲሞቀው በጕሉ ትተኛለች" አሉት።

3ከዚያም በመላው አስራኤል ቈንጆ ልጃገረድ ፈልገው ሱነማዊቷን አቢሳን አገኙ፤ ለንጉሡም አመጡለት። 4ልጃገረዲቱ እጅግ ቈንጆ ነበረች፤ ንጉሡንም ትንከባከበውና ታገለግለው ነበር፤ ንጉሥ ግን ከእርሷ ጋር ግንኙነት አልነበረውም።

5በዚህ ጊዜ ከሒጊት የተወለደው አዶንያስ፣ "እነግሣለሁ" ብሎ ተነሣ፤ ስለዚህ ሠረገሎችንና[a] ፈረሶችን እንዲሁም ከፊት ከፊቱ የሚሄዱ አምሳ ሰዎችን አዘጋጀ። 6አባቱም፣ "ለምን እንዲህ ታደርጋለህ?" ብሎ ገሥጾት አያውቅም ነበር፤ አዶንያስም እጅግ መልከ መልካምና የአቤሴሎም ታናሽ ወንድም ነበር።

7አዶንያስ ከጽሩያ ልጅ ከኢዮአብና ከካህኑ ከአብያታር ጋር ተመካከረ፤ እነርሱም ድጋፋቸውን ሰጡት። 8ነገር ግን ካህኑ ሳዶቅ፣ የዮዳሄ ልጅ በናያስ፣ ነቢዩ ናታን፣ ሳሚ፣ ሬሲና[b] የዳዊት የክብር ዘበኞች ከአዶንያስ ጋር አልተባበሩም።

9ከዚያም አዶንያስበዓይንሮጌል አቅራቢያ ባለው የዞሔልት ድንጋይ አጠገብ በጎችን፣ በሬዎችንና የሰቡ ጥጆችን ሠዋ፤ ወንድሞቹን ሁሉ፣ የንጉሡን ልጆች እንዲሁም የቤተ መንግሥቱ ሹማምት የነበሩትን የይሁዳ ሰዎች ሁሉ ጠራ፤ 10ይሁን እንጂ ነቢዩ ናታንንም ሆነ በናያስን፣ የክብር ዘበኞቹንም ሆነ ወንድሙን ሰሎሞንን አልጠራም።

11ከዚያም ናታን የሰሎሞንን እናት ቤርሳቤህን እንዲህ አላት፤ "ጌታችን ዳዊት ሳያውቅ የሒጊት ልጅ አዶንያስ መንገሡን አልሰማሽምን? 12አሁንም የራስሽንና የልጅሽን የሰሎሞንን ሕይወት እንዴት ማዳን እንደምትችዪ ልምከርሽ፤ 13ወደ ንጉሥ ዳዊት ሂጂና፣ 'ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ ልጅሽ ሰሎሞን ከእኔ ቀጥሎ ይነግሣል፤ በዙፋኔም ይቀመጣል' ብለህ 'ለእኔ

1፥3 ቊ፡15፤ ኢሱ፡19፥18፤ 2ሳሙ፡37፥ ነኀ፲2፥17:22
1፥5 1ሳሙ፡8፥11፤ 2ሳሙ፡3፥4
1፥6 1ሳሙ፡3፥13
1፥7 1ሳሙ፡22፥20፤ 2ሳሙ፡2፥13:18
1፥8 1ሳሙ፡2፥35፤ 2ሳሙ፡7፥2፤ 8፥17:18፤ 23፥8፤ ነኀ፻4፥18
1፥9 2ሳሙ፡17፥17፤ ዘኊ፡29፥24
1፥10 ቊ፡26፤ 2ሳሙ፡12፥24
1፥11 2ሳሙ፡3፥4፤ 12፥24
1፥12 ምሳ፲5፥22
1፥13 ቊ፡17:30
1፥15 ቊ፡3
1፥17 ቊ፡13
1፥19 ቊ፡9
1፥21 ዘፍ፡15፥15፤ ነኀ፲2፥10

ለአገልጋይህ አልማልህልኝም ነበር? ታዲያ አዶንያስ የነገሠው ስለ ምንድን ነው?' በዪው፤ 14እንቺ እዚያው ሆነሽ ይህን በምትሰማሪው ጊዜ እኔ እገባና ያልሽው ትክክል መሆኑን እረጋግጣለሁ።"

15ስለዚህ ቤርሳቤህ፣ ሱነማዊቷ አቢሳ በምታገለግልበት ክፍል እርጅና የተጫጫነውን ንጉሥ ለማነጋገር ሄደች። 16ቤርሳቤህም ለጥ ብላ እጅ ከነሣች በኋላ እፊቱ በጕልበቷ ተንበረከከች።

ንጉሡም፣ "ምን ትፈልጊያለሽ?" ሲል ጠየቃት።

17እርሷም እንዲህ አለችው፣ "ጌታዬ ሆይ፤ 'ልጅሽ ሰሎሞን ከእኔ ቀጥሎ ይነግሣል፤ በዙፋኔም ይቀመጣል' ብለህ አንተው ራስህ ለአገልጋይህ በአምላክህ በእግዚአብሔር ምለህልኝ ነበር። 18እነሆ፤ አሁንም አዶንያስ ነግሦአል፤ ንጉሥ ጌታዬ አንተ ግን ስለዚህ ነገር አታውቅም። 19እርሱ በሬዎችን፣ ኮርማዎችንና በጎችን በብዛት ሠውቶአል፤ የንጉሡን ልጆች በሙሉ፣ ካህኑን አብያታርንና የሰራዊቱን አዛዥ ኢዮአብን ጠርቶአል፤ አገልጋይህን ሰሎሞንን ግን አልጠራውም።

20ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ ከአንተ ቀጥሎ በጌታዬ በንጉሡ ዙፋን ላይ ማን መቀመጥ እንዳለበት እንድታሳውቀው የእስራኤል ዐይን ሁሉ አንተን ይመለከታል። 21ያለበለዚያ ግን ንጉሥ ጌታዬ ከአባቶቹ ጋር በሚያንቀላፋበት ጊዜ እኔና ልጄ ሰሎሞን እንደ ወንጀለኞች እንቈጠራለን።"

22እርሷ ከንጉሡ ጋር በመነጋገር ላይ ሳለች ነቢዩ ናታን ገባ። 23ለንጉሡም፣ "ነቢዩ ናታን መጥቶአል" ብለው ነገሩት፤ እርሱም ንጉሡ ፊት ቀርቦ ለጥ ብሎ እጅ ነሣ።

24ናታንም እንዲህ አለው፤ "ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ ለመሆኑ አዶንያስ ከአንተ ቀጥሎ እንደሚነግሥ፣ በዙፋንህም እንደሚቀመጥ አስታውቀሃልን? 25በዛሬው ቀን ታች ወርዶ ብዙ በሬዎች፣ ኮርማዎችና በጎች ሠውቶአል፤ የንጉሡን ልጆች በሙሉ፣ የሰራዊቱን አዛዦችና ካህኑን አብያታርንም ጠርቶአል፤ እነሆ፤ አሁን፣ 'አዶንያስ ለዘላለም ይኑር' እያሉ ከእርሱ ጋር በመብላትና በመጠጣት

[a] 1፥5 ወይም ሠረገሎች ተብሎ ሊተረጕም ይችላል።
[b] 1፥8 ወይም እና ጓደኞቹ ተብሎ ሊተረጕም ይችላል።

1፥6 **አባቱም ... ገሥጾት አያውቅም ነበር፤** እግዚአብሔር ከዚያም ዳዊት፣ ሰሎሞን የሚቀጥለው ንጉሥ እንዲሆን ቢወስኑም እንኳ (ቊ፡ 5፥17:30፤ 2፥15)፣ የዳዊት አራተኛው ልጅ አዶንያስ፣ ራሱን የእስራኤል ንጉሥ አድርጎ በመሾም በአባቱ ላይ ዐመፀ። (1) ዳዊት ቀደም ሲል በሠራው ኀጢአት በተፈረደበት ፍርድ ምክንያት (2ሳሙ፡ 11) እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ከልጆቹ ጋር ስምም አልነበረም፤ የተከበረ ንጉሥ እንደ ነበር በታሪክ የተመሰከረለት ቢሆንም እንኳ፤ በዘዳ 6፥1-9 ላይ በተጻፈው መሠረት ምናልባት ልጆቹን ሳይመክር ቀርቶአል፤ አልተቈጣቸውም፤ አልገሠጻቸውም። ከዚህም የተነሣ የዳዊት ሕይወት ሐዘንና ትካዜ የበዛበት ሆነ። የበኩር ልጁ አምኖን የአባቱን ልጅ እኅቱን ትዕማርን ደፈራት፣ በዚህም ምክንያት የአባቱ ልጅ አቤሴሎም ብዙ ሳይቆይ ገደለው (2ሳሙ፡ 13፥1-33)። የዳዊት ሦስተኛው ልጅ አቤሴሎም በአባቱ ላይ ዐመፀ፤ የሚያደም ሙከራ አደረገበት (2ሳሙ፡ 15—18)።

(2) ዳዊት የቤተሰቡን ሕይወት በተመለከተ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ባለመከተሉ፣ ዕድሜ ዘመኑ ሁሉ መከራ በመከራ ላይ ሆነበት። ስለዚህ ለትዳር ጓደኞቻችንና ለልጆቻችን ታማኝ በመሆን፣ እያስተማርንና አርአያ እየሆንን፣ በቅድስና ሕይወት እንዲጓዙ ከማድረግ የላቀ የደቀ መዝሙርነት ፍሬ የለም (በገጽ 1894 ላይ፣ "መላጆችና ልጆች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

ላይ ናቸው። [26]ነገር ግን እኔን አገልጋይህን፣ ካህኑን ሳዶቅን፣ የዮዳሄን ልጅ በናያስንና እገልጋይህን ሰሎሞንን አልጠራም፤ [27]ታዲያ ከእርሱ ቀጥሎ በንጉሥ ጌታዬ ዙፋን ላይ የሚቀመጠውን አገልጋዮቹን ሳያሳውቅ ይህ እንዲሆን ንጉሡ ፈቅዶአልን?"

ዳዊት ሰሎሞን እንዲነግሥ አደረገ

1፥28-53 ተጓ ምብ — 1ዜና 29፥21-25

[28]ከዚያም ንጉሥ ዳዊት፣ "ቤርሳቤህን ጥሩልኝ" አለ፤ እርሷም ንጉሡ ወዳለበት ገብታ በፊቱ ቆመች።

[29]ከዚያም ንጉሡ እንዲህ ሲል ማለ፤ "ነፍሴን ከመከራ ሁሉ ያዳናት ሕያው እግዚአብሔርን! [30]ልጅሽ ሰሎሞን ከእኔ ቀጥሎ ይነግሣል፤ በእኔም ምትክ በዙፋኔ ይቀመጣል' ብዬ በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር የማልሁልሽን ዛሬ በእውነት እፈጽማለሁ"

[31]ቤርሳቤህም ለጥ ብላ እጅ ከነሣች በኋላ፣ በንጉሡ ፊት ተንበርክካ፣ "ጌታዬ ንጉሥ ዳዊት ለዘላለም ይኑር!" አለች።

[32]ንጉሥ ዳዊትም፣ "ካህኑን ሳዶቅን፣ ነቢዩን ናታንንና የዮዳሄን ልጅ በናያስን ጥሩልኝ" አለ። እነርሱም ንጉሡ ፊት በቀረቡ ጊዜ፣ [33]እንዲህ አላቸው፤ "የጌታችሁን አገልጋዮች ይዛችሁ በመሄድ ልጄን ሰሎሞንን በራሴ በቅሎ ላይ አስቀምጡት፤ ወደ ግዮንም ይዛችሁት ውረዱ። [34]በዚያም ካህኑ ሳዶቅና ነቢዩ ናታን ቀብተው በእስራኤል ላይ ያንግሡት፤ ቀንደ መለከት ነፍታችሁም፣ 'ንጉሥ ሰሎሞን ለዘላለም ይኑር!' ብላችሁ ጩኹ። [35]አጅባችሁት ወደ ላይ ውጡ፤ ከዚያም መጥቶ በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ፤ በእኔም ምትክ ይግዛ፤ በእስራኤልና በይሁዳ ላይ ሾሜዋለሁ።"

[36]የዮዳሄ ልጅ በናያስም ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰ፤ "አሜን! የጌታዬ የንጉሡ አምላክ እግዚአብሔር ይህንኑ ያጽናው። [37]እግዚአብሔር ከጌታዬ ከንጉሡ ጋር እንደ ነበረ ሁሉ፣ ከሰሎሞንም ጋር ይሁን፤ ዙፋኑንም ከጌታዬ ከንጉሥ ዳዊት ዙፋን የበለጠ ያድርገው።"

[38]ስለዚህ ካህኑ ሳዶቅ፣ ነቢዩ ናታን፣ የዮዳሄ ልጅ በናያስ፣ ከሊታውያንና ፈሊታውያን ወርደው ሰሎሞንን በንጉሥ ዳዊት በቅሎ አስቀምጠው በማጀብ ወደ ግዮን አመጡት። [39]ካህኑ ሳዶቅም የዘይቱን ቀንድ ከመገናኛው ድንኳን ወስዶ ሰሎሞንን ቀባው፤ ከዚያም ቀንደ መለከቱን ነፋ፤ ሕዝቡም በሙሉ፣ "ንጉሥ ሰሎሞን ለዘላለም ይኑር!" በማለት ዳር እስከ ዳር አስተጋቡ። [40]ሕዝቡ ሁሉ እንቢልታ እየነፋና እጅግ እየተደሰተ አጀበው፤ ከድምፁ የተነሣም ምድሪቱ ተናወጠች።

[41]አዶንያስና የተጠሩት እንግዶች ሁሉ ግብዣውን በማገባደድ ላይ ሳሉ፣ ይህንኑ ሰሙ፤ ኢዮአብም የመለከቱን ድምፅ ሲሰማ፣ "ይህ በከተማዪቱ ውስጥ የሚሰማው ድምፅ ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀ።

[42]ኢዮአብ ገና ተናግሮ ሳይጨርስ፣ የካህኑ የአብያታር ልጅ ዮናታን ደረሰ፤ አዶንያስም፣ "እንዳንተ ያለ ታማኝ ሰው መልካም ዜና ሳይዝ አይመጣምና ግባ" አለው።

[43]ዮናታንም እንዲህ ሲል መለሰ፣ "ነገሩ ከቶ እንዲህ አይደለም! ጌታችን ንጉሥ ዳዊት ሰሎሞንን አንግሦታል። [44]ንጉሡ ካህኑ ሳዶቅ፣ ነቢዩ ናታን፣ የዮዳሄ ልጅ በናያስ፣ ከሊታውያንና ፈሊታውያን አብረውት እንዲሄዱ አድርጎአል፤ እነርሱም በንጉሡ በቅሎ አስቀመጡት። [45]ካህኑ ሳዶቅና ነቢዩ ናታን በግዮን ቀብተው አንግሠውታል። ከዚያም ደስ ብሎአቸው ወጥተዋል፤ ከተማዪቱም ይህንኑ አስተጋብታለች፤ እንግዲህ የሰማችሁት ድምፅ ይኸው ነው። [46]ከዚህም ሌላ ሰሎሞን በመንግሥቱ ዙፋን ላይ ተቀምጦአል። [47]የመንግሥቱ ሹማምትም ወደ ጌታችን ወደ ንጉሥ ዳዊት መጥተው፣ 'አምላክህ የሰሎሞንን ስም ከአንተ ስም የላቀ፣ ዙፋኑንም ከአንተ ዙፋን የበለጠ ያድርገው' በማለት መልካም ምኞታቸውን ገልጸውለታል። ንጉሡም ዐልጋው ላይ ሆኖ በመስገድ፣ [48]ዛሬ በዙፋኔ ላይ የሚቀመጠውን ወራሽ ዐይኔ እንዲያይ የፈቀደ፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፣ ምስጋና ይድረሰው' አለ።"

[49]በዚህም አዶንያስና የጠራቸው እንግዶች በሙሉ ደንግጠው ተነሡ፤ በየአቅጣጫውም ተበታተኑ። [50]አዶንያስ ግን ሰሎሞንን በመፍራት ሄዶ፣ የመሠዊያውን ቀንድ ያዘ። [51]ከዚያም፣ ለሰሎሞን፣ "አዶንያስ እነሆ፣ ንጉሥ ሰሎሞንን በመፍራት የመሠዊያውን ቀንድ ይዞ ተማጥኖአል፤ እርሱም፣ 'ባሪያውን በሰይፍ እንዳይገድለው ንጉሡ ሰሎሞን ዛሬውኑ ይማልልኝ' ብሎአል" ብለው ነገሩት።

[52]ሰሎሞንም፣ "አካሄዱን ካሳመረ ከራስ ጠጒሩ አንዲቱ እንኳ መሬት ላይ አትወድቅም፤ ጥፋት ከተገኘበት ግን ይሞታል" ሲል መለሰ። [53]ከዚያም ንጉሥ ሰሎሞን ሰዎች ልኮ ከመሠዊያው ላይ አወረዱት። አዶንያስም መጥቶ ለንጉሥ ሰሎሞን እጅ ነሣ፤ ሰሎሞንም፣ "በል ወደ ቤትህ ሂድ" አለው።

1፥26 ቍ 10
1፥29 2ሳሙ 4፥9
1፥30 ቍ 13፣ 1ዜና 23፥1
1፥32 1ሳሙ 2፥35
1፥33 ቍ 38፣ መሳ 10፥4፣ 2ዜና 32፥30፣ 33፥14፣ ዘካ 9፥9
1፥34 1ሳሙ 2፥35፣ 10፥1፣ 2ሳሙ 15፥10
1፥37 ቍ 47፣ ኢሱ 1፥5፣ 17
1፥38 ቍ 8፣ 33፣ 1ሳሙ 30፥14፣ 2ሳሙ 15፥18
1፥39 ቍ 34፣ ዘፀ 26፥1፣ 27፥21፣ 29፥7፣ ዘኍ 23፥21፣ 1ሳሙ 10፥1፣ 2ሳሙ 15፥10፣ 2ነገ 11፥12፣ 14፣ መዝ 47፥5፣ 89፥20፣ ዘካ 9፥9
1፥40 1ሳሙ 10፥5
1፥41
2ዜና 23፥12፣ 13
1፥42 2ሳሙ 15፥27፣ 36፣ 18፥26
1፥45 ቍ 40
1፥46 ዘዳ 17፥18
1፥47 ቍ 37
1፥48 1ነገ 3፥6
1፥50 ዘፀ 27፥2
1፥52
1ሳሙ 14፥45

1፥50 **የመሠዊያውን ቀንድ**፣ የመሠዊያው ቀንድ የእግዚአብሔር ምሕረት፣ ይቅርታና ጥበቃ ትእምርት ነው። ሰሎሞን በዚህ በተቀደሰ ስፍራ የማይገድለው ስለ መሰለው አዶንያስ ወደ መሠዊያው ሸሽ (ከዘፀ 21፥13-14 ጋር ያነጻጽሩ)።

ዳዊት ለሰሎሞን የሰጠው መመሪያ

2፥10-12 ተጓ ምብ — 1ዜና 29፥26-28

2 ዳዊት የሚሞትበት ጊዜ እንደ ተቃረበም፣ ልጁን ሰሎሞንን እንዲህ ሲል አዘዘው፤

2 "እነሆ፤ እኔ የምድሩን ሁሉ መንገድ ልሂድ ነው፤ እንግዲህ በርታ፤ ሰውም ሁን። 3 የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ፤ የምታደርገው ሁሉ እንዲከናወንልህ፣ በምትሄድበትም ሁሉ እንዲሳካልህ፣ በሙሴ ሕግ እንደ ተጻፈው በመንገዶቹ ተመላለስ፤ ሥርዐቶቹንና ትእዛዛቱን፣ ሕግጋቱንና ደንቦቹን ጠብቅ፤ 4 እግዚአብሔርም፣ 'ዘሮችህ መንገዳቸውን ቢጠብቁ፣ እንዲሁም በፍጹም ልባቸው፣ በፍጹም ነፍሳቸው በታማኝነት በፊቴ ቢመላለሱ፣ በእስራኤል ዙፋን የሚቀመጥ ሰው ከዘርህ አላጣህም' ሲል የሰጠኝን ተስፋ ይፈጽምልኛል።

5 "የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ በእኔ ላይ ያደረገውን፣ እንዲሁም በእስራኤል ሰራዊት አዛዦች በኔር ልጅ በአበኔርና በዬቴሩ ልጅ በአሜሳይ ላይ የፈጸመውን አንተው ራስህ ታውቃለህ፤ ጦርነት ሳይኖር በሰላሙ ጊዜ ደማቸውን አፍሶአል፤ በዚህም ደም ወገቡ ላይ የታጠቀውን ቀበቶና በእግሩ ላይ ያደረገውን ጫማ በክሎአል። 6 መደረግ ያለበትን በጥበብህ አድርግ፤ ከጎሽቦቱ በሰላም ወደ መቃብር እንዲወርድ አታድርግ።

7 "ከወንድምህ ከአቤሴሎም በሸሸህ ጊዜ መልካም ነገር አድርገውልኛልና ለገለዓዳዊው ለቤርዜሊ ልጆች ግን በጎ ነገር አድርግላቸው፤ ማእድህን ከሚካፈሉ ሰዎችም ጋር አብረው ይብሉ።

8 "ወደ መሃናይም በሄድህ ጊዜ፣ ክፉኛ የረገመኝ የባሑሪም ሰው የብንያማዊው የጌራ ልጅ ሳሚ እነሆ፤ ከአንተ ዘንድ ይገኛል፤ ሊቀበለኝ ወደ ዮርዳኖስ ሲወርድ፣ 'በሰይፍ አልገድልህም' ብዬ በእግዚአብሔር ስም ምዬለታለሁ፤ 9 አሁን ግን በደል እንደሌበት ሰው አትተወው፤ ጥበበኛ ነህና መደረግ ያለበትን ታውቃለህ፤ ሽበቱን በደም ወደ መቃብር አውርድ።"

10 ከዚያም ዳዊት ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤

2፥1 ዘፍ27፥2፤ ዘጕ27፥13
2፥2 ኢሱ1፥6፤ 23፥14
2፥3 ዘዳ4፥6፤ 10፥12፤ 17፥1420፤ ኢሱ1፥7፤ 1ዜና22፥13
2፥4 2ሳሙ7፥13፡15፤ 2ነገ18፥36፤ 20፥3፤ 2ዜና23፥3፤ መዝ26፥13፤ 132፥12
2፥5 1ሳሙ14፥50፤ 2ሳሙ2፥18፤ 3፥27፤ 17፥25
2፥6 ቍ9
2፥7 ዘፍ40፥14፤ 2ሳሙ9፥7፤ 17፥27፤ 19፥3139
2፥8 ቍ36-46፤ዘፍ32፥2፤ 2ሳሙ16፥5-13፤ 19፥18-23
2፥9 ቍ6
2፥10 2ሳሙ5፥7፤ ሐሥ2፥29
2፥11 2ሳሙ5፥4፡5
2፥12 ቍ46፤ 1ዜና17፥14፤ 29፥23፤
2ዜና1፥1፤ 9፥8፤ 12፥13፤ 17፥1፤ 21፥4
2፥13 1ሳሙ16፥4፤ 2ሳሙ3፥4
2፥17 1ነገ1፥3
2፥19 1ነገ15፥13፤ 2ነገ10፥13፤ 24፥15፤ 2ዜና15፥16፤ መዝ45፥9፤ ኤር13፥18፤ 22፥26፤ 29፥2
2፥21 1ነገ1፥3

በዳዊትም ከተማ ተቀበረ። 11 ዳዊት በኬብሮን ሰባት ዓመት፣ በኢየሩሳሌም ሠላሳ ሦስት ዓመት ባጠቃላይ አርባ ዓመት በእስራኤል ላይ ነገሠ። 12 ስለዚህ ሰሎሞን በአባቱ በዳዊት ዙፋን ተቀመጠ፤ መንግሥቱም እጅግ የጸና ሆነ።

የሰሎሞን መንግሥት መጽናት

13 በዚህ ጊዜ የአጊት ልጅ አዶንያስ ወደ ሰሎሞን እናት ወደ ቤርሳቤህ ሄደ፤ ቤርሳቤህም፣ "የመጣኸው በሰላም ነውን?" ስትል ጠየቀችው።

እርሱም፣ "አዎን በሰላም ነው" ብሎ መለሰ። 14 ከዚያም፣ "የምነግርሽ ጒዳይ አለኝ" አላት።

እርሷም፣ "እሺ ተናገር" ብላ መለሰችለት።

15 እርሱም፣ "መንግሥቱ የእኔ እንደ ነበረና እስራኤልም ሁሉ እኔ እንድነግሥ ዐይናቸውን ጥለውብኝ እንደ ነበር አንቺ ራስሽ ታውቂአለሽ፤ ሆኖም ነገሩ ከእግዚአብሔር የተቈረጠለት ሆነና ሁኔታዎች ተለዋውጠው፣ መንግሥቱ ለወንድሜ ተላለፈ። 16 አሁንም አንዲት ነገር እለምንሻለሁ፤ እንቢ አትበኝ" አላት።

እርሷም፣ "በል እሺ ተናገር" አለችው።

17 እርሱም፣ "ንጉሥ ሰሎሞን መቼም እምቢ አይልሽምና ሹነማዊቷን አቢሳን እንዲድርልኝ ለምኚልኝ" አላት።

18 ቤርሳቤህም፣ "መልካም ነውና ይህንኑ ለንጉሡ እነግርልሃለሁ" ብላ መለሰች።

19 ስለዚህም ቤርሳቤህ የአዶንያስን ጒዳይ ልትነግረው ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ሄደች፤ ንጉሡም ሊቀበላት ተነሣ፤ እጅ ከነሣትም በኋላ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ፤ ንጉሡም ለእናቱ ሌላ ዙፋን አስመጥቶ በቀኙ አስቀመጣት።

20 እርሷም፣ "የምለምንህ አንዲት ነገር አለችኝና እባክህ እሺ በለኝ" አለችው።

ንጉሡም፣ "እናቴ ሆይ፤ አላሳፍርሽምና ንገሪኝ" ሲል መለሰላት።

21 ስለዚህም፣ "ሱነማዊቷን አቢሳን

*2፥6 በዚህ ስፍራና በቍጥር 9 ላይ ዕብራይስጡ ሲኦል ይላል።

2፥4 **ዘሮችህ መንገዳቸውን ቢጠብቁ፤** ዳዊት በክብድ የሕይወት ገጠመኝና ተግሣጽ ውስጥ በማለፉ፣ ስኬታማነትና የእግዚአብሔር በረከት እውን ሊሆኑ የሚችሉት በእግዚአብሔር መንገድና እውነት ላይ ጸንቶ በመቆም መሆኑን ተገንዝቦ። ስለዚህ ሰሎሞን ትእዛዝን አክብሮና ታማኝ ሆኖ ይኖር ዘንድ ዳዊት ያስብ ነበር። ነገር ግን ሰሎሞንና ወንዶች ልጆቹ የዳዊትን ምክር በስተመጨረሻው በማቃለል፣ ከእግዚአብሔርና ከኪዳኑ ራቁ (ከ2ዜና 7፥17-22 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህም ከእግዚአብሔር ዘንድ በሰሎሞን ላይ ፍርድን አስከተለ (11፥1-13)፤ ይኸውም መንግሥቱ ተከፈለ (12፥1-33)፤ በመጨረሻም የሰሜኑና የደቡቡ መንግሥታት ሁለቱም ወደሙ። እግዚአብሔር ለዳዊት የገባው ቃል ዘሮ ዘሮ ፍጻሜ ላይ የደረሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (ሐሥ 15፥16-18)።

2፥5 **ኢዮአብ ... በሁለቱ የእስራኤል ሰራዊት አዛዦች፤** ኢዮአብ፣ አቤኔርንና አሜሳይን በግፍ በመግደሉ ሞት ይገባው ስለነበር (2ሳሙ 3፥27፤ 20፥9-10 ይመ፤ ከማቴ 26፥52 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ሰሎሞን ይህን ፍትሕ በመፈጸም አገዛዙን ይጀምር ዘንድ ዳዊት መመሪያ ሰጠው።

2፥9 **በደም ወደ መቃብር አውርድ፤** እርሱ ራሱ አላደረገውም ብሎ የማለበትን ጒዳይ፣ ዳዊት ለሰሎሞን የሰጠውና የተጻፈው የመጨረሻው የዳዊት መመሪያ እንዴት አሳዛኝ ነው (ከቍ 8 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ ዳዊት ለሳሚ የገባውን ቃል አጠፈ (2ሳሙ 19፥23 ይመ)፤ እንግዲህ ምሕረት የለሽ ጭከና፣ በእግዚአብሔር ፊት የሚያስደስትና ነቀፋም የሌለበት ተደርጎ መቈጠር የለበትም፣ በአዲስ ኪዳን መስፈርት መሠረት እንዲበየን ማሰብም ተገቢ አይደለም (ከሐሥ 17፥30 ጋር ያነጻጽሩ)።

ወንድምህ አዶንያስ ቢያገባትስ?" አለችው።
22ንጉሥ ሰሎሞንም እናቱን፣ "ስለምን ሱነማዊቷን አቢሳን ብቻ ለአዶንያስ ትጠይቂለታለሽ? ታላቅ ወንድሜ ስለሆነ መንግሥቱንም ጠይቂለት እንጂ፤ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን እንዲሁም ለካህኑ ለአብያታርና ለጽሩያ ልጅ ለኢዮአብ ጠይቂላቸው" አላት።
23ከዚያም ንጉሥ ሰሎሞን በእግዚአብሔር ስም እንዲህ ሲል ማለ፤ "አዶንያስ ይህን ስለ ጠየቀ በሞት ሳይቀጣ ቢቀር፣ እግዚአብሔር ይፍረድብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጣብኝ፤
24አሁንም በሚገባ ያጸናኝ፤ በአባቴ በዳዊት ዙፋን ያስቀመጠኝና በሰጠውም ተስፋ መሠረት ሥርወ መንግሥትን የመሠረተልኝ ሕያው እግዚአብሔርን አዶንያስ
ዛሬ ይሞታል!"
25ስለዚህም አዶንያስን እንዲገድለው ንጉሥ ሰሎሞን፣ የዮዳሄን ልጅ በናያስን አዘዘው፤ በናያስም አዶንያስን መቶ ገደለው።
26ንጉሡም ካህኑን አብያታርን፣ "ሞት የሚገባህ ሰው ነበርህ፤ ነገር ግን የልዑል እግዚአብሔርን ታቦት በአባቴ በዳዊት ፊት ስለ ተሸከምህ፣ አባቴ የተቀበለውንም መከራ ሁሉ አብረኸው ስለ ተቀበልህ፣ እኔ አሁን አልገድልህም፤ ዓናቶት ወዳለው ዕርሻህ ሂድ" አለው።
27ስለዚህ እግዚአብሔር ስለ ዔሊ ቤት በሴሎ የተናገረውን ቃል ለመፈጸም፣ ሰሎሞን አብያታርን ከእግዚአብሔር ክህነት አስወገደው።
28ከአቤሴሎም ጋር ሳይሆን ከአዶንያስ ጋር አሚሮ የነበረው ኢዮአብም ይህን በሰማ ጊዜ፣ ወደ እግዚአብሔር ድንኳን ሸሽቶ የመሠዊያውን ቀንድ ያዘ።
29ኢዮአብ ወደ እግዚአብሔር ድንኳን ሸሽቶ መሄዱንና በመሠዊያው አጠገብ መሆኑን ንጉሥ ሰሎሞን በሰማ ጊዜ፣ የዮዳሄን ልጅ በናያስን፣ "ሂድና ግደለው!" ብሎ አዘዘው።
30ስለዚህም በናያስ ወደ እግዚአብሔር ድንኳን ገብቶ ኢዮአብን፣ "'ንጉሡ፣ 'ከዚህ ውጣ' ይልሃል" አለው።
እርሱ ግን "አልወጣም፣ እዚሁ እሞታለሁ" አለው።
በናያስም፣ "ኢዮአብ የሰጠኝ መልስ ይህ ነው" በማለት ለንጉሡ ተናገረ።
31ንጉሡም በናያስን እንዲህ ሲል አዘዘው፤ "በል እንዳለው አድርግ፣ ግደልና ቅበረው፤ ኢዮአብ በከንቱ ካፈሰሰው ንጹሕ ደምም አእንና የአባቴን ቤት አንጻ።
32አባቴ ዳዊት ሳያውቅ ኢዮአብ በሁለቱ ሰዎች ላይ አደጋ ጥሎ በሰይፍ ገድሎአቸዋልና

2፥22 ዘፍ22፥24፤ 1ሳሙ22፥20፤ 1ነገ1፥3፤ 1ዜና3፥2
2፥23 ሩት1፥17
2፥24 2ሳሙ7፥11
2፥25 2ሳሙ8፥18፤ 12፥10
2፥26 ኢሱ21፥18፤ 1ሳሙ22፥20፤ 2ሳሙ15፥14፥24
2፥27 1ሳሙ2፥27-36
2፥28 ዘፀ27፥2
2፥29 ሶ 25፥ ዘፀ21፥14
2፥30 ዘፀ21፥14፤ 2ነገ11፥15
2፥31 ዘዳ19፥13
2፥32 ዘፍ4፥14፤ መሳ9፥24፥57፤ 2ሳሙ17፥25፤ 2ዜና21፥13

2፥34 ሶ 25፥ 2ሳሙ2፥18
2፥35 1ሳሙ2፥35፤ 2ሳሙ8፥18
2፥36 2ሳሙ16፥5
2፥37 ዘሌ20፥9፤ 2ሳሙ15፥23፤ ዮሐ18፥1
2፥39 1ሳሙ27፥2
2፥42 2ሳሙ19፥23
2፥44 2ሳሙ16፥5-13
2፥45 2ሳሙ7፥13

ስላፈሰሰው ደም እግዚአብሔር ይበቀልዋል። የእስራኤል ሰራዊት አዛዥ የኔር ልጅ አበኔርና የይሁዳ ሰራዊት አዛዥ የዬቴሩ ልጅ አሜሳይ ሁለቱም ከእርሱ የተሻሉና ይበልጥ ትክክለኛ ሰዎች ነበሩ።
33የደማቸውም ዕዳ ለዘላለም በኢዮአብና በዘሩ ራስ ላይ ይሁን። ነገር ግን በዳዊትና በዘሩ በቤቱና በዙፋኑ ላይ የእግዚአብሔር ሰላም ለዘላለም ጸንቶ ይኑር።"
34ስለዚህም የዮዳሄ ልጅ በናያስ ወጣ፤ ኢዮአብንም መቶ ገደለው፤ እርሱም በምድረ በዳ ባለው በገዛ ምድሩ ተቀበረ።
35ንጉሡም በኢዮአብ ቦታ የዮዳሄን ልጅ በናያስን በሰራዊቱ ላይ ሾመ፤ በአብያታርም ቦታ ካህኑን ሳዶቅን ተካ።
36ከዚያም ንጉሡ ሳሚን አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ "በኢየሩሳሌም ቤት ሠርተህ እዚያው ተቀመጥ፤ ከዚያ ግን የትም እንዳትሄድ፤
37ነገር ግን ከዚያ ወጥተህ የቄድሮንን ሸለቆ ከተሻገርህ እንደምትሞት ዕወቅ፤ ደምህም በራስህ ላይ ይሆናል።"
38ሳሚም መልሶ ንጉሡን፣ "መልካም፤ ባሪያህ ጌታዬ ንጉሡ ያለውን ይፈጽማል" አለው፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ብዙ ጊዜ ተቀመጠ።
39ከሦስት ዓመት በኋላ ግን፣ ከሳሚ አገልጋዮች ሁለቱ ወደ ጌት ንጉሥ፣ ወደ መዓካ ልጅ ወደ አንኩስ ኰበለሉ፤ ለሳሚም፣ "እነሆ፣ አገልጋዮችህ በጌት ናቸው" ተብሎ ተነገረው።
40ሳሚ ይህን ሲሰማም አህዮቹን ጭኖ አገልጋዮቹን ለመፈለግ ጌት ወዳለው ወደ አንኩስ ሄደ፤ አገልጋዮቹንም ከጌት መልሶ አመጣቸው።
41ሳሚ ከኢየሩሳሌም ወደ ጌት ሄዶ መመለሱን ሰሎሞን በሰማ ጊዜ፣ 42ንጉሡ ሳሚን አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ "'ወደ ሌላ ቦታ የሄድህ ዕለት እንደምትሞት ዕወቅ' ብዬ በእግዚአብሔር ስም አስምዬ አስጠንቅቄህ አልነበረምን? በዚያን ጊዜ አንተም፣ 'መልካም ነው፤ እኔም እታዘዛለሁ' ብለኸኝ ነበር፤ 43ታዲያ ለእግዚአብሔር የማልኸውን መሐላ ያልጠበቅኸውና እኔም የሰጠሁህን ትእዛዝ ያልፈጸምኸው ለምንድን ነው?"
44ንጉሡም መልሶ ሳሚን እንዲህ አለው፤ "በአባቴ በዳዊት ላይ ያደረግህበትን ክፉ ነገር ሁሉ ልብህ ያውቀዋል፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ስለ ክፉ ሥራህ ብድሩን ይከፍልሃል።
45ንጉሥ ሰሎሞን ግን ይባረካል፤ የዳዊትም ዙፋን በእግዚአብሔር ፊት ለዘላለም ጸንቶ

2፥27 **እግዚአብሔር ... የተናገረውን ቃል ለመፈጸም፤** ከአንድ መቶ ሃያ ዓመት በፊት አንድ የእግዚአብሔር ሰው በሊቀ ካህናቱ በኤሊ ቤት ላይ የሚደርሰውን የእግዚአብሔር ፍርድ በትንቢት ቃል ተናግሮ ነበር (ከ1ሳሙ 2፥27-36 ጋር ያነጻጽሩ)። ከተናገረው ትንቢት ውስጥ አንዳንዱ ወዲያውኑ ተፈጽሞአል (1ሳሙ 4፥10-22)፤ አንዳንዱ ደግሞ ረጅም ዘመን ወስዶአል። አብያታር ከሊቀ ካህናትነቱ መውረዱ እግዚአብሔር ለኤሊ ከተናገረው ትንቢት ውስጥ ፍጻሜ ያገኘ ነበር፤ እግዚአብሔር ቃሉን ፈጽሞ አይረሳም፤ አንዳንድ ጊዜ ረጅም ዘመን፣ ዐሥርት ዓመታትና ትውልድ አልፎ ትውልድ እስከሚተካ ድረስ ቢወስድም፤ የተናገረው ቃል መፈጸሙን ዘወትር ይከታተላል (ኤር 1፥12)፤ የእግዚአብሔር ቃል አንድ ቅንጣት ሳትቀር ፍጻሜ ላይ ትደርስለች።

---

*2፥34 ወይም በገዛ መቃብሩ

ይኖራል።" 46ከዚያም ንጉሡ የዮዳሄን ልጅ በናያስን አዘዘው፤ በናያስም ወጣ፤ ሳሚንም መቶ ገደለው።

በዚህ ጊዜም መንግሥቱ በሰሎሞን እጅ ጸና።

ሰሎሞን ጥበብን ከእግዚአብሔር መለመኑ

3፥4-15 ተጓ ምብ — 2ዜና 1፥2-13

3 ሰሎሞን የግብፅ ንጉሥ የፈርዖን ወዳጅ ሆነ፤ የፈርዖንንም ልጅ አገባ። እርሱም ቤተ መንግሥቱን፣ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና የኢየሩሳሌምን ዙሪያ ቅጥር ሠርቶ እስኪጨርስ ድረስ በዳዊት ከተማ አስቀመጣት።

2በዚያን ጊዜ ለእግዚአብሔር ስም ገና ቤተ መቅደስ ስላልተሠራ፣ ሕዝቡ አሁንም መሥዋዕት የሚያቀርበው በማምለኪያ ኰረብታ ላይ ነበር። 3ሰሎሞን እግዚአብሔርን ይወድ ነበር፤ በአባቱ በዳዊት ሥርዐትም

2፥46 ቊ 8፡12፣ 2ሳሙ 8፡18
3፥1 2ሳሙ 5፥7፣ 7፥2፣ 1ነገ 2፥10፣ 7፥8፣ 9፥10:24፣ 11፥1፣ 13፣ 2ዜና 8፥11
3፥2 ዘሌ 17፥3፣ 5፣ 26፥30፣ ዘዳ 12፥14፣ 14፥23፣ 1ነገ 15፥14፣ 22፥43
3፥3 ቊ 2፣ ዘሌ 17፥3፣ 5፣ ዘዳ 6፥5፣ 10፥12፣ 17፥19፣ ኢሱ 1፥7፣ 1ነገ 14፥8፣ 2ነገ 12፥3፣ 15፥4፣ 35፣ 16፥4፣ 21፥3፣ መዝ 31፥23፣ 145፥20
3፥4 ኢሱ 9፥3

ይሄድ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ በኰረብታዎች ላይ መሥዋዕት ይሠዋና ዕጣን ያጥን ነበር።

4ከሁሉ የሚበልጠው የማምለኪያ ኰረብታ ገባዖን ስለ ነበረ፣ ንጉሡ መሥዋዕት ለማቅረብ ወደዚያ ሄደ። ሰሎሞን በዚያ መሠዊያ ላይ አንድ ሺህ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ። 5በገባዖንም እግዚአብሔር ለሰሎሞን ሌሊት በሕልም ተገለጠለት፤ እምላክም፣ "እንድሰጥህ የምትፈልገውን ሁሉ ለምን" አለው።

6ሰሎሞን እንዲህ ሲል መለሰ፤ "አባቴ ዳዊት በእውነት፣ በጽድቅና በቅን ልቦና በፊትህ ስለ ተመላለሰ፣ ለባሪያህ ታላቅ ቸርነትን አሳይተኸዋል፤ ይህ ታላቅ ቸርነት እንዲቀጥል በማድረግ ዛሬም በዙፋኑ ላይ የሚቀመጥ ልጅ ሰጥተኸዋል።

7"እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ባሪያህ በአባቴ በዳዊት እግር ተተክቼ እንድነግሥ አድርገሃልኝ እኔ ግን ገና ትንሽ ልጅ ስለ ሆንሁ፣ መውጫና መግቢያዬን አላውቅም።

3፥5 1ነገ 9፥2፣ 11፥9፣ ማቴ 7፥7፣ 27፥9 3፥6 ዘፍ 17፥1፣ 1ነገ 8፥48 3፥7 ዘኍ 27፥17፣ 1ዜና 22፥5፣ 29፥1፣ ኤር 1፥6

3፥2 **መሥዋዕት የሚያቀርበው በማምለኪያ ኰረብታ፤** ቤተ መቅደሱ የመሥዋዕት ማእከል ሆኖ በኢየሩሳሌም ከመሠራቱ በፊት እስራኤላውያን በኰረብቶች ወይም በሌሎች ጉብታዎች፣ አንዳንድ ጊዜም ቀድሞ ከነዓናውያን ለጣዖቶቻቸው መሥዋዕት ያቀርቡበት በነበረው ቦታ ላይ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር። በከነዓናውያን ከፍታ ቦታዎች ላይ መሥዋዕት ማቅረብ በብሉይ ኪዳን ሕግ የተከለከለ ነው፤ የከነዓናውያን ከፍታ ቦታዎች ሁሉ መውደም ነበረባቸውና (ዘሌ 17፥35፣ ዘዳ 7፥5፣ 12፥13) ለማምለኪያና ለመሥዋዕት ማቅረቢያ የሚሆኑ መሠዊያዎች መሠራት የነበረባቸው እግዚአብሔር በወሰነው ስፍራ ላይ ብቻ ነበር (ዘፀ 20፥24፣ ዘዳ 12፥5:8:13-14)።

ኢየሩሳሌም በሰሎሞን ጊዜ

በግምት 950 ዓ.ክ.በ
ሰሎሞን ከተማዋን ከቀድሞ አቀማመጧ ወደ ሰሜን አቅጣጫ በማስፋት አስደናቂውን ቤተ መቅደሱን ሠራ። ቤተ መንግሥቱም እዚያው አጠገብ ነበር። ሆኖም የሕንጻው አሠራርና የተሠራበት ሥፍራ አይታወቅም።



© 1991 The Zondervan Corporation
© 1986 Hugh Claycombe

ሰባሪያህ አንተ በመረጥኸው ሕዝብ፣ ከብዛቱም የተነሣ ሊቈጠር በማይችል ታላቅ ሕዝብ መካከል ይገኛል። ⁹ስለዚህ መልካሙንና ክፉውን በመለየት ሕዝብህን ማስተዳደር እንዲችል ለባሪያህ አስተዋይ ልብ ስጠው፤ አለዚያማ ይህን ታላቅ ሕዝብህን ማን ሊያስተዳድር ይችላል?"

¹⁰ሰሎሞን ይህን በመለመኑ ጌታ ደስ አለው፤ ¹¹ስለዚህ እንዲህ አለው፤ "ለራስህ ረጅም ዕድሜ፣ ብልጽግና እንድታገኝ ወይም ጠላቶችህ እንዲጠፉልህ ሳይሆን፣ በትክክል ማስተዳደር እንድትችል ማስተዋልን ስለ ጠየቅህ፣ ¹²ይህንኑ እደርግልሃለሁ፤ ከአንተ በፊት ማንም ያልነበረውን፣ ከአንተም በኋላ ማንም የማያገኘውን ጥበብና አስተዋይ ልቡና እሰጥሃለሁ፤ ¹³ከዚህም በላይ እንተ ያልጠየቅኸውን ብልጽግናና ክብር እሰጥሃለሁ፤ ይኸውም በሕይወት ዘመንህ የሚተካከልህ ማንም ንጉሥ እንዳይኖር ነው። ¹⁴አባትህ ዳዊት እንዳደረገው በመንገዴ ብትሄድ፣ ሥርዐቴንና ትእዛዜን ብትጠብቅ ዕድሜህን አረዝመዋለሁ።"

¹⁵ሰሎሞንም ከእንቅልፉ ነቃ፤ እነሆ ሕልም መሆኑን ተረዳ።

ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ፣ በጌታ ኪዳን ታቦት ፊት ቆመ፤ የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት አቀረበ፤ ለሹማምቱም ሁሉ ግብዣ አደረገ።

ጥበብን የተሞላ ፍትሕ

¹⁶በዚህን ጊዜ ሁለት ዝሙት አዳሪዎች ወደ ንጉሡ መጥተው ከፊቱ ቆሙ። ¹⁷ከእነርሱም አንዲቱ እንዲህ አለች፣ "ጌታዬ ሆይ፤ ይህች ሴትና እኔ በአንድ ቤት አብረን እንኖራለን፤ አብራኝ እያለችም እኔ ልጅ ወለድሁ፤ ¹⁸እኔ ከወለድሁ ከሦስት ቀን በኋላም፣ ይህች ሴት ወለደች፤ ያለነው እኛ ብቻ ነን፤ ከሁለታችን በቀር በዚያ ቤት ማንም አልነበረም።

¹⁹"የዚህች ሴት ሕፃን ልጅ ስለ ተኛችበት ሌሊት ሞተ። ²⁰ስለዚህም በእኩለ ሌሊት ተነሥታ እኔ አገልጋይህ ተኝቼ ሳለሁ ልጄን ከአጠገቤ ወሰደችው፤ ከዚያም የእኔን ልጅ ራሷ ታቅፋ፣ የሞተ ልጇን አምጥታ በዕቅፌ አደረገችው። ²¹በማግሥቱ ልጄን ላጠባ ስነሣ እነሆ ሞቶአል፤ ነገር ግን በማለዳ ብርሃን ትክ ብዬ ስመለከተው እኔ የወለድሁት ልጅ አለመሆኑን ተገነዘብሁ።"

²²ሌላዪቱም ሴት፣ "ነገሩ አንቺ እንደምትዪው አይደለም፤ የሞተው የአንቺ፣ በሕይወት ያለውም የእኔ ነው" አለች።

የመጀመሪያዋ ሴት ግን አጠንክራ፣ "አይደለም! የሞተው የአንቺ፣ በሕይወት ያለው ግን የእኔ ልጅ ነው" አለች፤ በዚህ ሁኔታም በንጉሡ ፊት ተከራከሩ።

²³ንጉሡም፣ "ይህችኛዪቱ፣ 'የእኔ ልጅ በሕይወት ያለው ነው፣ የአንቺ የሞተው ነው' ትላለች፤ ያችኛዪቱ ደግሞ፣ 'አይደለም የአንቺ ልጅ ሞቶአል፣ በሕይወት ያለው የእኔ ነው' ትላለች" አለ።

²⁴ከዚያም ንጉሡ፣ "እንግዲያውስ ሰይፍ አምጡልኝ" አለ፤ ለንጉሡም ሰይፍ አመጡለት። ²⁵በዚህ ጊዜ ንጉሡ፣ "በሉ በሕይወት ያለውን ልጅ ከሁለት ክፈሉና ለአንዱ ግማሹን፣ ለሌላዪቱም ግማሹን ስጡ" ብሎ አዘዘ።

²⁶በሕይወት ያለው ልጅ እናት ለልጇ እጅግ ስለራራች ንጉሡን፣ "ጌታዬ ሆይ፤ እባክህ በሕይወት ያለውን ሕፃን ለእርሷ ስጣት፤ አትግደለው" አለች።

ሌላዪቱ ግን፣ "ለእኔም ሆነ ለአንቺ አይሰጥም፤ ሁለት ላይ ይከፈል!" አለች።

²⁷ከዚህ በኋላ ንጉሡ፣ "በሉ በሕይወት ያለውን ሕፃን ለመጀመሪያዪቱ ሴት ስጧት፤ አትግደሉት፤ እናቱ እርሷ ናት" አለ።

²⁸እስራኤላውያን ሁሉ ንጉሡ የሰጠውን ፍርድ ሲሰሙ ፈሩት፤ ፍትሕ ለመስጠት የእግዚአብሔር ጥበብ የታደለ መሆኑን አይተዋልና።

የሰሎሞን ሹማምት

4 ንጉሥ ሰሎሞን በእስራኤል ሁሉ ላይ ነገሠ፤ ²ዋና ዋና ሹማምቱም እነዚህ ነበሩ፤

የሳዶቅ ልጅ ዓዛርያስ፣ ካህን፤
³የሺሻ ልጆች ኤሊሖሬፍና አኪያ፣
ጸሓፊዎች፤
የአሒሉድ ልጅ ኢዮሣፍጥ፣ ታሪክ
ጸሓፊ፤
⁴የዮዳሄ ልጅ በናያስ፣ የሰራዊቱ ዋና
አዛዥ፤
ሳዶቅና አብያታር፣ ካህናት፤
⁵የናታን ልጅ ዓዛርያስ፣ የአውራጃ
ገገቦች የበላይ ጎላፊ፤
የናታን ልጅ ዛቡድ፣ ካህንና የንጉሡ
የቅርብ አማካሪ፤
⁶አሒሳር፣ የቤተ መንግሥቱ ሹም፤
አብዳ የተባለ የኢዮአቄም ልጅ፣
የግብር ሹም፤
⁷ሰሎሞን ለመላው እስራኤል ዐሥራ
ሁለት ገዥዎች ሾመ፤ እነርሱም
ለንጉሡና ለቤተ መንግሥቱ ሁሉ
ምግብ ያቀርቡ ነበር፤ እያንዳንዱ
ለዓመት አንድ ወር ተራ ነበረው።
⁸የገዥዎቹ ስም ይህ ነው፤
የኤፍሬም ኰረብታ አገር፣ የሁር ልጅ፤
⁹የማካዝ፣ የሻዓልቢም፣ የቤትሳሚስ፣
የኤሎንቤትሐናን አገር፣ የዴቃር
ልጅ፤
¹⁰የአሩቦት፣ የሶኮና የሔፌር ምድር
ሁሉ፣ የሔሴድ ልጅ፤
¹¹የዶር ኰረብታ አገር፣ የአቢናዳብ
ልጅ፤ እርሱም የሰሎሞን ልጅ
ጣፋት ሚስት ነበረች፤
¹²የታዕናክ፣ የመጊዶ፣ የቤትሳንና
ከጸሬታን አጠገብ ያለው የኢይዝራኤል
ምድር ሁሉ፣ ከቤትሳን እስከ አቤልመሖላ
እስከ ዮቅምዓም ማዶ ያለው፣ የአሒሉድ
ልጅ በዕና፤
¹³የራሞትገለዓድ፣ የገለዓድ የምናሴ
ልጅ የያዕር መንደሮች፣ የባሳን
ክልል ያለው የአርጎብ ምድር ሁሉ፣
ከቅጥርና ከናስ መወርወሪያ ጋራ
ስድሳ ታላላቅ ከተሞች፣ የኡሪ ልጅ
ጌቤር፤
¹⁴የማሃናይም፣ የዕዶ ልጅ አኪናዳብ፤
¹⁵የንፍታሌም፣ የአሒማዓጽ፣ ሰሎሞን
ባሴማት የተባለችውን የአልዓዛር
ልጅ የአኪማዓጽን ሴት ልጅ
አግብቶ ነበር፤
¹⁶የአሴርና የአሎት፣ የኩሳይ ልጅ
ባዕና፤
¹⁷የይሳኮር፣ የፋሩሕ ልጅ ዮሣፍጥ፤
¹⁸የብንያም፣ የኤላ ልጅ ሰሜኢ፤
¹⁹የኤፍሬም ልጅ የኡሪ፣ የገለዓድ
ምድር፣ የአሞራውያን ንጉሥ
የሴዎንና የባሳን ንጉሥ የዐግ
ምድር፤ በዚህ ምድር ውስጥ
የነበረው ገዥ ብቻ ነበር።

²⁰ይሁዳና እስራኤል ብዙ ነበሩ፤ ቍጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ ነበር፤ ሁሉም ይበሉ ይጠጡ ደስም ይሰኙ ነበር።

የሰሎሞን ግዛት

4 ²¹ሰሎሞንም ከኤፍራጥስ ወንዝ ጀምሮ እስከ ፍልስጥኤማውያን ምድር፣ እስከ ግብጽ ዳርቻ ድረስ ያሉትን መንግሥታት ሁሉ ገዛ፤ ለግብጽ ንጉሥ ግብር ይገብሩ ነበር፤ በሰሎሞንም ዘመን ሁሉ ተገዥ ሆነው ኖሩ።

²²የሰሎሞን የዕለት ምግብ ይህ ነበር፤ ሠላሳ መስፈሪያ ዱቄት፣ ስልሳ መስፈሪያ ጥሩ ዱቄት፣ ²³አሥር የሰቡ በሬዎች፣ ሃያ ከግጦሽ የመጡ በሬዎች፣ መቶ በጎች፣ ከዚህም በተጨማሪ ሚዳቋ፣ ዋላ፣ ፍየል፣ የሰቡ ወፎች። ²⁴ከኤፍራጥስ ማዶ ከጠፍሐ እስከ ጋዛ ድረስ በወንዙ ማዶ ያሉትን ነገሥታት ሁሉ ገዛ፤ በዙሪያውም ሁሉ ሰላም ነበር። ²⁵በሰሎሞን ዘመን ሁሉ ይሁዳና እስራኤል ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ እያንዳንዱ በገዛ ወይኑና በለሱ ሥር ተቀምጦ በሰላም ኖረ።

²⁶ሰሎሞን ለሠረገሎቹ አርባ ሺህ የፈረስ ጋጥ፣ ዐሥራ ሁለት ሺህ ፈረሰኞች ነበሩት። ²⁷ገዥዎቹም ለንጉሥ ሰሎሞንና ወደ ንጉሡ ማዕድ ለሚመጡት ሁሉ ምግብ ያቀርቡ ነበር፤ እያንዳንዱ በተመደበለት ወር ተራ ይሠራ ነበር፤ ምንም ነገር አይጐድልም ነበር። ²⁸ገዥዎቹ ለየራሳቸው ለሠረገሎቹና ለፈረሶቹ የሚያስፈልገውን ገብስና ገለባ ወደሚገባበት ቦታ ያመጡ ነበር።

የሰሎሞን ጥበብ

²⁹እግዚአብሔር ለሰሎሞን እጅግ ብዙ ጥበብና ማስተዋል፣ ከባሕር ዳር አሸዋ የሚያህል ሰፊ ዕውቀት ሰጠው። ³⁰የሰሎሞን ጥበብ ከምሥራቅ ሰዎች ሁሉ ጥበብ፣ ከግብጽም ጥበብ ሁሉ ይበልጥ ነበር። ³¹ከሰዎች ሁሉ ይልቅ ጠቢብ ነበር፤ ከኤዝራዊው ከኤታን፣ ከማሖል ልጆች ከሄማን፣ ከከልቆል፣ ከዳርዳ ይልቅ ጠቢብ ነበር፤ ዝናውም በአካባቢው ሁሉ ተሰማ። ³²ሦስት ሺህ ምሳሌዎችን ተናገረ፤ የዘፈኖቹም ቍጥር አንድ ሺህ አምስት ነበር። ³³ስለ ዕፀዋት ሁሉ ከዝግባ ዛፍ ጀምሮ በግንቡ ላይ እስከሚበቅለው ሂሶጵ ድረስ ተናገረ፤ ስለ እንስሳትም፣ ስለ ወፎችም፣ ስለ ተሳቢዎችም፣ ስለ ዓሦችም ተናገረ። ³⁴ከምድር ነገሥታት ሁሉ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከመጡት ሰዎች ሁሉ ዘንድ ዝናው ይሰማ ነበር።

3፥8 ዘፍ12፥2፤ ዘዳ7፥6፤ 1ዜና27፥23
3፥9 ዘዳ1፥16፤ 2ሳሙ14፥17፤ 2ቆሮ2፥16፤ ዕብ5፥14፤ ያዕ1፥5
3፥11 1ዜና22፥12፤ ያዕ4፥3
3፥12 2ሳሙ14፥20፤ 1ነገ4፥29-30፣31፤ 5፥12፤ 10፥23፤ መክ1፥16፤ 1ዮሐ5፥14-15
3፥13 1ነገ10፥23፤ 2ዜና9፥22፤ ነህ13፥26፤ ምሳ3፥12፣16፤ 8፥18፤ ማቴ6፥33፤ ኤፌ3፥20
3፥14 1ነገ9፥4፤ መዝ25፥13፤ 61፥6፤ 101፥2፤ 128፥1፤ ምሳ3፥12-16
3፥15 ሮሜ5፥3፤ ዘፍ28፥16፤ ዘሌ6፥8፣13፤ 7፥11-21፤ ኢሳ1፥3፤ 9፥8፤ 2፥18፤ 5፥8፤ 6፥14፤ 9፥17፤ ዳን5፥1
3፥26 መዝ102፥13፤ ኢሳ49፥15፤ 63፥15፤ ኤር3፥12፤ 31፥20፤ ሆሴ11፥8
3፥28 2ሳሙ14፥20፤ ቈላ2፥3
4፥2 1ነገ12፥6፤ 1ዜና6፥10፤ 2ዜና26፥17፤ ኢዮ12፥12
4፥3 2ሳሙ8፥16፣17
4፥4 2ሳሙ8፥17፣18

*3፥15 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል

3፥9 ለባሪያህ አስተዋይ ልብ ስጠው፤ ሰሎሞን አባቱን የጀመረው እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ በመጣልና እርሱንም በመውደድ ነበር (ሮሜ 3)። ጥበብና አስተዋይ ልብ ይኖረው ዘንድ ጸለየ (ሮሜ 5፥9)፤ እግዚአብሔርም በልመናው ተደሰተ (ሮሜ 10)፤ ጌሎቱንም ሰምቶ መለሰለት (ሮሜ 11፥14)፤ ይሁን እንጂ ሰሎሞን ከእግዚአብሔር የጥበብ ስጦታ ማግኘቱ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ሕይወት እንዲኖር ዋስትና አልነበረም፤ ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር ሰሎሞንን፣ "በመንገዴ ብትሄድ" ረጅም ዕድሜ ይሆንልሃል አለው (ሮሜ 14)። ሰሎሞን በኋለኛ ዘመኑ ታማኝነቱን በማጉደሉ፣ እግዚአብሔር ለእርሱ ይሆንለት ዘንድ የፈቀደው ሁሉ ሙሉ በሙሉ ሳይሳካለት ቀረ (11፥1-8)።

3፥10 ጌታ ደስ አለው፤ ምእመናን የእግዚአብሔርን ጥበብና አስተዋይ ልብ ይኖራቸው ዘንድ ሲጸልዩ፣ እግዚአብሔር ደስ ይለዋል፤ "ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጎድለው፣ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉም የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፤ ለእርሱም ይሰጠዋል (ያዕ 1፥5 ይመ፣ ከምሳ 2፥2-6፣ 3፥15፣ ከሉቃ 12፥31፣ ከኤፌ 5፥17፣ ከያዕ 3፥17 ጋር ያነጻጽሩ)።

6 አሒሳር፣ የቤተ መንግሥቱ አዛዥ፤
የዓብዳ ልጅ አዶኒራም የግዳጅ
ሥራ ተቈጣጣሪ።
7 እንዲሁም ሰሎሞን ለንጉሡና ለንጉሡ
ቤት የሚሆነውን ቀለብ ከመላው እስራኤል
የሚሰበስቡ ዐሥራ ሁለት የአውራጃ ገገርች
ነበሩት፤ እነዚህም እያንዳንዳቸው በዓመት
ውስጥ የወር ቀለብ የሚያቀርቡ ነበሩ።
8 ስማቸውም እንደሚከተለው ነው፤
ቤንሑር፣ በኰረብታማው በኤፍሬም
ምድር፤
9 ቤንጼቄር፣ በማቃጽ፣ በሻዓልቢምና
በቤትሳሜስ፣ በኤሎንቤትሐናንና፤
10 ቤንሔሴድ፣ በአሩቦት ውስጥ
የሚገኙት ሰኰትና የአፌር አገር
በሙሉ የእርሱ ነበር፤
11 ቤን አሚናዳብ፤ በናፎትዖ ዶርን፣
እርሱም የሰሎሞንን ልጅ ጣፈትን
አግብቶ የነበረ ነው፤
12 የአሒሉድ ልጅ በዓና፣ በታዕናክና
በመጊዶ እንዲሁም ከጻርታን
ቀጥሎ ቍልቍለ እስከ
ኢይዝራኤል ባለው በቤትሳን
ሁሉ፣ ከዚያም ዮቅምዓምን ተሻግሮ
እስከ አቤልምሖላና ድረስ፤
13 ቤንጌበር፣ በገለዓድ ራሞት ከተማ
እዚያው ገለዓድ ውስጥ የምናሴ
ልጅ የኢያዕር መንደሮች፣
በባሳንም የአርጎብ አውራጃ
እንዲሁም በሮቻ ቸው የናስ
መወርወሪያ በሆኑ ሥልሳ ባለ
ቅዋር ታላላቅ ከተሞች፤
14 የዓዶ ልጅ አሒናዳብ፤
በማሃናይም፣
15 አኪማአስ በንፍታሌም፣ እርሱም
የሰሎሞንን ልጅ ባስማትን አግብቶ
የነበረ ነው፤
16 የኩሲ ልጅ በዓና፣ በአሴርና
በበዓሎት፣
17 የፋሩዋ ልጅ ኢዮሣፍጥ በይሳኮር፣
18 የኤላ ልጅ ሳሚ በብንያም፣
19 የኡሪ ልጅ ጌበር፤
በአሞራውያን ንጉሥ በሴዎን
ምድር፣ በባሳን ንጉሥ በዐግ
አገር፣ እርሱም የአውራጃው ብቸኛ
ገዥ ነበር።

4፥6 ዘፍ41፥40፤ 49፥15፤ 2ሳሙ20፥24
4፥7 ቍ 27
4፥8 ኢሱ24፥33
4፥9 ኢሱ15፥10፤ መሳ1፥35
4፥10 ኢሱ12፥17፤ 15፥35
4፥11 ኢሱ11፥2
4፥12 ኢሱ3፥16፤ 17፥11፤ መሳ7፥22፤ 1ዜና6፥68
4፥13 ዘኍ32፥40፡41፤ ዘዳ3፥4
4፥14 ኢሱ13፥26
4፥15 2ሳሙ15፥27
4፥16 2ሳሙ15፥32
4፥18 1ነገ1፥8
4፥19 ዘዳ3፥8፤10፡ ኢሱ12፥2፡4
4፥20 ዘፍ12፥2፤ 32፥12፤ 1ዜና22፥9
4፥21 ዘፍ2፥14፤ ዘዳ23፥31፤ መሳ3፥15፤ 2ዜና9፥26፤ ዕዝ4፥20፤ መዝ72፥8፡11፤ ሰቆ1፥1፤ ሕዝ16፥13
4፥22 1ነገ10፥5
4፥23 ነህ5፥18
4፥24 ኢሱ14፥15፤ 2ነገ15፥16
4፥25 ዘዳ8፥8፤ መሳ20፥1፤ 2ነገ18፥31፤ 1ዜና22፥9፤ መዝ105፥33፤ ኢሳ36፥16፤ ኤር5፥17፤ 23፥6፤ ሕዝ28፥26፤ 39፥26፤ ኢል2፥22፤ ሚክ4፥4፤ ዘካ3፥10
4፥26 ዘዳ17፥16
4፥27 ቍ 7
4፥29 ዘፍ32፥12፤ 1ነገ3፥12

ለሰሎሞን በየቀኑ የሚገባለት ቀለብ

20 የይሁዳና የእስራኤል ሕዝቦች
ብዛታቸው እንደ ባሕር ዳር አሸዋ ሆነ፤
ይበሉ፣ ይጠጡና ይደሰቱም ነበር።
21 ሰሎሞንም ከወንዙ[ሀ] አንሥቶ እስከ
ፍልስጥኤማውያን ምድርና፣ ከዚያም እስከ
ግብፅ ዳርቻ ያሉትን መንግሥታት ሁሉ
ገዛ፤ እነዚህም አገሮች ግብር አመጡለት፤
በሕይወት ዘመኑም ሁሉ ተገዙለት።
22 ለሰሎሞን በየቀኑ የሚገባለትም ቀለብ
ይህ ነበር፤ ሠላሳ ኮሮ[ሁ] ማለፊያ ዱቄት፣
ሥልሳ ኮሮ[ሂ] መናኛ ዱቄት፣ 23 ዐሥር ቅልብ
ሰንጋዎች፣ ሃያ ግጦሽ መሬት ላይ የሚውሉ
በሬዎች፣ መቶ በግና ፍየል እንዲሁም
ዋሊያ፣ ሚዳቋ፣ የበረሓ ፍየልና ምርጥ
አዕዋፍ። 24 ከወንዙ በስተ ምዕራብ፣ ከቲፍሳ
እስከ ጋዛ ያሉትን መንግሥታት ስለ ገዛ፣
በሁሉም አቅጣጫ ሰላም ሆኖለት ነበር።
25 በሰሎሞን ዘመን ሁሉ ከዳን እንሥቶ
እስከ ቤርሳቤህ ያለው ይሁዳና እስራኤል፣
እያንዳንዱ ሰው ከወይኑና ከበለሱ ጥላ ሥር
በሰላም ለመኖር በቃ።
26 ሰሎሞን ሠረገላ የሚጐትቱ ፈረሶች
የሚያድሩበት አራት ሺህ ጋጣና ዐሥራ
ሁለት ሺህ ፈረሶች[ሀ] ነበሩት።
27 የየአውራጃው ሹሚምቱም፣ በየወር
ተራቸው ንጉሡን ሰሎሞንንና ወደ ንጉሡ
ማእድ የሚቀርቡትን ሁሉ ምንም ሳያንዱሉ
ይቀልቡ ነበር፤ 28 እንዲሁም ለሠረገላ ፈረሶችና
ለፈጣን ፈረሶች የተመደበውን ገብስና
ሳር ከተፈለገው ቦታ ድረስ ያመጡ ነበር።

የሰሎሞን ጥበብ

29 እግዚአብሔር ለሰሎሞን ጥበብንና እጅግ
ታላቅ ማስተዋልን እንዲሁም በባሕር
ዳር እንዳለ አሸዋ የልብ ስፋትን ሰጠው።

[ሀ] 4፥11 ወይም ቦናፎት ቋመት ተብሎ ሊተረጐም ይችላል
[ሀ] 4፥21 በዚህና በቍ 24 ላይ የተጠቀሰው የኤፍራጥስ ወንዝ ነው።
[ሁ] 4፥22 6.6 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ሂ] 4፥22 13.2 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ሀ] 4፥26 ዕብራይስጡና እንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉሞች አርባ ይላሉ።
[ሀ] 4፥26 ወይም ሠረገለኞች ተብሎ መተርጐም ይችላል።

4፥24 **በሁሉም አቅጣጫ ሰላም**፤ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት እስራኤል በጎያልነት፣ በሰላምና በብልጽግና ከፍተኛ አመርቃ ላይ ደረሰች (ቍ 20-28)። በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ የሰሎሞን አገዛዝ ስኬታማ ነበር፤ ይሁን እንጂ ሰሎሞን ወደ ጣዖት አምልኮ በማዘንበሉ፣ አገዛዙ በመንፈሳዊ ረገድ ሲታይ ያልተሳካ ነው (11፥1-8)።

4፥29 **እግዚአብሔር ለሰሎሞን ... ሰጠው**፤ ከቍጥር 29-34 እንደምንረዳው የሰሎሞን ጥበብ የማስተዋልን ጥልቀት፣ የንጉሥነትንም ጎላፊነት አካቶ የያዘ ነበር (ከ3፥9 *ጋር ያነጻጽሩ*)። ሦስት ሺህ ምሳሌዎችን ጻፈ (ቍ 32)፤ ከእነዚህም ብዙዎቹ በመጽሐፈ ምሳሌ ላይ ሰፍረው ይገኛሉ። (1) እንዲህ ያለ ጥበብ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ሰሎሞን፣ በመጨረሻ እግዚአብሔርን ትቶ እንዴት ወደ ጣዖት አምልኮ ይገባል? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡ ጥበብን ገንዘብ ማድረግና ጥበብን መከተል የተለያዩ ነገሮች እንደ ሆኑ ግልጽ ነው። የሰሎሞን ትልቁ ጥፋቱ በየትኛውም ዐይነት የሕይወቱ ፈርጅ መንፈሳዊ ጥበቡን ሥራ ላይ አለማዋሉ ነው። በዘመኑ እጅ የሌለው ጥበበኛ ቢሆንም እንኳ፣ በጥበብ እንደተመላለሱት እንዳንድ የእግዚአብሔር ታማኝ ሰዎች አልኖረም።

(2) ሰሎሞን ወደ መንፈሳዊ ድቀት የገባው ቀድሞውኑ አያሌ ባዕድ ሴቶችን በማግባቱ ነው (11፥1-8)። በዚህም ጉዳይ ሁለት ነገሮች ተሳስረው ተገኝተዋል፡ (ሀ) ይህን ያደረገው በፖለቲካም ሆነ በሙር ኀይል ረገድ ግንባር ለመፍጠር ሲሆን፣ እግዚአብሔር

30የሰሎሞን ጥበብ ከምሥራቅ ሰዎች ሁሉ
ጥበብ በጣም የላቀ ከግብፅም ጥበብ ሁሉ
የበለጠ ነበር፤ 31እርሱም ከማንም ሰው ይልቅ
ጥበበኛ ነበር፣ ከኢይዝራኤላዊው ከኤታን፣
ከማሑል ልጆች ከሄማንና ከከልቀድ ደግሞም
ከደራል ይልቅ ጥበበኛ ነበር፤ ዝናውም
በዙሪያው ባሉት አሕዛብ ሁሉ ተሰማ።
32እርሱም ሦስት ሺህ ምሳሌዎችን ተናገረ፤
የመሓልዩም ቊጥር ሺህ አምስት ነበር።
33ከሊባኖስ ዝግባ አንሥቶ በቅጥር ግንብ
ላይ እስከሚበቅለው ሂሶጵ ስለ ዕፀዋት
ተናግሮአል፤ እንዲሁም ስለ እንስሳትና ስለ
ወፎች፣ በሆዳቸው ስለሚሳቡ እንስሳትና
ስለ ዓሦችም ተናግሮአል፤ 34ጥበቡን
ከሰሙት ከዓለም ነገሥታት ሁሉ የተላኩ፣
የየአገሩ ሰዎች ሁሉ የሰሎሞንን ጥበብ
ለማድመጥ መጡ።

ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የተደረገ ዝግጅት

5፥1-16 ተጓ ምብ — 2ዜና 2፥1-18

5 የጢሮስ ንጉሥ ኪራም በዘመኑ ሁሉ
ለዳዊት ወዳጅ ስለ ነበር፣ ሰሎሞን
በአባቱ እግር ለመተካት መቀባቱን በሰማ
ጊዜ፣ መልእክተኞቹን ወደ ሰሎሞን ላከ።
2ሰሎሞንም እንዲህ የሚል መልእክት ወደ
ኪራም መልሶ ላከ፤

3"አባቴ ዳዊት በዙሪያው ሁሉ
ስላጠመው ጦርነት የተነሣ፣
እግዚአብሔር ጣላቶቹን ከእግሩ
በታች እስኪጥልለት ድረስ
በስሙላኩ ለእግዚአብሔር ስም ቤተ
መቅደስ መሥራት እንዳልቻለ
ታውቃለህ። 4አሁን ግን አምላኪ
እግዚአብሔር በዙሪያዬ ሁሉ ሰላም
ሰጥቶኛል፤ ጠላትም የለብኝም።
5እነሆ፣ እግዚአብሔር ለአባቴ
ለዳዊት፣ 'ለስሜ ቤተ መቅደስ
የሚሠራልኝ ከአንተ ቀጥሎ
በዙፋንህ የማስቀምጠው ልጅህ
ነው' ብሎ እንደ ነገረው፣ በስሙላኪ
ለእግዚአብሔር ስም ቤተ መቅደስ
ለመሥራት አስቤአለሁ።
6"ስለዚህ የሊባኖስ ዝግባ
እንዲቈረጥልኝ ትእዛዝ ስጥ፤
ሰዎቼ ከሰዎችህ ጋር አብረው
ይሠራሉ፤ የሰዎችህንም ደመወዝ
አንተ በወሰንኸው እከፍልሃለሁ፤

4፥30 ዘፍ25፥6፣ መሳ6፥3፣ ኢሳ19፥11፣ ዳን1፥20፣ ማቴ2፥1፣ ሐሥ7፥22
4፥31 1ነገ3፥12
4፥32 መዝ78፥63፣ ምሳ1፥1፣ 10፥1፣ 25፥1፣ መክ12፥9፣ ሚሕ1፥1፣ ሕዝ33፥32
4፥33 ዘሌ14፥49
4፥34 2ዜና9፥23
5፥1 2ሳሙ5፥11
5፥3 2ሳሙ7፥5፣ 22፥40፣ 1ዜና22፥8፣ 28፥3፣ መዝ8፥6፣ 110፥1፣ ማቴ22፥44፣ 1ቆሮ15፥25
5፥4 ኢሱ14፥15፣ 1ነገ11፥14፣23፣ 1ዜና22፥9፣ ሉቃ2፥14
5፥5 ዘዳ12፥5፣ 2ሳሙ7፥13፣ 1ዜና17፥12፣ 1ቆሮ3፥16፣ ራእ21፥22
5፥6 1ዜና14፥1፣ 22፥4

5፥7 1ነገ10፥9፣ ኢሳ60፥6
5፥9 ቊ11፣ ዕዝ3፥7፣ ሕዝ27፥17፣ ሐሥ12፥20
5፥11 ቊ9
5፥12 ኢሱ9፥7፣ 1ነገ3፥12፣ 15፥19፣ አሞ1፥9
5፥13 ዘፍ49፥15፣ ዘሌ25፥39፣ 1ነገ9፥15
5፥14 2ሳሙ20፥24፣ 1ነገ4፥6፣ 2ዜና10፥18
5፥16 1ነገ9፥23

ከሰዎቼ መካከል እንደ ሲዶናውያን
ዕንጨት በመቍረጥ እስከዚህ
የሠለጠነ ሰው አለመኖሩን ራስህም
ታውቃለህና።"
7ኪራም የሰሎሞን መልእክት በደረሰው
ጊዜ እጅግ ደስ ስላለው፣ "ይህን ታላቅ
ሕዝብ እንዲመራ ለዳዊት ጥበበኛ ልጅ
ሰጥቶታልና ዛሬ ምስጋና ለእግዚአብሔር
ይግባው" አለ።
8ስለዚህ ኪራም፣ ለሰሎሞን እንዲህ
ሲል ላከበት፤
"የላክኸው መልእክት
ደርሶኛል፤ የዝግባውንና
የጥዱን ግንድ በማቅረብ ረገድ
የምትፈልገውን ሁሉ ለማድረግ
ዝግጁ ነኝ፤ 9ሰዎቼ ግንዱን
ከሊባኖስ እስከ ባሕሩ ድረስ
ጐትተው ያወርዳሉ፤ እኔም
ግንዱ ሁሉ ታስሮ አንተ እስክ
ወሰንኸው ስፍራ በባሕር ተንሳፎ
እንዲደርስ አደርጋለሁ፤ እዚያም
እኔ እፈታዋለሁ፣ አንተም
ትወስደዋለህ፤ አንተም ለቤተ
ሰቤ ቀለብ በመስጠት ፍላጎቴን
ታሟላለህ።"
10በዚህ ሁኔታ ኪራም ለሰሎሞን
የሚያስፈልገውን የዝግባና የጥድ ግንድ
በሙሉ ያቀርብለት ጀመር፤ 11ሰሎሞን
ደግሞ ለኪራም ቤተ ሰው ቀለብ እንዲሆን
ሃያ ሺህ የቆሮስ መስፈሪያ* ስንዴ፣ ሃያ ሺህ
ኮር† ንጹሕ የወይራ ዘይት ሰጠው። ይህን
ባለ ማቋረጥ በያመቱ ለኪራም ይሰጥ ነበር።
12እግዚአብሔርም በገባለት ተስፋ መሠረት
ለሰሎሞን ጥበብን ሰጠው፤ በኪራምና
በሰሎሞን መካከልም መልካም ግንኙነት
ነበር፤ ሁለቱም ቃል ኪዳን አደረጉ።
13ንጉሥ ሰሎሞን ከመላው እስራኤል
የጕልበት ሠራተኞችን መለመለ፤
ቍጥራቸውም ሠላሳ ሺህ ነበር። 14እነዚህንም
አንድ ወር በሊባኖስ እንዲሠሩ፣ ሁለት ወር
በቤታቸው እንዲያርፉ በማድረግ፣ ዐሥር
ዐሥር ሺዉን ወር ተራ አግብቶ ላካቸው።
የጕልበት ሠራተኞቹም አለቃ አዶኒራም
ነበር። 15ሰሎሞንም በኰረብታማው አገር
ሰባ ሺህ ተሸካሚዎችና ሰማንያ ሺህ
ድንጋይ ጠራቢዎች ነበሩት፤ 16እንዲሁም

*5፥11 4400 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።
†5፥11 ሰብራይስጡና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ሃያ ኮር ይላሉ (2ዜና 2፥10 ይመ)
‡5፥11 440 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።

ክዕዳን ጥቃት ሊጠብቀው የሚችል መሆኑን ማመን
እቃተው። (ለ) ሌትን የሚያሳድድ በመሆኑም ፍትወተ
ሥጋውን ለመግታት አልቻለም፣ ይህም በአንድ በተወሰነ
ወቅት የአባቱ የዳዊት ችግር ነበር።

5፥5 ለእግዚአብሔር ስም ቤተ መቅደስ ለመሥራት ከምዕ 5—8 ባለው ክፍል እግዚአብሔር
ዘወትር ሀልዎቱንና ክብሩን የሚገልጽበትን ቤተ መቅደስ
ለመሥራት ስለሰሞን በቅደም ተከተል ያደረገው ከንዋኔ
ተመዝግቦ ይገኛል። ቤተ መቅደሱ የእግዚአብሔር
ማደሪያና ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ በአንድ
ላይ የሚሆኑበት ስፍራ ነበር (ከ8፥15-21፣
ከ2ሳሙ 7፥12-13 ጋር ያነጻጽሩ)፣ የተሠራውም
በኢየሩሳሌም በሞሪያ ተራራ ሲሆን (2ዜና 3፥1 ይመ፣
ከዘፍ 22፥2 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ለማጠናቀቅ ሰባት ዓመት
ፈጅቶአል (6፥38፣ 6፥2 እና ማብ ይመ)። እግዚአብሔር
ለዳዊት የቤተ መቅደሱን ንድፍ በመንፈስ ቅዱስ ገለጠለት
(1ዜና 28፥12)፣ ዳዊትም ከመሞቱ በፊት ለማንበታው
አስፈላጊ የሆነውን ብዙውን ነገር አዘጋጀ።

ሥራውን የሚቈጣጠሩ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ፣ ኀላፊዎች ነበሩ። 17እነርሱም በንጉሡ ትእዛዝ ለቤተ መቅደሱ መሠረት የሚሆን ታላላቅና ምርጥ ድንጋይ ፈልፍለው በማውጣት የተጠረበ ድንጋይ አዘጋጁ። 18የሰሎሞንና የኪራም የእጅ ባለ ሙያዎች እንዲሁም የጌባል ሰዎች[ኦ] ለቤተ መቅደሱ የሚያስፈልገውን ዕንጨትና ድንጋይ ፈልጠው አዘጋጁ።

ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን መሥራት ጀመረ

6፥1-29 ተጓ ምብ — 2ዜና 3፥1-14

6 እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡ በአራተ መቶ ሰማንያ[ሐ] ዓመት፣ ሰሎሞን በእስራኤል ላይ በነገሠ በአራተኛው ዓመት፣ ዚፍ በተባለው በሁለተኛው ወር ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ መሥራት ጀመረ።

2ንጉሥ ሰሎሞን ለእግዚአብሔር የሠራው ቤተ መቅደስ ርዝመቱ ሥልሳ ክንድ፣ ወርዱ ሃያ ክንድ፣ ቁመቱ ሠላሳ ክንድ[መ] ነበር።

3በቤተ መቅደሱ ዋነኛ አዳራሽ ፊት ለፊት ያለው በረንዳ ወርዱ እንደ ቤተ መቅደሱ ወርድ ሁሉ ሃያ ክንድ[ሠ] ሲሆን፣ ርዝመቱ ዐሥር ክንድ[ረ] ወደ ውጭ የወጣ ነበር። 4ለቤተ መቅደሱም ባለ ዐይነ ርግብ መስኮቶች አበጀ። 5በዋናው ቤተ መቅደስና በቅድስተ ቅዱሳኑ ግድግዳ ዙሪያ ልዩ ክፍሎች ያሉት ተቀጥላ ግንብ ሠራ። 6የምድር ቤቱ ወርድ አምስት ክንድ፣[ሰ] የመካከለኛው ፎቅ ስድስት ክንድ፣[ሸ] የሦስተኛው ፎቅ ሰባት ክንድ[ቀ] ነበር፤ የቤተ መቅደሱን ግድግዳ ዘልቆ እንዳይገባም፣ ከቤተ መቅደሱ ግንብ ውጭ ዙሪያውን አርከኖች አደረገ።

7ቤተ መቅደሱ የተሠራው እዚያው ድንጋዩ ተቈፍሮ ከወጣበት ቦታ በተዘጋጀ ድንጋይ በመሆኑ የመራጃ፣ የመሮ ወይም የሌላ ብረት ነክ መሣሪያ ድምፅ በቤተ መቅደሱ አካባቢ አልተሰማም ነበር።

5፥17 1ነገ16፥7፣ 1ዜና22፥2
5፥18 ኢሳ13፥5፣ 2ሳሙ5፥11
6፥1 ዕዝ3፥8፤ 5፥11
6፥2 ዘፀ26፥1
6፥3 ሕዝ40፥49
6፥4 ሕዝ41፥16
6፥5 ኤር35፥2፣ ሕዝ41፥56
6፥7 ዘፀ20፥25፣ ዘዳ27፥5

6፥9 ማሕ1፥17
6፥11 1ነገ12፥22፣ 13፥20፣ 16፥1፣ 17፥2፣ 21፥17፣ ኤር40፥1
6፥12 2ሳሙ7፥12-16፣ 1ነገ9፥5፣ 11፥10
6፥13 ዘሌ26፥11፣ ዘዳ31፥6፣ ዮሐ14፥18፣ ዕብ13፥5
6፥14 1ዜና28፥20፣ 2ዜና5፥1፣ ሐሥ7፥47
6፥15 1ነገ7፥7፣ ሕዝ41፥1516
6፥16 ዘፀ26፥33

8የምድር ቤቱ መግቢያ በስተ ደቡብ በኩል ባለው የቤተ መቅደሱ ጐን ሲሆን ወደ መካከለኛውና ከዚያም ወደ መጨረሻው ፎቅ የሚያስወጣ ደረጃ ነበረው። 9ቤተ መቅደሱንም በዚሁ ሁኔታ ሠርቶ ጨረሰ፤ ለጣራው ተሸካሚ አደረገለት፤ በዝግባ ሳንቃም ከደነው። 10በቤተ መቅደሱም ዙሪያ በሙሉ፣ ቁመታቸው አምስት አምስት ክንድ የሆነ ክፍሎች ሠራ፤ እነዚህንም ከቤተ መቅደሱ ጋር በዝግባ አግዳሚ ዕንጨቶች አያያዛቸው።

11የእግዚአብሔርም ቃል እንዲህ ሲል ወደ ሰሎሞን መጣ፤ 12"ስለምትሠራው ስለዚህ ቤተ መቅደስ ሥርዐቴን ብትከተል፣ ፍርዴን ብተግባር ብትገልጸው፣ ትእዛዛቴን ብትጠብቅና ብትመላለስባቸው ለአባትህ ለዳዊት የሰጠሁትን ተስፋ በአንተ እፈጽመዋለሁ፤
13በእስራኤላውያን መካከል እኖራለሁ፤
ሕዝቤን እስራኤልንም
አልተውም።"

14ስለዚህ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠርቶ ፈጸመ፤ 15የውስጡን ግድግዳ ከቤተ መቅደሱ ወለል እስከ ጣራው ድረስ በዝግባ ሳንቃ ለበጠ፤ የቤተ መቅደሱንም ወለል የጥድ ሳንቃ አስበሰው። 16በቤተ መቅደሱም ውስጥ በስተኋላ በኩል፣ ሃያውን ክንድ ቅድስተ ቅዱሳን እንዲሆን፣ ከወለሉ[ተ] እንሥቶ እስከ ጣራው ድረስ በዝግባ ሳንቃዎች ጋረደው።[ቸ]

*5፥16 ዕብራይስጡና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ይላሉ።
^5፥18 ይኸውም ቢብሎስ የተባለው ስፍራ ነው
ᵇ6፥1 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም አራት መቶ አርባ ይላሉ
ᶜ6፥2 ርዝመቱ 27 ሜትር፣ ወርዱ 9 ሜትር እንዲሁም ቁመቱ 13.5 ሜትር ያህል ነው
ᵈ6፥3 16.9 ሜትር ያህል ነው
ᵉ6፥3 4.5 ሜትር ያህል ነው
ᶠ6፥6 በዚህ እንዲሁም በቍ 10 እና 24 ላይ 2.3 ሜትር ያህል ነው
ᵍ6፥6 2.7 ሜትር ያህል ነው
ʰ6፥6 3.1 ሜትር ያህል ነው
ᶦ6፥8 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን የመካከለኛው ደርብ ይላሉ

6፥1 በወጡ በአራት መቶ ሰማኒያ ዓመት፣ እስራኤል ከግብፅ የወጡበት ዕለት በዚህ ጊዜ ነው ብሎ ለመወሰን ይህ ጥቅስ ቁልፍ ጥቅስ ነው። ሰሎሞን የጌታን ቤተ መቅደስ መሥራት የጀመረው በ966 ዓ.ቅ.ክ. ነው፤ ይህ ዓመት የተወሰነው ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን ሙሁራዊ ከአሥራውያን የዘመን መዛግብት ጋር በማገናዘብ ነው፤ ይኸው የአሥራውያን የዘመን መዝገብም ቅደም ተከተልን የጠበቀ ነበር። እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡት ከዚያ ጊዜ 480 ዓመት ቀደም ብሎ ነው፤ ይህም የወጡበትን ዓመት ወደ 1446 ዓ.ቅ.ክ. ገደማ ያደርሰዋል (ከሐሥ 13፥19-20 ጋር ያነጻጽሩ)።

6፥2 ለእግዚአብሔር ... ቤተ መቅደስ፣ ቤተ መቅደሱ፣ የኪዳኑን ታቦት በመያዝ በሕዝቡ ዘንድ የእግዚአብሔርን ዕልምትና ባሕርይ በትእምርትነት ይገልጣል። እግዚአብሔር በሕዝቡ ዘንድ ለመኖር ያለውን ፍላጎትና ይህም ደግሞ እውነት መሆኑን ቤተ መቅደሱ ያመለክታል (ዘሌ 26፥12 ይመ፤ ከዮሐ 14፥21-33 ጋር ያነጻጽሩ)። ቤተ መቅደሱ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባውን የኪዳን ተስፋ በገሀድ የሚያሳይ ምልክት ነው (ዘፀ 29፥45-46)፤ የተሠራውም የእግዚአብሔር ስም ማደሪያ እንዲሆን ነው (5፥5፣ 8፥16፣9፥3)። የእግዚአብሔር ስም፣ "ቅዱስ" ነው (ዘሌ 20፥3፣ 1ዜና 16፥10፣35፣ ሕዝ 39፥7)። ስለዚህ እግዚአብሔር በእስራኤል ዘንድ ቅዱስና ሕዝቡንም የሚቀድስ ተብሎ እንዲታወቅ ይፈልጋል (ዘፀ 29፥43-46፣ ሕዝ 37፥26-28)። በሰፊው የታተተውን ለመረዳት በገጽ 641 ላይ፣ "ቤተ መቅደሱ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

6፥12 ሥርዐቴን ብትከተል፣ መጽሐፈ ነገሥት አንደኛና ሁለተኛ የእግዚአብሔር ሕዝብ በተደጋጋሚ ይህን ቅድመ ሁኔታ የሳቱ መሆናቸውን በመግለጽ ዘግበው ይዘዋል (ከ2፥3-4፣ 3፥14 ጋር ያነጻጽሩ)።

17በቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት ያለው
ዋና አዳራሽ ርዝመቱ አርባ ክንድ[ሀ] ነበር።
18የቤተ መቅደሱም፣ ውስጡ በሙሉ በዝግባ
የተለበጠ ሲሆን፣ ይህም በእንቡጥ አበቦችና
በፈኩ አበቦች ቅርጽ የተጌጠ ነበር፤ በሙሉ
ዝግባ እንጂ የሚታይ ድንጋይ አልነበረም።
19በቤተ መቅደሱም ውስጠኛ ክፍል
የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት
የሚቀመጥበትን ቅድስተ ቅዱሳን ሠራ።
20ቅድስተ ቅዱሳኑም ርዝመቱ ሃያ ክንድ፣
ወርዱ ሃያ ክንድ፣ ቁመቱም ሃያ ክንድ[ነ]
ነበር፤ ውስጡን በንጹሕ ወርቅ ለበጠው፤
ከዝግባ የተሠራውንም መሠዊያ በወርቅ
ለበጠው። 21ሰሎሞንም ቤተ መቅደሱን
በውስጥ በኩል በንጹሕ ወርቅ ለበጠው፤
በወርቅ በተለበጠው ቅድስተ ቅዱሳን
ፊት ለፊትም የወርቅ ሰንሰለቶች ዘረጋ።
22ስለዚህ ውስጡን በሙሉ በወርቅ ለበጠው፤
በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ያለውን መሠዊያም
እንደዚሁ በወርቅ ለበጠው። 23በቅድስተ
ቅዱሳኑም ውስጥ ቁመታቸው ዐሥር ክንድ[ጣ]
የሆነ ሁለት የኪሩቤል ቅርጽ

ከወይራ ዕንጨት ሠራ፤ 24የአንደኛው
ኪሩብ አንዱ ክንፍ አምስት ክንድ ሲሆን፣
ሌላውም ክንፉ እንደዚሁ አምስት ክንድ
ነበር፤ ይህም ከአንዱ ክንፍ ጫፍ እስከ
ሌላው ክንፍ ጫፍ ዐሥር ክንድ ማለት ነው።
25የሁለተኛውም ኪሩብ ክንፍ እንደዚሁ ዐሥር
ክንድ ሆነ፣ ሁለቱ ኪሩቤል በመጠንና በቅርጽ
እንድ ዐይነት ነበሩና። 26የእያንዳንዱም ኪሩብ
ቁመት ዐሥር ክንድ ነበር። 27ክንፎቻቸው
እንደ ተዘረጋ፣ ኪሩቤልን ወስዶ በቅድስተ
ቅዱሳኑ አኖራቸው፤ የአንዱ ኪሩብ ክንፍ
አንዱን ግድግዳ ሲነካ፣ የሌላው ኪሩብ ክንፍ
ደግሞ ሌላውን ግድግዳ ይነካ ነበር፤ ሌሎቹ
ክንፎቻቸውም በቅድስተ ቅዱሳኑ መካከል
እርስ በርሳቸው ይነካኩ ነበር። 28ኪሩቤልንም
በወርቅ ለበጣቸው።

29በመቅደሱ ግድግዳ ዙሪያ ላይ
ሁሉ በውስጥም በውጭም ኪሩቤልን፣
ከዘንባባ ዛፎችና ከፈነዱ አበቦች ጋር
ቀረጸ። 30እንዲሁም የቅድስተ ቅዱሳኑንና
የመቅደሱን ወለል በሙሉ በወርቅ ለበጠ።

31ለቅድስተ ቅዱሳኑም መግቢያ የወይራ
ዕንጨት ደጃፎች ሠራ፤ መቃኖቻቸውንና
መድረኮቻቸውን ባለ አምስት ማእዘን አደረገ።
32በሁለቱ የወይራ ዕንጨት መዝጊያዎችም
ላይ ኪሩቤልን፣ የዘንባባ ዛፎችንና የፈነዱ
አበቦችን ቀረጸ፤ በወርቅም ለበጣቸው።
33እንዲሁም ለዋናው አዳራሽ መግቢያ ባለ
አራት ማእዘን የወይራ ዕንጨት መቃን ሠራ፤
34እያንዳንዳቸው በማጠፊያ የተያያዙ ሁለት
ሁለት ሳንቃዎች ያሏቸው ሁለት መዝጊያዎች
አበጀ። 35ኪሩቤልን፣ የዘንባባ ዛፎችንና
የፈኩ አበቦችንም ቀረጸባቸው፤ ቅርጹን
ሠራ፤ ጥሩ አድርጎም በወርቅ ለበጠው።

36የውስጠኛውን አደባባይ በሦስት ረድፍ
ጥርብ ድንጋይና በአንድ ረድፍ የዝግባ
ጣንቃ ሠራው።

37የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም
በአራተኛው ዓመት ዚፍ በተባለው ወር
መሠረቱ ተጣለ፤ 38በዐሥራ አንደኛው
ዓመት ቡል በተባለውም በስምንተኛው ወር
ቤተ መቅደሱ በዝርዝር ጥናቱ መሠረት እንደ
ታቀደው ተፈጸመ፤ ሠርቶ የጨረሰውም
በሰባት ዓመት ጊዜ ውስጥ ነበር።

ሰሎሞን ቤተ መንግሥቱን ሠራ

7 ሰሎሞን የራሱን ቤተ መንግሥት
ሠርቶ ለመጨረስ ዐሥራ ሦስት ዓመት
ወስዶበታል፤ 2የሊባኖስ ዱር የተባለ ቤተ
መንግሥት ሠራ፤ ይህም ርዝመቱ መቶ
ክንድ፣ ወርዱ አምሳ ክንድ፣ ቁመቱ ሠላሳ
ክንድ ሲሆን፣ በአራት ረድፍ የቆሙ የዝግባ
ምሰሶች ደግፈው የያዟቸው አግዳሚ የዝግባ
ተሸካሚዎች ነበሩት። 3ቤቱ ከምሰሶቹ
ላይ ያረፉ አግዳሚ ተሸካሚዎች አሉት፤
በእያንዳንዱ ዐምድ ላይ ዐሥራ አምስት፣
በድምሩ አርባ አምስት ተሸጋጋሪዎች ሲኖሩ፣
ከእነዚህም ተሸጋጋሪዎች በላይ ከዝግባ
የተሠራ የጣሪያ ክዳን ነበር። 4መስኮቶቹም
ከፍ ብለው የተሠሩ በሦስት ምድብ
የተከፈሉና ትይዩ ነበሩ። 5በሮቹ በሙሉ ባለ
አራት ማእዘን መቃኖች ያሏቸው፣ በሦስት
ምድብ የተከፈሉና ትይዩ[ኀ] ነበሩ።

6ሰሎሞን፣ "ባለ ብዙ ምሰሶ አዳራሽ"
የተባለ ቤት ሠራ፤ የዚህም ርዝመቱ አምሳ
ክንድ፣ ወርዱ ሠላሳ ክንድ፣[ኀ] ነበር፤ በስተ
ፊት በኩልም ጣራ ያለውና በአዕማድ
የተደገፈ መመላለሻ ነበረው።


7ዳኝነት የሚያይበትንም የዙፋን
ችሎት አዳራሽ ሠራ፤ ይኸውም የፍትሕ
አዳራሽ የተባለው ነው፤ ይህንንም ከወለሉ
እንሥቶ እስከ ጣራውም[ሠ] ድረስ በዝግባ ሳንቃ
ሸፈነው። 8ካአዳራሹ በስተ ጀርባ ባለው
አደባባይ መኖሪያው እንዲሆን የተሠራው
ቤተ መንግሥትም የዚሁ ተመሳሳይ ነበር።
ሰሎሞን ላገባት ለፈርዖን ልጅ ይህንኑ ቤተ
መንግሥት የመሰለ አዳራሽ ሠራ።

9ከውጭ እንሥቶ እስከ ትልቁ አደባባይ፣
ከመሠረቱ እንሥቶ እስከ ድምድማቱ ያለው
የሕንጻ ሥራ በሙሉ፣ በውስጥም በውጭም
በልክ በልኩ በተቈረጠና አምሮ በተስተካከለ
ምርጥ ድንጋይ የተሠራ ነበር። 10መሠረቱም
ዐሥርና[ፋ] ስምንት ክንድ[ፐ] ርዝመት

ሀ 6፥18 ሶ 29፥ መዝ 74፥6፣ ሕዝ 41፥18
ነ 6፥19 ዘፀ 25፥10፣ 1ሳሙ 3፥3፣ 1ነገ 8፥6
ጣ 6፥20 ዘፀ 30፥1፣ ሕዝ 41፥34
ሠ 6፥23 ዘፀ 37፥7
ረ 6፥27 ዘፍ 3፥24፣ ዘፀ 25፥18
ቀ 6፥29 ሶ 18:32:35፣ ሕዝ 41፥18:25
በ 6፥32 ሕዝ 41፥23
ተ 6፥36 1ነገ 7፥12፣ 2ዜና 4፥9፣ ዕዝ 6፥4
ኀ 6፥38 ዘፀ 25፥9፣ 1ዜና 28፥19፣ ዕዝ 8፥5
ሠ 7፥1 2ሳሙ 7፥2
ረ 7፥2 2ሳሙ 7፥2፣ 1ነገ 10፥17፣ 2ዜና 9፥16፣ ኢሳ 22፥8፣ 37፥24፣ ኤር 22፥6:23
ሸ 7፥7 1ሳሙ 7፥15፣ 1ነገ 6፥15፣ መዝ 122፥5፣ ምሳ 20፥8
ቀ 7፥8 1ነገ 3፥1

ሀ 6፥17 18 ሜትር ያህል ነው
ነ 6፥20 ርዝመቱ፣ ወርዱና ቁመቱ 9 ሜትር ያህል ነው
ጣ 6፥23 4.5 ሜትር ያህል ነው
ሠ 7፥2 ርዝመቱ 46 ሜትር፣ ወርዱ 23 ሜትር እንዲሁም ቁመቱ 13.5 ሜትር ያህል ነው
ረ 7፥5 በዕብራይስጥ የክፍሉ መልእክት በትክክል አይታወቅም።
ቀ 7፥6 ርዝመቱ 23 ሜትር፣ ወርዱ 13.5 ሜትር ያህል ነው።
በ 7፥7 ቩልጌትና የሱርስቱ ትርጉም ከዚህ ጋር ሲስማሙ ዕብራይ ስሙ ግን፣ ወለል ይላል
ተ 7፥10 4.5 ሜትር ያህል ነው።
ኀ 7፥10 3.6 ሜትር ያህል ነው።


የሰለሞን ቤተ መቅደስ



የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ከንጉሡ ቤተ መንግሥት ጎን የተቀመጠ ሲሆን፣ እንደ እግዚአብሔር ዙፋን መቀመጫና ለእስራኤላዊያን ደግሞ ብሔራዊ የአምልኮ ማዕከል ሆኖ ያገለግል ነበር። እግዚአብሔር ለሰሎሞን እንዲህ አለው፤ «ስሜን በዚያ ለዘላለም እንዲኖር በማድረግ ቀድሼዋለሁ፤ ለአባትህ ለዳዊት... በሰጠሁት ተስፋ መሰረት ዙፋንህን በእስራኤል ላይ ለዘላለም አጸናለሁ» /1ነገ 9፤ 3-5/። መቅደሱ በተፈጠረው ዓለም ላይ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ሲያሳስብ፣ በተመሳሳይም በእስራኤል ላይ የእርሱን ራስነት ያመለክታል።

© 1991 The Zondervan Corporation, © 1991 Hugh Claycombe

የቤተ መቅደስ ዕቃዎች



© 1991 The Zondervan Corporation

ዓላቸውና ምርጥ በሆኑ ታላላቅ ድንጋዮች የተሠራ ነበር። [11]በላዩም ላይ ምርጥ የሆኑ በልክ በልኩ የተቈረጡ ድንጋዮችና የዝግባ ዛንቃዎች ነበሩ። [12]የአግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጠኛ አደባባይ ከመመላለሻ ፀረንዳው ሥምር እንደ ትልቁ አደባባይ አምሮ በተጠረበ ሦስት ረድፍ ድንጋይና ተስተካክሎ በተከረከመ በአንድ ረድፍ የዝግባ ሳንቃ የታጠረ ነበር።

የቤተ መቅደሱ ዕቃዎች

ዜና2፫-26 ተጓ ምብ — 2ዜና 4፥2-5
ዜ፫8-51 ተጓ ምብ — 2ዜና 4፥6፣10—5፥1

[13]ንጉሥ ሰሎሞንም መልእክተኛ ልኮ ኪራምን የተባለውን ሰው ከጢሮስ አስመጣ፤ [14]የኪራም እናት ከንፍታሌም ነገድ ስትሆን፣ እርሷም መበለት ነበረች፤ አባቱ የጢሮስ ሰው ሲሆን፣ የናስ ሥራ ባለሙያ ነበር። ኪራም ብማናቸውም የናስ ሥራ ጥበብን፣ ግስተዋልንና ዕውቀትን የተሞላ ሰው ነበር፤ እርሱም ወደ ንጉሥ ሰሎሞን መጥቶ የተመደበለትን ሥራ ሁሉ አከናወነ።

[15]ኪራም የእያንዳንዱ ቁመት ዐሥራ ስምንት ክንድ፣ ዙሪያው ዐሥራ ሁለት ክንድ የሆነ ሁለት የናስ ምሰሶዎች ሠራ። [16]እንዲሁም በምሰሶዎቹ አናት ላይ የሚሆኑ ሁለት ጕልላት ከቀለጠ ናስ ሠራ፤ የእያንዳንዱም ጕልላት ቁመት አምስት ክንድ ነበር። [17]በምሰሶዎቹ አናት ላይ ላሉት ጕልላቶችም ጌጥ እንዲሆኑ ለእያንዳንዳቸው ሰባት የመረብ ሰንሰለት አበጀ፤ [18]ደግሞም በምሰሶዎቹ ላይ ያሉትን ጕልላቶች ለሚሸፍጥ የእያንዳንዱን መረብ ዙሪያ የሚከቡ ሮማኖች በሁለት ረድፍ ሠራ፤ ለሁለቱም ጕልላቶች ያደረገው ተመሳሳይ ነበር። [19]በመመላለሻው ምሰሶዎች አናት ላይ ያሉት ጕልላቶች ቁመታቸው አራት ክንድ ሲሆን፣ የሱፍ አበባ ቅርጽ ነበራቸው። [20]በሁለቱም የምሰሶ ጕልላቶችና ከመርበቡ ቀጥሎ ባለው የክብ ቅርጽ ላይ ዙሪያውን በሙሉ ሁለት መቶ ሮማኖች በተርታ ነበሩ። [21]ምሰሶዎቹንም ለቤተ መቅደሱ መመላለሻ ላይ አቆመ፤ ቀኙ ደቡብ ያቆመውን ምሰሶ ያቂም፣ ግራው ሰሜን በኩል ያለውንም ቦዔዝ ብሎ ጠራው። [22]አናቱ ላይ ያሉት ጕልላቶች የሱፍ አበባ ቅርጽ ነበራቸው። የምሰሶዎቹም ሥራ በዚህ ሁኔታ ተፈጸመ።

[23]ቅርጹ ክብ፣ ስፋቱ ከዳር እስከ ዳር ዐሥር ክንድ፣ ቁመቱ አምስት ክንድ የሆነ ክብ ገንዳ ከቀለጠ ብረት ሠራ፤ ዙሪያውም ሌላ ሠላሳ ክንድ ሆነ። [24]ከከንፈሩም ዝቅ ብሎ፣ በእያንዳንዱ ክንድ ላይ እንደ ቅል ያሉ ዐሥር ቅርጾች ዙሪያውን በሁለት ረድፍ ከበውታል፤ እነዚህም ከገንዳው ጋር አንድ ወጥ ሆነው በሁኔት ረድፍ ቅርተው ነበር።

[25]ገንዳውም፣ ሦስቱ ፊታቸውን ወደ ሰሜን፣ ሦስቱ ወደ ደቡብ፣ ሦስቱ ወደ ምዕራብ፣ ሦስቱ ወደ ምሥራቅ ባዙሩ የዐሥራ ሁለት በሬዎች ምስሎች ላይ የተቀመጠ ሲሆን፣ ገንዳው በላያቸው ሆኖ የሁሉም የኋላ አካል በመካከል ላይ የገጠመ ነበር። [26]የገንዳው ውፍረት አንድ ጋት ሲሆን፣ የከንፈሩ ጠርዝ ደግሞ እንደ አበባ ቅርጽ ሆኖ፣ የጽዋ ከንፈር የመሰለ ነው፤ ይህም አርባ ሁለት ሺህ ሊትር[ፕ] ያህል ውሃ የሚይዝ ነበር።

[27]እንዲሁም ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ዐሥር ባለመንኰራኵር የዕቃ ማስቀመጫዎች ከመዳብ ሠራ፤ የእያንዳንዱም ርዝመት አራት ክንድ፣ ወርድ አራት ክንድ፣ ቁመትም ሦስት ክንድ ነበር። [28]የዕቃ ማስቀመጫዎቹ የተሠሩት እንደዚህ ነው፤ እነዚህም ቀጥ ብለው ከቆሙ ደጋፊዎች ጋር የተያያዙ ባለ አራት ማእዘን ጠፍጣፋ ናሶች ነበሯቸው። [29]ዳርና ዳር ባሉት ድጋፎች መካከል በሚገኙት ጠፍጣፋ ናሶች ላይ የአንበሶችን፣ የኮርማዎችንና የኪሩቤልን ምስል አደረገ፤ በድጋፎቹም ላይ እንደዚሁ አደረገ። ከአንበሶቹና ከኮርማዎቹ በላይና በታች በኩል ደግሞ የአበባ ጕንጕን የሚመስሉ ተቀጥ ቅጠው የተሠሩ ቅርጾች ነበሩ። [30]እያንዳንዱ የዕቃ ማስቀመጫ አራት የናስ መንኰራኵርና መንኰራኵሮቹ የሚሽከረከሩባቸው የናስ ወስከምቶች እንዲሁም እያንዳንዳቸው ብአራቱም ማእዘን ገጽ ላይ የአበባ ጕንጕን ቀልጠ የተሠራባቸው የመታጠቢያ ገንዳ መደገፊያዎች ነበረው። [31]በዕቃ ማስቀመጫውቹም ውስጥ ጥልቀቱ አንድ ክንድ የሆነ ባለ ክብ ክፍተት ነበር፤ ይህም ክፍተት ድሁልሁል ሆኖ ከታችከመቆሚያው በኩል ደግሞ አንድ ክንድ ተኩል ወርድ ሲኖረው፣ በክፍተቱም ዙሪያ ቅርጾች ነበሩ፤ ክፈፎቹ ግን ባለ አራት ማእዘን እንጂ

[ሀ]*7፥13* በዚህ ስፍራ እንዲሁም በሦ 40 እና 45 ላይ ኪራም የሚ ሰው ዕብራይስጡ ሂራም ይለዋል።
[ለ]*7፥15* ቁመቱ 8.1 ሜትር፣ ዙሪያው 5.4 ሜትር ያህል ነው።
[ሐ]*7፥16* በዚህና በሦ 23 ላይ 2.3 ሜትር ያህል ነው።
[መ]*7፥18* ሁለት የዕብራይስጥ ቅጆችና የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ከዚህ ጋር ሲስማሙ፣ አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ በሁለት ረድፍ አዕማደሥራ ይላሉ።
[ሠ]*7፥18* ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆችና የሱርስቱ ትርጉም ከዚህ ጋር ሲስማሙ፣ አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን ሮማኖች ይላሉ።
[ረ]*7፥19* በዚህና በሦ 38 ላይ 1.8 ሜትር ይላል።
[ሰ]*7፥21* ምናልባት አነጸ ማለት ሊሆን ይችላል።
[ሸ]*7፥21* ምናልባት በእርሱ ዘንድ ጥንሬ አለ ማለት ሊሆን ይችላል
[ቀ]*7፥23* 4.5 ሜትር ያህል ነው።
[በ]*7፥23* 13.5 ሜትር ያህል ነው።
[ተ]*7፥26* 8 ሴንቲ ሜትር ያህል ነው።
[ቸ]*7፥26* 44 ኪሎ ሊትር ያህል ነው። የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ይህን ዐረፍተ ነገር አይጨምርም።
[ኀ]*7፥27* ርዝመቱና ወርዱ 1.8 ሜትር ያህል ሲሆን ቁመቱ 1.3 ሜትር ያህል ነው።
[ነ]*7፥31* 0.5 ሜትር ያህል ነው።
[ኘ]*7፥31* በዚህና በሦ 32 ላይ 0.7 ሜትር ያህል ነው።

7፥12 1ነገ6፥36
7፥13 ሶ45፥
2ዜና2፥13፣ 4፥16
7፥14 ዘፀ31፥2-5፣ 35፥31፣ 2ዜና4፥11
7፥15 2ነገ11፥14፣ 23፥3፣ 25፥17፣ 2ዜና3፥15፣ 23፥13፣ 34፥31፣ ኤር27፥19፣ 52፥17፡21፣ ሕዝ40፥49
7፥16 ሶ20:42፣ 2ነገ25፥17፣ ኤር52፥22
7፥20 ሶ18፥
2ዜና3፥16፣ 4፥13
7፥21 2ዜና3፥17
7፥22 2ነገ25፥17
7፥23 ሶ47፥
2ነገ25፥13፣ 1ዜና18፥8፣ 2ዜና4፥18፣ ኤር31፥39፣ 52፥17፣ ዘካ2፥1፣ ራእ4፥6
7፥25 ኤር52፥20
7፥27 2ነገ16፥17
7፥30 2ነገ16፥17

ክብ አልነበሩም። 32አራቱ መንኰራኵሮች በዕቃ ማስቀመጫው ጠፍጣፋ ናስ ሥር ሲሆኑ፣ የመንኰራኵሮቹ ወስከምቶች ደግሞ ከዕቃ ማስቀመጫዎቹ ጋር የተያያዙ ነበሩ፤ የእያንዳንዱም መንኰራኵር ስፋት አንድ ክንድ ተኩል ነበር። 33መንኰራኵሮቹ የሠረገላ መንኰራኵር መሰል ሲሆኑ፣ ወስከ ምቶቹ የመንኰራኵሮቹ ክፈፎችና ዐቃፊዎቻቸው እንዲሁም ወስከምቶቹ የሚገቡባቸው ቧምቧዎች በሙሉ ከቀለጠ ብረት የተሠሩ ነበሩ።

34እያንዳንዱ የዕቃ ማስቀመጫ አራት ወጣ ያለ እጀታ ነበረው። 35በዕቃ ማስቀመጫው ጫፍ ላይ ግማሽ ክንድ የሆነ ዙሪያ ክብ ነበረበት፤ ድጋፎቹና ጠፍጣፋ ናሶቹ ከዕቃ ማስቀመጫው አናት ጋር የተያያዙ ነበሩ። 36እርሱም በድጋፎቹና በጠፍጣፋ ናሶቹ ላይ ባለው ቦታ ሁሉ፣ ዙሪያውን የአበባ ጕንጕን እያደረገ ኪሩቤልን፣ አንበሶችንና የዘንባባ ዛፎችን ቀረጸ። 37ዐሥሩም የዕቃ ተሽካሚዎች የተሠሩት በዚህ ሁኔታ ነበር፤ ሁሉም ከአንድ ቅርጽ ቀልጠው የወጡ ስለ ሆነ፣ በመጠንና በቅርጽ ፍጹም ተመሳሳይ ነበሩ።

38ከዚያም ለእያንዳንዱ የዕቃ ማስቀመጫ የሚሆን፣ እያንዳንዱ ሰሞንት መቶ ሰማንያ ሊትር የሚይዝ ዐሥር የናስ መታጠቢያ ገንዳ ሠራ፤ ስፋቱም አራት ክንድ ነበር። 39ከዕቃ ማስቀመጫዎቹም አምስቱን ከመቅደሱ በስተ ደቡብ፣ አምስቱን በስተ ሰሜን በኩል አኖረ፤ ገንዳውንም ከቤተ መቅደሱ በደቡብ ምሥራቅ ጫፍ ላይ በስተ ደቡብ አኖረው። 40እንዲሁም ምንቸቶችን፣ መጫሪያዎችንና ድስቶችን ሠራ፤

ኪራምም በዚህ ሁኔታ ለንጉሥ ሰሎሞን የሠራውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሥራ እንደሚከተለው ፈጸመ፤

41ሁለቱን ምሰሶዎች፣
በምሰሶዎቹ አናት ላይ
በክብ ቅርጽ የተሠሩ ሁለት
ጕልላቶችን፤
በምሰሶዎቹ ላይ ያሉትን በክብ
ቅርጽ የተሠሩትን ሁለት
ጕልላት ያስጌጡትን ሁለት
መረቦች፤
42በምሰሶዎቹ አናት ላይ ያሉትንና
ክብ ቅርጽ የያዙትን፣
በሁለት ረድፍ የተቀረጹትን
መረቦች፣
የሚያስጌጡትን አራት መቶ
ሮማኖች፤
43ዐሥሩን የዕቃ ማስቀመጫዎች፣

7፥38 ዘፀ30፥18
7፥40 ዘፀ27፥3፤ ኤር52፥18
7፥42 ቊ 16

7፥45 ቊ 13፤ ዘፀ27፥3፤ ኤር52፥18
7፥46 ዘፍ13፥10፤ 33፥17፤ ኢሱ3፥16
7፥47 ቊ 23፤ ዘፀ36፥57፤ ዘዜ22፥3፤ ኤር52፥20
7፥48 ዘፀ25፥23፡30፤ 39፥32-43
7፥49 ዘፀ25፥31
7፥50 ዘኍ7፥14፤ 2ነገ25፥13፤ ኤር52፥19
7፥51 2ሳሙ8፥11፤ 2ነገ12፥13፤ 24፥13፤ ኤር27፥19
8፥1 ዘኍ7፥2፤ 1ሳሙ3፥3፤ 2ሳሙ5፥7፤ ራእ11፥19

ከዐሥር መታጠቢያ
ገንዳዎቻቸው ጋር፤
44ግንዳውንና በሥሩ ያሉትን ዐሥራ
ሁለት በሬዎች፤
45ድስቶችን፣ መጫሪያዎችንና
ጐድጓዳ ሳሕኖች።

ኪራም ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገልግሎት እንዲውሉ እነዚህን ዕቃዎች ሁሉ ለንጉሥ ሰሎሞን የሠራለት ከተወለወለና ከሚብረቀረቅ ናስ ነበር። 46ንጉሡም እነዚህን በማቅለጥ በሸክላ ቅርጽ ውስጥ ፈሰው እንዲወጡ ያደረገው በሱኮትና በጻርታን መካከል ባለው በዮርዳኖስ ሸለቆ ነበር። 47ሰሎሞን ከብዛታቸው የተነሣ እነዚህ ሁሉ ዕቃዎች እንዲመዘኑ አላደረገም፣ ስለዚህም የናሱ ክብደት ምን ያህል እንደ ነበረ አልታወቀም።

48እንዲሁም ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገልግሎት እንዲውሉ ከዚህ የሚከተሉትን ዕቃዎች ሁሉ ሠራ፤
የወርቅ መሠዊያን፣
ገጸ ኅብስቱ የሚቀመጥበትን የወርቅ
ጠረጴዛ፤
49በቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት
አምስቱ በቀኝ፣ አምስቱ
በግራ የሚቀመጡ፣ ከንጹሕ ወርቅ
የተሠሩ መቅረዞችን፣ ከወርቅ
የተሠሩ
አበቦችን፣ የመብራት ቀንዲሎችንና
መቈስቈሻዎችን፤
50የንጹሕ ወርቅ ሳሕኖችን፣
የመብራት መኰስተሪያዎችን፣
ለመርጫ የሚሆኑ ጐድጓዳ
ሳሕኖችንና ሞልፋዎችን፣
የዕጣን ማቅረቢያ ዕቃዎችን፣
ለውስጠኛው ክፍል ለቅድስተ
ቅዱሳኑ በሮችና እንዲሁም ለቤተ
መቅደሱ በሮች የሚሆኑ የወርቅ
ማጠፊያዎችን።

51ንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሥራ ሁሉ ከፈጸመ በኋላ አባቱ ዳዊት ለእግዚአብሔር የለየውን ብሩንና ወርቁን እንዲሁም ዕቃውን አምጥቶ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ግምጃ ቤት አኖረ።

ታቦቱ ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ

8፥1-21ተጓ ምብ — 2ዜና 5፥2—6፥11

8 ከዚያም ንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን የኪዳኑን ታቦት ከዳዊት ከተማ ከጽዮን

^7፥35 0.2 ሜትር ያህል ነው።

8፥1 **የእግዚአብሔር የኪዳኑን ታቦት፤** በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ከቃል ኪዳኑ ታቦት በቀር ሌላ ነገር አይገኝም ነበር። ባለአራት ማእዘኑ ታቦት፣ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፣ ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል፣ ከፍታውም አንድ ክንድ ተኩል ነበር። ከግራር እንጨት ተሠርቶ በውስጥና በውጭ በንጹሕ ወርቅ ተለብጦአል። ከመጀመሪያ ታቦቱ፣ እግዚአብሔር የእስራኤል ሉዓላዊ ንጉሥ መሆኑን የሚከተሉት ሦስት ነገሮች መኖራቸው ያስታወሰ ነበረ፡ (1) ዐሥርቱ ትእዛዛት የተጻፉባቸው የድንጋይ ጽላቶች (ከዘፀ 25፥16:21፣ 40፥20 ጋር ያነጻጽሩ፡ ዘፀ 25፥10 እና ማብ ይመ)፡ (2) እስራኤል በምድረ በዳ በነበሩበት ወቅት እግዚአብሔር በየዕለቱ የሰጣቸውን መና የሚያስታውስ (ዘፀ 16፥32-34) በመና የተሞላ የወርቅ ማሰሮ፣ (3) በታምር ያቈጠቈጠችው

ለማምጣት፣ የእስራኤልን ሽማግሌዎች፣ የእስራኤልን ነገድ አለቆችና የእስራኤልን ጐሣዎች ሹማምት ሁሉ እርሱ ወዳለበት ወደ ኢየሩሳሌም ጠራቸው። ²በዓሉ በሚከበርበት ኤታኒም በተባለው በሰባተኛው ወር፣ የእስራኤል ወንዶች ሁሉ ንጉሥ ሰሎሞን ወዳለበት ተሰበሰቡ።

³የእስራኤል ሽማግሌዎች ሁሉ በመጡ ጊዜም ካህናቱ ታቦቱን አነሡ፤ ⁴የእግዚአብሔርን ታቦት፣ የመገናኛውን ድንኳንና በውስጡ ያሉትን ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ አመጡ፤ ካህናቱና ሌዋውያኑም ይህን ሁሉ ተሸከሙ። ⁵ንጉሥ ሰሎሞንና አብሮት በዚያ የተሰበሰበው መላው የእስራኤል ጉባኤም በታቦቱ ፊት በመሆን ስፍር ቍጥር የሌለው በግና በሬ ሠዉ።

⁶ካህናቱ የእግዚአብሔርን የኪዳኑን ታቦት አምጥተው በቤተ መቅደሱ ውስጥ ወዳለው ማደሪያው፣ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ በማስገባት ከኪሩቤል ክንፍ በታች አኖሩት። ⁷ኪሩቤልም ታቦቱ ባለበት ቦታ ላይ ክንፋቸውን ዘርግተው፣ ታቦቱንና መሎጊያዎቹን ጋረዱ። ⁸መሎጊያዎቹ ከመርዘማቸው የተነሣ ጫፎቻቸው ከቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት ካለው ከመቅደሱ ሆኖ ይታዩ ነበር፤ ከመቅደሱ ውጪ ላለ ሰው ግን አይታዩም ነበር፤ እስከ ዛሬም ድረስ እዚያው ይገኛሉ። ⁹የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር በወጡ ጊዜ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ኪዳን በገባበት በኮሬብ፣ ሙሴ በታቦቱ ውስጥ ካስቀመጣቸው ሁለት የድንጋይ ጽላቶች በቀር በታቦቱ ውስጥ ምንም አልነበረም።

¹⁰ካህናቱ ከዚያ መቅደሱ በወጡ ጊዜ፣ ደመና የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሞላው። ¹¹የእግዚአብሔር ክብር ቤተ መቅደሱን ሞልቶት ስለ ነበር፣ ካህናቱ በደመናው ምክንያት አገልግሎታቸውን ማከናወን አልቻሉም ነበር።

¹²ከዚያም ሰሎሞን እንዲህ አለ፤

"እግዚአብሔር ጥቅጥቅ ባለ ደመና ውስጥ እንደሚኖር ተናግሮአል፤ ¹³እነሆ፣ እኔም ለዘላለም የምትኖርበትን ታላቅ ቤተ መቅደስ ሠርቼልሃለሁ።"

¹⁴መላው የእስራኤል ጉባኤ በዚያ ቆሞ ሳለ፣ ንጉሡ ፊቱን ወደ እነርሱ መልሶ ጉባኤውን ባረከ። ¹⁵ከዚያም እንዲህ አለ፤

"ለአባቴ ለዳዊት በገዛ አፉ
ተናግሮ የሰጠውን ተስፋ፣ እርሱ
ራሱ በእጁ የፈጸመ የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር የተመሰገነ
ይሁን፤ እርሱም እንዲህ ብሎ
ነበርና፤ ¹⁶'ሕዝቤን እስራኤልን
ከግብፅ ምድር ካወጣሁበት ዕለት
አንሥቶ፣ ስሜ በዚያ እንዲጠራና
ቤተ መቅደስ እንዲሠራበት
ከመላው የእስራኤል ነገድ አንድም
ከተማ አልመረጥሁም፤ ሕዝቤን
እስራኤልን እንዲመራ ግን
ዳዊትን መረጥሁት።'
¹⁷"አባቴ ዳዊት ለእስራኤል
አምላክ ለእግዚአብሔር ስም ቤተ
መቅደስ ለመሥራት በልቡ
አስቦ ነበር፤ ¹⁸እግዚአብሔር ግን
አባቴን ዳዊትን እንዲህ አለው፤
'ለስሜ ቤተ መቅደስ ለመሥራት
አስበሃልና፣ ይህን በልብህ ማሰብህ
መልካም ነው፤ ¹⁹ይሁን እንጂ ቤተ
መቅደሱን የምትሠራው አንተ
ሳትሆን፣ ከአንተ የሚወለደው
ልጅህ ነው፤ አዎን ለስሜ ቤተ
መቅደስ የሚሠራው እርሱ ነው።'
²⁰"እግዚአብሔር የሰጠውን
ተስፋ ፈጽሞአል፤ እግዚአብሔር
በሰጠው ተስፋ መሠረት በአባቴ
በዳዊት እግር ተተክቻለሁ፤
በእስራኤል ዙፋን ተቀምጫለሁ፤
እንዲሁም ለእስራኤል አምላክ

8፡2 ቍ65፤ ዘሌ23፡34፡36፤ ዙኁ29፡12፤ ነህ8፡17
8፡3 ኢሳ3፡3
8፡4 ዘሌ17፡4፤ 1ዜና15፡13
8፡5 2ሳሙ6፡13፤ 2ዜና30፡24
8፡6 ዘኍ3፡24፤ ዘፀ25፡18፤ 26፡33፤ 2ሳሙ6፡17፤ ራእ11፡19
8፡7 ዘፀ25፡20
8፡8 ዘፀ25፡13-15
8፡9 ዘፀ16፡34፤ 25፡16፤ ዕብ9፡4
8፡10 ዘፀ16፡10፤ ዘሌ16፡2፤ ራእ15፡8
8፡11 ዘፀ16፡7፤ 29፡43፤ 2ዜና7፡2፤ ራእ15፡8
8፡12 ዘፀ40፡34፤ 2ሳሙ22፡10
8፡13 ዘፀ15፡17፤ መዝ132፡13፤ 135፡21፤ ማቴ23፡21
8፡14 ዘፀ39፡43
8፡15 1ዜና6፡36፤ ሉቃ1፡68
8፡16 ዘፀ3፡10፤ ዘኍ12፡5፤ 1ሳሙ9፡16፤ 16፡1፤ መዝ89፡34
8፡17 1ሳሙ10፡7፤ 2ሳሙ7፡27፤ 1ዜና22፡7፤ መዝ26፡8፤ 132፡5፤ ሐሥ7፡46
8፡19 2ሳሙ7፡5፡13
8፡20 2ሳሙ7፡12፤ 1ዜና28፡6

የእሮን በትር። ይሁን እንጅ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ታቦቱ የያዘው ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶች ብቻ ነበር (2ዜና 5፡10)። በታቦቱ አናት ላይ የተገጠመው "የስርየት መክደኛው" ሲሆን፣ በእርሱም ላይ በዓመት አንድ ጊዜ፣ በስርየት ቀን ሊቀ ካህናቱ የመሥዋዕቱን ደም ይረጭበት ነበር። ከንፋቸውን ዘርግተው ትይዩና አንድ ዐይነ ሆነው ከወርቅ የተሠሩት ሁለት ኪሩቤል በቀስት ርዝመት የስርየት መክደኛው ላይ ረብበው ይታያሉ። የስርየት መክደኛው መሀል ላይ፣ የእግዚአብሔር ህልዎት "ሽኪና" ተብሎ በሚጠራው ጺበ ተፈጥሮአዊ ብርሃን እጅግ በሚያብረቀርቅ ብርሃን፣ በትእምርትነት ተመስሎአል (በገጽ 1205 ላይ፣ "የእግዚአብሔር ክብር" ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ)።

8፡4 የመገናኛውን ድንኳን፣ የመገናኛው ድንኳን፣ የድንኳን ዐይነት አወቃቀር የነበረው ሲሆን፣ እስራኤል ምድረ በዳ ሲዝሙ ተንቀሳቃሽ የመገናኛ ቦታ በመሆን አገልግሎአል። እስራኤላውያን በአገራቸው ተደላድለው ከተቀመጡ በኋላ፣ ዳዊት ቋሚ የሆነ የማምለኪያ ቤት ለእግዚአብሔር ለመሥራት ያለውን ፍላጎት ገለጸ (2ሳሙ 7፡13፤ እንዲሁም በገጽ 641 ላይ፣ "ቤተ መቅደሱ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

8፡11 የእግዚአብሔር ክብር፣ የቃል ኪዳኑ ታቦት በውስጡ ከተቀመጠ በኋላ፣ የእግዚአብሔር ክብር ቤተ መቅደሱን ሞላው (ቍ 5-11)። የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የተከበረ በሆነበት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔር ክብር ይኖራል (ዘፀ 40፡34 እና ማብ ይመ፤ ከዮሐ 15፡7-11፣ 17፡17-22 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1205 ላይ፣ "የእግዚአብሔር ክብር" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

8፡13 የምትኖርበትን፣ እግዚአብሔር በቤተ መቅደስ ኖረ ማለት በሌላ ቦታ አይኖርም ማለት አይደለም፤ እግዚአብሔር በየትም ቦታ ይኖራልና (ከቍ 27 ጋር ያነጻጽሩ)፤ እንዲህ ሲባል ግን የእግዚአብሔር ህልውትና ጎይል በቤተ መቅደሱ ውስጥ በተለየ ሁኔታ ይገለጣል ማለት ነው፤ እንደዚሁም ምእመናን በስሙ ሲሰበሰቡ (ማቴ 18፡20)፤ የክርስቶስ ህልውት በሕዝቡ ዘንድ በተለየ ሁኔታ ይገለጣል።

ለእግዚአብሔር ስም ቤተ መቅደስ
ሠርቻለሁ። [21]ከግብፅ ባወጣቸው
ጊዜ ከአባቶቻችን ጋር የገባው
የእግዚአብሔር ኪዳን በውስጡ
ላለበት ታቦት መኖሪያ ስፍራ
በዚያ አዘጋጅቻለሁ።"

ሰሎሞን በምረቃው ላይ ያቀረበው ጸሎት

8፡22-53 ተጓ ምብ — 2ዜና 6፡12-40

[22]ከዚያም ሰሎሞን መላው የእስራኤል
ጉባኤ ባለበት በእግዚአብሔር መሠዊያ ፊት
ቆመ፤ እጆቹንም ወደ ሰማይ ዘርግቶ፣
[23]እንዲህ አለ፤

"የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔር ሆይ፤ በፊትህ
በፍጹም ልባቸው ጸንተው
ለሚኖሩ አገልጋዮችህ ኪዳንህን
የምትጠብቅ፣ ጽኑ ፍቅርህን
የምትገልጥ አንተ ነህ፤ በላይ
በሰማይ፣ በታችም በምድር
እንዳንተ ያለ አምላክ ኩኖ የለም፤
[24]ለባሪያህ ለአባቴ ለዳዊት
የሰጠኸውን ተስፋ ጠብቀሃልፅ
በአፍህ ተናገርህ፤ ይህንኑም
በዛሬው ዕለት በእጅህ ፈጸምኸው።
[25]"አሁንም የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔር ሆይ ለአባቴ ለባሪያህ
ለዳዊት፣ 'አንተ እንዳደረግኸው
ሁሉ፣ ልጆችህ በፊቴ ለመመላለስ
በሚያደርጉት ሁሉ ይጠንቀቁ ብቻ
እንጂ በእስራኤል ዙፋን ላይ ዐፈቴ
የሚቀመጥ ሰው አታጣም' ስትል
የሰጠኸውን ተስፋ ፈጽምለት።
[26]አሁንም የእስራኤል አምላክ
ሆይ፤ ለባሪያህ ለአባቴ ለዳዊት
የሰጠኸው የተስፋ ቃል ይፈጸም።
[27] "ነገር ግን አምላክ በእርግጥ
በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ፤
ሰማይ፣ ከሰማያትም በላይ ያለው
ሰማይ እንኳ ይይዝህ ዘንድ
አይችልም፤ ታዲያ እኔ የሠራሁት
ይህ ቤተ መቅደስማ ምኑ ሊበ"!
[28]አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፤
ይህም ሆኖ የባሪያህን ጸሎትና
ልመና ስማ፤ በዛሬው ዕለት ባሪያህ
በፊትህ የሚያቀርበውን ፈጬትና
ልመና አድምጥ። [29]ባሪያህ ወደዚህ
ቦታ የሚያቀርበውን ጸሎት ትሰማ
ዘንድ፣ 'ስሜ በዚያ ይሆናል'
ወዳልኸው በዚህ ስፍራ ወዳለው
ቤተ መቅደስ ዐይኖችህ ሌትና
ቀን የተከፈቱ ይሁኑ። [30]ባሪያህና
ሕዝብህ እስራኤል ወደዚህ ስፍራ
ጸሎት በሚያቀርቡበት ጊዜ፣

8፡22 ዘ09፡29
8፡23 ዘ09፡14፡
ዘጸ7፡9፡12፡
ነህ1፡5፡ 9፡32፡
ዳን9፡4
8፡25
2ሳሙ7፡15፡
1ዜና17፡23፡
2ዜና1፡9
8፡26
2ሳሙ7፡25
8፡27 ዘጸ10፡14፡
2ዜና2፡6፡
መዝ139፡7-16፡
ኢሳ66፡1፡
ኤር23፡24፡
ሐሥ7፡48፡
17፡24
8፡29 ቁ 52፡
ዘጸ11፡12፡
12፡11፡
2ሳሙ7፡13፡
2ነገ19፡16፡
2ዜና7፡15፡
ነህ1፡6፡ መዝ5፡1፡
28፡2፡ 31፡2፡
102፡17፡
130፡2፡ 138፡2፡
ኢሳ37፡17፡
ዳን6፡10
8፡30 ቁ 39፡47፡
ዘዳ34፡7፡9፡
ዘሌ26፡40-42፡
ነህ1፡6፡ መዝ34፡6፡
85፡2፡
ኤር29፡12፡
ዳን9፡4

8፡31 ዘ022፡11
8፡32 ዘጸ25፡1፡
ሕዝ18፡20
8፡33
ዘሌ26፡17፡39፡
ኢሳ37፡1፡14፡38
8፡35 ዘጸ28፡24፡
2ሳሙ1፡21፡
ኤር5፡25
8፡36 ቁ 35፡
ዘጸ8፡3፡
1ሳሙ12፡23፡
1ነገ17፡1፡
18፡1፡45፡
መዝ5፡8፡
27፡11፡ 107፡7፡
ምሳ11፡5፡
ኢሳ45፡13፡
ኤር5፡24፡ 6፡16፡
7፡23፡ 10፡3፡
14፡22፡ 31፡21፡
ዘካ10፡1
8፡37 ዘ010፡13፡
30፡12፡
ዘሌ26፡25፡26፡
ዘጸ28፡22፡
መዝ105፡34
8፡38 ዘ09፡29
8፡39 ቁ 30፡
ኢሱ22፡22፡

ልመናቸውን ተቀበልፅ መኖሪያህ
በሆነው በሰማይ ስማ፤ ሰምተህም
ይቅር በልፅ።
[31]"አንድ ሰው ባልንጀራውን
በድሎ መማል ኖሮበት ቢመጣና
በዚህ ቤተ መቅደስ ውስጥ
በመሠዊያህ ፊት ቢምልፅ [32]ይህን
በሰማይ ሆነህ ስማ፤ አድርግም፤
በባሪያዎችህ መካከል ፍረድ፤
ለበደለኛው ስለ አድራጎቱ የእጁን
ክፈልፅ ከበደል ነጻ ለሆነውም
ንጽሕናውን ይፋ በማድረግ
ይህንኑ አረጋግጥለት።
[33]ሕዝብህ እስራኤል
አንተን ከመበደላቸው የተነሣ፤
በጠላቶቻቸው ድል በሚሆኑበት
ጊዜ፣ ወደ አንተም ተመልሰው
ስምህን ቢጠሩ፣ በዚህም ቤተ
መቅደስ ወደ አንተ ቢጸልዩና
ልመናቸውን ቢያቀርቡ፣
[34]በሰማይ ሆነህ ስማ፤ የሕዝብህ
የእስራኤልን ኀጢአት ይቅር በልፅ
ለአባቶቻቸው ወደ ሰጠሃቸውም
ምድር መልሰህ አግባቸው።
[35]"ሕዝቡም አንተን
ከመበደላቸው የተነሣ፤ ሰማይ
ተዘግቶ ዝናብ ሳይዘንብ ቢቀርና
ወደዚህ ስፍራ ቢጸልዩና ስምህን
ቢጠሩ፣ ስላስጨነቅሃቸውም
ከበደላቸው ቢመለሱ፣ [36]በሰማይ
ሆነህ ስማ፤ የባሪያዎችህን
የሕዝብህን የእስራኤልን ኀጢአት
ይቅር በልፅ የሚሄዱበትን ቀናውን
መንገድ አስተምራቸው፤ ርስት
አድርገህ ለሕዝብህ ለሰጠሃትም
ምድር ዝናብ አውርድ።
[37]"በምድሪቱ ላይ ራብ ወይም
ቸነፈር በሚመጣበት፣ ዋግ ወይም
አረማሞ በሚከሠትበት፣ አንበጣ
ወይም ኵብኩባ በሚወርድበት
ወይም በምድሪቱው ውስጥ
ባሉት ከተሞቻቸው ጠላት
ቢከባቸው እንዲሁም ማንኛውም
ዐይነት ጥፋት ወይም በሽታ
በሚመጣባቸው ጊዜ፣ [38]ከሕዝብህ
ከእስራኤል ማንኛውም ሰው
የልቡን ቊንቊት ዐውቆ እጆቹን
ወደዚህ ቤት በመዘርጋት ጸሎትና
ልመና በሚያቀርብበት ጊዜ ሁሉ፣
[39]በማደሪያህ በሰማይ ሆነህ ስማ፤
ይቅር በልፅ

አድርግም። አንተ ብቻ የሰውን
ሁሉ ልብ የምታውቅ ስለ ሆንህ
ልቡን ለምታውቀው ለእያንዳንዱ

8፡39 መዝ44፡21፡ 130፡4፡ ዮሐ2፡24፡ ራእ2፡23

8፡29 **ስሜ**፤ የእግዚአብሔር ስም ህልውቱን፣ ሥራው ሁሉ ክፈለው፤ ከኀጢአታቸው ተመልሰው
ባሕርይውንና ክብሩን ይወክላል። በሐዘንና በጸጸት ንስሓ ከገቡ (ቁ 35-36)፣
8፡39 **ይቅር በል፤ አድርግም፤** ለ ... ሰው እንደ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይቅር እንደሚል ሰሎሞን አስተዋለ።

ሰው እንደ ሥራው ሁሉ ክፈለው፤
40 ይህም እነርሱ ለአባቶቻችን
በሰጠሃቸው ምድር በሚኖሩበት
ጊዜ ሁሉ፣ አንተን እንዲፈሩ ነው።
41 "ከሕዝብህ ከእስራኤል ወገን
ያልሆነ፣ ግን ከስምህ ታላቅነት
የተነሣ ከሩቅ የመጣ የባዕድ
አገር ሰው ቢኖር፣ 42 ስምኽ ከሩቅ
የሚመጡት ስለ ታላቁ ስምህ፣
ስለ ጠንካራዪቱ እጅህ፣ ስለ
ተዘረጋችው ክንድህ ሰምተው
ነውና፤ እንግዳው መጥቶ ወደዚህ
ቤተ መቅደስ ቢጸልይ፣ 43 አንተ
በማደሪያህ በሰማይ ሆነህ ስማ፤
የጠየቀህንም ሁሉ ፈጽምለት፤
ይኸውም የምድር ሕዝቦች ሁሉ
ስምህን ዐውቀው፣ ሕዝብህ
እስራኤል አንተን እንደሚፈሩት
ሁሉ እንዲፈሩህ፣ እኔ የሠራሁትም
ይህ ቤት በስምህ መጠራቱን
እንዲያውቁ ነው።
44 "ሕዝብህ ጠላታቸውን
ለመውጋት አንተ ወደምትልካቸው
ወደ የትኛውም ቦታ ለጦርነት
በሚወጡበት ጊዜ፣ አንተ ወደ
መረጥሃት ከተማና እኔ ለስምህ ወደ
ሠራሁት ቤተ መቅደስ ፊታቸውን
መልሰው ለእግዚአብሔር ቢጸልዩ፣
45 ጸሎትና ልመናቸውን በሰማይ
ሆነህ ስማ፤ ርዳቸውም።
46 "መቼም ኀጢአት
የማይሠራ የለምና ሕዝብህ
በእንተ ላይ ኀጢአት ቢሠሩ
አንተም ተቈጥተህ ሩቅ ወይም
ቅርብ ወደ ሆነው ምድሩ ማርኮ
ለሚወስደው ጠላት አሳልፈህ
ብትሰጣቸው፣ 47 ተማርከው
በሚኖሩበት አገር ሳሉ ልባቸው
ቢመለስ፣ በተማረኩበትም ምድር
ሆነው ንስሓ ቢገቡና 'ኀጢአት
ሠርተናል፤ በድለናል፤ ክፉ
ድርጊትም ፈጽመናል' ብለው
ቢለምኑህ፣ 48 እንዲሁም ማርኮው
በወሰዷቸው ጠላቶቹ ምድር
ሳሉ በፍጹም ልባቸውና በፍጹም

8፥40 ዮሐ 3940፡
ዘዳ 6፥13፡ 12፥1፡
መዝ 103፥11፡
130፥4
8፥41 ዘፍ 31፥15፡
ኢሳ 56፥3፡6፡
61፥5
8፥42 ዘዳ 3፥24፡
1ነገ 10፥1፡
ኢሳ 60፥3፡
ሐሥ 8፥27
8፥43 ዘዳ 28፥10፡
ኢያ 4፥24፡
1ሳሙ 17፥46፡
መዝ 102፥15
8፥44 1ዜና 5፥20፡
2ዜና 14፥11
8፥45 መዝ 9፥4፡
140፥12
8፥46
ዘሌ 26፥33-39፡
ዘዳ 4፥27፡ 21፥10፡
28፥64፡
2ነገ 25፥21፡
መዝ 130፥3፡
143፥2፡
ምሳ 20፥9፡
ሮሜ 3፥9
8፥47 ዮሐ 30፡ ዘሌ
5፥5፡ ዕዝ 9፥7፡15፡
ነህ 1፥6፡
መዝ 106፥6፡
ኤር 3፥25፡ 14፥20
8፥48
ዘዳ 4፥29፡30፡
12፥11-14፡
ነህ 1፥9፡ መዝ 5፥7፡
11፥4፡ ኤር 23፥3፡
31፥8፡ ዮና 2፥4፡
1ዮሐ 1፥8፡10

8፥50 2ነገ 25፥28፡
2ዜና 30፥9፡
መዝ 106፥46፡
ዳን 1፥9
8፥51 ዘዳ 1፥13፡
34፥9፡ ዘዳ 9፥29፡
ኢሳ 48፥10፡
ኤር 11፥4
8፥52 ዮሐ 29፡
ኢዮ 30፥20፡
መዝ 3፥4፡ 22፥2፡
77፥1፡ 142፥1
8፥53 ዘፀ 19፥5፡
34፥9

ኀፍሳቸው ወደ አንተ ቢመለሱ፣
ለአባቶቻቸው ወደ ሰጠሃት
ወደዚህች ምድር ወደ መረጥሃትም
ወደዚህች ከተማና እኔም ለስምህ
ወደ ሠራሁት ቤተ መቅደስ
ፊታቸውን መልሰው ቢጸልዩ፣
49 "ከማደሪያህ ከሰማይ ሆነህ
ጸሎታቸውን ስማ፤ ልመናቸውንም
ተቀበል፤ ርዳቸውም። 50 በአንተ
ላይ ስለ ሠሩት ኀጢአት፣
አንተንም ስለ በደሉህ በደል
ሁሉ ሕዝብህን ይቅር በል፤
የማረኳቸውም እንዲራራላቸው
አድርግ። 51 ከዚያች እንደ ብረት
ማቅለጫ እቶን እሳት ከሆነ
ችው፣ ከግብፅ ምድር ያወጣሃቸው
ሕዝብህም ርስትህም ናቸውና።
52 "አሁንም ዐይኖችህ
ለባሪያህና ለሕዝብህ ለእስራኤል
ልመና የተከፈቱ ይሁኑ፤ ወደ
አንተ በሚጮኹበትም ጊዜ ሁሉ
ስማቸው፤ 53 አምላኬ እግዚአብሔር
ሆይ፤ አባቶቻችንን ከግብፅ ባወጣህ
ጊዜ፣ በባሪያህ በሙሴ አማካኝነት
እንደ ተናገርኸው ሁሉ፣ ርስትህ
ይሆኑ ዘንድ ከምድር ሕዝቦች ሁሉ
ለይተሃቸዋልና።"
54 ሰሎሞንም ይህን ሁሉ ጸሎትና ልመና
ለእግዚአብሔር አቅርቦ ከፈጸመ በኋላ፣
እጆቹን ወደ ሰማይ በመዘርጋት፣ በጕልበቱ
ተንበርክኮ ከነበረበት ከእግዚአብሔር
መሠዊያ ፊት ተነሣ። 55 ከዚያም ቆሞ
መላውን የእስራኤልን ጉባኤ ከፍ ባለ ድምፅ
እንዲህ ሲል መረቀ፤
56 "በሰጠው ተስፋ መሠረት
ለሕዝቡ ለእስራኤል ዕረፍትን
ለሰጠ እግዚአብሔር ምስጋና
ይግባውና፤ በባሪያው በሙሴ
አማካይነት ከተሰጠው መልካም
ተስፋ ሁሉ አንድም ቃል
አልቀረምና። 57 አምላካችን
እግዚአብሔር ከአባቶቻችን

8፥55 ዘዳ 39፥43፡ ዘኍ 6፥23 8፥56 ዘዳ 33፥14፡
ዘዳ 12፥10፡ ኢሱ 23፥15፡ ኤር 29፥10፡ ዕብ 4፥8
8፥57 ዘዳ 4፥31፡ 31፥6፡ ማቴ 28፥20፡ ዕብ 13፥5

---

*በ ምድር በሚኖሩበት ጊዜ ሁሉ ... አንተን እንዲፈሩ" (ቍ 40) በማለት፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን መገሠጽ ወይም መቅጣት እንሚኖርበትም ዐወቀ።

8፥46 መቼም ኀጢአት የማይሠራ የለምና፤ የሰሎሞን ቃል የራሱንም ሆነ የእስራኤልን ኀጢአት ይመዘገፍ ለመከራከር አልነበረም፤ ይልቁንስ የገለጸው እውነት፣ ኀጢአት በዓለም ውስጥ በየትም ቦታ አለና ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ሊለዩ ይችላሉ በማት ነው (ቍ 46-50 ይመ፡ ከሮሜ 3፥23፡ ከ1ዮሐ 1፥10 ጋር ያንጻጽሩ)። ከሀዲት የሚከሠት ቢሆንም እንኳ፣ ንስሓ ገብተው ወደ እግዚአብሔር ከተመለሱ ቅድማና ለእነርሱ እውን ሊሆንላቸው ይችላል (ቍ 46-51)።

8፥57 አምላካችን እግዚአብሔር ... ከእኛ ጋር ይሁን፤ የሰሎሞን ጸሎት ከጌታ ጋር ስንራመድ ምኞታችን ምን መሆን እንዳለበት የሚያመለክት ድንቅ ምሳሌ ነው። ሰሎሞን የሚከተለውን ለመነ፡ (1) የጌታ ጥበቃ፡ ሀልዎትና ርዳታ ከእነርሱ ጋር እንዲሆን (ቍ 57)፣ (2) እግዚአብሔር የገባውን በጎ የተስፋ ቃል በመፈጸም ቃሉን እንዲያጸናላቸው (ቍ 26:56)፣ (3) የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ይጠብቁና የጽድቅ መንገዱንም ይወዱ ዘንድ (ቍ 58)፣ በልባቸው ውስጥ የመለኰት የጸጋ ሥራ እንዲከናወን፣ (4) እግዚአብሔር የየዕለቱን ጸሎት እንዲሰማና በየዕለቱ የሚያስፈልጋቸውንም እንዲያሟላላቸው (ቍ 59)፣ (5) የእግዚአብሔርን ታላቅና አስፈሪ ባሕሪ በይበልጥ እንዲረዱ (ቍ 60) እናም፣ (6) ለእግዚአብሔርና ለፈቃዱ ሙሉ በሙሉ የሚገዛ ልብ እንዲኖራቸው (ቍ 61)።

ጋር እንደ ነበረ ሁሉ፣ ከእኛም
ጋር ይሁን፤ አይተውን፤
አይጣለንም። 58በመንገዱም
ሁሉ እንድንሄድ፣ ለአባቶቻችን
የሰጣቸውን ትእዛዞች፣
ሥርዐቶችና ደንቦች እንድንጠብቅ
ልባችንን ወደ እርሱ ይመልስ።
59በየዕለቱም ባሪያውንና ሕዝቡን
እስራኤልን በሚያስፈልጋቸው
ሁሉ እንዲረዳቸው፣ ይህች
በእግዚአብሔር ፊት ያቀረብኋት
የራሴ ልመና በቀንና በሌሊት ወደ
አምላካችን ወደ እግዚአብሔር ፊት
ትቅረብ። 60ይኸውም የምድር
ሕዝቦች ሁሉ እግዚአብሔር ብቻ
አምላክ እንደ ሆነና ከእርሱ በቀር
ሌላ እንደ ሌለ ያውቁ ዘንድ ነው።
61ስለዚህ እንደ ዛሬው ዕለት ሁሉ፣
በሥርዐቱ እንድትኖሩና ትእዛዙን
እንድትጠብቁ ልባችሁ ለአምላካችሁ
ለእግዚአብሔር የተገዛ ይሁን።"

የቤተ መቅደሱ መመረቅ

8፥62-66 ተጓ ምብ — 2ዜና 7፥1-10

62ከዚያም ንጉሡና ከእርሱ ጋር ያሉት
እስራኤል ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት
መሥዋዕት አቀረቡ። 63ሰሎሞንም ሃያ
ሁለት ሺህ በሬ፣ መቶ ሃያ ሺህ በግና
ፍየል የኅብረት መሥዋዕት[ሸ] አድርጎ
ለእግዚአብሔር አቀረበ፤ ንጉሡና
እስራኤላውያንም ሁሉ የእግዚአብሔርን
ቤተ መቅደስ በዚህ ሁኔታ ቀደሱ።

64በዚያኑ ዕለትም ንጉሡ በእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ ፊት ለፊት ያለውን
የአደባባዩን መካከለኛ ክፍል ቀደሰ፤
በዚያም የሚቃጠለውን መሥዋዕት፣ የእህል
ቍርባንና የኅብረት መሥዋዕቱን ስብ
አቀረበ፤ ይህን ያደረገውም በእግዚአብሔር
ፊት የነበረው የናስ መሠዊያ ከትንሽነቱ
የተነሣ የሚቃጠለውን መሥዋዕት የእህሉን
ቍርባንና የኅብረት መሥዋዕቱን ስብ
መያዝ ባለመቻሉ ነበር።

65በዚያን ጊዜም ሰሎሞን አብረውት
ካሉት የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ጋር፣ ማለትም
ከሐማት መተላለፊያ እስከ ግብፅ ደረቅ
ወንዝ[ቸ] ካለው ምድር ከተሰበሰበው ታላቅ
ጉባኤ ጋር በዓሉን አከበረ። እነርሱም ሰባት
ቀን፣ በተጨማሪም ሌላ ሰባት ቀን በድምሩ
ዐሥራ አራት ቀን በአምላካችን በእግዚአብሔር
ፊት በዓሉን አከበሩ። 66በሚቀጥለው ቀን

8፥58 ኢሱ24፥23
8፥60 ዘጸ4፥35፣ ኢሱ44፥24
8፥61 ዘጸ6፥5፣ 1ነገ9፥4፣ 11፥4፣ 15፥3፣14፣ 22፥43፣ 2ነገ20፥3፣ 1ዜና28፥9፣ 29፥19፣ 2ዜና16፥9፣ 17፥6፣ 25፥2፣ መዝ119፥80፣ ኢሳ38፥3
8፥62
2ሳሙ6፥13፣ 1ዜና29፥21፣ ሕዝ45፥17
8፥63 ዕዝ6፥16
8፥64 ዘፀ27፥1፣ 29፥13፣ 2ሳሙ6፥17፣ 2ነገ16፥14፣ 2ዜና4፥1፣ 8፥12፣ 15፥8፣ ሕዝ43፥13-17
8፥65 ቍ 2፣ ዘኍ15፥18፣ ሆሴ13፥21
8፥66 ዘፀ18፥9

9፥1 2ሳሙ7፥2
9፥2 1ነገ3፥5
9፥3 ዘፀ20፥24፣ ዘኍ11፥12፣ 12፥5፣ 1ሳሙ9፥16፣ 2ነገ19፥20፣ 20፥5፣ መዝ10፥17፣ 34፥17
9፥4 ዘኍ17፥1፣ ዘዳ17፥20፣ 1ነገ3፥14፣ 14፥8፣ 15፥5፣ 1ዜና28፥9፣ ምሳ4፥4
9፥5 2ሳሙ7፥15፣ 1ዜና22፥10
9፥6 ዘዳ28፥15፣ 2ሳሙ7፥14፣ 1ነገ11፥10፣ 2ነገ18፥12፣ ኤር17፥27፣ 26፥4፣ 32፥23፣ 44፥23
9፥7
ዘሌ18፥24-28፣ ዘዳ4፥26፣ 12፥5፣ 28፥37፣ ኢሱ23፥13፣ 2ነገ17፥23፣ ኢዮ17፥6፣ መዝ44፥14፣

ሕዝቡን አሰናበተ፤ ሕዝቡም ንጉሡን
መረቁ፤ እግዚአብሔር ለባሪያው ለዳዊትና
ለሕዝቡ ለእስራኤል ባደረገው በጎ ነገር
ሁሉ ከልብ ጥዳስተው ሐሤት በማድረግ
ወደየቤታቸው ተመለሱ።

እግዚአብሔር ለሰሎሞን ዳግመኛ ተገለጠ

9፥1-9 ተጓ ምብ — 2ዜና 7፥11-22

9 ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና
የራሱን ቤተ መንግሥት ሠርቶ ከጨረሰና
ለመሥራት የፈለገውንም ሁሉ ካከናወነ በኋላ፣
2እግዚአብሔር ለሰሎሞን በገባዖን ተገልጦለት
እንደ ነበረ ሁሉ ዳግም ተገለጠለት።
3እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤

"በፊቴ ያቀረብኸውን ጸሎትና
ልመና ሰምቻለሁ፤ ይህን
የሠራኸውንም ቤተ መቅደስ
ስሜን በዚያ ለዘላለም እንዲኖር
በማድረግ ቀድሼዋለሁ፤ ዐይኖቼና
ልቤ ምንጊዜም በዚያ ይሆናሉ።
4 "አንተም አባትህ ዳዊት
እንዳደረገው፣ በልበ ቅንነትና
በትክክለኛነት ብትሄድና የማዝህን
ሁሉ ብትፈጽም፣ ሥርዐቴንና
ሕጌን ብትጠብቅ፣ 5ለእባትህ
ለዳዊት፣ 'በእስራኤል ዙፋን ላይ
የሚቀመጥ ከዘርህ ሰው አታጣም'
በማለት በሰጠሁት ተስፋ መሠረት
ዙፋንህን በእስራኤል ላይ ለዘላለም
አጸናለሁ።
6 "'ነገር ግን አንተም ሆንህ
ልጆችህ እኔን ከመከተል ወደ
ኋላ ብትመለሱ፣ የሰጠኋችሁን
ትእዛዞችና ሥርዐቶች ሳትጠብቁ
ብትቀሩ፣ ሂዳችሁም ሌሎችን
አማልክት ብታመልኩና
ብትሰግዱላቸው፣ 7እኔም
እስራኤልን ከሰጠኋቸው ምድር
እነቅላቸዋለሁ፤ ስለ ስሜ
የቀደስሁትን ይህን ቤተ መቅደስም
እተወዋለሁ፤ ከዚያም እስራኤል
በሕዝቦች ሁሉ ዘንድ መተረቻና

9፥7 ኤር7፥14፣ 24፥9፣10፣ ሕዝ5፥15፣ ኢል2፥17

[ሸ]8፥63 በዚህና በቍ 64 ላይ በትውፊት፣ የሰላም መሥዋዕት ይባላል።
[ቸ]8፥65 ወይም ከመግቢያው ጀምሮ ተብሎ መተርጐም ይችላል።
[ኀ]9፥6 የዕብራይስጡ ትርጒም የብዙ ቍጥርን ያመለክታል

9፥3 እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤ ሰሎሞን ላቀረበው ጸሎት እግዚአብሔር የሰጠው መልስ ጸሎቱ የተሰማለትና የተመለሰለት መሆኑን ያረጋግጣል። ይሁን እንጂ የሰሎሞን ዙፋንና የእስራኤል መንግሥት ጸንቶ የሚኖረው እርሱና ሕዝቡ ከትእዛዛቱ ሳይርቁ ጸንተው በታማኝነት ሲቆሙ መሆኑንም እግዚአብሔር አክሎ ገልጾታል (ቍ 4-9)። ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያረጋግጡትም ይህንኑ ነው፤ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ሁሉ ተፈጻሚነት የሚኖረው እርሱንና መንገዱን ለመከተል ፍለጋ ስናደርግ ብቻ ነው (ዮሐ 14፥13-21፤ 15፥7)።

9፥7 ይህን ቤተ መቅደስም እተወዋለሁ፤ ሕዝቡ መንገዱን በቅንነት የማይከተሉ ከሆነ (ቍ 6-9)፣ ከእንግዲህ እግዚአብሔር ሀልዎቱን፣ ኃይሉንና ክብሩን በቤተ መቅደስ ላይ እንደማይገልጥ ተናገረ፤ ለአዲስ ኪዳን ትውልድም ይህ ማስጠንቀቂያ ተገቢነት አለው።

መዘባበቻ ይሆናሉ፤ [8]ይህ ቤተ መቅደስ አሁን የሚያስገርም ቢሆንም እንኳ፣ የፍርስራሽ ክምር ይሆናል፤ ዐላፊ አግዳሚውም ሁሉ ይገረማል፤ እያፌዘም፣ 'እግዚአብሔር በዚህች ምድርና በዚህ ቤተ መቅደስ ላይ እንዲህ ያለውን ነገር ያደረገው ስለምን ይሆን?' ይላል፤ [9]'ራሱ መልሶም፣ 'አምን እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ጥፋት ያመጣባቸው አባቶቻቸውን ከግብፅ ምድር ያወጣውን አምላካቸውን እግዚአብሔርን ትተው ሌሎች አማልክትን በመከተል ስለ ሰገዱላቸውና ስላመለኳቸው ነው' ይላል።"

ሰሎሞን ያከናወናቸው ሌሎች ሥራዎች

9፡10-28 ተጓ ምብ — 2ዜና 8፡1-18

[10]ሰሎሞን ሁለቱን ሕንጻዎች፣ ማለትም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና የንጉሡን ቤተ መንግሥት ሠርቶ በፈጸመ በሃያኛው ዓመት መጨረሻ፣ [11]ንጉሥ ሰሎሞን በገሊላ የሚገኙትን ሃያ ከተሞች ለጢሮስ ንጉሥ ለኪራም ሰጠው፤ ንጉሡ ይህን ያደረገውም የሚያስፈልገውን ሁሉ ዝግባ፣ ጥድና ወርቅ ኪራም ሰጥቶት ስለ ነበር ነው፤ [12]ይሁን እንጂ ኪራም ከጢሮስ ተነሥቶ ሰሎሞን የሰጠውን ከተሞች ለማየት በሄደ ጊዜ አልተደሰተባቸውም፤ [13]እርሱም፣ "ወንድሜ ሆይ፤ እነዚህ የሰጠኸኝ ከተሞች ምንድን ናቸው?" አለ፤ እነዚህንም "ካቡል[o] ምድር' እላቸው፤ እስከ ዛሬም በዚህ ስም ይጠራሉ። [14]በዚያን ጊዜ ኪራም ለንጉሡ መቶ ሃያ መክሊት[m] ወርቅ ልኮለት ነበር።

[15]ንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ፣ የራሱን ቤተ መንግሥት፣ ሚሎን፣ የኢየሩሳሌምን ቅጥር፣ ሐጾርን፣ መጊዶንና ጌዝርን ለመሥራት የጐልበት ሥራተኞች መልምሎ ነበር። [16]የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን ወጥቶ በጌዝር ላይ አደጋ ጥሎ ያዛትን፣ አቃጠላትም፤ ነዋሪዎቿን ከነዓናውያንን ገድሎ ለልጁ ለሰሎሞን ሚስት መጻሪያ አድርጎ ሰጥቶአት ነበር፤ [17]ሰሎሞንም ጌዝርን መልሶ ሠራት፤ እንዲሁም የታችኛውን ቤትሖሮንን፣ [18]ባዕላትን፣ በይሁዳ ምድር በምድረ በዳው የምትገኘውን ተድሞርን[w] ሠራ፤ [19]ደግሞም ግናቸውንም በኢየሩሳሌም፣ በሊባኖስና በሌሎች ግዛቶቹ ሁሉ ለመሥራት የፈለገውን፣ ሥንቅ የሚከማችባቸውን፣ መረገሎች[p] የሚጠበቁባቸውን እንዲሁም ፈረሰኞች የሚቀመጡባቸውን ከተሞችና መንደሮች ሁሉ ሠራ።

9፡8 ዘሌ26፡32፣ ዘዳ29፡24፣ ኤር7፡4-15፣ ማቴ23፡38
9፡9 ዘጕ25፡3፣ ዘዳ29፡25፣ 31፡29፣ 2ነገ22፡17፣ ኤር5፡19፣ 13፡22፣ 16፡11፡13፣ 22፡9፣ 40፡3፣ 44፡23፣ ሰቆ4፡12
9፡11 ቊ14
9፡13 ኢሱ19፡27
9፡14 ቊ11
9፡15 ኢሱ10፡33፣ 11፡10፲1፣ 2ሳሙ5፡9፣ 1ነገ5፡13
9፡16 1ነገ3፡1፣ መዝ45፡12፣ 68፡29፣ 72፡10
9፡17 ኢሱ10፡10
9፡18 ኢሱ19፡44
9፡19 ዘወ1፡11፣ ዘዳ17፡16፣ 1ነገ4፡26፣ 2ዜና1፡14፣ 9፡25
9፡20 ዘጕ13፡29፣ ኢሱ11፡3
9፡21 ዘፍ9፡2526፣ 49፡15፣ ዘወ1፡11፣ ዘዳ20፡11፣ ኢሱ15፡63
9፡22 ዘሌ25፡39
9፡23 1ነገ5፡16
9፡24 2ሳሙ5፡9፣ 1ነገ3፡1፣ 11፡27
9፡25 ዘወ23፡14
9፡26 ዘጕ33፡35፣ 1ነገ10፡22፣ 22፡48፣ 2ነገ14፡22፣ 16፡6፣ 2ዜና20፡37፣ ኢሳ2፡16
9፡27 ሕዝ27፡8
9፡28 ቊ14፣ ዘፍ10፡29፣ 1ነገ10፡10፲11፣ 14፡21፣ 2ዜና1፡15፣ መክ2፡8
10፡1 ዘፍ10፡7፲28፣ 25፡3፣ ዘጕ12፡8፣ መሳ14፡12፣ ሕዝ16፡14፣ ማቴ12፡42፣ ሉቃ11፡31
10፡2 ዘፍ24፡10

[20]ከእስራኤል ሕዝብ ያልሆኑትን ከአሞራውያን፣ ከኬጢያውያን፣ ከፈሪዛውያን፣ ከኤዊያውያንና ከኢያቡሳውያን ሕዝቦች ሁሉ የተረፉትን፣ [21]እስራኤላውያን ዘሮቻቸውን ለማጥፋት ያልቻሉትንና በምድሪቱ የቀሩትን እነዚህን እስከ ዛሬ እንደሚደረገው ሁሉ፣ ሰሎሞን ለግዳጅ ሥራ መለመላቸው። [22]ይሁን እንጂ ሰሎሞን ከእስራኤላውያን ማንንም ባሪያ አላደረገም፤ እነርሱ ወታደሮቹ፣ ሹማምቱ፣ የጦር አለቆቹ፣ ሻምበሎቹ፣ ባለደራሶቹ ነበሩ። [23]እነዚህም ሰሎሞን የሚያሠራውን የሕንጻ ሥራ የሚያከናውኑትን ሠራተኞች የሚቈጣጠሩ ናቸው፤ ቍጥራቸውም አምስት መቶ አምሳ ነበር።

[24]የፈርዖን ልጅ ከዳዊት ከተማ ሰሎሞን ወዳሠራላት ቤተ መንግሥት ከመጣች በኋላ ሰሎሞን ሚሎንን ሠራ።

[25]ሰሎሞንም ለእግዚአብሔር ባሠራው መሠዊያ ላይ በዓመት ሦስት ጊዜ የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት በማቅረብ፣ ከዚሁ ጋር በእግዚአብሔር ፊት ዕጣን ያሳርግ ነበር፤ በዚህ ሁኔታም የቤተ መቅደሱን ግዳጅ ተወጣ።

[26]እንዲሁም ንጉሡ ሰሎሞን በኤዶምያስ ምድር፣ በኤሎት አጠገብ፣ በቀይ ባሕር ዳርቻ ላይ ባለችው በዔጽዮንጋብር መር ከቦችን ሠራ። [27]በመርከቦቹም ላይ ከሰሎሞን ሰዎች ጋር አብረው እንዲሠሩ፣ ኪራም ባሕሩን የሚያውቁ የራሱን መርከበኞች ላከ። [28]እነዚያም ወደ ኦፌር ሄደው አራት መቶ ሃያ መክሊት[m] ወርቅ ይዘው ተመለሱ፤ ይህንም ለንጉሥ ሰሎሞን ሰጡት።

ንግሥተ ሳባ ሰሎሞንን እንደ ጐበኘች

10፡1-13 ተጓ ምብ — 2ዜና 9፡1-12

10 ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ዝና እና ከእግዚአብሔር ስም ጋር ያለውን ግንኙነት በሰማች ጊዜ፣ አስቸጋሪ በሆኑ ጥያቄዎች ልትፈትነው መጣች። [2]ታላቅ አጀብ አስከትላ ሽቶ፣ እጅግ ብዙ ወርቅና የከበሩ ዕንቆች በግመል አስጭና ኢየሩሳሌም

[o]9፡13 ከቡል የሚለው የዕብራይስጥ ቃል፣ የመልካም ነገር ተምሳሌት ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ የሆነ ድምፅ አለው።
[m]9፡14 4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[w]9፡18 በዕብራይስጥ ታምር ተብሎ ይነበባል
[p]9፡19 ወይም ሠረገሎች ተብሎ መተርጐም ይችላል
[ዖ]9፡21 የዕብራይስጡ ቃል ሰውን ወይም ሦስን ፈጽሞ በማጥ ፋት ለእግዚአብሔር መስጠት የሚለውን ያመለክታል
[ሄ]9፡25 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል
[ኀ]9፡26 የዕብራይስጡ ያም ስውፍ ይሸውም የደንገል ባሕር ማለት ነው
[ሠ]9፡28 14.5 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው

እንዲት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ቃልና የአዲስ ኪዳን ሐዋርያትን ትምህርት ሳትታዘዝ ቀርታ፣ በምትኩ ግን ወደ ተሳሳተ አስተምህሮትና ወደ ረከሰው የዓለም መንገድ ፊቷን ብታቀና፣ የእግዚአብሔር መንፈስና ኀይል ከእርሷ ላይ ይወሰዳል፤ እግዚአብሔርም ከመንግሥቱ ያስወግዳታል (ራእ 2፡5 እና ማብ ይመ)።

ከደረሰች በኋላ፣ ወደ ሰሎሞን ገብታ በልቧ ያለውን ጥያቄ ሁሉ አቀረበችለት።
3ሰሎሞንም የጠየቀችውን ሁሉ መለሰላት፤ ንጉሡ አቅቶት የቀረ አንዳች ጥያቄ አልነበረም። 4ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ሁሉ፣ የሠራውንም ቤተ መንግሥት ስትመለከት፣ 5እንዲሁም በገበታው ላይ የሚቀርበውን መብል፣ የሹማምቱን አቀማመጥ፣ አሳላፊዎቹን ከነደንብ ልብሳቸው፣ ጠጅ አሳላፊዎቹን፣ ደግሞም በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ያቀረበውን የሚቃጠል መሥዋዕትሡ ስታይ እጅግ ተደነቀች።
6ንጉሡንም እንዲህ አለችው፤ "ስላከናወንኸው ሥራና ስለ ጥበብህ ባገሬ ሳለሁ የሰማሁት ትክክል ነው፤ 7ይሁን እንጂ፣ ራሴ መጥቼ እነዚህን ነገሮች በዐይኔ እስካይ ድረስ አላመንሁም ነበር፤ በእርግጥ ግማሹን እንኳ አልነገሩኝምና፤ ጥበብህና ብልጽግናህ ከሰማሁት በላይ ነው። 8ሰዎችህ እንዴት ያሉ ዕድለኞች ናቸው! ሁል ጊዜ በፊትህ ቆመው ጥበብህን የሚሰሙ ሹማምትህስ እንዴት የታደሉ ናቸው! 9በእንተ ዳስ ተሰኝቶ በእስራኤል ዙፋን ላይ ያስቀመጠህ እግዚአብሔር አምላክህ የተመሰገነ ይሁን፤ እግዚአብሔር በዘላለም ፍቅሩም እስራኤልን ከመውደዱ የተነሣ፣ ፍትሕና ጽድቅ እንዲሰፍን አንተን ንጉሥ አድርጎ አስነሣህ።"
10ለንጉሡም መቶ ሃያ መክሊት[ሀ] ወርቅ፣ እጅግ ብዙ ሽቶና የከበረ ድንጋይ ሰጠችው፤ ንግሥተ ሳባ ለንጉሥ ሰሎሞን ያበረከተ ችለትን ያን ያህል ብዛት ያለው ሽቶ ከዚያ በኋላ ከቶ አልመጣም።
11ከኦፌር ወርቅ ያመጡት የኪራም መር ከቦችም እጅግ ብዙ የሰንደል ዕንጨትና[ሀ] የከበሩ ዕንቆችም አመጡ። 12ንጉሡም የሰ ንደሉን ዕንጨት ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና ለቤተ መንግሥቱ መደገፊያ፣ ለበ ገናና ለመሰንቆ መሥሪያ አዋለው። ይህን ያህል ብዛት ያለው የሰንደል ዕንጨት እስከ ዛሬ ድረስ ከቶ አልመጣም፤ አልታየምም።
13ንጉሥ ሰሎሞንም ለንግሥተ ሳባ ከቤተ መንግሥቱ በልግስና ከሚሰጣት ሌላ፣ የፈለገችውንና የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣት፤ ከዚያም ከአሽቢዎቿ ጋር ወደ አገሯ ተመለሰች።

የሰሎሞን ብልጽግናና ክብር

10፥14-29 ተጓ ምብ — 2ዜና 1፥14-17፤ 9፥13-28

14ለሰሎሞን በየዓመቱ የሚገባለት ስድስት መቶ ሥልሳ ስድስት መክሊት[ሠ] ወርቅ ነበር። 15ይህም ከንግድና ከሌላ ገቢ ላይ የሚከፈለውን ቀረጥ፣ የዐረብ ነገሥታት ሁሉ የሚያገቡትንና አገረ ገዦች የሚሰበስቡትን ግብር ሳይጨምር ነው።
16ንጉሥ ሰሎሞንከተጠፈጠፈ ወርቅሁለት መቶ ታላላቅ ጋሻ አሠራ፤ በእያንዳንዱም ጋሻ የገባው ሦስት መቶ ሰቅል[ረ] ወርቅ ነበር። 17እንዲሁም ከተጠፈጠፈ ወርቅ ሦስት መቶ ትንንሽ ጋሻ አሠራ፤ በእያንዳንዱ ጋሻ የገባው ደግሞ ሦስት ምናን[ሰ] ወርቅ ነው። ንጉሡም እነዚህን የሊባኖስ ዱር በተባለው ቤተ መንግሥት አኖረ።
18ከዚያም ንጉሡ ከዝሆን ጥርስ ትልቅ ዙፋን አሠርቶ በንጹሕ ወርቅ አስለበጠው። 19ዙፋኑ ባለ ስድስት ደረጃ ነው፤ በስተ ኋላውም ዐናቱ ላይ ክብ ቅርጽ ሲኖረው፣ ግራና ቀኙ ባለመደገፊያ ነው፤ በመደገፊያዎቹም አጠገብ ሁለት አንበሶች ቆመዋል። 20በስድስቱም ደረጃ ዎቹ ላይ ግራና ቀኝ ስድስት ስድስት አንበሶች ቆመዋል። ይህን የመሰለም ዙፋን በየትኛውም አገር መንግሥት ከቶ ተሠርቶ አያውቅም። 21ንጉሥ ሰሎሞን የሚጠጣበት ዋንጫ ሁሉ የወርቅ ሲሆን፣ የሊባኖስ ዱር በተባለው ቤተ መንግሥት ውስጥ የነበረው ዕቃ በሙሉ ከንጹሕ ወርቅ የተሠራ ነበር፤ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ብር ይህን ያህል ዋጋ ስላልነበረው፣ ከብር የተሠራ ዕቃ ፈጽሞ አልነበረም። 22ንጉሡ ከኪራም መርከቦች ጋር አብረው በባሕር ላይ የሚጓዙ የተርሴስ የንግድ መርከቦች[ሀ] ነበሩት። እነዚህም በየሦስት ዓመቱ አንድ ጊዜ ወርቅ፣ ብርና የዝሆን ጥርስ፣ ጦጣዎችና ዝንጀሮዎች ያመጡ ነበር።
23ንጉሥ ሰሎሞንም በሀብትና በጥበብ ከምድር ነገሥታት ሁሉ ይበልጥ ነበር። 24ዓለሙ ሁሉ እግዚአብሔር በሰሎሞን ልብ ያኖረውን ጥበብ ለመስማት ወደ እርሱ መምጣት ይፈልግ ነበር። 25በየዓመቱም የሚመጣውን ሰው ሁሉ የብርና የወርቅ ዕቃ፣ ልብስ፣ የጦር መሣሪያ፣ ሽቶ፣ ፈረስና በቅሎ ስጦታ አድርጎ ያመጣለት ነበር።
26ሰሎሞን ሠረገሎችና[ሀ] ፈረሶች ሰበሰበ፤ አንድ ሺህ አራት መቶ ሠረገሎችና ዐሥራ ሁለት ሺህ ፈረሶች ነበሩት። እነዚህንም ሁሉ ሠረገሎች በሚያኖርበት ከተሞችና ራሱ በሚኖርበት በኢየሩሳሌም እንዲሆኑ አደረገ። 27ንጉሡም ብሩን በየቦታው እንደሚገኝ ድንጋይ አደረገ፤ የዝግባውም ዕንጨት ብዛት በቁላ እንደሚበቅል ሾላ ሆነ። 28የሰሎሞን ፈረሶች የመጡት ከግብፅና[ሐ] ከቀዌ ሲሆን፣ እነዚህንም ከቀዌ ገዝተው ያመጧቸው የቤተ መንግሥቱ ንግድ ሰዎች ነበሩ።

ሀ *10፥5* ወይም ወደ ላይ የሚመጣባቸው ደረጃዎች
ተብሎ መተር ጕም ይችላል
ሀ *10፥10* 4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
ሀ *10፥11* በዚህና በቍ. 12 ላይ፣ የአልጉም ዕንጨት ከሚባለው ጋር ተመሳሳ
ሠ *10፥14* 23 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
ረ *10፥16* 3.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው
ሰ *10፥17* 1.7 ኪሎ ግራም ያህል ነው
ሀ *10፥22* ዕብራይስጡ የተርሴስ መርከቦች ይላል
ሀ *10፥26* ወይም ሠረገሎች ተብሎ መተርጕም ይችላል
ሀ *10፥28* በዚህና በቍ. 29 ላይ ምናልባት በቂልቂያ የምትገኘዋ ሙዘር ልትሆን ትችላለች
ሐ *10፥28* ምናልባትም ኪልቂያ ልትሆን ትችላለች

10፥5 1ነገ14፥22
10፥7 ዘፍ45፥26፤ 1ዜና29፥25
10፥8 ምሳ8፥34
10፥9 ዘዳ7፥8፤ 1ነገ5፥7፤ መዝ11፥7፤ 33፥5፤ 72፥2፤ 99፥4፤ 103፥6፤ ኢሳ42፥10
10፥10 1ነገ9፥28፤ ኢሳ60፥6
10፥11 ዘፍ10፥29
10፥14 1ነገ9፥28
10፥16 2ሳሙ8፥7
10፥17 1ነገ7፥2
10፥21 ኢሳ60፥17
10፥22 1ነገ9፥26፡27፤ መዝ48፥7፤ ኢሳ2፥16፤ 23፥1፡14፤ 60፥6፡9
10፥23 1ነገ3፥12፡13፤ ማቴ6፥29፤ 12፥42
10፥24 2ሳሙ14፥20
10፥25 1ሳሙ10፥27
10፥26 ዘዳ17፥16
10፥27 ዘዳ17፥17፤ 1ዜና27፥28፤ ኢዮ 27፥16፤ ኢሳ60፥17፤ አሞ7፥14

29እንዲሁ ሠረገላ ከግብፅ የሚያመጡት በስድስት መቶ ሰቅል[a] ብር ሲሆን፣ ፈረሱን ደግሞ በመቶ አምሳ ሰቅል[b] ብር ያመጡ ነበር፤ ለኬጢያውያንና ለሶርያ ነገሥታትም እምጥተው ይሸጡላቸው ነበር።

የሰሎሞን ሚስቶች

11 ንጉሥ ሰሎሞን ከፈርዖን ልጅ ሌላ ብዙ የባዕድ አገር ሴቶችን ግለትም ሞዓባውያትን፣ አሞናውያትን፣ ኤዶማውያትን፣ ሲዶናውያትን፣ ኬጢያውያትን አፈቀረ። 2እነዚህም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን፣ "ልባችሁን ወደ አማልክታቸው በርግጥ ይመልሱታልና ከእነርሱ ጋር መጋባት የለባችሁም" ካላቸው አሕዛብ ወገን ነበሩ፤ ሆኖም ሰሎሞን ከእነዚሁ ጋር ፍቅሩ ጠና። 3እርሱም ከነገሥታት

10፥29 ዘኍ13፥29 11፥1 ዕዝ3፥ ዘፀ34፥16፡ 1ነገ14፥21፡31 11፥2 ዘፀ34፥16፡ 1ነገ16፥31 11፥3 ዕዝ1፥ ዘፍ22፥24፡ ዘዳ17፥17፡ ነህ13፥26፡ አስ2፥14፡ ምሳ31፥3

11፥4 ዘፀ34፥16፡ 1ነገ8፥61፡ 1ዜና29፥19 11፥5 ዕዝ7፥ ዘሌ 18፥21፡ መሳ2፥13፡ ኢሳ57፥9፡ ሰፎ1፥5

የተወለዱ ሰባት መቶ ሚስቶችና ሦስት መቶ ቁባቶች ነበሩት፤ ሚስቶቹም ልቡ ወደ ሌላ እንዲያዘነብል አደረጉት። 4ሰሎሞን በሸመገለ ጊዜ ሚስቶቹ ልቡን ወደ ሌሎች አማልክት መለሱት፤ የአባቱ የዳዊት ልብ እንደ ተገዛ ሁሉ፣ በፍጹም ልቡ ለእግዚአብሔር አልተገዛም። 5ሰሎሞንም የሲዶናውያንን ሴት አምላክ አስታሮትን፣ አስጸያፊውን የአሞናውያንን አምላክ ሚልኮምን ተከተለ። 6ስለዚህ ሰሎሞን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ፤ እንደ አባቱ እንደ ዳዊትም እግዚአብሔርን እስከ መጨረሻው አልተከተለም።

7ሰሎሞን ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ

11፥6 ዘዳ4፥25 11፥7 ዘሌ18፥21፡ 20፥25፡ ዘኍ21፥29፡ 2ነገ23፥13፡ ሐሥ7፥43

[a] *10፥29* 7 ኪሎ ግራም ያህል ነው
[b] *10፥29* 1.7 ኪሎ ግራም ያህል ነው

11፥1 ሰሎሞን ... ብዙ የባዕድ አገር ሴቶችን ... አፈቀረ፤ ምዕ 11 የሰሎሞንን መንፈሳዊ ውድቀትና ውድቅቱም ያስከተለበትን ውጤት ይገልጻል፡ (1) ሰሎሞን ከመጀመሪውኑ የእግዚአብሔር ሰው ነበረ፣ በእግዚአብሔር ሥርዓት መሠረት ተመላለሰ፣ ለእግዚአብሔርም ቤተ መቅደስ ሠራ (3፥3፣ 6፥1)፡ የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ ጸጋና ድነት ተለማመደ (3፥3፣ 6፥1)፡ የተለየ መንፈሳዊ ማስተዋል ተሰጥቶት ነበር (3፥10-14፡ 2ሳሙ 12፥24)፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶም ቅዱሳት መጻሕፍትን ጻፈ (4፥29-34 እና ማብ ይመ)።

(2) ሆኖም ግን ሰሎሞን በጎጢአት ተታለለ፣ ልቡን በማደንዳን ሌሌችን አማልክት ለማምለክ ከእግዚአብሔር መንገድ ፈቀን መለሰ፡ እግዚአብሔርን ለቀሥ አነሣሣው፡ ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር ቀጣው (ዕኑ 1-13፡ ይመ፡ ከዘዳ 29፥14-21፡ 30፥15-20፡ ከኦብ 3፥12-14 ጋር ያነጻጽሩ)።

(3) የሰሎሞን ከባዱ በደል ከባዕድ አምልኮና ከጎጢአት ጋር ተስማምቶና ተቻችሎ በመኖር ሥልጣንን፣ ስኬታማነትን፣ ሀብትንና የሥጋ ፍላጎት እርካታን መሻቱ ነው። ይህንኑ ለማሟላት ሰሎሞን የሚከተሉትን ፈጸመ፡ (ሀ) ያልተቀደሰ ግንኙነት ከባዕድ አገሮች ጋር መሠረተ (ከጢሮስ 9፥10-14፡ ከግብፅ 3፥1፡ 10፥28-29 እና ከሌሎች አገሮች ጋር 9፥25—10፥13)፡ (ለ) ይህን ግንኙነት ለማጽደቅም አያሌ ባዕድ ሚስቶችን አገባ፡ ቀኖቶችን አስቀመጠ (ዕኑ 1-8፡ የሚቀጥለውን ማብ ይመ፡ ዘፍ 29፥28 እና ማብ ይመ)፡ እንዲሁም (ሐ) ከነበረው የላቀ ሀብትና ክብር ይኖረው ዘንድ አብዝቶ ፈለገ (10፥14-19 ይመ፡ ከ1ጢሞ 6፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

(4) ከባዕዳን ጋር መተባበርን፣ ከግብፅ አገር ፈረሶችን ማስመጣትን፣ አያሌ ሴቶችን ማግባትንና ብዙ ብርን ወይም ወርቅን ማከማቸትን አስመልክቶ በዘዳ 17፥14-20 ላይ የሰፈረውን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ያንብቡ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰሎሞን የሕይወት ፍጻሜ ዘግልጽ የተናገረው የለም (ዕኑ 43 እና ማብ ይመ)።

11፥2 ከእነርሱ ጋር መጋባት የለባችሁም፤ ሰሎሞን አያሌ ሚስቶችን በማግባቱ የተላለፈው ትእዛዝ ነገሥታት ብዙ ሚስቶችን እንዳያገቡ የሚከለክለውን (ከዘዳ 17፥17 ጋር ያነጻጽሩ) ብቻ ሳይሆን፣ ከከነዓናውያን ወገን የሆኑትን አሕዛብ ሴቶችን እንዳያገቡ (ዘፀ 34፥12-16፡ ኢያ 23፥12-13) የሚከለክለውን ሕግ ጭምር ነው። ሰሎሞን በግልጽ መታዘዝ ያቃተው፣ "አምላኩን እግዚአብሔርን ማክበር ይማር ዘንድ፣ የዚህን ሕግ ቃል ሁሉና ይህን ሥርዐት በጥንቃቄ ይከተል ዘንድ ከእርሱ ጋር ይሁን" (ዘዳ17፥19)፣ የሚለውንም ቃል ነው።

11፥4 የአባቱ የዳዊት ልብ እንደ ተገዛ ሁሉ፣ በፍጹም ... አልተገዛም፤ የዳዊት ልብ፣ "በሙሉ የተገዛ ነበር" ሲባል እግዚአብሔርን ፈጽሞ አሳዝኖ አያውቅም ማለት ሳይሆን፣ ወደ ጣዖት አምልኮና ወደ ሌሎች አማልክት ፊቱን አላዞረም ማለት ነው። ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ዝሙት በመፈጸሙና፣ ያንኑ ለመሸፈን ባደረገው ተንኰል እግዚአብሔርንና ቃሉን አቃልሎአል (2ሳሙ 12፥9-10)፡ ይሁን እንጂ አያሌ የእስራኤል ነገሥታት እንዳደረጉት፣ ፈጽሞ ባዕዳን አማልክትን አላመለከም፡ ወይም በሌሎች አማልክት ላይ አምኑቱን አልጣለም (ከ15፥5 ጋር ያነጻጽሩ)።

11፥5 አስታሮትን ... ሚልኮምን ተከተለ፤ ሰሎሞን በመጀመሪያ ለሚስቶቹ አማልክት ሁኔታዎችን አመቻቸ፡ ከዚያም ልቡን ለእነዚሁ አማልክት አሳልፎ ሰጠ (ዕኑ 2-9)፡ (1) ሰሎሞን እግዚአብሔርን እያመለከ በተጨማሪ የሲዶናውያን አምላክ የሆነችውን አስታሮትን (ይህም ኢግብረገባዊ ሥርዐትንና የከዋክብትን አምልኮ የሚያካትት ነው)፣ የሞዓውያን አምላክ ሚሌክን (ልጅን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብን የሚመለከት ነው፡ ከዘሌ 18፥21፡ 20፥1-5 ጋር ያነጻጽሩ) እንዲሁም የአሞናውያንን አምላክ ካሞሽን (የፀሐይ አምላክ) አመለከ። ከዚህ በኋላ ሰሎሞን እውነተኛው አምላክ የኪዳን ጌታ ብቻ ነው አላለም (ከዘዳ 6፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ሰሎሞን ካለመታዘዙ የተነሣ ያጋጠመው ውድቀት ወደ ክህደት ይመራል። የጎጢአት ምንጩ ልብ ስለሆነ፣ ይህንኑ መቋቋም የሚቻለው የሰው ልብ በእምነትና በፍቅር ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ ብቻ ነው (ዘዳ 6፥4-9 ይመ፡ 1ነገ 3፥9 እና ይመ)። ሌሎችን ያስጠነቅቅ የነበረው ሰባኪው ሰሎሞን የመናፍስትን አምልኮ በመደገፉ፣ ርኩሰትንና ጭካኔን ይበጅ ብሎ በመቀበሉ፣ ይህን ከመሰለ አሳፋሪ ኀጢአት ላይ ወድቆ፣ እስራኤልን አረከሰ፡ ለእውነተኛው አምላክ ለእግዚአብሔር የሚገባውንም ክብር አሳጣ።

ባለው ተራራ ላይ ለአስጸያፊው የሞዓብ አምላክ ለካሞሽ እንዲሁም አስጸያፊ ለሆነው ለአሞናውያን አምላክ ለሞሎክ ማምለኪያ ኰረብታ ሠራ። 8ለአማልክቶቻቸው ዕጣን ለሚያጥኑና መሥዋዕት ለሚያቀርቡ ለሌሎቹ ሚስቶቹም ሁሉ በዚሁ ዐይነት ሠራላቸው።

9ሰሎሞን ሁለት ጊዜ ከተገለጠለት ከእስራኤል አምላክ ከእግዚአብሔር ልቡ ስለሸፈተ፣ እግዚአብሔር ተቈጣው። 10ምንም እንኳ ሌሎች አማልክትን እንዳይከተል ሰሎሞንን ቢከለክለውም፣ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አልጠበቀም፤ 11ስለዚህ እግዚአብሔር ሰሎሞንን እንዲህ አለው፤ "ይህን በማድረግህ ያዘዝሁህን ኪዳኔንና ሥርዐቴንም ባለመጠበቅህ፣ መንግሥትህን ከአንተ ወስጄ ከአገልጋዮችህ ለአንዱ አሰጠዋለሁ፤ 12ይህን ግን ስለ አባትህ ስለ ዳዊት ስል በዘመንህ አላደርገውም፤ መንግሥትህን የምቀዳት ከልጅህ እጅ ነው። 13ይህም ሆኖ መንግሥቱን በሙሉ አልነጥቀውም፤ ነገር ግን ስለ ባሪያዬ ስለ ዳዊትና ስለ መረጥኋት ስለ ኢየሩሳሌም ስል ለልጅህ አንድ ነገድ አሰጠዋለሁ።"

የሰሎሞን ጠላቶች

14እግዚአብሔር ከኤዶም ንጉሣዊ ቤተ ሰብ ኤዶማዊውን ሃዳድን በሰሎሞን ላይ አስነሣው። 15ከዚያ በፊት ዳዊት ከኤዶም ጋር በተዋጋ ጊዜ፣ የሞቱትን ለመቅበር መጥቶ የነበረው የሰራዊቱ አዛዥ ኢዮአብ የኤዶምን ሰዎች ሁሉ ፈጅቶ ነበር። 16ኢዮአብና እስራኤላውያን ሁሉ፣ በኤዶም ያሉትን ወንዶች በሙሉ እስኪያጠፋ ድረስ፣ እዚያው ስድስት ወር ቈይተው ነበርና። 17ሃዳድ ግን ገና በልጅነቱ አባቱን ካገለገሉ ጥቂት ኤዶማውያን ጋር ወደ ግብፅ ሸሸ፤ 18እነርሱም ከምድያም ተነሥተው ወደ ፋራን ሄዱ፤ ከፋራንም ሰዎች ይዘው ወደ ግብፅ በመምጣት፣ ወደ ግብፅ ንጉሥ ወደ ፈርዖን ገቡ። ንጉሡም ለሃዳድ ቤትና መሬት ሰጠው፤ ቀለብም አዘዘለት።

19ፈርዖንም ሃዳድን እጅግ ወደደው፤ ስለዚህም ከሚስቱ ከንግሥት ጣፍኔስ እኅት ጋር አጋባው። 20የጣፍኔስም እኅት ጌንባት የተባለውን ልጅ ወለደችለት፤ ጣፍኔስ በፈርዖን ቤት አሳደገችው፤ ጌንባትም ከፈርዖን ልጆች ጋር አደገ።

21ሃዳድ በግብፅ ሳለ ዳዊት ከአባቶቹ ጋር ማንቀላፋቱንና የሰራዊቱ አዛዥ ኢዮአብም መሞቱን ሰማ። ሃዳድም ፈርዖንን፣ "ወደ አገሬ እንድመለስ አሰናብተኝ" አለው።

22ፈርዖንም፣ "እዚህ ምን ጐደለብህና ነው ወደ አገርህ ለመግባት የፈለግኸው?" ሲል ጠየቀው።

11፥9 1ነገ3፥5
11፥10 1ነገ6፥12፣ 9፥6
11፥11 ቊ31፥ ዘሌ 18፥4፣ 1ሳሙ15፥27፣ 2ነገ17፥21፣ ማቴ21፥43
11፥12 መዝ89፥33
11፥13 ዘዳ12፥11፣ 2ሳሙ7፥15፣ 1ነገ12፥20
11፥14 1ነገ5፥4
11፥15 1ዜና18፥12
11፥18 ዘጸ10፥12

11፥23 2ሳሙ8፥3፣ 1ነገ5፥4
11፥24 2ሳሙ8፥5
11፥25 ዘፍ10፥22፣ 2ሳሙ10፥19
11፥26 2ዜና13፥6
11፥27 1ነገ9፥24
11፥28 ዘፍ39፥4፣ ሩት2፥1፣ ምሳ22፥29
11፥29
11፥29 1ነገ12፥15፣ 14፥2፣ 2ዜና9፥29፣ 10፥15
11፥30
11፥31 1ሳሙ15፥27
11፥31 ቊ11፥ 1ሳሙ15፥27
11፥32 2ሳሙ7፥15
11፥33 መሳ2፥13፣ 1ነገ3፥3፣ 2ነገ21፥22

ሃዳድም፣ "ምንም የጐደለብኝ የለም፣ ብቻ እንድሄድ ፍቀድልኝ" አለ።

23እግዚአብሔርም ከጌታው ከሱባ ንጉሥ ኰበለሎ የነበረውን የኤልያዳን ልጅ ሬዞንን ሌላ ጠላት አድርጎ በሰሎሞን ላይ አስነሣው፤ 24ዳዊት የሱባን ጎይል በደመሰሰ ጊዜ፣ ሬዞን ሰዎቹን በዙሪያው አሰባስቦ የወንበዴ አለቃ ሆነ፤ ሰዎቹም ወደ ደማስቆ ሄደው ተቀመጡ፤ በዚያም አነገሡት። 25ሃዳድ ካስከተለበት ችግር ሌላ ሬዞን በሰሎሞን ዘመን ሁሉ ሌላው የእስራኤል ተቃዋሚ ሆነ፤ ሬዞን ሶርያን ገዛ፤ እስራኤልንም ይጠላ ነበር።

ኢዮርብዓም በሰሎሞን ላይ ዐመፀ

26እንዲሁም ከሰሎሞን ሹማምት አንዱ የሆነው የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም በንጉሡ ላይ ዐመፀ፤ እርሱም ከጸሬዳ የመጣ ኤፍሬማዊ ሲሆን፣ እናቱ ጽሩዓ የተባለች መበለት ነበረች።

27በንጉሡ ላይ ያመፀበትም ምክንያት እንዲህ ነው፤ ሰሎሞን ድጋፍ የሚሆኑ እርከኖች በመሥራት የአባቱን የዳዊትን ከፋማ ቅጥር ይጠግን ነበር። 28ኢዮርብዓም ከፍተኛ ችሎታ ያለው ሰው ነበር፤ ሰሎሞንም ወጣቱ ሥራውን እንዴት በሚገባ እንደሚያከናውን ባየ ጊዜ፣ በዮሴፍ ነገድ ለሚሠራው የጕልበት ሥራ ሁሉ ኀላፊ አደረገው።

29በዚያ ጊዜም ኢዮርብዓም ከኢየሩሳሌም ሲወጣ፣ የሴሎው ነቢይ አኪያ በመንገድ ላይ ተገናኘውና፣ አኪያም አዲስ መጐናጸፊያ ለብሶ ነበር፤ ሁለቱ ብቻቸውን ሳሉ፣ 30አኪያ የለበሰውን አዲስ መጐናጸፊያ ይዞ ዐሥራ ሁለት ቦታ ቀደደው። 31ከዚያም ኢዮርብዓምን እንዲህ አለው፤ "ዐሥሩን ቍራጭ ለራስህ ውሰድ፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤ 'እነሆ፤ መንግሥቱን ከሰሎሞን እጅ አቀዳለሁ፤ ዐሥሩን ነገድ ለአንተ እሰጣለሁ፤ 32ነገር ግን ስለ ባሪያዬ ስለ ዳዊትና ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ ስለ መረጥኋት ስለ ኢየሩሳሌም ስል አንድ ነገድ ይቀርለታል፤ 33ይህን የማደርገውም እኔን ትተው፣ የሲዶናውያንን አምላክ አስታሮትን፣ የሞዓብን አምላክ ካሞሽን፣ የአሞናውያንን አምላክ ሚልኮምን ስላመለኩ እንዲሁም አባቱ ዳዊት እንዳደረገው በመንገዴ ስላልሄዱ፣ በፊቴ ትክክለኛውን ነገር ስላላደረጉ፣ ሥርዐቴንና ሕጌን ስላልጠበቁ ነው።

ሰ11፥24 ዕብራይስጡ በደመሰሳቸው ጊዜ ይላል።
ሸ11፥33 የዕብራይስጡ፣ የሰብዓ ሊቃናት፣ የቩልጌትና የሶርስት ትርጕሞች፣ እኔን ስለ ተወ ይላሉ።

11፥11 መንግሥትህን ከአንተ ወስጄ፤ እግዚአብሔር በሰሎሞን ላይ ያስተላለፈው ፍርድ፣ የእስራኤል መንግሥት ከሁለት እንዲከፈል ሲያደርግ፣ ከእርሱ በኋላ የነገሡት ነገሥታት የገዙት አንዱን ክፍለ ግዛት፣ ይኸውም የይሁዳን ግዛት ብቻ ነው (9-13:31)፣ (የስምዖን ነገድም የእነርሱ ግዛት ነበር፤ ከኢሳ 19፥1 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የመሲሑ ትውልደ ሐረግ ይጠበቅም ዘንድ ይኸው ግዛት ለልጁ ለሮብዓም ተሰጥቶ ነበር (ቊ13:32)፤ ውሉ ሳያድርም ዐመፁ ነገዶች ለኢዮርብዓም እንዲሰጡ ሆነ (ቊ 31-36)።

34 "'ይሁን እንጂ መንግሥቱን በሙሉ ከእጁ አልወሰድበትም፤ ስለ መረጥሁትና ትእዛዜንና ሥርዐቴን ስለ ጠበቀው ስለ ባሪያዬ ስለ ዳዊት ስል በሕይወት ዘመኑ ሁሉ እንዲገዛ አድርጌዋለሁ። 35መንግሥትን ከልጁ እጅ እወስዳለሁ፤ ለእነተም ዐሥሩን ነገድ እሰጥሃለሁ። 36ስሜ እንዲኖርባት በመረጥኋት በዚያች በኢየሩሳሌም ከተማ ለባሪያዬ ለዳዊት ምን ጊዜም በፊቴ መብራት እንዲኖረው፣ ለልጁ አንድ ነገድ እሰጣለሁ። 37አንተን ግን እኔ እወስድሃለሁ፤ ልብህ በወደደው ሁሉ ላይ ትነግሣለህ፤ የእስራኤልም ንጉሥ ትሆናለህ። 38ባሪያዬ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ አንተም ያዘዝሁህን ሁሉ ብትፈ ጽም፣ በመንገዴ ብትሄድ፣ ሥርዐቴንና ትእዛዜን በመጠበቅ ትክክል የሆነውን ነገር በፊቴ ብታደርግ፣ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ የዳዊትን ሥርወ መንግሥት እንዳጸናሁ፣ ለአንተም አጸናልሃለሁ፤ እስራኤልንም ለአንተ እሰጣለሁ። 39ከዚህ የተነሣም የዳዊትን ቤት አዋርዳለሁ፤ ነገር ግን ለዘላለም አይደለም።'"

40ሰሎሞን ኢዮርብዓምን ለመግደል ፈለገ፤ ኢዮርብዓም ግን ወዶ ግብፅ ሸሸ፤ ወደ ንጉሥ ወደ ሺሻቅ ሄዶ፣ ሰሎሞን እስኪሞት ድረስ በዚያው ተቀመጠ።

የሰሎሞን መሞት

11፥41-43 ተጓ ምብ — 2ዜና 9፥29-31

41 ስለ ሰሎሞን የቀረው በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት የተከናወነው፣ የሠራውም ሁሉ፣ ጥበቡም በሰሎሞን የታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ የለምን? 42ሰሎሞን በመላው እስራኤል ላይ በኢየሩሳሌም የነገሠው አርባ ዓመት ነው። 43ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በአባቱ በዳዊት ከተማ ተቀበረ፤ ልጁም ሮብዓም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

እስራኤል በሮብዓም ላይ ዐመፀ

12፥1-24 ተጓ ምብ — 2ዜና 10፥1—11፥4

12 እስራኤላውያን ሁሉ ሊያነግሡት ወደ ሴኬም ስለ ሄዱ፣ ሮብዓም ወደዚያው ሄደ። 2የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ይህን በሰማ ጊዜ፣ ከንጉሥ ሰሎሞን ሸሽቶ ይኖርበት ከነበረው ግብፅ ተመልሶ መጣ። 3ስለዚህም ወደ ኢዮርብዓም ላኩበት፤ እርሱና መላው የእስራኤል ጉባኤም ወደ ሮብዓም መጥተው፣ 4"አባትህ ከባድ ቀንበር ጫነብን፤ አንተ ግን አሁን የአባትህን ያሥቸጋሄ አገዛዝ የጫነብንንም ከባድ ቀንበር ብታቀልልን እንገዛልሃለን" አሉት።

5ሮብዓምም፣ "እንግዲያውስ ሂዱ፤ ከሦስት ቀን በኋላ ተመልሳችሁ ወደ እኔ ኑ" አላቸው። ስለዚህ ሕዝቡ ሄዱ።

6ከዚያም ሮብዓም አባቱ ሰሎሞን በሕይወቱ ሳለ ካገለገሉት ሽማግሌዎች ጋር ተማከረ፤ "ለዚህ ሕዝብ ምን መልስ እንድሰጥ ትመክሩኛላችሁ?" አላቸው።

7እነርሱም፣ "ዛሬ አንተ ለዚህ ሕዝብ አገልጋይ ብትሆንና ብትገዛለትና ደስ የሚያሰኝ መልስ ብትሰጠው፣ ምን ጊዜም የአንተ አገልጋይ ይሆናል" ብለው መለሱለት።

8ሮብዓም ግን ሽማግሌዎቹ የሰጡትን ምክር ንቆ፣ አብሮ አደግ የሆኑትንና እርሱን የሚያገለግሉትን ወጣቶች፣ 9"ሐሳብ ለማግኘት፣ የእናንተስ ምክር ምንድን ነው? 'አባትህ የጫነብንን ቀንበር አቅልልን' ለሚሉኝ ለእነዚህ ሰዎች ምን መልስ እንስጥ?" ሲል ጠየቃቸው።

10ወጣት አብሮ አደጎቹም፣ እንዲህ አሉት፣ "'አባትህ ከባድ ቀንበር ጫነብን፣ አንተ ግን ቀንበራችንን አቅልልን' ላሉህ ለእነዚህ ሰዎች፣ 'ትንሿ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ይልቅ ትወፍራለች፤ 11አባቴ ከባድ ቀንበር ጫነባችሁ፤ እኔማ ከዚያ ይብስ አከብደዋለሁ፤ አባቴ በዐለንጋ ገረፋችሁ፤ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ' በላቸው!" አሉ።

12ንጉሡ፣ "በሦስተኛው ቀን ተመልሳችሁ ኑ" ብሎአቸው ስለ ነበር፣ ኢዮርብዓምና ሕዝቡ ሁሉ በሦስተኛው ቀን ወደ ሮብዓም ተመልሰው መጡ። 13ንጉሡም በሽማግሌዎቹ የተሰጠውን ምክር ትቶ፣ ሕዝቡን የሚያስከፋ መልስ ሰጣቸው፤ 14ወጣቶቹ የሰጡትን ምክርም ተቀብሎ፣ "አባቴ ቀንበራችሁን አከበደባችሁ፤ እኔ ደግሞ ከዚያ ይብስ አከብደዋለሁ፤ አባቴ በአለንጋ ገረፋችሁ፤ እኔ ደግሞ በጊንጥ እገርፋችኋለሁ" አላቸው። 15እግዚአብሔር በሴሎናዊው በአኪያ አማካይነት ስለ ናባጥ ልጅ ስለ ኢዮርብዓም የተናገረው ቀድሞውኑ እግዚአብሔር የወሰነው ስለሆነ፣ መፈጸም ነበረበትና ንጉሡ ሕዝቡን አልሰማም።

16እስራኤልም ሁሉ ንጉሡ ሊሰማቸው አለመፈለጉን በተረዱ ጊዜ፣ ለንጉሡ እንዲህ በማለት መለሱ፤

"ከዳዊት ምን ድርሻ አለን?
ከእሴይስ ልጅ ምን የምናገኘው አለ?
እስራኤል ሆይ፤ ወደየድንኳንህ
ተመለስ፤

*12፥2 ወይም በግብፅ ቀረ ተብሎ መተርጕም ይችላል።

11፥36 2ሳሙ21፥17፤ 1ነገ11፥17
11፥37 2ሳሙ3፥21፤ 1ነገ14፥7
11፥38 ዘፀ1፥21፤ ዘዳ12፥25፤ 17፥19፤ 2ሳሙ8፥15
11፥40 1ነገ12፥2፤ 2ዜና10፥2፤ 12፥2
11፥43 ማቴ1፥7
12፥1 ቊ25፥ ዘፍ12፥6፤ ኢሱ24፥32
12፥2 1ነገ11፥40
12፥4 1ሳሙ8፥11-18፤ 1ነገ4፥20-28
12፥6 1ነገ4፥2
12፥7 ምሳ15፥1
12፥8 ዘሌ19፥32
12፥14 ዘፀ1፥14
12፥15 ዘዳ2፥30፤ 1ነገ11፥29፤ 2ዜና25፥20
12፥16 ዘፍ31፥14፤ 2ሳሙ20፥1፤ ኢሳ7፥17

11፥43 እንቀላፋ፤ የሰሎሞንን ከሀዲት የሚያሳያው ይኸው ምዕራፍ፣ ስለ ሰሎሞን ንስሐ ገብቶ ወደ እግዚአብሔር መመለሱን ሳያመለክት ሞቱን ይገልጻልና፤ የዜና መዋዕል ጸሐፊ ዳዊት ለልጁ ለሰሎሞን የሰጠውን "ማስጠንቀቂያ፣ ከተውከው ግን ለዘላለም ይተውሃል" (1ዜና 28፥9) በማለት ገልጾአል። እዚህ ላይ የተገለጸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አውነት፣ በጸጋ ውስጥ የነበረው ሰሎሞን፣ በዚያ ብታቀልልን እንገዛልሃለን" አሉት።

5ሮብዓምም፣ "እንግዲያውስ ሂዱ፤ ከሦስት ቀን በኋላ ተመልሳችሁ ወደ እኔ ኑ" አላቸው። ስለዚህ ሕዝቡ ሄዱ።

6ከዚያም ሮብዓም አባቱ ሰሎሞን በሕይወቱ ሳለ ካገለገሉት ሽማግሌዎች ጋር ተማከረ፤ "ለዚህ ሕዝብ ምን መልስ እንድሰጥ ትመክሩኛላችሁ?" አላቸው።

7እነርሱም፣ "ዛሬ አንተ ለዚህ ሕዝብ አገልጋይ ብትሆንና ብትገዛለትና ደስ የሚያሰኝ መልስ ብትሰጠው፣ ምን ጊዜም የአንተ አገልጋይ ይሆናል" ብለው መለሱለት።

8ሮብዓም ግን ሽማግሌዎቹ የሰጡትን ምክር ንቆ፣ አብሮ አደግ የሆኑትንና እርሱን የሚያገለግሉትን ወጣቶች፣ 9"ሐሳብ ለማግኘት፣ የእናንተስ ምክር ምንድን ነው? 'አባትህ የጫነብንን ቀንበር አቅልልን' ለሚሉኝ ለእነዚህ ሰዎች ምን መልስ እንስጥ?" ሲል ጠየቃቸው።

10ወጣት አብሮ አደጎቹም፣ እንዲህ አሉት፣ "'አባትህ ከባድ ቀንበር ጫነብን፣ አንተ ግን ቀንበራችንን አቅልልን' ላሉህ ለእነዚህ ሰዎች፣ 'ትንሿ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ይልቅ ትወፍራለች፤ 11አባቴ ከባድ ቀንበር ጫነባችሁ፤ እኔማ ከዚያ ይብስ አከብደዋለሁ፤ አባቴ በዐለንጋ ገረፋችሁ፤ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ' በላቸው!" አሉ።

12ንጉሡ፣ "በሦስተኛው ቀን ተመልሳችሁ ኑ" ብሎአቸው ስለ ነበር፣ ኢዮርብዓምና ሕዝቡ ሁሉ በሦስተኛው ቀን ወደ ሮብዓም ተመልሰው መጡ። 13ንጉሡም በሽማግሌዎቹ የተሰጠውን ምክር ትቶ፣ ሕዝቡን የሚያስከፋ መልስ ሰጣቸው፤ 14ወጣቶቹ የሰጡትን ምክርም ተቀብሎ፣ "አባቴ ቀንበራችሁን አከበደባችሁ፤ እኔ ደግሞ ከዚያ ይብስ አከብደዋለሁ፤ አባቴ በአለንጋ ገረፋችሁ፤ እኔ ደግሞ በጊንጥ እገርፋችኋለሁ" አላቸው። 15እግዚአብሔር በሴሎናዊው በአኪያ አማካይነት ስለ ናባጥ ልጅ ስለ ኢዮርብዓም የተናገረው ቀድሞውኑ እግዚአብሔር የወሰነው ስለሆነ፣ መፈጸም ነበረበትና ንጉሡ ሕዝቡን አልሰማም።

16እስራኤልም ሁሉ ንጉሡ ሊሰማቸው አለመፈለጉን በተረዱ ጊዜ፣ ለንጉሡ እንዲህ በማለት መለሱ፤

"ከዳዊት ምን ድርሻ አለን?
ከእሴይስ ልጅ ምን የምናገኘው አለ?
እስራኤል ሆይ፤ ወደየድንኳንህ
ተመለስ፤

*12፥2 ወይም በግብፅ ቀረ ተብሎ መተርጕም ይችላል።

11፥43 እንቀላፋ፤ የሰሎሞንን ከሀዲት የሚያሳያው ይኸው ምዕራፍ፣ ስለ ሰሎሞን ንስሐ ገብቶ ወደ እግዚአብሔር መመለሱን ሳያመለክት ሞቱን ይገልጻልና፤ የዜና መዋዕል ጸሐፊ ዳዊት ለልጁ ለሰሎሞን የሰጠውን "ማስጠንቀቂያ፣ ከተውከው ግን ለዘላለም ይተውሃል" (1ዜና 28፥9) በማለት ገልጾአል። እዚህ ላይ የተገለጸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አውነት፣ በጸጋ ውስጥ የነበረው ሰሎሞን፣ በዚያ ጸጋ ውስጥ ለዘለቄታው ጸንቶ እንዳልኖረ የሚያመለክት ነው። ከዚህ ላይ የእግዚአብሔር ቃል የሚያስጠነቅቀን የሚከተለውን ነው፣ ይህን የመሰለ ታላቅ ስጦታ፣ አገልግሎትና ጸጋ የነበረው ንጉሥ እንዲህ የሚወድቅ ከሆነ፣ የቆመ ሁሉ እንዳይወድቅ ይጠነቀቅ ዘንድ ይገባል (1ቆሮ 10፥12)።

ዳዊት ሆይ፤ እንግዲህ የገዛ ቤትህን
ጠብቅ!
ስለዚህም እስራኤላውያን ወደ ድንኳኖቻቸው
ተመለሱ። 17ሮብዓምም በይሁዳ ምድር
በሚኖሩት እስራኤላውያን ላይ ገዥ ሆነ።
18ንጉሥ ሮብዓም የጉልበት ሠራተኞች
አለቃ የነበረውን አዶኒራምን[ሀ] ላከው፤ ነገር
ግን እስራኤል ሁሉ በድንጋይ ወግረው
ገደሉት። ንጉሡ ሮብዓም ግን እንደ ምንም
ብሎ ሠረገላው ላይ በመውጣት ወደ
ኢየሩሳሌም ሸሸ። 19ስለዚህ ሕዝቡ በዳዊት
ቤት ላይ እስከ ዛሬ ድረስ እንዳመፀ ነው።
20ኢዮርብዓም መመለሱን እስራኤላውያን
ሁሉ በሰሙ ጊዜ፣ ወደ ጉባኤያቸው
በማስጠራት በመላው እስራኤል ላይ
አነገሡት። ለዳዊት ቤት በታማኝነት ጸንቶ
የተገኘው የይሁዳ ቤት ብቻ ነው።
21ሮብዓም ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ፣
የእስራኤልን ቤት ወግተው መንግሥቱን
ለሰሎሞን ልጅ ለሮብዓም እንዲመልሱ
መላ ውን የይሁዳ ቤትና የብንያምን ነገድ
ሰበሰበ፤ የሰራዊቱም ቍጥር አንድ መቶ
ሰማንያ ሺህ ነበር።
22ነገር ግን ይህ የእግዚአብሔር ቃል፣ የእግዚአብሔር
ሰው ወደ ሆነው ወደ ሳማያ መጣ፤ 23"ለይሁዳ
ንጉሥ ለሰሎሞን ልጅ ለሮብዓም፣ ለመላው
የይሁዳ ቤትና ለብንያም ነገድ፣ ለቀረውም
ሕዝብ ሁሉ እንዲህ በል፤ 24'እግዚአብሔር
የሚለው ይህ ነው፤ ይህ ነገር ከእኔ የሆነ
ነውና ወንድሞቻችሁን እስራኤላውያንን
ለመውጋት አትውጡ፤ እያንዳንዳችሁ
ወደየቤታችሁ ተመለሱ።' ስለዚህ
እግዚአብሔር እንዳዘዘው የእግዚአብሔርን
ቃል ሰሙ፤ ወደየቤታቸውም ተመለሱ።

በቤቴልና በዳን የቆሙ የወርቅ ጥጆች

25ከዚያም ኢዮርብዓም በኰረብታው
አገር በኤፍሬም የምትገኘውን ሴኬምን
ምሽግ አድርጎ ሠራ፤ በዚያም ተቀመጠ።
ደግሞም ያንን ትቶ በመውጣት የድኒኤልን
ምሽግ ሠራ።
26ኢዮርብዓም በልቡ እንዲህ ሲል
አሰበ፤ "መንግሥቱ ለዳዊት ቤት የሚመለስ
ይመስላል፤ 27ይህ ሕዝብ መሥዋዕት
ለማቅረብ ኢየሩሳሌም ወዳለው ወደ
እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሚወጣ ከሆነ፣
እንደገና ልቡን ወደ ጌታው ወደ ይሁዳ
ንጉሥ ወደ ሮብዓም ሊያዞር ነው። ከዚያም
እኔን ይገድሉኛል፤ ወደ ንጉሡም ወደ
ሮብዓም ይመለሳል።"
28ንጉሡ ከመከረበት በኋላ ሁለት የወርቅ
ጥጆች አሠርቶ ሕዝቡን፣ "እስራኤል ሆይ፤
ወደ ኢየሩሳሌም እስካሁን የወጣኸው
ይቢቃል፤ ከግብፅ ምድር ያወጡህ
አማልክትህ እነዚህ ናቸው" አለ። 29አንዱን
በቤቴል ሌላውንም በዳን አቆመው።

[ሀ] 12፥18 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆችና የሱርስት
ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ (1ነገ 4፥6፤ 5፥14
ይመ) ዕብራይስጡ፣ አዶራም ይላል
[ሐ] 12፥25 ዕብራይስጡ ጸኦኤል ይለዋል

12፥17 1ነገ 11፥13፡36
12፥18 ኢሴ 7፥25፤ 2ሳሙ 20፥24
12፥19 2ነገ 17፥21
12፥20 1ነገ 11፥13፡32፤ ሕዝ 37፥16
12፥21 1ነገ 14፥30፤ 15፥6፡16፤ 2ዜና 11፥1
12፥22 ዘዳ 33፥1፤ 2ነገ 4፥7፤ 2ዜና 12፥57
12፥25 ፍሥ 1፤ መሳ 8፥8
12፥27 ዘዳ 12፥56
12፥28 ዘፀ 32፥4፡8፤ 2ዜና 11፥15
12፥29 ዘፍ 12፥8፤ ኢሴ 7፥2፤ መሳ 18፥27-31፤ አሞ 8፥14

12፥20 **ኢዮርብዓም ... በመላው እስራኤል ላይ አነገሡት፤** ሰሎሞን ሲሞት (11፥43)፣ የዕብራውያን መንግሥት ለሁለት ተከፈለ፡ (1) እስራኤል የተባለውን የሰሜኑን መንግሥት በመጀመሪያ የገዛው ኢዮርብዓም ነበር፡ ይሁዳ የተባለውን የደቡቡን መንግሥት ደግሞ የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም ይገዛው ነበር (ቍ 17)። ይኸው መከፈልም ዐሥሩ ነገዶች በአሦር እስከ ተማረኩበት እስከ 722 ዓ.ክ. ቀጠለ። የደቡቡ መንግሥት በባቢሎናውያን የተማረከውም በ586 ዓ.ክ. ላይ ነው። የሁለቱ መንግሥታት ታሪክ በ1ነገ 12—22፣ 2ነገ 1—25፣ እና በ2ዜና 10—36 ላይ ተጽፎ ይገኛል።


(2) የእስራኤልና የይሁዳ ታሪክ የሚያሳየው በተደጋጋሚ እምቢተኛ ሆነው የእግዚአብሔርን ኪዳን ማፍረሳቸውን ነው። የሰሜኑ ነገሥታት አንዳቸው ሳይቀሩ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ማድረጋቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጸል (ለምሳሌ 16፥25፡30፣ 22፥52፤ 2ነገ 3፥3፣ 10፥29)፣ ብዙዎቹ የይሁዳ ነገሥታት ከኪዳኑ ተለዩ፡ "በእግዚአብሔር ፊት መልካም ነገር አደረገ" (2ነገ 18፥3፣ 22፥2) የተባሉት በጣም ጥቂት ሲሆኑ፣ ከእነርሱም ዕውቅ የሆኑት ሕዝቅኤል (2ነገ 18፥1—20፥21) እና ኢዮስያስ ናቸው (2ነገ 22፥1—23፥29)።

12፥24 **ይህ ነገር ከእኔ የሆነ ነውና፤** የገዛ ሕዝቡ እንዲከፈል ያደረገው እግዚአብሔር ራሱ ነው፡ ሁለት ሕዝብ ሆነው ይኖሩ ዘንድ ያቀደው እርሱ ነው፡ ይኸውም፣ (1) ጣዖትን በማምለካቸው የደረሰባቸው ቅጣት ነው፡ እንዲሁም (2) ከይሁዳ ነገድ ታማኝ በመሆን የቀሩት ማለትም ትሩፋኑ ተጠብቀው ይኖሩ ዘንድ ነው (11፥13)፡ መላው እስራኤል ከእግዚአብሔር የራቁ ቢሆኑም እንኳ ከይሁዳ ነገድ ውስጥ ትሩፋኑ በታማኝነታቸው ጸንተዋል፡ በእነርሱም በኩል እግዚአብሔር ተስፋውንና የመቤዠት ተግባሩን ፈጸመ።

12፥28 **ሁለት የወርቅ ጥጆች ... አማልክትህ እነዚህ ናቸው፤** የሰሜኑ መንግሥት ንጉሥ ኢዮርብዓም ሰዎች ጣዖታትን አማልክታቸው አድርገው እንዲያመልኳቸው በማድረግ (ቍ 27-30 ይመ፤ ከዘፀ 20፥3-4 ጋር ያነጻጽሩ) ተጻራሪ የሆነ የሃይማኖት ሥርዐት ዘረጋ፡ ይኸውም አሮን እንደ አበጀው የወርቅ ጥጃ ዐይነት ሠርቶ እንዲያመልኩ በማድረግ ነው፡ ከዚህም በላይ ሌዋውያን ወገን ያልሆኑ ካህናትንም ሾመ (ቍ 31)። እንግዲህ የእግዚአብሔርን ሕግ መስፈርት የማያሟሉትን ሰዎች ካህናት አድርጎ ሾመ ማለት ነው (የሚቀጥለውን ማብ ይመ)።

ኢዮርብዓም የመሠረተው ስሑት የሃይማኖት ሥርዐት ሁለት መዘዝ አስከተለ፡ (1) በሰሜኑ መንግሥት የሚኖረው አብዛኛው ሕዝብ የበአል አምልኮን ኢግብረገባዊ ከሆነው የዝሙት ድርጊቱ ጋር ተከተለ፡ (2) ለእግዚአብሔርና ለሕጉ ታማኝ ሆነው መኖርን የመረጡት አብዛኞዎቹ ትሩፋን፣ በመጀመሪያ በሰጠው ራእይና በትእዛዛቱ መሠረት እግዚአብሔርን ያመልኩ ዘንድ (2ዜና 11፥13-14)፣ "ንብረታቸውን ሁሉ ትተው" ወደ ደቡብ መንግሥት በተሰደዱ ጊዜ በእጅጉ ተሠቃዩ፡ ያደረጉትም እንደሚከተለው ተገልጸአል፡ "ከእያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ ከልባቸው የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ሁሉ፣ ለአባቶቻቸው አምላክ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርቡ ዘንድ፣ ሌዋውያኑን ተከትለው ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ" (2ዜና 11፥16 ይመ ከ15፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

የተከፋፈለው መንግስት



© 1991 The Zondervan Corporation

30 ይህም አድራጎት ኀጢአት ሆነ፤ ሕዝቡም
በዚያ ላለው ለመስገድ እስከ ዳን ድረስ ርቆ
ሄደ። 31 ኢዮርብዓም በማምለኪያ ኰረብቶች
ላይ አብያተ ጣዖታትን ሠራ፤ ከሕዝቡ
የተለያዩ ክፍሎች ሁሉ፣ ሌዋውያን ካልሆኑት
ካህናትን ሾመ። 32 በይሁዳ እንደሚደረገው
ሁሉ እርሱም በስምንተኛው ወር ዐሥራ
አምስተኛው ቀን በዓል እንዲሆን ወሰነ፤
በመሠዊያውም ላይ መሥዋዕት አቀረበ።
ለሠራቸው ጥጆች መሥዋዕት በማቅረብም
እንዲህ ያለውን ድርጊት በቤቴል ፈጸመ፤
በማምለኪያ ኰረብቶች ላይ ላሠራቸው
አብያተ ጣዖታት በቤቴል ካህናቱን መደበ።
33 ራሱ በመረጠው በስምንተኛው ወር፣
በዐሥራ አምስተኛው ቀን በቤቴል ባቆመው
መሠዊያ ላይ መሥዋዕት አቀረበ፤ ስለዚህ
ለእስራኤላውያን በዓል ወሰነላቸው፤ ዕጣንም
ለማቅረብ ወደ መሠዊያው ወጣ።

ከይሁዳ የመጣ የእግዚአብሔር ሰው

13 ኢዮርብዓም መሥዋዕት ለማቅረብ
በመሠዊያው አጠገብ ቆሞ
ሳለ፣ በእግዚአብሔር ቃል ታዞ አንድ
የእግዚአብሔር ሰው ከይሁዳ ወደ ቤቴል መጣ።
2 መሠዊያውንም በእግዚአብሔር ቃል
በመቃወም እንዲህ አለ፤ "አንተ መሠዊያ
ሆይ! እንግዲህ እግዚአብሔር የሚለው ይህ
ነው፤ 'እነሆ፤ ኢዮስያስ የተባለ ለዳዊት
ቤት ይወለዳልና፤ እርሱም አሁን እዚህ
መሥዋዕት የሚያቀርቡትን የኰረብታ
ማምለኪያ ካህናት በላይህ ይሠዋቸዋል፤
የሰዎችም ዐጥንት በአንተ ላይ ይነዳል።' "
3 በዚያች ዕለት ያ የእግዚአብሔር ሰው፣
እንዲህ ሲል ምልክት ሰጠ፤ "እግዚአብሔር
የሰጠውም ምልክት፣ 'እነሆ፣ መሠዊያው
ይሰነጠቃል፤ በላዩም ላይ ያለው ዐመድ
ይፈላል'." የሚል ነው።
4 ንጉሥ ኢዮርብዓምም ያ የእግዚአብሔር
ሰው በቤቴል መሠዊያ ላይ ጮኾ የተናገረውን
ሲሰማ፣ እጁን መሠዊያው ካለበት
በመዘርጋት፣ "ያዙት!" አለ፤ ነገር ግን ያች
የዘረጋት እጁ ደርቃ ቀረች፤ ሊመልሳትም
አልቻለም 5 እንዲሁም ያ የእግዚአብሔር ሰው
በእግዚአብሔር ቃል ተመርቶ በሰጠው
ምልክት መሠረት መሠዊያው ተሰነጠቀ፤
ዐመዱም ፈሰሰ።
6 ከዚያም ንጉሡ የእግዚአብሔርን ሰው፣
"እጁ ወደ ቦታዋ እንድትመለስ ወደ
ስምላክህ ወደ እግዚአብሔር ለምንልኝ፤
ጸልይልኝም" አለው። ስለዚህም የእግዚአብሔር
ሰው እግዚአብሔርን ለመነ፤ የንጉሡ
እጅ ወደ ቦታዋ ተመለሰች፤ እንደ
ቀድሞዋም ሆነች።
7 ንጉሡም የእግዚአብሔርን ሰው፣ "አብረኸኝ
ወደ ቤት እንሂድ፤ አንድ ነገር ቅመስ፤
ስጦታም አደርግልሃለሁ" አለው።
8 የእግዚአብሔር ሰው ግን ለንጉሡ እንዲህ
ሲል መለሰለት፤ "ግማሽ ሀብትህን ብትሰጠኝ
እንኳ፣ አብሬህ አልሄድም፤ እዚህ፣
እንጀራ አልበላም፤ ውሃም አልጠጣም።
9 በእግዚአብሔር ቃል፤ 'እንጀራ እንዳትበላ፣
ውሃም እንዳትጠጣ፣ በሄድህበትም መንገድ
እንዳትመለስ' ተብዬ ታዝዣለሁና።"
10 ስለዚህም በመጣበት ሳይሆን በሌላ መንገድ
ወደ ቤቴል ተመለሰ።
11 በዚያን ጊዜ በቤቴል የሚኖር አንድ
ሽማግሌ ነቢይ ነበር፤ ልጆቹም መጥተው
በዚያች ዕለት የእግዚአብሔር ሰው እዚያ
ያደረገውን ሁሉና ንጉሡንም ምን እንዳለው
ለአባታቸው ነገሩት። 12 አባታቸውም፣
"ለመሆኑ የተመለሰው በየትኛው መንገድ
ነው?" በማለት ሐየቃቸው፤ ልጆቹም ከይሁዳ
የመጣው የእግዚአብሔር ሰው የተመለሰበትን
መንገድ ለአባታቸው አሳዩት። 13 ስለዚህም
ልጆቹን፣ "በሉ አህያውን ጫኑልኝ"
አላቸው። እነርሱም አህያውን ጫኑለትና
ተቀምጠበት 14 እየጋለበ ያን የእግዚአብሔር
ሰው ተከተለው። ከዚያም በአንድ የወርካ
ዛፍ ሥር ተቀምጦ አገኘውና፣ "ከይሁዳ
የመጣኸው የእግዚአብሔር ሰው አንተ ነህን?"
ሲል ጠየቀው።
እርሱም፣ "አዎን እኔ ነኝ" ብሎ
መለሰለት።
15 ስለዚህ ነቢዩ፣ "አብረን ወደ ቤት
እንሂድና ምግብ ብላ" አለው።
16 የእግዚአብሔርም ሰው እንዲህ ሲል
መለሰለት፤ "ተመልሼ ከአንተ ጋር
አልሄድም፤ በዚህ ቦታም አብሬህ እንጀራ
አልበላም፤ ውሃም አልጠጣም፤ 17 እዚያ
እንጀራ እንዳትበላ፣ ውሃም እንዳትጠጣ፣
በሄድህበትም መንገድ እንዳትመለስ' ተብዬ
በእግዚአብሔር ቃል ታዝዣለሁና" አለው።
18 ሽማግሌው ነቢይ ግን፣ "እኔም
እኮ እንዳንተው ነቢይ ነኝ፤ መልአክ
በእግዚአብሔር ቃል፣ 'እንጀራ እንዲበላና
ውሃ እንዲጠጣ መልሰህ ወደ ቤትህ አምጣው'

12፥30
1ነገ13፥34፤
14፥16፤
15፥26:30፤
16፥2፣ 2ነገ3፥3፤
10፥29፤ 13፥2፤
17፥21
12፥31 ዘፀ29፥9፤
ዘሌ26፥30፤
1ነገ13፥32:33፤
2ነገ17፥29:32፤
2ዜና11፥1415፤
13፥9
12፥32
ዘጸ29፥12፤
2ነገ10፥29
12፥33
2ነገ23፥15፤
አሞ7፥13
13፥1 ዘፀ33፥1፤
መሳ13፥6፤
አሞ7፥13
13፥2 ዘሌ26፥30፤
2ነገ23፥1516:20፤
2ዜና34፥5
13፥3 ዘፍ24፥14፤
ዘፀ4፥8፤ ዮሐ2፥11
13፥6 ዘፍ20፥7፤
ዘጸ11፥2፤
ኤር37፥3፤
ሐሥ8፥24

13፥7 1ሳሙ9፥7
13፥8 ሶ16፥
ዘጸ22፥18
13፥16 ሶ8
13፥18
ዘፍ19፥14፤
ዘፀ13፥3፤
1ነገ22፥6:12፤
2ዜና35፥21፤
ኢሳ36፥10

19
17፥1
24

12፥31 **ሌዋውያን ካልሆኑት ካህናትን ሾመ፤** ኢዮርብዓም በዘጸ 3፥6-9፤ 8፥5-20 ላይ ከተመለከተው ከእግዚአብሔር መስፈርት ውጭ የሆኑትን ካህናት ሾመ። በአዲስ ኪዳን ግን የሌዊ የክህነት ሥርዐት ቀርቶአል፤ ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ወይም መሪዎች ለሚሆኑት አገልጋዮች እግዚአብሔር ዐበይት የሆኑትን መስፈርቶች በቃሉ ላይ አጽንቶአል፤ እነዚህ መንፈሳዊና ሥነምግባራዊ መስፈርቶችም በ1ጢሞ 3፥17 እና በቲቶ 1፥5-9 ተዘርዝረዋል፤ (በገጽ 1925 ላይ፣ «*የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

13፥2 **ኢዮስያስ፤** ይህ ትንቢት ኢዮስያስ ከመወለዱ ከ300 ዓመት በፊት ተነገረ፤ ይህ ትንቢት ስለመፈጸሙ 2ነገ 23፥15-20 ይመልከቱ።

13፥9 **በእግዚአብሔር ቃል፤** ነቢዩ እግዚአብሔርን ወክሎ የሚናገር በመሆኑ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ሙሉ በሙሉ በመከተል ይመላለስ ዘንድ ግዴታ ነበረበት። ይኸው ነቢይ ከጊዜ በኋላ የእግዚአብሔርን ቃል ሳይከተል በመቅረቱ ሕይወቱን ለሞት ዳረገ (ሶ 11-24)።

ብሎኝ ነው" አለው፤ ነገር ግን ውሸቱን ነበር። 19ስለዚህ የእግዚአብሔርም ሰው አብሮት ተመልሶ በቤቱ በላ፤ ጠጣም።

20በማእድ ተቀምጠው ሳሉ፣ የእግዚአብሔር ቃል መልሶ ወደ አመጣው ወደ ሽማግሌው ነቢይ መጣ፤ 21ከይሁዳ ለመጣውም የእግዚአብሔር ሰው፣ "እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፣ 'የእግዚአብሔርን ቃል አቃለሃል፤ ከምላከህ እግዚአብሔር የሰጠህንም ትእዛዝት አልጠበቅህም፤ 22ተመልሰህ በመምጣት እንዳትበላና እንዳትጠጣ በነገረህ ቦታ እንጀራ በላህ፤ ውሃም ጠጣህ። ስለዚህ ሬሳህ በአባቶችህ መቃብር አይቀበርም' " ሲል ሥጭ ተናገረው።

23የእግዚአብሔርም ሰው በልቶና ጠጥቶ ካበቃ በኋላ፣ ያ መልሶ ያመጣው ነቢይ አህያውን ጫነለት። 24ሲሄድ ሳለም አንበሳ መንገድ ላይ አግኝቶ ገደለው፤ ሬሳውም በመንገድ ላይ ተጋደመ፤ አህያውና አንበሳውም አጠገቡ ቆመው ነበር። 25በዚያ ያለፉ ሰዎች ሬሳው በመንገድ ላይ ተጋድሞ፣ አንበሳውም አጠገቡ ቆሞ ስላዩ፣ ሽማግሌው ነቢይ ወዳለበት ከተማ ሄደው ይህንኑ ተናገሩ።

26ያም ከመንገድ የመለሰው ነቢይ ይህን ሲሰማ፣ "ይህ የእግዚአብሔርን ቃል ያቃለለው ያ የእግዚአብሔር ሰው ነው፤ እግዚአብሔር ባስጠነቀቀው ቃል መሠረት አሳልፎ ሰጥቶት አንበሳ ሰብሮ ገድሎታል" አለ።

27ከዚያም ነቢዩ ልጆቹን፣ "በሉ አህያ ጫኑልኝ" አላቸውና ጫኑለት። 28ከዚያም ሄዶ ሬሳው መንገድ ላይ ተጋድሞ አንበሳውና አህያው በአጠገቡ ቆመው አገኘ፤ አንበሳው ሬሳውን አልበላውምና፣ አህያውንም አልሰበረውም። 29ስለዚህ፣ ነቢዩ የዚያን የእግዚአብሔር ሰው ሬሳ አንሥቶ በአህያው ላይ ጫነ፤ አልቅሶ ለመቅበርም ራሱ ወደሚኖርበት ከተማ አመጣው። 30ከዚያም ሬሳውን በራሱ መቃብር ቀበረው፤ "አወይ ወንድሜን" እያሉም አለቀሱለት።

31ከቀበሩትም በኋላ ልጆቹን እንዲህ አላቸው፤ "እኔም በምሞትበት ጊዜ የእግዚአብሔር ሰው በተቀበረበት መቃብር ቅበሩኝ፤ ዐጥንቶቼንም በዐጥንቶቹ አጠገብ አኑሩ። 32በቤቴል ባለው መሠዊያ፣ በሰማርያ ከተሞችና በየኰረብታው ባሉ ማምለኪያ ስፍራዎች ላይ በእግዚአብሔር ቃል ሥጭ ያሰማው መልእክት በትክክል የሚፈጸም ነውና።"

33ይህም ሁሉ ሆኖ ኢዮርብዓም ከክፉ መንገዱ አልተመለሰም፤ ይልቁንም በኰረብታ ማምለኪያዎች ከየትኛውም ክፍል እንደ ገና ካህናትን ይሾም ጀመር፤ ካህን ለመሆን የሚፈልገውንም ሁሉ ለየኰረብታ ማምለኪያዎቹ ለየ። 34ይህም ኀጢአት የኢዮርብዓም ቤት እንዲወድቅና ከምድር ገጽም እንዲደመሰስ ምክንያት ሆነ።

አኪያ በኢዮርብዓም ላይ የተናገረው ትንቢት

14 በዚያን ጊዜ የኢዮርብዓም ልጅ አብያ ታመመ፤ 2ኢዮርብዓም ሚስቱን እንዲህ አላት፤ "ተነሺ፣ የኢዮርብዓም ሚስት መሆንሽ እንዳይታወቅብሽ ሆነሽ፣ ወደ ሴሎ ሂጂ፤ በዚህ ሕዝብ ላይ እንደምነግሥ የነገረኝ ነቢይ አኪያ እንሆ፤ በዚያ ይገኛል። 3ስትሄጂም ዐሥር እንጀራ፣ ጥቂት ሙልሙል ዳቦ እና አንድ እንስራ ማር ይዘሽ ሂጂ፤ እርሱም በልጁ ላይ የሚደርሰውን ይነግርሻል።" 4ስለዚህ የኢዮርብዓም ሚስት ያላትን አድርጋ በሴሎ ወደ ሚገኘው ወደ አኪያ ቤት ሄደች።

በዚህ ጊዜ አኪያ ከማርጀቱ የተነሣ ዐይኖቹ ፈዘው ነበር። 5እግዚአብሔር ግን ለአኪያ፣ "እነሆ፤ የኢዮርብዓም ሚስት ስለ ታመመው ልጅ ልትጠይቅህ ሌላ ሴት መስላ ትመጣለችና እንዲህ ብለህ መልሳት" ብሎ ነገረው።

6አኪያም የእግሯን ኮቴ ድምፅ አበሩ ላይ እንደ ሰማ እንዲህ አላት፤ "የኢዮርብዓም ሚስት ሆይ ግቢ፤ ግን ለምንድን ነው ሌላ ሴት መስለሽ ለመታየት የፈለግሽው? ለአንቺ ከባድ ነገር እንድነግርሽ ተልኬአለሁ። 7አሁንም ሂጂና ኢዮርብዓምን የእስራኤል

13፡21-22 **የእግዚአብሔርን ቃል አቃለሃል፤** ስሙ ያልተገለጸው ነቢይ ታሪክ ተጽፎ የሚገኘው ዛሬ ለምንገኘው ምእመናን መቀጣጫና ማስጠንቀቂያ (ከ1ቆሮ 10፡1-3 ጋር ያነጻጽሩ) ይሆነን ዘንድ ነው። (1) አንድ ክርስቲያን በማንኛውም የሕይወት ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ፣ ምን የሚጸንባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው። የአንድ ዕውቅ የእግዚአብሔር አገልጋይ ቃል ወይም የመላእክት ቃል እንኳ ቢሆን፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያቱ ከመሰከሩት የመጀመሪያውና መሠረታዊው ቃል ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ፣ ተቀባይነት ማግኘት የለበትም (1ቆሮ 14፡29፤ ገላ1፡8-9፤ እንዲሁም 1ዮሐ 4፡1 እና ማብ ይመ)።

(2) ያለፈው ታማኝነትም ሆነ አገልግሎት የቱንም ያህል ከፍተኛ ቢሆን (ቊ 20-25)፣ እግዚአብሔር ያዘዘውን ተላልፈው ከተገኙ፣ ትእዛዙን አለማክበር ቅጣት ማስከተሉ አይቀርም።

(3) አንድ ምእመን የእግዚአብሔርን ቃል አቃሎ የሚይዝ ከሆነ፣ ሕይወቱ ከፍተኛ አደጋ ላይ ወድቆአል ማለት ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የሞት የሽረት ጉዳይ አድርገው አለመያዛቸው፣ ለውድቀታቸው ዋናው መንሥኤ ይሆናል (ዘፍ 3፡4 እና ማብ ይመ)።

(4) እግዚአብሔር ቃሉን እንዲሰብኩ የተጠሩት ለቃሉ ታማኝ ሎሌዎች ሆነው እንዲያገለግሉት ይፈልጋል (ከ1ጢሞ 3፡1-11፤ ቲቶ 1፡5-9፤ ከያዕ 3፡1 ጋር ያነጻጽሩ)። ለእግዚአብሔር ሰዎች አርአያ ሆነው እንዲታዩም ግዴታ አለባቸው።

13፡24 **አንበሳ ... ገደለው፤** ከዚህ ሞት በኋላ ይህ ነቢይ ዘላለማዊ ቅጣትን ተቀበለ ተብሎ መታሰብ የለበትም፤ የእርሱ አለመታዘዝ ሙሴ ካሳየው አለመታዘዝ ጋር በተመሳሳይ ደረጃ ይመደባል (ዘፍ 20፡12 እና ማብ ይመ)።

ስምላክ እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው ብለሽ ንገሪው፤ ከሕዝቡ መካከል አንሥቼ የሕዝቤ የእስራኤል መሪ አደረግሁህ፤ ⁸ከዳዊት ቤት መንግሥቱን ቀድጄ ለአንተ ሰጠሁህ፤ አንተ ግን በፊቴ መልካም ነገር በማድረግ ብቻ ትእዛዜን እንደ ጠበቀው፤ በፍጹም ልቡም እንደ ተከተለኝ እንደ ባሪያዬ እንደ ዳዊት አልሆንህም። ⁹ከአንተ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ አንተ የከፋ ሥራ ሠራህ፤ ለራስህም ከቀለጠ ብረት ሌሎች አማልክትን ሠራህ፤ ቊጣዬን አነሣሣህ፤ ወደ ኋላህም ጣልኸኝ።

¹⁰ʷ ‘ስለዚህ እኔም በኢዮርብዓም ቤት ላይ ጥፋትን አመጣለሁ፤ ባሪያም ይሁን ነጻ ዜጋ የኢዮርብዓምን ወንድ ልጅ ሁሉ ከእስራኤል አስወግዳለሁ፤ ኩበትም ዐመድ እስኪሆን ድረስ እንደሚቃጠል፣ እኔም የኢዮርብዓምን ቤት እንዲሁ አቃጥላለሁ። ¹¹ከኢዮርብዓም ወገን በከተማ የሞተውን ውሾች፣ በሳላገር የሞተውን ደግሞ የሰማይ አሞሮች ይበሉታል፤ እግዚአብሔር ተናግሮአልና!’

¹²ˣ እንግዲህ አንቺም ወደ ቤትሽ ሂጂ፤ የምትኖሪበትን ከተማ እግርሽ እንደ ረገጠ፣ ልጁ ይሞታል፤ ¹³እስራኤልም ሁሉ አልቅሰው ይቀብሩታል። የእስራኤል ስምላክ እግዚአብሔር ከኢዮርብዓም ቤት ሁሉ መልካም ነገር ያገኘበት እርሱ ብቻ ስለ ሆነ፣ በወግ በማዕረግ የሚቀበር እርሱ ብቻ ነው።

¹⁴ʸ ‘ከዚህም በላይ፣ እግዚአብሔር የኢዮርብዓምንከተሰብየሚያስወግድንጉሥ በእስራኤል ላይ ለራሱ ያስነሣል፤ ይህም ዛሬ፣ አሁኑኑ ይሆናል።ᶻ ¹⁵እግዚአብሔር እስራኤልን በውሃ ውስጥ እንደሚንቀጠቀጥ ሸንበቆ ያንቀጠቀጠዋል፤ የአሼራን ምስል ዐምድ በመሥራት እግዚአብሔርን ለቊጣ ያነሣሡት ስለ ሆነ፣ እግዚአብሔር ለቀድሞ አባቶቻቸው ከሰጣቸው ከዚህች ከመልካሚቱ ምድር እስራኤልን ይነቅላቸዋል፤ ከወንዙም ማዶ ይበትናቸዋል። ¹⁶ኢዮርብዓም ኀጢአት ሠርቶ፣ እስራኤልንም እንዲሠሩ በማድረጉ፣ እግዚአብሔር እስራኤልን ይተዋቸዋል።’

¹⁷የኢዮርብዓም ሚስትም ተነሥታ ወደ ቴርሳ ሄደች፤ የቤቱን መድረክ ወዲያው እንደ ተራመደች ልጁ ሞተ፤ ¹⁸ከዚያም ቀበሩት፤ እግዚአብሔር በባሪያው በአኪያ አማካይነት እንደ ተናገረ፣ እስራኤል ሁሉ አለቀሱለት።

¹⁹የቀረው የኢዮርብዓም ታሪክ፣ ያደረገው ጦርነትና አገዛዙም ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎአል። ²⁰እርሱም ሃያ ሁለት ዓመት ነግሦ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ ልጁ ናዳብም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

የይሁዳ ንጉሥ ሮብዓም

14፥21፤25፥31 ተጓ ምብ — 2ዜና 12፥9-16

²¹የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም በይሁዳ ነገሠ፤ በነገሠም ጊዜ ዕድሜው አርባ አንድ ዓመት ነበር፤ እርሱም እግዚአብሔር ለስሙ መጠሪያ እንድትሆን ከእስራኤል ነገድ ሁሉ በመረጣት በኢየሩሳሌም ዐሥራ ሰባት ዓመት ገዛ። እናቱ ናዕማ የተባለች አሞናዊት ነበረች።

²²ይሁዳ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረገ፤ ከአባቶቻቸው ይልቅ እነርሱ በሠሩት ኀጢአት ይበልጥ የቅናት ቊጣውን አነሣሡ፤ ²³እንዲሁም በእያንዳንዱ ኰረብታና በየቅልልቁ ዛፍ ጥላ ሥር የማምለኪያ ኰረብቶችን አዕማደ ማየታት፣ የአሼራን ምስል ዐምድ ለራሳቸው አቆሙ። ²⁴ካህያም ይልቅ፣ የቤተ ጣዖት ወንዶችም በምድሪቱ ላይ ነበሩ፤ እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ፊት አሳዶ ያስወጣቸው አሕዛብ የፈጸሙትን አስጸያፊ ድርጊት ሁሉ እነዚህም ፈጸሙ።

²⁵ሮብዓም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት የግብፅ ንጉሥ ሺሻቅ በኢየሩሳሌም ላይ አደጋ ጣለ፤ ²⁶የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና የቤተ መንግሥቱን ሀብት ወሰደ፤ ሰሎሞን ያሠራቸው የወርቅ ጋሻዎች እንኳን ሳይቀሩ ሁሉንም ነገር አጋዘ።

14፥23 ዘፀ23፥24፤ ዘዳ12፥2፡3፤ 16፥22፤ ሕዝ6፥13፤ ሆሴ10፥1፤ 14፥24 ዘዳ23፥17፤ 1ነገ11፥57፤ 2ነገ21፥2፤ ዕዝ9፥11፤ ምሳ21፥27፤ ኢሳ1፥13፤ ኤር16፥18፤ 32፥35፤ 44፥4 14፥25 2ዜና12፥2 14፥26 2ሳሙ8፥7፤ 1ነገ15፥15፡18

ˣ14፥14 በዕብራይስጡ የዚህ ዐረፍተ ነገር ትርጕም በትክክል አይታወቅም
ʸ14፥15 በዚህም ሆነ በሌሎቹም የመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ክፍሎች፣ የአሼራ ጣዖት አምላክ ምስል ነው
ᶻ14፥15 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው

14፥8
1ሳሙ15፥27፤ 2ሳሙ8፥15፤ 1ነገ3፥ 15፥5፤ 2ነገ14፥3፤ 15፥3፡34፤ 16፥2፤ 18፥3፤ 20፥3፤ 22፥2
14፥9 ዘፀ20፥4፤ 32፥4፤ ዘዳ32፥16፤ 1ነገ16፥2፡30፡33፤ 21፥25፤ 2ነገ21፥9፡11፤ 24፥3፤ 2ዜና11፥15፤ ነህ9፥26፤ መዝ50፥17፤ 78፥58፤ ኤር2፥27፤ 7፥18፤ 8፥19፤ 32፥32፡33፤ 44፥3፤ ሕዝ8፥17፤ 16፥26፤ 23፥35
14፥10 ዘዳ32፥36፤ ኢሳ23፥15፤ 1ሳሙ12፥25፤ 15፥26፤ 1ነገ13፥34፤ 15፥29፤ 2ነገ9፥89፤ ሆሴ13፥11
14፥11
ዘፍ40፥19፤ ዘዳ28፥26፤ 1ነገ16፥4፤ 21፥24
14፥13
2ዜና12፥12፤ 19፥3
14፥15 ዘዳ12፥3፤ 29፥28፤ 2ዜና7፥20፤ ኤር44፥3
14፥16
1ነገ12፥30፤ 15፥26
14፥17
ኢሳ12፥24፤ 1ነገ15፥33

14፥21 1ነገ11፥1
14፥22 ዘዳ32፥21፤ 2ነገ17፥19፤ 2ዜና12፥1፤ መዝ78፥58፤ ኤር44፥3፤ 1ቆሮ10፥22

ቀበሩት፤ እግዚአብሔር በባሪያው በአኪያ አማካይነት እንደ ተናገረ፣ እስራኤል ሁሉ አለቀሱለት።

¹⁹የቀረው የኢዮርብዓም ታሪክ፣ ያደረገው ጦርነትና አገዛዙም ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎአል። ²⁰እርሱም ሃያ ሁለት ዓመት ነግሦ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ ልጁ ናዳብም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

የይሁዳ ንጉሥ ሮብዓም

14፥21፤25፥31 ተጓ ምብ — 2ዜና 12፥9-16

²¹የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም በይሁዳ ነገሠ፤ በነገሠም ጊዜ ዕድሜው አርባ አንድ ዓመት ነበር፤ እርሱም እግዚአብሔር ለስሙ መጠሪያ እንድትሆን ከእስራኤል ነገድ ሁሉ በመረጣት በኢየሩሳሌም ዐሥራ ሰባት ዓመት ገዛ። እናቱ ናዕማ የተባለች አሞናዊት ነበረች።

²²ይሁዳ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረገ፤ ከአባቶቻቸው ይልቅ እነርሱ በሠሩት ኀጢአት ይበልጥ የቅናት ቊጣውን አነሣሡ፤ ²³እንዲሁም በእያንዳንዱ ኰረብታና በየቅልልቁ ዛፍ ጥላ ሥር የማምለኪያ ኰረብቶችን አዕማደ ማየታት፣ የአሼራን ምስል ዐምድ ለራሳቸው አቆሙ። ²⁴ካህያም ይልቅ፣ የቤተ ጣዖት ወንዶችም በምድሪቱ ላይ ነበሩ፤ እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ፊት አሳዶ ያስወጣቸው አሕዛብ የፈጸሙትን አስጸያፊ ድርጊት ሁሉ እነዚህም ፈጸሙ።

²⁵ሮብዓም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት የግብፅ ንጉሥ ሺሻቅ በኢየሩሳሌም ላይ አደጋ ጣለ፤ ²⁶የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና የቤተ መንግሥቱን ሀብት ወሰደ፤ ሰሎሞን ያሠራቸው የወርቅ ጋሻዎች እንኳን ሳይቀሩ ሁሉንም ነገር አጋዘ።

14፥23 ዘፀ23፥24፤ ዘዳ12፥2፡3፤ 16፥22፤ ሕዝ6፥13፤ ሆሴ10፥1፤ 14፥24 ዘዳ23፥17፤ 1ነገ11፥57፤ 2ነገ21፥2፤ ዕዝ9፥11፤ ምሳ21፥27፤ ኢሳ1፥13፤ ኤር16፥18፤ 32፥35፤ 44፥4 14፥25 2ዜና12፥2 14፥26 2ሳሙ8፥7፤ 1ነገ15፥15፡18

ˣ14፥14 በዕብራይስጡ የዚህ ዐረፍተ ነገር ትርጕም በትክክል አይታወቅም
ʸ14፥15 በዚህም ሆነ በሌሎቹም የመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ክፍሎች፣ የአሼራ ጣዖት አምላክ ምስል ነው
ᶻ14፥15 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው

14፥15 ከወንዙም ማዶ ይበትናቸዋል፤ አኪያ እስራኤል እንደሚማረኩ ተነበየ፤ በ722 ዓ.ቅ.ክ. እስራኤል ተሸንፈው ከአገዛዙም በሺዎች የሚቈጠሩት ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ በአሦራውያን እንዲሰደዱ ተደረገ (ከ2ነገ 15፥29፤ 17፥6፡18 ጋር ያነጻጽሩ)።

14፥22 ይሁዳ ... ክፉ ነገር አደረገ፤ በሮብዓም የሚገዙት የይሁዳ ነገዶች (ቊ 21)፣ ከዐሥሩ የእስራኤል ነገዶች የተሻለ ነገር ያደረጉት እጅግ በጥቂቱ ነው፤ እነርሱም እግዚአብሔርን ትተው ራሳቸውን ለከፋ ኀጢአት አሳልፈው ሰጡ (ቀጥሎ ያለውን ማብ ይመ፤ (ከ2ዜና 11—12 ጋር ያነጻጽሩ)።

14፥24 የቤተ ጣዖት ወንዶች፤ የይሁዳ ክህደት ወደ ግብረሰዶማዊነትና ወደ ወንዶች የከፋ ድርጊት አመራ (ከሮሜ 1፥25-28 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ "አሕዛብ የፈጸሙትን አስጸያፊ ድርጊት ሁሉ" አሜን ብለው በመቀበላቸው፣ ቅድስና በሌላቸው አሕዛብ ተሸነፉ (ቊ 25-26)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዓለም ጋር ተስማምተው በሚኖሩት ሁሉ ላይ እንደሚደርስ በመግለጽ በዚህ የፍርድ መርሕ ላይ በድጋሚ አጽንዖት አደረገ ማቴ 5፥13 እና ማብ ይመ)።

14፥26 የ ... ቤተ መቅደስና ... ሀብት ወሰደ፤ እግዚአብሔር የግብፅ ንጉሥ ሺሻቅ ቤተ መቅደሱን በመውረር ንብረቱን እንዲያግዝ ፈቀደ። የእግዚአብሔር ሕዝብ የእርሱን የጽድቅ መንገድ እየተዉ በመሄዳቸው፣ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ

27ስለዚህ ንጉሥ ሮብዓም እነዚህን ለመተካት ሲል፣ የናስ ጋሻዎች አሠርቶ የቤተ መንግሥቱን በር የሚጠብቁት ዘበኞች አዛዦች እንዲይዙ አደረገ። 28ንጉሡ ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በሚሄድበት ጊዜ ሁሉ፣ ዘቦቹ ጋሻዎቹን ያንግባሉ፤ ከዚያም በዘብ ጥበቃው ክፍል መልሰው ያስቀምጡ ነበር።

29የቀረው የሮብዓም አገዛዝ፣ ያደረገውም ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? 30በሮብዓምና በኢዮርብዓም መካከል ያላቋረጠ ጦርነት ተደርጎ ነበር። 31ሮብዓምም ከአባቶቹ ጋር እንቀላፋ፤ እነርሱ በተቀበሩበትም በዳዊት ከተማ ተቀበረ። እናቱ ናዓማ የተባለች አሞናዊት ነበረች። ልጁ አብያም፣ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

የይሁዳ ንጉሥ አብያ

15፥1-2፥6-8 ተጓ ምብ — 2ዜና 13፥1-2፥22—14፥1

15 የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም በነገሠ በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት አብያ በይሁዳ ነገሠ፤ 2በኢየሩሳሌም ሆኖ ሦስት ዓመት ገዛ፤ እናቱ መዓካ የተባለች የአቢሴሎም ልጅ ነበረች።

3እርሱም አባቱ ከእርሱ በፊት የሠራውን ኀጢአት ሁሉ ሠራ፤ እንደ አባቱ እንደ ዳዊትም በፍጹም ልቡ በታማኝነት ለእግዚአብሔር አልተገዛም። 4ነገር ግን ክእርሱ ቀጥሎ እንዲነግሥና ኢየሩሳሌምን እንዲያጸናት፣ እምባከ እግዚአብሔር ሰለ ዳዊት ሲል በኢየሩሳሌም መብራት ሰጠው። 5ዳዊት በኬጢያዊው በኦርዮ ላይ ካደረሰው በደል በቀር፣ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር አድርጓል፤ በሕይወት ዘመኑም ሁሉ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ፈቀቅ ያለበት ጊዜ አልነበረም።

6አብያም በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ በሮብዓምና በኢዮርብዓም መካከል ጦርነት ነበር። 7ሊላው አብያ በዘመኑ የፈጸመውና ያደረገው ሁሉ፣ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? በአብያና በኢዮርብዓም መካከልም ጦርነት ነበር። 8አብያም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በዳዊትም ከተማ ተቀበረ። ልጁም አሳ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

የይሁዳ ንጉሥ አሳ

15፥9-22 ተጓ ምብ — 2ዜና 14፥2-3፤ 15፥16—16፥6
15፥23-24 ተጓ ምብ — 2ዜና 16፥11—17፥1

9የእስራኤል ንጉሥ ኢዮርብዓም በነገሠ በሃያኛው ዓመት፣ አሳ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ፤ 10በኢየሩሳሌምም አርባ አንድ ዓመት ነገሠ፤ አያቱ መዓካ ትባላለች፤ አርዳም የአቤሴሎም ልጅ ነበረች።

11አሳ አባቱ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነውን ነገር አደረገ። 12የቤተ ጣዖት ወንደቃዎችን ከምድሪቱ አባረረ፤ አባቶቹ የሠሯቸውን ጣዖታት ሁሉ አስወገደ። 13አስጸያፊውን የአሼራ ምስል ዐምድ በማቆሟ፣ አያቱን መዓካን ከእቴጌነቷ ሻራት፤ ጣዖቷንም ሰባብሮ በቄድሮን ሸለቆ አቃጠለው። 14አሳ የማምለኪያ ኰረብታዎችን ፈጽሞ ባያስወግድም እንኳ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ፣ ልቡ ለእግዚአብሔር የተገዛ ነበር። 15አባቱና እርሱ ለእግዚአብሔር የቀደሱትን ብርና ወርቅ እንዲሁም ዕቃዎችን አምጥቶ ወደ እግዚአብሔር ቤት አስገባ።

16አሳና የእስራኤል ንጉሥ ባአስ ዘመነ መንግሥታቸውን ያሳለፉት፣ እርስ በርስ በሙዋጋት ነበር። 17የእስራኤል ንጉሥ ባአስ ይሁዳን ለመውጋት ወጣ፤ ከዚያም ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ አሳ ግዛት ማንም እንዳይገባና እንዳይወጣ ለመቈጣጠር ራማን ምሽግ አድርጎ ሠራት።

18አሳም በእግዚአብሔር ቤትና በቤተ መንግሥቱ ግምጃ ቤት የቀረውን ብርና

14፥10 ሶ 2
15፥11 ነገ19፥4
15፥12 ነገ14፥24፤ 2ዜና15፥8
15፥13 ሶ 2፥ ዘፀ34፥13፤ ነገ12፥19
15፥14 ነገ18፥61፤ 2ዜና14፥5፤ 17፥6
15፥15 2ሳሙ8፥11
15፥16 ሶ 6፥ ነገ12፥21
15፥17 ኢሳ18፥25
15፥18 ሶ 18-20፥ ነገ14፥26፥ 20፥1፤ 2ነገ16፥24፤ 12፥18፤ 13፥3፤ 16፥8፤ 18፥14-16፤ ኤር49፥27፤ ኢል3፥5

14፥27 ነገ11፥5
14፥30 2ሳሙ3፥1፤ ነገ12፥21
14፥31 ነገ11፥1
15፥2 ሶ 10፥13፤ 2ዜና11፥20
15፥3 ነገ8፥61
15፥4 2ሳሙ21፥17
15፥5 ዘዳ5፥32፤ 2ሳሙ11፥2-7፤ 12፥9፤ ነገ9፥4
15፥6 ሶ 16፥32፤ ነገ12፥21፤ 2ዜና16፥9

ዘመን ላይ እግዚአብሔር ክብሩን የገለጠበት ቤተ መቅደስ (8፥11)፣ ሰሎሞን በሞተ ልክ በአምስተኛው ዓመት የውርደት ቦታ ሆነ።

15፥3 በፍጹም ልቡ ... አልተገዛም፤ በፍጹም ልብ አለመገዛትን በመሠረቱ የሚያመለክተው ባዕድ አምላኪ የሆነውን ሰው ነው፤ ዳዊት በፍጹም ልቡ ለጌታ እንደ ተገዛ ተገልጸአል፤ ይህም የሆነበት ምክንያት ልቡን ለሌሎች አማልክት ባለማስገዛቱ ነው፤ በፍጹም የተገዛ ልብ ሲባል እንከን አልባ የሆነ የማብረ ንብ ሰው ነበር ማለት አይደለም (ከሶ 5 ጋር ያነጻጽሩ፤ 11፥4 እና ግብ ይመ)።

15፥4 መብራት፤ እዚህ ላይ «መብራት» ሲባል የሚያመለክተው እግዚአብሔር የዳዊትን የዘር ሐረግና ኪዳን ለማጥፋት አለመፈለጉን ነው። ከጊዜ በኋላም ይኸው መብራት በጌታ በኢየሱስ ማንነት በኩል፣ «የዓለም ብርሃን» ሆነ (ዮሐ 8፥12 ይመ፤ ከሉቃ 2፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

15፥9 አሳ፤ አሳ መልካም ንጉሥ ሲሆን፣ ዘመነ መንግሥቱም ለእግዚአብሔር ባለው ታማኝነት የታወቀ ነበር። ይሁን እንጅ በኋለኛው የዕድሜ ዘመኑ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ ሳይታመን ቀረ (2ዜና 16 ይመ)። የእርሱ ዘመነ መንግሥት ሕዝቡ ፈረሀ እግዚአብሔር የሌለበትን መንገዳቸውን ትተው ከከነዓናውያን ክፉ ድርጊት እንዲመለሱ በማድረግ የታወቀ ነበር። እውነተኛ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ምንጊዜም ቢሆን እግዚአብሔርን ከሚያስቈጣውና ቃሉን ችላ ከሚለው ልምድ መመለስን ያካትታል (ስለ አሳ ዘመነ መንግሥት ይበልጥ ለማወቅ 2ዜና 14—16 ይመ)።

ᵀ14፥31 አንዳንድ የዕብራይስጥና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ትርጒሞች ግን፣ አቢጃም ይላሉ
ᵃ15፥1 በዚህ ስፍራና በሶ 7 እና 8 ላይ አንዳንድ የዕብራይስጥና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብ ዛኞቹ የዕብርይስጥ ትርጒሞች ግን፣ አቢጃም ይላሉ
ᵇ15፥6 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ አንዳንድ የዕብራይስጥና የሱርስት ትርጒሞች ግን፣ አቢጃም ይላሉ

ወርቅ በሙሉ ወሰደ፤ ከዚያም በታማኝ ሹማምቱ እጅ በደማስቆ ይገዛ ለነበረው፣ ለጠብሪሞን ልጅ፣ የአዚን የልጅ ልጅ ለሆነው ለሶርያ ንጉሥ ለቤን ሀዳድ ላከው። 19እንዲህም አለ፤ "በአባቴና በአባትህ መካከል የሰመመነት ውል እንደ ነበረ ሁሉ፣ አሁንም በእኔና በእንተ መካከል ይኑር፤ እነሆ፣ የብርና የወርቅ ገጸ በረከት ልኬልሃለሁ። አሁንም የእስራኤል ንጉሥ ባአስ ወደ መጣበት እንዲመለስ፣ ሂደህ ከእርሱ ጋር ያደረግኸውን የሰመመነት ውል አፍርስ።"

20ቤን ሀዳድም የንጉሥ አሳን ሐሳብ ተቀብሎ፣ የሠር አዛዦቹን በእስራኤል ከተሞች ላይ አዘመተ፤ ዒዮንን፣ ዳንን፣ አቤልቤት ማዕካን እንዲሁም ንፍታሌምን ጨምሮ ጌንሳሬጥን በሙሉ ድል አደረገ። 21ባአስም ይህን ሲሰማ፣ በራማ የጀመረውን የምሽግ ሥራ አቁሞ ወደ ቴርሳ ተመለሰ። 22ንጉሥ አሳ አንድም ሰው እንዳይቀር በይሁዳ ሁሉ ዐዋጅ አስነገረ፤ ከዚያም ሕዝቡ ባአስ በራማ አስቀምጦት የነበረውን ድንጋይና ዕንጨት አጋዘ፤ ንጉሡም በዚሁ ምጽዳንና በብንያም ውስጥ ጌባን ሠራ። 23በአሳ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው ነገር በሙሉ፣ ያደረገውም ሁሉና የሠራቸውም ከተሞች በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፈው የሚገኙ አይደሉምን? ንጉሥ አሳ በሸመገለ ጊዜ ግን እግሮቹ ታመሙ። 24አሳ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ እነርሱ በተቀበሩበትም በአባቱ በዳዊት ከተማ ተቀበረ፤ ልጁ ኢዮሣፍጥም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

የእስራኤል ንጉሥ ናዳብ

25በይሁዳ ንጉሥ በአሳ ዘመነ መንግሥት በሁለተኛው ዓመት የኢዮርብዓም ልጅ ናዳብ በእስራኤል ላይ ነገሠ፤ ሁለት ዓመትም ገዛ። 26እርሱም በአባቱ መንገድ በመሄድና አባቱ የሠራውንና እስራኤልም እንዲሠሩ ያደረገውን ኀጢአት በመሥራት በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ።

27ናዳብና መላው እስራኤል በፍልስጥኤም የምትገኘውን የገባቶንን ከተማ ከበው ሳሉ፣ ከይሳኮር ነገድ የተወለደው የአኪያ ልጅ ባአስ ዐምፆ በመነሣት ናዳብን በገባቶን ገደለው። 28ባአስ ናዳብን የገደለውና በእግሩ ተተክቶ የነገሠው፣ የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሦስተኛው ዓመት ነው።

29ወዲያውኑ እንደ ነገሠም የኢዮርብዓምን ቤተ ሰብ በሙሉ ፈጀ። እግዚአብሔር በሴሎናዊው ባሪያው በአኪያ በኩል እንደ ተናገረው፣ ከኢዮርብዓም ቤተ ሰብ አንድም ሰው በሕይወት ሳያስቀርና ሁሉንም አጠፋቸው፤ 30ይህም የሆነው ኢዮርብዓም በሠራው ኀጢአትና እስራኤልም እንዲሠሩ በማድረጉም ክንያት፣ የእስራኤል ስምላክ እግዚአብሔርን ለቍጣ በማነሣሣቱ ነው።

31ሌላው በናዳብ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው፣ እርሱም ያደረገው ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? 32አሳና የእስራኤል ንጉሥ ባአስ ዘመነ መንግሥታቸውን ያሳለፉት እርስ በርስ በመዋጋት ነበር።

የእስራኤል ንጉሥ ባአስ

33የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሦስተኛው ዓመት የአኪያ ልጅ ባአስ በቴርሳ ከተማ በእስራኤል ሁሉ ላይ ነገሠ፤ ሃያ አራት ዓመትም ገዛ። 34በኢዮርብዓም መንገድ በመሄድና እስራኤልም እንዲሠሩ ያደረገውን ኀጢአት በመፈጸም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠራ።

16 ከዚያም የእግዚአብሔር ቃል በባአስ ላይ እንዲህ ሲል ወደ አናኒ ልጅ ወደ ኢዩ መጣ፤ 2"ከትቢያ አንሥቼህ የሕዝቤ የእስራኤል መሪ አደረግሁህ፤ አንተ ግን በኢዮርብዓም መንገድ ሄደህ፤ ሕዝቤ እስራኤል ኀጢአት እንዲሠራ፣ በኀጢአቱም ለቍጣ እንዲያነሣሣኝ አሳሳትኸው። 3ስለዚህ ባአስንና ቤቱን ፈጽሜ አጠፋለሁ፤ ቤትህንም እንደ ናባጥ ልጅ እንደ ኢዮርብዓም ቤት አደርገዋለሁ። 4በከተማዪቱ ውስጥ የሚሞቱትን የባአስን ወገኖች ሁሉ ውሾች ይበሏቸዋል፤ በገጠር የሚሞቱትንም ሁሉ የሰማይ አሞሮች ይቀራመድቷቸዋል።"

5ባአስ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው፣ ሌላው ያደረገው ሥራው በሙሉ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? 6ባአስ፣ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በቴርሳም ተቀበረ። ልጁም ኤላ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

7ከዚህም በቀር የእግዚአብሔር ቃል በነቢዩ ኢዩ አማካይነት በባአስና በቤቱ ላይ የመጣበት ምክንያት፣ በእጁ ሥራ ያስቈጣው ዘንድ እንደ ኢዮርብዓም ቤት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራን ሁሉ በማድረጉና ኢዮርብዓምን በማጥፋቱም ጭምር ነው።

የእስራኤል ንጉሥ ኤላ

8የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በዛያ

15፥19 ዘዳ23፥32፤ 1ነገ15፥12
15፥20 1ነገ20፥34
15፥21 ኢሱ18፥25፤ 1ነገ16፥15-17
15፥22 ሶፎ924፤ ኢሱ11፥3፤ 18፥24፤ 2ነገ23፥8፤ ኤር41፥9
15፥24 ማቴ1፥8
15፥26 ዘፃ4፥25፤ 1ነገ12፥30
15፥27 ኢሱ19፥44፤ 1ነገ14፥14
15፥29 1ነገ13፥34
15፥30 1ነገ12፥30፤ 16፥26፣ 2ነገ3፥3፤ 14፥24፣ 15፥28፤ 21፥16
15፥31 1ነገ11፥41
15፥32 ቍ6
15፥33 1ነገ14፥17፤ 16፥6፣23፤ 2ነገ15፥14፤ ሚሕ6፥4
15፥34 ቍ26
16፥1 ቍ7፤ 2ዜና16፥7፤ 19፥2፣ 20፥34
16፥2 1ሳሙ2፥8፤ 1ነገ12፥30፤ 14፥7፣9
16፥3 ቍ11፤ 1ነገ21፥22፤ 2ነገ9፥9
16፥4 ዘፍ40፥19፤ 1ነገ14፥11
16፥5 1ነገ15፥31
16፥6 1ነገ15፥33
16፥7 ቍ1፤ 1ነገ16፥11

15፥24 ኢዮሣፍጥ፤ ኢዮሣፍጥ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ያውቁ ዘንድ ለማስተማር ጥረት ያደረገና እርሱም ራሱ ለጌታ ታማኝ ሆኖ ለመኖር ጥረት ያደረገ ንጉሥ ነበር (ስለ እርሱ ዘመነ መንግሥት ይበልጥ ለመረዳት 22፥41-50፤ 2ዜና17፥1—21፥1 ይመ)።

16፥7 በነቢዩ ኢዩ፤ እግዚአብሔር የሾማቸው መሪዎችና ሕዝቡ ሕጉን ትተው ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌለውን የከነዓናውያንን መንገድ ሲከተሉ፣ እግዚአብሔር የእርሱን እውነትና ጽድቁን ያውጁ ዘንድ ነቢያትን ላከ። እንደነዚህ ያሉ ነቢያት ዛሬም ቢሆን አስፈላጊዎች ናቸው፤ በገጽ 1009 ላይ፣ "ነቢይ በብሉይ ኪዳን" እና በገጽ 1866 ላይ፣ "የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች" በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ።

ስድስተኛው ዓመት የባኦስ ልጅ ኤላ በእስራኤል ላይ ነገሠ፤ በቴርሳ ተቀምጦም ሁለት ዓመት ገዛ።

⁹ባሸማምሒ አንዱና የግማሽ ሠረገሎቹ አዛዥ የሆነው ዘምሪ ዐመፃ ተነሣበት፤ በዚያን ጊዜ ኤላ በቴርሳ ከተማ የቤተ መንግሥቱ ጎላፊ በሆነው በአርጻ ቤት ጠጥቶ ሰክሮ ነበር፤ ¹⁰ዘምሪም ገብቶ ኤላን ገደለውና እርሱም በኤላ እግር ተተክቶ፣ የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሃያ ሰባተኛው ዓመት ነገሠ።

¹¹ዘምሪ ወዲያው እንደ ነገሠና በዙፋን እንደ ተቀመጠ፣ የባኦስን ቤተ ሰብ በሙሉ ገደለ፤ የሥጋ ዘመድም ሆነ ወዳጅ አንድም ወንድ አላስቀረም። ¹²በዚህ ሁኔታም በነቢዩ በኢዩ አማካይነት በባኦስ ላይ በተነገረው በእግዚአብሔር ቃል መሠረት፣ የባኦስን ቤተ ሰብ ሁሉ ፈጀ። ¹³ይህም የሆነው ባኦስና ልጁ ኤላ፣ ፀሓይረቡ ጣዖቶቻቸው ምክንያት የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ያስቈጡት ዘንድ በሠሩት ኀጢአት ሁሉና፣ እስራኤልም እንዲሠሩ በማድረጉ ነበር።

¹⁴ሌላው ኤላ በዘመኑ የፈጸመውና ያረገው ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?

የእስራኤል ንጉሥ ዘምሪ

¹⁵የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሃያ ሰባቻኛው ዓመት ዘምሪ በቴርሳ ሆኖ ሰባት ቀን ብቻ ገዛ። በዚህ ጊዜ ሰራዊቱ የፍልስጥኤማውያን ከተማ የሆነችውን ገባቶንን ከበ ሰፍሮ ነበር። ¹⁶በዚያም ሰፈር የነበሩ እስራኤላውያን ዘምሪ ዐምዖ ንጉሡን መግደሉን እንደ ሰሙ፣ የሲራዊቱን አዛዥ ዖምሪን በዚያኑ ዕለት እዚያው ሰፈር ውስጥ በእስራኤል ላይ ማንገሣቸውን ዐወጁ። ¹⁷ከዚያም ዖምሪና አብረውት ያሉት እስራኤላውያን ሁሉ ከገባቶን ወደ ላይ ወጥተው ቴርሳን ከበቡ። ¹⁸ዘምሪ ከተማዪቱ መያዟን ሲያይ፣ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ወዳለው ግንብ ገብቶ በቤተ መንግሥቱ ላይ እሳት ለቀቀበትና በዚሁ ሞተ። ¹⁹ይህ የሆነውም በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ክፉ ሥራ በመሥራትና በኢዮርብዓም መንገድ በመሄዱ፣ እንዲሁም ራሱ በሠራው ኀጢአትና እስራኤልም እንዲሠሩ ባደረገው ኀጢአት ምክንያት ነው።

²⁰ሌላው ዘምሪ በዘመኑ የፈጸመው ድርጊትና ያካሄደውም ዐመፅ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አደለምን?

የእስራኤል ንጉሥ የምሪ

²¹ከዚያም የእስራኤል ሕዝብ ከሁለት ተከፈለ፣ ይህም ግማሹ የጎናትን ልጅ ታምኒን ለማንገሥ ሲሆን፣ የቀረው ደግሞ የምሪን በመደገፍ ነበር። ²²ሆኖም የየምሪ ተከታዮች ከጎናት ልጅ ከታምኒ ተከታዮች ይልቅ በረቱ፤ ስለዚህ ታምኒ ሞተ፤ የምሪም ነገሠ።

²³የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሠላሳ አንደኛው ዓመት፣ የምሪ በእስራኤል ላይ ነገሠ፤ ዐሥራ ሁለት ዓመትም ገዛ፤ ከዚህም ውስጥ ስድስቱን ዓመት የገዛው በቴርሳ ሆኖ ነው። ²⁴እርሱም የሰማርያን ኰረብታ በሁለት መክሊት ጥሬ ብር ከሳምር ላይ ገዝቶ ከተማ ሠራባት፤ ሰሚንም በቀደሞው የተራራዋ ባለቤት በሳምር ስም ሰማርያ ብሎ ጠራት።

²⁵ይሁን እንጂ የምሪ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ፤ ከእርሱ አስቀድሞ ከነበሩትም ይልቅ የበለጠ ኀጢአት ሠራ። ²⁶እርሱም እስራኤል በማይረቡ ጣዖቶቻቸው፣ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ለቍጣ እንዲያነሣሡት ባደረገው በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም መንገድ ሁሉና እርሱም ኀጢአት ሠርቶ እስራኤልም እንዲሠሩ ባደረገው ኀጢአት ተመላለሰ።

²⁷ሌላው የምሪ በዘመኑ የፈጸመው፣ ያደረገውና ያከናወነው ሁሉ በእስራኤል የነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? ²⁸የምሪ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በሰማርያም ተቀበረ፤ ልጁም አክዓብ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

አክዓብ የእስራኤል ንጉሥ ሆነ

²⁹የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሠላሳ ስምንተኛው ዓመት፣ የየምሪ ልጅ አክዓብ በእስራኤል ላይ ነገሠ፣ በሰማርያም ሆኖ እስራኤልን ሃያ ሁለት ዓመት ገዛ። ³⁰የየምሪ ልጅ አክዓብ ከእርሱ አስቀድሞ ከነበሩት ሁሉ ይልቅ፣ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረገ። ³¹የናባጥን ልጅ የኢዮርብዓምን ኀጢአት እንደ ቀላል ነገር ከመቍጠሩም በላይ የሲዶናውያንን ንጉሥ የኤትበአልን ልጅ ኤልዛቤልን አገባ፤ ሄዶም በኣልን አመለከ፤ ሰገደለትም። ³²ሰማርያ ላይ በሠራውም የበኣል ቤተ ጣዖት ለበኣል መሠዊያ አቆመለት። ³³ደግሞም አክዓብ የአሼራን ምስል ዐምድ በማቆም ከእርሱ በፊት ከነበሩት የእስራኤል ነገሥታት ይልቅ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ለቍጣ የሚያነሣሣ ድርጊት ፈጸመ።

³⁴የቤቴል ሰው አኪኤል፣ በአክዓብ ዘመን

16:9 1ነገ18:3፤ 1ነገ20:12,16፤ ምሳ31:45
16:10 2ነገ9:31
16:11 ሞ3
16:13 ዘጸ32:21
16:15 ኢሱ19:44
16:23 ኢሱ12:24፤ 1ነገ15:33
16:24 1ነገ13:32፤ ሚሳ10:5
16:25 ሞ25-26፤ ዘጸ34:25፤ ሚኅ6:16
16:26 ዘጸ32:21፤ 1ነገ15:30
16:28 1ነገ13:32
16:30 1ነገ14:9
16:31 መሳ2:11፤ 3:6፤ 1ነገ11:2፤ 2ነገ9:34
16:32 መሳ6:28፤ 2ነገ10:27፤ 11:18፤ ኤር43:12
16:33 መሳ3:7፤ 1ነገ14:9፤ 21:25፤ 2ነገ13:6
16:34 ኢሱ6:26

16:30 አክዓብ፤ በአክዓብ ዘመን መንግሥት በእስራኤል ላይ ኀጢአትና ክፉት እያደር እየከፋ ሄደ። ገሃድ የወጣ ዐመፅና ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ላለመገዛት የልብ ድንዳኔ እያየለ መጣ፤ በኣልንም ማምለክ እየተስፋፋ ሄደ። በዚህ ሁኔታ ክህደት ተስፋፍቶ ሳለ፣ ብልሹ የሆነውን የሃይማኖት ሥርዐት በመቃወም፣ እግዚአብሔር ለመንግሥቱ ያለውን ዕቅድ ሊያውጅ ታላቁን ነቢይ ኤልያስን እግዚአብሔር ላከ (17፥1)።

16:31 በኣል፤ ኢሱ 23፥12 እና ማብራሪያውን፤ መሳ 2፥13 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ)።

ኢያሪኮን መልሶ ሠራት። እግዚአብሔር በነቄ ልጅ በኢያሱ አማካይነት የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ መሠረቷን ሲያኖር በኵር ልጁ አቢሮን ሞተ፤ የቅጽር በሮቿንም በሚሠራበት ጊዜ የመጨረሻው ልጁ ሠጉብ ሞተ።

ኤልያስን ቊራዎች መገቡት

17 በዚህ ጊዜ ከገለዓድ ነዋሪዎች አንዱ የሆነው ቴስብያዊው ኤልያስ አክዓብን፣ "የማመልከው ሕያው እግዚአብሔርን፣ በእኔ ቃል ካልሆነ በቀር፣ በሚቀጥሉት ዓመታት ዝናብ ወይም ጠል አይኖርም" አለው።

[2]ከዚያም እንዲህ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ለኤልያስ መጣለት፤ [3]"ከዚህ ተነሥተህ ወደ ምሥራቅ ሂድ፤ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ባለው በኮራት ወንዝ ተሸሸግ። [4]ውሃ ከወንዙ ትጠጣለህ፤ ቊራዎችም አዚያው እንዲመግቡህ አዝዣለሁ።"

[5]ስለዚህ እግዚአብሔር ያዘዘውን ፈጸመ፤ ከዮርዳኖስበስተምሥራቅ ወዳለው ወደኮራት ወንዝ ሄዶ በዚያ ተቀመጠ። [6]ቊራዎችም ጧትና ማታ እንጀራና ሥጋ ያመጡለት ነበር፤ ውሃም ከወንዙ ይጠጣ ነበር።

የሰራፕታዪቱ መበለት

[7]በምድሪቱ ላይ ዝናብ ባለመዝነቡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወንዙ ደረቀ። [8]ከዚያም እንዲህ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤልያስ መጣ፤ [9]"ተነሥና ሲዶና ውስጥ ወሻለችው ወደ ሰራፕታ ሂደህ ተቀመጥ፤ በዚያም አንዲት መበለት እንድትመግብህ አዝዣለሁ።" [10]ስለዚህ ተነሥቶ ወደ ሰራፕታ ሄደ። ወደ ከተማዪቱ በር እንደ ደረሰም፣ አንዲት መበለት ሞራሮ ስትለቃቅም አገኛት፤ ጠርቶም፣ "የምጠጣው ውሃ በዕቃ ታመጪልኛለሽን?" ሲል ለመናት። [11]ልታመጣለት ስትሄድ አሁንም ጠራትና፣ "እባክሽን፣ ቊራሽ እንጀራም ይዘሽልኝ ሂጂ" አላት።

[12]እርሷም መልሳ፣ "እምላክህን ሕያው እግዚአብሔርን! በማድጋ ካለው ዕፍኝ ዱቄትና በማሰሮ ካለው ጥቂት ዘይት በቀር ምንም የለኝም። እነሆ፤ ለራሴና ለልጄ ምግብ አዘጋጅቼ በልተን እንድንሞት ሞራሮ ለቃቅሜ ወደ ቤት ልወስድ ነው" አለችው።

[13]ኤልያስም መልሶ እንዲህ አላት፤ "አይዞሽ አትፍሪ፤ ወደ ቤት ገብተሽ እንዳልሽው አድርጊ፤ በመጀመሪያ ግን ከዚያችው ካለችሽ ትንሽ እንጎቻ ጋግረሽ አምጪልኝ፤ ከዚያም ለራስሽና ለልጅሽ ጋግሪ፤ [14]የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤ 'እግዚአብሔር ለምድሪቱ ዝናብ እስከሚሰጥበት ዕለት ድረስ፤ ከማድጋው ዱቄት አይጐፍም፤ ከማሰሮውም ዘይት አያልቅም።' "

[15]እርሷም ሂዳ ኤልያስ እንደ ነገራት እንዲህ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤልያስ መጣ፤ [9]"ተነሥና ሲዶና ውስጥ ወሻለችው ወደ ሰራፕታ ሂደህ ተቀመጥ፤ በዚያም አንዲት መበለት እንድትመግብህ አዝዣለሁ።" [10]ስለዚህ ተነሥቶ ወደ ሰራፕታ ሄደ። ወደ ከተማዪቱ በር እንደ ደረሰም፣ አንዲት መበለት ሞራሮ ስትለቃቅም አገኛት፤ ጠርቶም፣ "የምጠጣው ውሃ በዕቃ ታመጪልኛለሽን?" ሲል ለመናት። [11]ልታመጣለት ስትሄድ አሁንም ጠራትና፣ "እባክሽን፣ ቊራሽ እንጀራም ይዘሽልኝ ሂጂ" አላት።

[12]እርሷም መልሳ፣ "እምላክህን ሕያው እግዚአብሔርን! በማድጋ ካለው ዕፍኝ ዱቄትና በማሰሮ ካለው ጥቂት ዘይት በቀር ምንም የለኝም። እነሆ፤ ለራሴና ለልጄ ምግብ አዘጋጅቼ በልተን እንድንሞት ሞራሮ ለቃቅሜ ወደ ቤት ልወስድ ነው" አለችው።

[13]ኤልያስም መልሶ እንዲህ አላት፤ "አይዞሽ አትፍሪ፤ ወደ ቤት ገብተሽ እንዳልሽው አድርጊ፤ በመጀመሪያ ግን ከዚያችው ካለችሽ ትንሽ እንጎቻ ጋግረሽ አምጪልኝ፤ ከዚያም ለራስሽና ለልጅሽ ጋግሪ፤ [14]የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤ 'እግዚአብሔር ለምድሪቱ ዝናብ እስከሚሰጥበት ዕለት ድረስ፤ ከማድጋው ዱቄት አይጐፍም፤ ከማሰሮውም ዘይት አያልቅም።' "

[15]እርሷም ሂዳ ኤልያስ እንደ ነገራት

17፥1 ዘዳ11፥17፤ 28፥24፤ መሳ12፥4፤ 2ሳሙ1፥21፤ 1ነገ8፥36፤ ኢዮ12፥ 15፤ ሚል4፥5፤ ማቴ11፥14፤ 17፥3፤ ሉቃ4፥25 17፥3 1ነገ18፥4፡10፤ ኤር36፥19፡26 17፥4 ዘፍ8፥7 17፥6 ዘፀ16፥8

17፥9 አሞ1፥20፤ ሉቃ4፥26 17፥10 ዘፍ24፥17፤ ዮሐ4፥7 17፥12 2ነገ4፥2 17፥14 ሮሜ1

17፥1 ኤልያስ፣ ኤልያስ በአክዓብና ክልጁ በአካዝያስ ዘመነ መንግሥት በሰሜኑ መንግሥት የነበረ ነቢይ ነው፤ ኤልያስ የሚለው ስም ትርጉም፣ "እግዚአብሔር አምላኬ ነው" የሚል ሲሆን፣ የኤልያስን የማይናወጥ የእምነት ሕይወት በመወከል ያመለክታል (18፥21:39)። ስለነቢዩ የተሰጡት ወቢይት ትረካዎች የሚገኙት በ1ነገ 17—19፥ 21፥17-29፤ 2ነገ 1—2 ላይ ነው።

(1) የኤልያስ ሕይወት ተግክሎ የሚገኘው እግዚአብሔርን በማምለክና በአልን በማምለክ መካከል በነበረው ግጭት ነው። የእርሱ ተልእኮ እስራኤልን ከክህደታቸው በማውጣት፣ የእስራኤልን አምላክ ተመልሰው ያመልኩ ዘንድ ጥሪ ማቅረብ ነበር (18፥21:36-37)። ስለዚህ ኤልያስ ኪዳንን ለማደስ ባደረገው ጥረት አኳያ ሲታዩ፣ የቀደመውን መላኸና ተሐድሶን አራማጅ ነበር።

(2) የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ፣ "እነሆ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት ነቢዩ ኤልያስን እልክላችኋለሁ" በማለት በመጨረሻ ይደመድማል (ሚል 4፥5)። ይህም ትንቢት መጥ ምቁ ዮሐንስ በመጣ ጊዜ በክፊል ተፈጽሞአል (ማቴ 11፥7-14፤ ሉቃ 1፥17)፤ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከመሆኑም በፊት መፈጸሙ አይቀርም (ከማቴ 17፥11፤ ከራእ 11፥3-6 ጋር ያነጻጽሩ፤ ራእ 11፥3 እና ማብ ይመ)።

(3) ኤልያስ በጽናት ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ታማኝ መሆኑ እንዲሁም ከፍተኛ ተቃውሞና ስደት በነበረበት ጊዜ፣ በእምነት በደፋርነትና በታማኝነት ለእግዚአብሔር የመቆሙ ሁኔታ ለዘላለም በምሳሌነት የሚጠቀስ ሰው አድርጎታል።

17፥1 ዝናብ ወይም ጠል፣ ኤልያስ የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንደ መሆኑ መጠን በማይታዘዙት እስራኤል ላይ የፍርድ ቃል ተናገረ። እግዚአብሔር ለሦስት ዓመት ተኩል ዝናብ እንዳይዘንብ ያደርጋል (ከዘዳ 11፥13-17 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህም የፍርድ ቃል በበአል ላይ የፌዝ ቃል ነው፣ በአልን የሚያመልኩት፣ "አምላካችን ዝናብን ይቈጣጠራል፣ ከፍተኛ መከር እንዲታሪስም ቸርነት ያደርጋል" በማለት ያምኑ ነበርና። ኤልያስ ብርቱ ጸሎት ከመጸለዩ የተነሣ፣ ይህ ድርቅ በእስራኤል ላይ መጣ በማለት አዲስ ኪዳን ይገልጻል (ያዕ 5፥17)።

17፥4 ቊራዎች እዚያው እንዲመግቡህ አዝዣለሁ፣ ሕዝቡ የገቡበትን ክህደት በመቃወም ኤልያስ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አድርጎ ስለነበር፣ እግዚአብሔር በኮራት ወንዝ ቊራዎችን በመላክ ይመግበው ነበር (ቊ 3-7 ይመ፤ ከመዝ 25፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። ኤልያስ የእግዚአብሔር ሽክም ስለተሸከመ፣ እግዚአብሔር ደግሞ በዚህ ጊዜ የእርሱን ሽክም ተሸከመለት (ከመዝ 68፥19-20 ጋር ያነጻጽሩ)።

17፥7 ወንዙ ደረቀ፣ ወንዙ በደረቀ ጊዜ የበአል አምላኪዎች ወደ ሚኖሩበት የጣዖት አምላኪዎች ምድር ኤልያስ ይሄድ ዘንድ እግዚአብሔር መራው፣ በዚያም በአንዲት ድኻ መበለት አማካይነት የሚያስፈልገውን ሰጠው። ይህም ልምምዱ እግዚአብሔር ለሚታመኑበት ምን ያህል ቸርነት እንደሚያደርግ በማሳየት የኤልያስን እምነት በይበልጥ አጠነከረለት። አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ብንሆንም እንኳ ችግር ሊደርስብን ይችላል፣ ይህን በመሰለ አጋጣሚም እኛ ካሰብነውና ከገመትነው በላይ በተለየና ታላቅ በሆነ መንገድ ይረዳናል።

አደረገችኝ፤ በዚህ ሁኔታም ኤልያስ፣ መበለቲቱና ቤተ ሰቧ ብዙ ቀን ተመገቡ፤ [16]በኤልያስ በተነገረው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት ከማድጋው ዱቄት አልጠፋም፤ ከማሰሮውም ዘይት አላለቀም ነበርና።

[17]ከዋቂት ጊዜ በኋላም የባለቤቲቱ ልጅ ታመመ፤ ሕመሙ እየጠናበት ሄደ፣ በመጨረሻም ትንፋሹ ቀጥ አለ። [18]እርሷም ኤልያስን፤ "የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፤ እኔ ምን አደረግሁህ? እዚህ የመጣኸው ኀጢአቴን አስታውሰህ ልጄን ለመግደል ነውን?" አለችው።

[19]ኤልያስም መልሶ፣ "ልጅሽን ስጪኝ" አላት፤ ልጁንም ከዕቅፏ ወስዶ እርሱ ወደሚኖርበት ሰገነት በማውጣት በዐልጋው ላይ አስተኛው። [20]ከዚያም፣ "አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፤ ልጂን እንዲሞት በማድረግ ተቀብላ በምታስተናግደኝ በዚህች መበለት ላይም መከራ ታመጣባታለህን?" ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። [21]በልጁም ላይ ሦስት ጊዜ ተዘርግቶ፣ "አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፤ የዚህ ልጅ ነፍስ ትመለስለት" ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ።

[22]እግዚአብሔርም የኤልያስን ፀሎት ሰማ፤ የልጁም ነፍስ ተመለሰችለት፤ እርሱም ዳነ። [23]ከዚያም ኤልያስ ልጁን አስነሥቶ ከሰገነቱ ወደ ምድር ቤት አወረደው፤ ለእናቱም ልጅሽ ይኸውልሽ፤ ድኖልሻል!" ብሎ ሰጣት።

[24]ከዚያም ሴቲቱ ኤልያስን፣ "አሁን የእግዚአብሔር ሰው መሆንህን፣ ከአንደበትህም የወጣው የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆኑን ዐወቅሁ" አለችው።

ኤልያስና አብድዩ

18 ከብዙ ጊዜ በኋላም በሦስተኛው ዓመት እንዲህ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ለኤልያስ መጣለት፤ "ሄደህ ለአክዓብ ተገለጥ፤ እኔም በምድሪቱ ላይ ዝናብ አዘንባለሁ።" [2]ስለዚህም ኤልያስ ራሱን በአክዓብ ፊት ለመግለጥ ሄደ።

በዚህ ጊዜ ራብ በሰማርያ ክፋኛ ጸንቶ ነበር። [3]አክዓብም የቤተ መንግሥቱን አዛዥ አብድዩን ጠራውና፤ አብድዩም እግዚአብሔርን በጣም የሚፈራ ሰው ነበር። [4]ኤልዛቤል የእግዚአብሔርን ነቢያት እያስገደለች በነበረበት ጊዜ፣ አብድዩ መቶውን ነቢያት ወስዶ አምሳ አምሳውን በሁለት ዋሻ ውስጥ ሸሽጎ እንጀራና ውሃ ይሰጣቸው ነበር። [5]አክዓብም አብድዩን፣ "ተነሣና በአገሪቱ ውስጥ ወዳሉት ምንጮችና ሸለቆዎች ሂድና ፈረሶቻችንና በቅሎዎቻችን እንዳይሞቱ በሕይወት እንዲቈዩ ምናልባት ሣር እናገኝ ይሆናል።" አለው። [6]ስለዚህ የሚሄዱበትን ምድር ተከፋፈሉ፤ አክዓብ በአንድ በኩል፣ አብድዩም በሌላ በኩል ሄደ።

[7]አብድዩ በመንገድ ላይ ሳለም ኤልያስን አገኘው። አብድዩም ዐወቀውና ወደ መሬት ለጥ ብሎ እጅ በመንሣት፣ "ጌታዬ ኤልያስ ሆይ፤ በእርግጥ አንተ ነህን?" አለው።

[8]እርሱም፣ "አዎን እኔ ነኝ፤ ሂድና ለጌታህ፣ 'ኤልያስ እዚሁ አለልህ' ብለህ ንገረው" ሲል መለሰለት።

[9]አብድዩም እንዲህ አለው፤ "ምነው ምን አጠፋሁና ነው ባሪያህ እንዲሞት ለአክዓብ አሳልፈህ የምትሰጠው? [10]አምላክህን ሕያው እግዚአብሔርን! ጌታዬ አንተን ለመፈለግ መልእክተኛ ያላከበት ሕዝብና መንግሥት የለም፤ የትኛውም ሕዝብ ሆነ መንግሥት አንተ በዚያ አለመኖርህን ባስታወቀው ጊዜ ሁሉ አንተን አለማግኘቱን ለማረጋገጥ ያስምለው ነበር። [11]አሁን ግን አንተ ወደ ጌታዬ ሂጂ፣ 'ኤልያስ እዚህ አለልህ' እንድለው ትፈልጋለህ፤ [12]ተለይቼህ ስሄድ የእግዚአብሔር መንፈስ የት እንደሚወስድህ አላውቅም፤ ታዲያ ሄጄ ለአክዓብ ከነገርሁት በኋላ ሳያገኝህ ቢቀር እኔን ይገድለኛል፤ ነገር ግን እኔ ባሪያህ ከጕልማሳነቴ ጀምሮ እግዚአብሔርን አመልካለሁ። [13]ጌታዬ ሆይ፤ ኤልዛቤል የእግዚአብሔርን ነቢያት ባስገደለች ጊዜ ምን እንዳደረግሁ አልሰማህምን? መቶውን የእግዚአብሔር ነቢያት ወስጄ አምሳ አምሳውን በሁለት ዋሻ በመሸሸግ እህልና ውሃ ሰጠኋቸው። [14]ታዲያ አንተ ሂጂ ለጌታዬ፤ 'ኤልያስ እዚህ

17፥15 **ብዙ ቀን ተመገቡ፤** የመበለቲቱ ፍላጎትና ችግር በእግዚአብሔር ዘንድ ቀላል ተደርጎአልተቈጠረም፥ ሁሉም ነገር አክትሞለታል ብላ ተስፋ በቈረጠችበት ወቅት (ቊ 12)፣ እምነቷን ያጸናላትና ለኑሮዋ አስፈላጊ የሆነውን ይሰጣት ዘንድ ኤልያስን ላከላት። መበለቲቱ በነቢዩ በኤልያስ አማካይነት በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ ያላት እምነት እርግጠኛ ካለመሆን እርግጠኛ ወደ መሆን፣ ከማይታየው ወደሚታየው እንድትሸጋገር ረዳት (ቊ 10-16 ይመ፣ ከዕብ 11፥27 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህች ፀእምነቷ ጸንታ የተገኘችው መበለት ከእግዚአብሔር ነቢይ የተቀበለችው ምድራዊ በረከትን ብቻ ሳይሆን፣ መንፈሳዊ በረከትንም ነው።

17፥17 **ልጅ ... ትንፋሹ ቀቀ አለ፤** እዚህ ላይ የተገለጸውን ሐሳብ ስንመለከት የሕይወት እንቆቅልሽ ከሆኑት ነገሮች ከአንዱ ጋር እንፋጠጣለን። እግዚአብሔር በታምር ዱቄትና ዘይት እየሰጠ እያለ ችግርና ሐዘንም ተከሠቱ። አንዳንድ ጊዜ ሕመም ወይም መሪር ሐዘን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚፈጽሙትና በመንግሥቱም ሥራ ንቁ ተሳትፎ ባላቸው ላይ ሊደርስ ይችላል።

17፥22 **እግዚአብሔርም የኤልያስን ጩኸት ሰማ፤** እግዚአብሔር የኤልያስን ጸሎት ሰምቶ ልጁ እንደገና በሕይወት እንዲኖር አደረገ። አንድ ሰው ከሞት ሰለመነሣቱ ጉዳይ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ተጽፎ የምናገኘው ይህን ታሪክ ነው (ከ2ነገ 4፥34፤ ከሐሥ 20፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። በምዕ 17 ላይ በሚያስደንቅ ሁኔታ የተመለከቱት ሦስቱ ታምራት የእግዚአብሔርን ኀይልና ፍቅር ያሳያሉ፥ ይኸውም የእግዚአብሔር ኀይልና ፍቅር እርሱን ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡም ለተጠሩት፣ የሚያሳዝን ሁኔታ በተከሠተበት ጊዜ እንኳ፣ እውን እንደሚሆኑ ለኤልያስና ለመበለቲቱ ጉልህ ሆኖላቸዋል (ሮሜ 8፥28 እና ማብ ይመ)።

17፥18 ሉቃ5፥8
17፥20 2ነገ4፥33
17፥21 2ነገ4፥34፤ ሐሥ20፥10
17፥23 ዕብ11፥35
17፥24 ሮሜ18፥ 1ነገ22፥16፤ መዝ119፥43፤ ዮሐ16፥30፤ 17፥7
18፥1 ሮሜ15፥ ዘዳ28፥12፤ 1ነገ17፥1፤ ሉቃ4፥25
18፥2 ዘሌ26፥26
18፥3 1ነገ16፥9፤ ነህ7፥2
18፥4 1ነገ17፥3፤ 21፥23፤ 2ነገ9፥7፤ ኢሳ16፥3፤ 25፥4፤ 32፥2፤ ኤር26፥24፤ አብ1፥14
18፥5 ዘፍ47፥4፤ ኤር14፥3
18፥7 2ነገ1፥8፤ ዘካ13፥4
18፥10 1ነገ17፥3
18፥12 2ነገ2፥16፤ ሕዝ3፥14፤ ሐሥ8፥39

አለልህ' እንድለው ትፈል ጋለህ፤ እርሱም ይገድለኛል!"

15ኤሊያስም፣ "በፊቱ የቆምሁት ሁሉን የሚገዛ ጌታ እግዚአብሔርን፣ ዛሬ በእክዓብ ፊት በርግጥ እገለጣለሁ" አለ።

ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ

16ስለዚህ አብድዩ ሄዶ ይህንኑ ለአክዓብ ነገረው፤ አክዓብም ኤልያስን ለማግኘት ሄደ። 17ኤልያስንም ባየው ጊዜ፤ "እስራኤልን የምታውክ አንተ ነህን?" አለው።

18ኤልያስም መልሶ እንዲህ አለ፤ "አንተና የአባትህ ቤት እንጂ እኔ እስራኤልን አላወክህም። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተዋችሁ፣ እነ በኣልንም ተከተላችሁ። 19አሁንም ሕዝቡ በቀርሜሎስ ተራራ እንዲገናኘኝ ለመላው እስራኤል ጥሪ አድርግ። ከኤልዛቤል ማእድ የሚቀለቡትን አራት መቶ አምሳውን የበኣል ነቢያት፣ አራት መቶውንም የአሼራ ነቢያት አምጣቸው።"

20ስለዚህ አክዓብ በመላው እስራኤል ጥሪ አደረገ፣ ነቢያቱንም በቀርሜሎስ ተራራ ሰበሰበ። 21ኤልያስም በሕዝቡ ፊት ቀርቦ፤ "በሁለት ሐሳብ የምትዋልሉት እስከ መቼ ድረስ ነው? እግዚአብሔር አምላክ ከሆነ እግዚአብሔርን ተከተሉ፤ በኣል አምላክ ከሆነም በኣልን ተከተሉ" አለ።

ሕዝቡ ግን አንዲት ቃል አልመለሱም።

22ከዚያም ኤልያስ እንዲህ አላቸው፤ "ከእግዚአብሔር ነቢያት የተረፍሁ እኔ ብቻ ነኝ፤ በኣል ግን አራት መቶ አምሳ ነቢያት አሉት። 23ሁለት ወይፈኖች ስጡኝ፤ እነርሱም አንዱን መርጠው ይውሰዱ፤ በየብልቱም ቈራርጠው፣ በዕንጨት ላይ ያኑሩት፤ ግን እሳት አያንደዱበት፤ እኔም ሁለተኛውን ወይፈን አዘጋጅለሁ፤ በዕንጨትም ላይ እኖረዋለሁ፤ እሳት አላነድበትም። 24ከዚያ እናንተ የአምላካችሁን ስም ጥሩ፤ እኔም

18፥15 ሶ1 18፥17 ኢሉ7፥25፣ 1ሳሙ14፥29፣ 1ነገ21፥20፣ ኤር38፥4
18፥18 ዘዳ31፥16፣ 1ነገ16፥33፣ 21፥25
18፥19 ኢሉ19፥26፣ 2ነገ9፥22፣ 10፥19
18፥20 2ነገ2፥25፣ 4፥25
18፥21 ሶ39፣ ኢሉ24፥15፣ 2ነገ17፥41፣ መዝ100፥3፣ 118፥27፣ 119፥113፣ ማቴ6፥24
18፥22 1ነገ19፥10፣ ኤር2፥8፣ 23፥13
18፥24 ሶ38፣ ዘፍ4፥26፣ ዘዳ19፥18፣ ዘሌ9፥24፣ 1ሳሙ7፥8
18፥26 መዝ115፥4-5፣ 135፥16፣ ኢሳ41፥26-28፣ 44፥17፣ 45፥20፣ 46፥7፣ ኤር10፥5፣ 1ቆሮ8፥4፣ 12፥2
18፥27 ዕን2፥19
18፥28 ዘሌ19፥28
18፥29 ዘዳ29፥4፣ 2ነገ19፥12፣ ኢሳ16፥12፣ ኤር10፥5፣
18፥30 1ነገ19፥10
18፥31 ዘፍ17፥5፣ 2ነገ17፥34
18፥32 ዘዳ18፥7፣ ቈዳ3፥17

የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ፤ ሰምቶ በእሳት የሚመልሰውም እርሱ እውነተኛ አምላክ ነው።"

ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ፣ "ያልኸው መልካም ነው" አሉ።

25ኤልያስም ለበኣል ነቢያት፣ "እናንተ ብዙ ስለ ሆናችሁ በመጀመሪያ አንዱን ወይፈን መርጣችሁ አዘጋጁ፤ የአምላካችሁን ስም ጥሩ፤ ግን እሳት አታንድዱበት" አላቸው። 26ስለዚህ የተሰጣቸውን ወይፈን ወስደው አዘጋጁት። ከዚያም ከጧት እስከ እኩለ ቀን የበኣልን ስም ጠሩ፤ "በኣል ሆይ ስማን" እያሉ ሥጫቸው ድምፅ ግን የለም፤ የሚመልስ አልነበረም፤ በሠሩት መሠዊያ ዙሪያም እየዘለሉ ያሸበሽቡ ነበር።

27እኩለ ቀንም ላይ ኤልያስ፣ "ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ጩኹ እንጂ አምላክ አይደለም እኮ! ምናልባት በሐሳብ ተውጦ ወይም ሥራ በዝቶበት፣ አልያም በጒዞ ላይ ይሆናል፤ ተኝቶም ከሆነ ቀስቅሱት" እያለ ያፌዝባቸው ጀመር። 28ስለዚህ እየጮኹ እንደ ልማዳቸው ደማቸው እስኪፈስ ድረስ ሰውነታቸውን በሰይፍና በጩቤ ያቈስሉ ነበር። 29እኩለ ቀን ዐለፈ፤ እነርሱም የሠርክ መሥዋዕት እስኪቀርብ ድረስ የሚዘላብድ ትንቢት ይናገሩ ነበር፤ ሆኖም ድምፅ የለም፤ የመለሰና ከቁም ነገር የቈጠረውም አልነበረም።

30ከዚያም ኤልያስ ሕዝቡን በሙሉ፣ "ወደ እኔ ቅረቡ" አላቸው፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ ቀረቡ፤ እርሱም ፈርሶ የነበረውን የእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ። 31ከዚያም ኤልያስ፣ "ስምህ እስራኤል ይባላል" ተብሎ የእግዚአብሔር ቃል በመጣለት በያዕቆብ ልጆች ነገድ ቍጥር ልክ ዐሥራ ሁለት ድንጋይ ወሰደ፤ 32በድንጋዮቹም ለእግዚአብሔር ስም መሠዊያ ሠራ፤ በመሠዊያውም ዙሪያ ዐሥራ አምስት ሊትር ውሃ የሚይዝ ጒድጓድ ቈፈረ፤

18፥18 **የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተዋችሁ፤** ኤልያስ ከአክዓብና በጽድቅ መንገድ ካልሄዱትው ከእስራኤል ጋር ያደረገው ብርቱ ተቃውሞ፣ ለእስራኤል በእርኢያነት የሚታዩ ነቢዩና ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ ጠራጊውም አምሳያ ለመሆን የላቀ ብቁ ሰው አደረገው (ከሚል 4፥5-6፣ ከሉቃ 1፥17 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) እርሱ በእውነት፣ "የእግዚአብሔር ሰው ነበር" (1ጢሞ 6፥11)፣ ይኸውም የሚናገረው ሰውን የሚያስደስት ሰው በመሆን ሳይሆን፣ ታማኝ የእግዚአብሔር አገልጋይ በመሆን ነበር (ከገላ 1፥10፣ ከ1ተሰ 2፥4 ጋር ያነጻጽሩ፣ ሉቃ 1፥17 እና ማቀ ይመ)።

(2) ኤልያስ ለእውነተኛው የእስራኤል አምላክ ይቆም ዘንድ እንደተጠራ ሁሉ፣ የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች ሁሉ፣ የክርስቶስን ወንጌል ከጥመት፣ ተስማምቶ ከማለፍና ከዝቅጠት ይጠብቁ ዘንድ መከላከል አለባቸው (ፊል 1፥17 እና ማቀ፣ ይሁ 1፥3 እና ማቀ ይመ)።

18፥21 **እግዚአብሔር አምላክ ከሆነ እግዚአብሔርን ተከተሉ፤** እግዚአብሔርን ወይም በኣልን ከሁለት አንዱን በመምረጥ ቀርጠኛ ውሳኔ ያደርጉ ዘንድ ኤልያስ ሕዝቡን ወጥሮ ያዘ (ከሕዝ 20፥31፡39 ጋር ያነጻጽሩ)። እግዚአብሔርንም ሆነ አማልክትን በአንድ ላይ ማምለክ ይቻላል በማለት እስራኤላውያን አመኑ፡ ሁለት ጌቶችን በአንድ ላይ ለማምለክ በመፈለጋቸው የተከፈለ ልብ ነበራቸውና በዚህ በደለኞች ሆኑ (ከዘዳ 6፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ)፡ ከእንዲህ ወይነቱ አደገኛ አዝማሚያ ክርስቲያኖች ይጠበቁ ዘንድ ክርስቶስ ራሱ አስጠንቅቆአል (ማቴ 6፥24 ይመ፣ ከዘዳ 30፥19፡ ከኢሱ 24፥14-15 ጋር ያነጻጽሩ፣ እንዲሁም በገጽ 1826 ላይ፣ "የአማኞች መለየት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

18፥27 **ኤልያስ ... ያፌዝባቸው ጀመር፤** ኤልያስ በበኣል ነቢያት ላይ ማፌዙ፣ እስራኤል የረከሰውንና የከፋውን የጣዖት አምልኮ በመከተሏ፣ ነቢዩ የቱን ያህል እንደተበሳጨ ያሳያል፤ ልማዳውና የሚወላውለው አቋሙ፣ ለሚወደውና ለሚያገለግለው እግዚአብሔር የቱን ያህል ቈራጥ አቋም እንዳለው ያመለክታል፤ የኤልያስን ውሳኔ የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ እንዲረክስ ሲደረግ፣ ጌታ ኢየሱስ ካሳየው ቍጣና ተቃውሞ ጋር አነጻጽር (ሉቃ 19፥45 እና ማቀ ይመ)።

33ዕንጨቱን ረበረበ፤ የወ ይፈኑንም ሥጋ
በየብልቱ ከቈረጠ በኋላ በዕንጨቱ ላይ
አኖረው። ከዚያም፣ "ውሃ በአራት ጋን
ሞልታችሁ፣ በመሥዋዕቱና በዕንጨቱ
ላይ አፍስሱ" አላቸው። 34ደግሞም፣
"እንደገና ጨምሩበት" አላቸው፤ እነርሱም
ጨመሩበት። "ሦስተኛም ጨምሩበት"
ሲል አዘዛቸው፤ እነርሱም ለሦስተኛ ጊዜ
ጨመሩበት። 35ውሃውም በመሠዊያው
ዙሪያ ፈሰሰ፤ ጕድጓዱንም ሞላው።

36የሠርክ መሥዋዕት በሚቀርብበትም
ጊዜ ኤልያስ ወደ መሠዊያው ቀረብ
ብሎ እንዲህ ሲል ጸለየ፤ "የአብርሃም፣
የይስሐቅና የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
ሆይ፤ አንተ የእስራኤል አምላክ መሆንህ፣
እኔም የአንተ አገልጋይ መሆኔና ይህን ሁሉ
በትእዛዝህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይታወቅ።
37ይህ ሕዝብ፣ አንተ አምላክ እግዚአብሔር
እውነተኛ መሆንህንና ልባቸውን
የመለስኸው አንተ መሆንህን ያውቁ ዘንድ
እባክህ ስማኝ፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ እባክህ
መልስልኝ።"

18፥33 ዘፍ22፥9
18፥36
ዘፍ24፥12፣
ዘፀ4፥5፣
29፥39፡41፣
ዘኍ16፥28፣
ኢሱ4፥24፣
1ሳሙ17፥46፣
መዝ46፥10፣
ማቴ22፥32
18፥37 ኢሱ4፥24

18፥38 ቊ 24፥
ዘፀ19፥18፣
ዘሌ9፥24፣
2ነገ1፥10፣
1ዜና21፥26፣
2ዜና7፥1፣
ኢዮ1፥16
18፥39 ቊ 21፥
ዘሌ 9፥24፣
መዝ46፥10
18፥40 ዘዳ22፥20፣
ዘዳ17፥12፣
መሳ4፥7፣
2ነገ1፥18

38ከዚያም የእግዚአብሔር እሳት ወርዳ
መሥዋዕቱን፣ ዕንጨቱን፣ ድንጋዩንና
ዐፈሩን ፈጽማ በላች፤ በጕድጓዱ ውስጥ
ያለውንም ውሃ ላሰች።

39ሕዝቡም ሁሉ ይህን ሲያዩ፣
በግንባራቸው ተደፍተው፣ "እግዚአብሔር እርሱ እውነተኛ ነው!
እግዚአብሔር እርሱ እውነተኛ አምላክ
ነው!" አሉ።

40ከዚያም ኤልያስ፣ "የበአልን ነቢያት
ያዟቸው! አንድም ሰው እንዳያመልጥ"
ሲል አዘዘ፤ ሕዝቡም ያዟቸው፤ ኤልያስም
ወደ ቂሶን ወንዝ አውርዶ አሳረዳቸው።

41ኤልያስም አክዓብን፣ "የከባድ ዝናብ
ድምፅ ይሰማልና ሂድና ብላ፤ ጠጣም"
አለው። 42ስለዚህ አክዓብ ሊበላና ሊጠጣ
ሄደ፤ ኤልያስ ግን ወደ ቀርሜሎስ ተራራ
ጫፍ ወጣ፤ ፊቱንም በጕልበቶቹ መካከል
አድርጎ ወደ መሬት አቀረቀረ።

ኢዮ 1፥6-22

18፥42 1ሳሙ12፥17፣ ያዕ5፥18

ᵐ18፥32 15 ሊትር ያህል ነው

18፥36 ኤልያስ ... ጸለየ፣ "**የአብርሃም ... አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤** በቤዛነት አጠቃላይ ታሪክ ውስጥ የኤልያስ ቈራጥነትና እምነት እጅ የለውም እስከማለት መድረስ ይቻላል፤ በንጡሥ ላይ ያደረገው ተቃውሞ (ቊ 16-19)፣ በእስራኤል ሁሉ ላይ የሰነዘረው ዘለ (ቊ 21-24)፣ እንዲሁም ከ450 የበአል ነቢያት ጋር ያደረገው መጋፈጥ (ቊ 22:27) በጸሎትና በእግዚአብሔር ላይ በተመሠረተ እምነት መሣሪያነት የተካሄደ ፍልሚያ ነበር። በእግዚአብሔር ላይ ያለው መታመን የታየው እጥር ምጥን (በዕብራይስጥ 41 ቃላት ናቸው) ያልና የቃላት ጋጋታ የሌለበት ጸሎት በማቅረቡ ነው (ቊ 36-37፤ እንዲሁም በገጽ 528 ላይ፣ "*መልስ ሚያስገኝ ጸሎት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

18፥37 ልባቸውን የመለስኸው፤ ኤልያስ ከበአል ነቢያት ጋር የተጋፈጠውና ቆይቶም ጸሎት ያደረገበት ምክንያት ለወገኖቹ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመግለጥ ነበር፤ ልባቸውንም ወደ እግዚአብሔር እንዲመልሱ ፈለገ (ቊ 37)። እንዲሁም የአዲስ ኪዳኑ፣ "ኤልያስ" የሆነው መጥምቁ ዮሐንስ (17፥1- እና ማብ ይመ)፣ ለክርስቶስ መምጣት ይዘጋጁ ዘንድ፣ የብዙዎችን ልብ ወደ እግዚአብሔር የመመለስ ዐላማ ነበረው።

18፥38 የእግዚአብሔር እሳት ወርዳ፤ መሥዋዕቱን ትበላ ዘንድ እሳትን በታምር እሳትን እወረደ (1ዜና 21፥26፣ 2ዜና 7፥1)፣ ይህ ታምር ኤልያስ የእግዚአብሔር ነቢይ መሆኑን፣ ማገልገል ያለባቸውም የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ብቻ እንደ ሆነ አረጋገጠ፤ በተመሰሳይ መንገድም አማኞች፣ መጸለይና በመንፈስ ቅዱስ በኩል የእግዚአብሔርን መገለጥ መጠባበቅ አለባቸው (1ቆሮ 12፥4-11፤ 14፥1-40 ይመ)።

18፥40 አስረዳቸው፤ ስለ በአል ነቢያት መታረድ የሚከተለውን አስተውሉ፤ (1) የሙሴን ሕግ በመታዘዝ የተከናወነ ስለሆነ (ዘዳ 13፥6-9፣ 17፥2-5) በሞት ፍርድ መቀጣታቸው ትክክል ነበር። አዲስ ኪዳን እንዲህ ያለ ትእዛዝ የለውም፤ እነርሱን እርግፍ አድርጎ መተውና ከእነርሱ መለየት አስፈላጊ እንደ ሆነ ቢያዝም፣ በስህተት ትምህርት አስተማሪዎች ላይ የጎላል እርምጃ እንዳይወስድባቸው ተከልክሎአል (ማቴ 24፥23-24፤ 2ቆሮ 6፥14-18፤ ገላ 1፥6-9፤ 2ዮሐ 7—11፤ ይሁ 1፥3-4፤ እንዲሁም በገጽ 1519 ላይ፣ "*የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) በሐሰተኛ ነቢያት ላይ ኤልያስ የወሰደው እርምጃ፣ የተመረጠ ሕዝቡን እምነትና መንፈሳዊ ቅርስ ለማጥፋት በሚጥሩት ላይ የእግዚአብሔርን ቊጣና ኤልያስ ሁሉን ላስቻለው አምላኩ ያለውን ፍቅርና ታማኝነት ይገልጻል። ስለዚህ መንፈሱና ልቡ ከእግዚአብሔር ጋር ስምም ነበሩ፤ እስራኤላውያን ከወደዳቸውና ከተቤዣቸው፣ ከኪዳኑም አምላካቸው ሲያፈነግጡ ማበረገባዊና መንፈሳዊ ስሜቱ ለቊጣ ተነሣሣ።

(3) ኤልያስ ሐሰተኛ ነቢያት እንዲታረዱ ማድረጉ፣ በሐሰተኛ እምነት የተነሣ መንፈሳዊ ሞት እየሞቱ ለነበሩት እስራኤላውያን የቱን ያህል ግድ እንደ ነበረው ያሳያል። ኢየሱስም ተመሳሳይ ሙንቀት ነበረው (ማቴ 23፤ እንደዚሁም ሉቃ 19፥27 ይመ)፤ ጳውሎስም እንደዚሁ (ገላ 1፥6-9፤ ገላ1፥9 እና ማብ ይመ)። ከዚህም በላይ፣ "ትክክለኛ ፍርዱ ሲገለጥ በእግዚአብሔር የቊጣ ቀን" (ሮሜ 2፥5 ይመ ከ11፥22፤ ከራእ 19፥11-21፤ 20፥7-10 ጋር ያነጻጽሩ) እንቢተኛ በሆኑትና ንስሐ በማይገቡት ላይ የእግዚአብሔር ቊጣ እንደሚወርድባቸው አስተውል።

18፥42 ኤልያስ ... ፊቱንም በጕልበቶቹ መካከል አድርጎ፤ አዲስ ኪዳን፣ ጸሎት የቱን ያህል ኀይል እንዳለው ለማሳየት የኤልያስን እምነትና የማያቋርጥ ምልጃ፣ ታማኝ ለሆኑት የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ አርአያና ማበረታቻ አድርጎ ይጠቅሳል (ያዕ 5፥18፤ እንዲሁም በገጽ 528 ላይ፤ "*መልስ ሚያስገኝ ጸሎት*" በሚል የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። የኤልያስ ጸሎት የሚከተለው ነው፤ (1) የጻድቅ ሰው ጸሎት ነበር (ያዕ 5፥16 ይመ፤ ከመዝ 66፥18 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (2) እንደ እኛ ሰብአዊ ተፈጥሮ የነበረው ሰው ያቀረበው ጸሎት ነበር (ያዕ 5፥17)፤ (3) በብርታትና በጽናት የቀረበ የእምነት ጸሎት ነበር

መልስ የሚያስገኝ ጸሎት

1ነገ 18፥42-45 "ኤልያስ ግን ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ጫፍ ወጣ፤ ፊቱንም በጉልበቶቹ መካከል አድርጎ ወደ መሬት አቀረቀረ። አገልጋዩንም፣ "ውጣና ወደ ባሕሩ ተመልከት" አለው። አገልጋዩም ሄደ ተመለከተና፣ "በዚያ ምንም የለም" አለው። ኤልያስ ሰባት ጊዜ፣ "እንደገና ሂድ" አለው። በሰባተኛው ጊዜ አገልጋዩ፣ "እነሆ፣ የሰው እጅ የምታህል ትንሽ ደመና ከባሕሩ እየወጣች ነው" አለው። ኤልያስም፣ "ሂድና አክዓብን፣ 'ዝናቡ ሳያግድህ ሠረገላህን ጭነህ ውረድ' ብለህ ንገረው" አለው። ወዲያውኑም ሰማዩ በጥቍር ደመና ተሸፈነ፥ ዥዋሱ ነፈሰ፣ ከባድ ዝናብ ጣለ፣ አክዓብም በሠረገላ ተቀምጦ ወደ ኢይዝራኤል ሄደ።"

ጸሎት አማኞች በተለያየ መልኩ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነት ያመለክታል። "ጸሎት" እና "መጸለይ" ከተባሉት ቃላት በተጨማሪ ይህ የተግባር እንቅስቃሴ እንደሚከተለው ተገልጸአል፤ እግዚአብሔርን መጥራት (መዝ 17፥6)፣ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት (ዘፍ 4፥26)፣ ወደ እግዚአብሔር መጮህ (መዝ 3፥4)፣ ነፍስን ወደ እግዚአብሔር ማንሣት (መዝ 25፥1)፣ እግዚአብሔርን መፈለግ (ኢሳ 55፥6)፣ ወደ ጸጋው ዙፋን በሙሉ ልብ መቅረብ (ዕብ 4፥16)፣ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ (ዕብ 10፥22)።

የጸሎት አስፈላጊነት መጽሐፍ ቅዱስ፣ የእግዚአብሔር ሰዎች ለምን መጸለይ እንዳለባቸው ግልጽ የሆኑ ምክንያቶችን ሰጥቶአል፤ (1) ከሁሉ አስቀድሞ የሚጠቀሰው ክርስቲያኖች ይጸልዩ ዘንድ በእግዚአብሔር መታዘዛቸው ነው። የጸሎት ትእዛዝ የመጣው በመዝሙረኞች (1ዜና 16፥11፤ መዝ 105፥4)፣ በነቢያት (ኢሳ 55፥6፤ አሞ 5፥4፡6)፣ በሐዋርያት (ኤፌ 6፥17-18፤ ቈላ 4፥2፤ 1ተሰ 5፥17) እና በራሱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አንደበት ተነግሮአል (ማቴ 26፥41፤ ሉቃ 18፥1፤ ዮሐ 16፥24)። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ኅብረት ይኖረው ዘንድ ይፈልጋል፤ ስለዚህ በጸሎት አማካይነት ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት እናጸናለን።

(2) ጸሎት የእግዚአብሔርን በረከት፣ ኀይልና የተስፋውን ፍጻሜ የምንቀበልበት አስፈላጊ ድልድይ ነው። አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይህንኑ መርሕ አጉልተው ያሳያሉ። የሰማይ አባታቸው በር እንዲከፈት አጥብቀው ቢለምኑ፣ ቢፈልጉና ቢያንኳኩ መንፈስ ቅዱስን እንደሚቀበሉ ጌታ ኢየሱስ ቃል ገብቶአል (ሉቃ 11፥5-13)። ስለዚህ ጌታ ከዐረገ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ በጸንጠ ቈስጤ ዕለት (ሐሥ 2፥1-4) መንፈስ ቅዱስ በኀይል እስከወረደበት ቀን ድረስ (ከሐሥ 1፥8 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በአንድ ላይ ሆነው ያለሚቋረጥ በላይኛው ሰገነት ይጸልዩ ነበር (ሐሥ 1፥14)። ሐዋርያት በአይሁድ ባለሥልጣናት ታስረው ከተፈቱ በኋላ ቃሉን ሲናገሩ በድፍረትና በኀይል እንዲናገሩ መንፈስ ቅዱስ ይወርድላቸው ዘንድ በቅን ልቦና ጸለዩ፤ "ከጸለዩም በኋላ የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፣ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፣ የእግዚአብሔርንም ቃል በድፍረት ተናገሩ" (ሐሥ 4፥31)። ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ክርስቲያኖች ካልጸለዩለት በቀር አገልግሎት እንደማይሳካለት በመረዳት አዘውትሮ የጸሎት ጥያቄ አቀረበ (ለምሳሌ ሮሜ 15፥30-32፤ 2ቆሮ 1፥11፤ ኤፌ 6፥18-20፤ ፊል 1፥19፤ ቈላ 4፥3-4 ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1280 ላይ፣ "የምልጃ ጸሎት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ያዕቆብ ለአማኝ ፈውስ የሚመጣለት "በእምነት የቀረበ ጸሎት" እንደ ሆነ በግልጽ ይናጋራል (ያዕ 5፥14-15)።

(3) እግዚአብሔር በሰው ዘር የድነት ዕቅድ ውስጥ፣ ክርስቲያኖች በመቤዠት ሂደት አብረው ሠራተኞች ይሆኑ ዘንድ በጎ ፈቃዱ ሆኖአል። በአንድ በኩል ሲታይ እግዚአብሔር የድነት ሥራውን የሚያከናውነው በሌላ ሳይሆን፣ በተቀደሰ፣ እምነት በተሞላና በማያቋርጥ በሕዝቡ ጸሎት ነው። በእግዚአብሔር መንግሥት በምእመናን የምልጃ ጸሎት ካልሆነ በቀር በሌላ ረገድ የማይከናወን በርካታ ጉዳይ አለ (ዘፀ 33፥11 እና ማብ ይመ)። ለምሳሌ እግዚአብሔር ሠራተኞችን ወደ ወንጌል መከር መላክ ይፈልጋል፤ ይህ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ሙሉ ዓላማ ሊላካ የሚችለው በደቀ መዛሙርቱ ጸሎት እንደ ሆነ ክርስቶስ ያስተምራል፤ "ስለዚህ የመከሩ ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት" (ማቴ 9፥38)፤ በሌላ አነጋገር ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር መንግሥት እንድትስፋፋ በቅን ልቦና ጸሎት ሲያቀርቡ ብቻ አያሌ ዕቅድ ይከናወን ዘንድ የእግዚአብሔር ኀይል ይመጣል። ባንጸልይ ለእኛ ለእያንዳንዳችንና አንድ

አካል ሆና ለቆመችው ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ያቀደውን የመቤዠት ዐላማ ልንገድብ እንችላለን።

መልስ ለሚያስገኝ ጸሎት የሚያስፈልጉ ነገሮች፤ እግዚአብሔር የሚሰማውን ጸሎት ለማቅረብ፤ የምናቀርበው ጸሎት ይሰማ ዘንድ አንዳንድ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፤ (1) እውነተኛ ልብና ሙሉ እምነት ከሌለን በቀር ጸሎታችን አይመለስም)፤ ኢየሱስ "ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደተቀበላችሁት እድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል" (ማር 11፥24) አለ። ልጁ በጋኔን ተይዘበት ለነበረውም ሰው፤ "ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻላል" (ማር 9፥23) አለ። የዕብራውያን ጸሓፊ፤ "በእውነተኛ ልብና በሙሉ እምነት ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ" በማለት ይገፋፋናል፤ ያዕቆብም ልመና ስናቀርብ፤ "ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን" በማለት ያደፋፍረናል። (ያዕ 1፥6 ይመ፤ ከያዕ 5፥15 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ጸሎት በኢየሱስ ስም መቅረብ አለበት፤ ይህንኑ መርሕ ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ገልጾታል፤ "አብ በወልድ እንዲከብር፣ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ፤ ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑኝ እኔ አደርገዋለሁ" (ዮሐ 14፥13-14)። ጸሎታችን ከጌታችን ማንነት፣ ባሕርይና ፈቃድ ጋር የሚስማማ ሆኖ መቅረብ አለበት (ዮሐ 14፥13 እና ማብ ይመ)።

(3) ጸሎት መልስ የሚያገኘው እንደ እግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ ሲቀርብ ብቻ ነው፤ "በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ ማንኛውም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን እርሱ ይሰማናል (1ዮሐ 5፥14 እንዲሁም በገጽ 1075 ላይ፣ "የእግዚአብሔር ፈቃድ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ኢየሱስ ያስተማረውን ጸሎት ማለትም የጌታ ጸሎት፤ "ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን" (ማቴ 6፥10 ይመ፤ ከሉቃ 11፥2 ጋር ያነጻጽሩ፤ ጌታ ኢየሱስ ራሱ በጌቴሰማኔ ያደረገውን ጸሎት ያስተውሉ፤ ማቴ 26፥42)፣ የሚለው ይህንኑ ያጸናል። ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ እንችላለን፣ እርሱ ፈቃዱን በመጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ ገልጦልናልና። እግዚአብሔር በቃሉ ላይ በሰጠው ተስፋ መሠረት በትክክል የቀረበ ማንኛውም ጸሎት፣ መልስ ሊያገኝ እንደሚችል እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። ኤልያስ የእስራኤል አምላክ ጸሎቱን በእሳት በኋላም በዝናብ እንደሚመልስለት እርግጠኛ ነበር፣ የጌታ ትንቢታዊ ቃል መጥቶለት ነበርና (1ነገ 18፥1)። ማንኛቸውም የአሕዛብ አማልክት ከእስራኤል ጌታና አምላክ እንደማይበልጡ ወይም እንደ እርሱ ያለ ኀይል እንደሌላቸው እርግጠኛ ነበር (1ነገ 18፥21-24)። በሌላ ጊዜም የእግዚአብሔር ፈቃድ ግልጽ ከሆነልን፣ ምን እንደ ሆነም ካወቅን፣ እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ ዐውቀን በሙሉ ልብና በእምነት መጸለይ እንችላለን።

(4) መጸለይ ያለብን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ ጸሎታችንን ሰምቶ ይመልስልን ዘንድ፣ እኛም በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መገኘት ይኖርብናል። እግዚአብሔር ያቀረብነውን ጸሎት የሚመልስልን አስቀድመን መንግሥቱንና ጽድቁን ስንፈልግ ነው (ማቴ 6፥33 እና ማብ ይመ)። ሐዋርያው ዮሐንስ ግልጽ በሆነ ቋንቋ "ትእዛዛቱንም ስለምንጠብቅና በፊቱም ደስ የሚያሰኘውን ስለምናደርግ የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እንቀበላለን" (1ዮሐ 3፥22 እና ማብ ይመ)። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መጠበቅ፣ እርሱን መውደድና እርሱንም ማስደሰት ጸሎት መልስ ያገኝ ዘንድ አስፈላጊ የሆኑ ግዴታዎች ናቸው። ያዕቆብ፣ "የጻድቅ ሰው ጸሎት ኀይል አለው" ብሎ ሲጽፍ፣ "ጻድቅ" ሲል ለማለት የፈለገው ሁለት ነገር ነው፤ ይኸውም በክርስቶስ በማመኑ ጻድቅ የሆነ ሰው፣ ነቢዩ ኤልያስ እንደኖረውም ሁሉ፣ ለጽድቅ እግዚአብሔርን በመፍራትና በታዛዥነት ሕይወት የኖረ ሰው ማለት ነው (ያዕ 5፥16-18 ይመ፤ ከመዝ 34፥13-14 ጋር ያነጻጽሩ)። በብሉይ ኪዳንም ይኸው ጉዳይ ከዘሁ ቀደም አጽንዖት ተሰጥቶታል። ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ ሲል ያቀረበው ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት መልስ ሊያገኝ የቻለው ከጌታ ጋር የታዛዥነት ግንኙነት ስለነበረውና ለእርሱም ታማኝ ስለሆነ ነበር (ዘፀ 33፥17 እና ማብ ይመ)። በአንዳንድ ቡነጢአታችን ብንኖር ግን፣ ጌታ ጸሎታችንን እንደማይሰማ መዝሙረኛው ግልጽ አድርጎአል (መዝ 66፥18፤ ያዕ 4፥3 እና ማብ ይመ)። እግዚአብሔር ጣዖት አምላኪና ክፉ የሆኑትን የእስራኤላውያንን ጸሎት ያልሰማው ከዚህ የተነሣ ነው (ኢሳ 1፥15)። ይሁን እንጅ የእግዚአብሔር ሕዝብ ንስሐ ገብተው ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ፣ ጌታ ዳግም እንደሚሰማቸው፣ ኀጢአታቸውን ይቅር እንደሚላቸው፣ ምድራቸውንም እንደሚፈውስ ቃል ገብቶአል (2ዜና 7፥14 ይመ፤ ከ6፥36-39፤ ከሉቃ 18፥14 ጋር ያነጻጽሩ)። በስርየት ቀን የእስራኤላውያን ኀጢአት ይቅር ይባል ዘንድ ሊቀ ካህኑ የሚያቀርበው ጸሎት፣ የራሱ የሊቀ ካህናቱ ሕይወት ኵነኔ ካልነጻ በቀር የማይሰማ እንደ ነበር ያስተውሉ (ዘፀ 26፥33 እና ማብ፤ በገጽ 202 ላይ፣ "የስርየት ቀን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(5) በመጨረሻም ጸሎታችን ይሰማልን ዘንድ ያለማቋረጥ መጸለይ ይኖርብናል። ያለመታከት የጸለየችው መበለት ምሳሌነት የሚያስተምረው ዋና ትምህርት ይህንኑ ነው (ሉቃ 18፥1-7፥ 18፥1 እና ማብ ይመ)። ኢየሱስ፣ "ለምኑ ... ፈልጉ ... አንኳኩ" (ማቴ 7፥7-8) በማለት የሰጠው ትምህርት በአጽንዖት የሚያሳየው በጽናት መጸለይን ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም ራሳችንን የጸሎት ሰዎች እንድናደርግ ያደፋፍረናል (ቈላ 4፥2 እና ማብ፤ 1ተሰ 5፥17 እና ማብ ይመ)። የብሉይ ኪዳን ቅዱሳንም ይህንኑ መርሕ አስተውለውታል። ለምሳሌም እስራኤላውያን ከአማሌቃውያን ጋር ሲዋጉ ሳለ ድል ሊያገኙ የቻሉት፣ ሙሴ እጁን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ ወደ እግዚአብሔር በጸለየ ጊዜ ብቻ ነበር (ዘፀ 17፥11 እና ማብ ይመ)። ኤልያስ ዝናብ እንደሚመጣ የትንቢትን ቃል ከተቀበለ በኋላ ዝናብ እስከሚዘንብ ድረስ ጸሎቱን ቀጠለ (1ነገ 18፥41-45)። ቀደም ባለው ወቅትም ለሰራጥታዋ መበለት ልጅ፣ ጌታ ዳግም ሕይወት እስኪሰጠው ድረስ ነቢዩ ያለማቋረጥ በትጋት ልመናውን ወደ እግዚአብሔር አቀረበ (1ነገ 17፥17-23)።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሖችና መልስ የሚያስገኝ ጸሎት የሚቀርብበት መንገድ፤ (1) አንድን ጸሎት መልስ የሚያስገኝ የሚያደርጉት ነገሮች ምንድን ናቸው? (ሀ) ጸሎታችን ፍሬ የሚያስገኝ ጸሎት ይሆን ዘንድ እግዚአብሔርን ከልብ ማወደስና ማሞገስ ይኖርብናል (መዝ 150፤ ሐሥ 2፥47፤ ሮሜ 15፥11 እንዲሁም በገጽ 802 ላይ፣ "ምስጋና" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። (ለ) ከዚህ ጋር በጥብቅ የተሳሰረውና በእኩል ደረጃ አስፈላጊ የሆነው ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ነው (መዝ 100፥4፤ ማቴ 11፥25-26፤ ፊል 4፥6 ይመ)። (ሐ) በእምነት ለሚቀርብ ጸሎት፣ በግልጽ ከሚታወቅ ኀጢአት ከልብ የሆነ ንስሐ መግባት አስፈላጊ ነው። (ያዕ 5፥15-16 ይመ፤ ከመዝ 51፤ ከሉቃ 18፥13፤ ከ1ዮሐ 1፥9 ጋር ያነጻጽሩ)። (መ) እንደ ፍላጎታችን ሳይሆን፣ አስፈላጊያችን እንደሆኑት ነገሮች መጠን ልመናችንን እንድናቀርብ እግዚአብሔር ያዘናል፤ የምንፈልገውን ነገር የማናገኘው አንድም ባለመጠየቃችን አሊያም አጉል በሆነ መሻት ተነሣሥተን ልመና በማቅረባችን ነው (ያዕ 4፥2-3፤ ከመዝ 27፥7-12፤ ከማቴ 7፥7-11፤ ከፊል 4፥6 ጋር ያነጻጽሩ)። (ሠ) ለሌሎችም በሙሉ ልብና ፍቅር መጸለይ ይኖርብናል (ዘኍ 14፥13-19፤ መዝ 122፥6-9፤ ሉቃ 22፥31-32፤ 23፥34 እንዲሁም በገጽ 1280 ላይ፣ "የምልጃ ጸሎት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) መጸለይ ያለብን እንዴት ነው? ባዶ ቃላት በማነብነባችን ብቻ የማንሰማ በመሆናችን (ማቴ 6፥7) ከልብና ከእውነት የሆነ ልመና እንድናቀርብ ኢየሱስ በአጽንዖት ያስተምራል። ድምጽ ሳናሰማ በለጐሳስ መጸለይ እንችላለን (ነህ 9፥4፤ ሕዝ 11፥13)። የራሳችንን ቃላት ወይም የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃላት በመጠቀም መጸለይ እንችላለን። በአእምሮ መጸለይ እንችላለን፤ ወይም በመንፈስ መጸለይ እንችላለን፤ ይኸውም በልሳን ማለት ነው (1ቆሮ 14፥14-18)፤ በሰው ቋንቋ ወይም ባልተሰማ ቋንቋ (ሮሜ 8፥26) የቀረበውን ልመና መንፈስ ቅዱስ ወደ ጌታ እንደሚያቀርብልን በመተማመን፣ የሰውን ቋንቋ እንኳ ሳንጠቀም በመቃተት ብቻ መጸለይ እንችላለን። ሌላው የጸሎት ዘዴ ደግሞ ለጌታ መዝሙር በማቅረብ ነው (መዝ 92፥1-2፤ ኤፌ 5፥19-20፤ ቈላ 3፥16)። ብርቱ ጸሎት አንዳንድ ጊዜ ከጾም ጋር ሊቀርብ ይችላል (ዕዝ 8፥21፤ ነህ 1፥4፤ ዳን 9፥3-4፤ ሉቃ 2፥37፤ ሐሥ 14፥23፤ ማቴ 6፥16 እና ማብ ይመ)።

(3) እንዴት ሆነን ነው መጸለይ የሚገባን? መጽሐፍ ቅዱስ ቆመው ሳለ (1ነገ 8፥22፤ ነህ 9፥4-5)፣ ተቀምጠው ሳለ (1ዜና 17፥16፤ ሉቃ 10፥13)፣ በመንበርከክ (ዕዝ 9፥5፤ ዳን 6፥10፤ ሐሥ 20፥36፣ አልጋ ላይ ተጋድመው ሳለ (መዝ 63፥6)፣ ወይም በመስገድ (ዘፀ 34፥8፤ መዝ 95፥6)፣ በመሬት ላይ በመዘርጋት (2ሳሙ 12፥16፤ ማቴ 26፥39) እንዲሁም እጅን ወደ ሰማይ በማንሣት (መዝ 28፥2፤ ኢሳ 1፥15፤ 1ጢሞ 2፥8) ጸሎት መቅረቡን አስፍሮ ይገኛል።

መልስ የሚያስገኝ ጸሎት ምሳሌዎች፤ መጽሐፍ ቅዱስ በአርአያነት በሚጠቀሱ፣ ኀይል በነበራቸውና መልስ ባስገኙ ጸሎቶች የተሞላ ነው፤ (1) ሙሴ፣ እግዚአብሔር የመለሰለት አያሌ የምልጃ ጸሎቶች ነበሩት፤ እርሱ ካቀረበው ልመና በተለየ መንገድ የሚመልስለት መሆኑን እግዚአብሔር በነገረው ጊዜ እንኳ ጸሎቱ ተመልሶለታል (በገጽ 1280 ላይ፣ "የምልጃ ጸሎት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። (2) ንስሐ የገባው ሳምሶን የሕይወት ዘመኑን ተልእኮ፣ ይፈጽም ዘንድ ፍልስጥኤማውያንን ለማሸነፍ አንድ የመጨረሻ ዕድል እንዲሰጠው ጸለየ፤ እግዚአብሔርም የአማልክታቸውን ኀይልነት ያከብሩበት የነበረውን ሕንጻ ምሰሶዎች ገፍቶ የሚደረምስበትን ኀይል በመስጠት መለሰለት (መሳ 16፥21-30)። (3) ነቢዩ ኤልያስ ቢያንስ ቢያንስ አራት ኀይል ያላቸው ጸሎቶች ጸልዮ ተመልሶለታል፤ ሁሉም ለእስራኤል አምላክ ክብር አስገኝተዋል (1ነገ 17-18 ይመ፤ ከያዕ 5፥17-18 ጋር ያነጻጽሩ)። (4) ንጉሥ ሕዝቅኤል በጸና ታሞ ነበር፤ ኢሳይያስም እንደሚሞት ነገረው (2ነገ 20፥1፤ ኢሳ 38፥1)። ሕዝቅያስ ሕይወቱም

ሆነ ሥራው ፍጻሜ ላይ እንዳልደረሰ ስለተሰማው፣ ተጨማሪ የዕድሜ ዘመን ይሰጠው ዘንድ ፊቱን ወደ ግንቡ ሰማዞር በብርቱ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። እግዚአብሔርም ኢሳይያስ ወደ ሕዝቅኤል መልሶ በመላክ፣ በዕድሜው ላይ ዐሥራአምስተ ዓመት በመጨመርና ከሕመሙ በመፈወስ የጸሎቱን መልስ አረጋገጠለት (2ነገ 20፥2-6፣ ኢሳ 38፥2-6)። (5) ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ተጥሎ ሳለ፣ አፋቸውን በመዝጋት ያድነው ዘንድ ወደ ጌታ ሳይጸልይ አልቀረም፣ እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰማው (ዳን 6፥10፡16-22)። (6) የቀደሙት ክርስቲያኖች ጴጥሮስ ከእስር ቤተ ይመጣ ዘንድ አጥብቀው ጸለዩ፣ እግዚአብሔርም መልአኩን ልኮ ከእስር ቤት አወጣው (ሐሥ 12፥3-11 ይመ፡ 12፥5 እና ግብ ይመ)። እንዲህ ያሉት ምሳሌዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተመለከቱት መርሖች መሠረት፣ መልስ የሚያስገኝ ጸሎት እንድናቀርብ በቅዱስ ምኞትና በእምነት እንዲሞሉን ያስፈልጋል።

43አገልጋዩንም፣ "ውጣና ወደ ባሕሩ ተመልከት" አለው።
አገልጋዩም ሄዶ ተመለከተና፤ "በዚያ ምንም የለም" አለው።
ኤልያስ ሰባት ጊዜ፣ "እንደ ገና ሂድ" አለው።
44በሰባተኛው ጊዜ አገልጋዩ፣ "እነሆ፤ የሰው እጅ የምታህል ትንሽ ደመና ከባሕሩ እየወጣች ነው" አለው።
ኤልያስም፣ "ሂድና አክዓብን፣ 'ዝናቡ ሳያግድህ፣ ሠረገላህን ጭነህ ውረድ' ብለህ ንገረው" አለው።
45ወዲያውኑም ሰማዩ በጥቊር ደመና ተሸፈነ፤ ነፋሱ ነፈሰ፤ ከባድ ዝናብ ጣለ፤ አክዓብም በሠረገላ ተቀምጦ ወደ ኢይዝራኤል ሄደ። 46የእግዚአብሔርም ኀይል በኤልያስ ላይ ወረደ፤ ኤልያስም ልብሱን ከፍ አድርጎ በቀበቶው ካጠበቀ በኋላ እስከ ኢይዝራኤል ድረስ አክዓብን ቀድሞት ሮጠ።

2ነገ 4፥18-37

18፥44 ኢሳ6፥15፤ ሉቃ12፥54
18፥45 1ሳሙ29፥1፤ 1ነገ8፥36፤ ኢዮ37፥13፤ ሆሴ1፥4
18፥46 መሳ3፥10፤ 1ሳሙ11፥6፤ 2ነገ4፥29፤ 9፥1፤ ሉቃ1፥35፤ 4፥14

19፥1 ዘፀ22፥20፤ 1ነገ16፥31
19፥2 ሩት1፥17፤ መዝ13፥4፤ ኤር20፥10፤ 26፥21፤ 36፥26
19፥3 ዘኍ19፥17፤ 31፥21፤ ኢሳ19፥2
19፥4 ዘጥ11፥15፤ ኢዮ6፥9፤ 7፥16፤ 10፥1፤ 30፥4፤

ኤልያስ ወደ ኮሬብ ኰበለለ

19 አክዓብ በዚህ ጊዜ፣ ኤልያስ ያደረገውን በሙሉ፣ ነቢያቱንም ሁሉ እንዴት በሰይፍ እንዳስገደላቸው ለኤልዛቤል ነገራት። 2ስለዚህም እርሷ፣ "ነገ በዚህ ሰዓት ያንተንም ነፍስ ከእነዚያ እንደ አንዱ ነፍስ ሳላደርጋት ብቀር አማልክት እንዲህ ያድርጉብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጡብኝ" ስትል ወደ ኤልያስ መልእክተኛ ላከች።

3ኤልያስም ፈርቶ[ዐ] ስለ ነበር፣ ሕይወቱን ለማትረፍ ሲል ሸሸ። በይሁዳ ምድር ወዴለችው ወደ ቤርሳቤህ እንደ መጣም አልጋዩን በዚያ ተወው፤ 4በምድረ በዳም ውስጥ የአንድ ቀን መንገድ ተጓዘ፤ ወደ አንድ ኪትክታ ዛፍ እንደ መጣም፣ ከሥሩ

19፥4 መዝ69፥19፤ ኤር20፥18፤ ዮና4፥8

[ዐ] 19፥3 ወይም ኤልያስ አይቶ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል

(ቊ 18፥42-44፤ ያዕ 5፥17 ይመ፤ ከማቴ 21፥21-22፤ ከማር 9፥23፤ ከሉቃ 18፥1፤ ከኤፌ 6፥18፤ ከዕብ 11፥6 ጋር ያነጻጽሩ)፤ እና (4) አያሌ ውጤት ያስገኘ ጸሎት ነበር (ቊ 45፤ ያዕ 5፥16-17)።

18፥43 ኤልያስ ሰባት ጊዜ ... አለው፤ ሰባት ቊጥር በቅዱሳት መጻሕፍት ሙሉና ፍጹም የሆነውን ነገር በትእምርትነት ያመለክታል። በዚህ ምዕራፍ ላይ ኤልያስ በሦስት ረገድ ፍጹም ምልጃ ውስጥ ገብቶ ይገኛል፤ (1) መሠዊያውና የእግዚአብሔር ክብር ወደ ምድራቱ ይመለሱ ዘንድ ምልጃ አቀረበ (ቊ 21፥24:30-39)፤ (2) ከስሑት ሃይማኖት፣ ከበኣልና ከአሼራ ጣዖት አምልኮ ጋር መንፈሳዊ ጦርነት ለማድረግ ምልጃ አቀረበ (19፥27:40)፣ እና (3) ዝናብ ይዘንብ ዘንድ (ቊ 41-46) ብርቱና የማያቋርጥ ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት አቀረበ።

ብሉይ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ከዝናብ መውረድ ጋር እስካነጻጸረው ድረስ (ለምሳሌ ሆሴ 6፥1-3፤ ኢል 2፥23-29)፣ ኤልያስ ከበኣል እምነት ጋር ያደረገው ትግል ሦስቱን ዐይነት የእግዚአብሔር ሕዝብ የምልጃ ጸሎት ባሕርያት ያሳያል፤ (1) የእግዚአብሔር ክብርና ሞገስ ይመለስ ዘንድ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ተሐድሶ እንዲኖር ምልጃ ማቅረብ፤ (2) የአጋንንትን ብርቱ ምሽግ ለማፍረስ ለሚደረገው መንፈሳዊ ፍልሚያ የሚደረግ ምልጃ፤ እና (3) መንፈሳዊ ሕይወት በሚቀዘቅዝበት ወቅት ይኸው ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ መውረድና በመንፈሳዊ መነቃቃት ይሻር ዘንድ የሚደረግ ምልጃ ናቸው (በገጽ 1280 ላይ፣ «*የምልጃ ጸሎት*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኲረት ጽሑፍ ይመ)።

19፥3 ኤልያስም ፈርቶ ስለነበር፣ ሕይወቱን ለማትረፍ ሲል ሸሸ፤ የኤልያስ እምነትና በምዕ 18 ላይ የተገለጸው ታምራዊ ድል፣ ያስከተለው ፍርሃትን፣ ሕይወትን ለማትረፍ መሸሽንና ተስፋ መቁረጥን ሲሆን፣ ይህም ሁሉ የተከሠተው ኤልዛቤል ሕይወቱን ለማጥፋት ከነበራት ዕቅድ የተነሣ ነበር (ቊ 2)። (1) በኢይዝራኤል ይቆይ ዘንድ ኤልያስ ከእግዚአብሔር መልእክት ስላልተቀበለ፣ በዚያ መቆየት ሳያስፈልግ ሕይወትን ለአደጋ መዳረግ ነበር ጋር ያነጻጽሩ)፤ መድረሻውም የኮሬብ ተራራ ሆ የሲራ ተራራ) ነበርና።

(2) ኤልያስ ሳይወድ በግድ ከእስራኤል ወደ ይሁዳና ወደ ምድረ በዳው እንዲሰደድ መደረጉ፣ «ስለ ጽድቅ» ብለው (ማቴ 5፥10 እና ማብ ይመ) ማፍ የደረሰባቸውንና በምድረ በዳ፣ በተራሮች፣ በዋሻዎችና በጉድጓዶች ውስጥ እንዲንከራተቱ የተገደዱት ወገኖች ምሳሌ መሆኑን ያመለክታል (ዕብ 11፥37-38)። ዛሬም ቢሆን ቤተ ክርስቲያናቸውን ትተው ፍተሰዱ ነቢያት፣ ከምስባካቸው የተባረሩ ሰባኪያን፣ ወደ ማስተማሪያ ክፍላቸው እንዳይገቡ የተደረጉ መምህራን፣ ከሥራቸው የተፈናቀሉ ምዕመናን የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽ በመናገራቸው፣ ስለ ስሙም ሲሉ የጽድቅን መንገድ በመከተላቸው ነው፤ በሰማይ የሚያገኙት ሽልማት ትልቅ ነውና (ማቴ 5፥10-12)።

19፥4 ነፍሴን ውሰዳት፣ በመታከት፣ ተስፋ በመቁረጥና በሐዘን የተሸነፈው ኤልያስ እግዚአብሔር ይህን ከባድ የነቢይነት ሸክም አንሥቶለት ወደ ሰማያዊ ዕረፍቱ ያሻግረው ዘንድ ጸሎት አቀረበ፤ በዚህ ጊዜ የኤልያስ ናፍቆት (1) «ከዚህ መለየትና ከክርስቶስ ጋር መሆን» (ፊል 1፥23) ብሎ ከጸለየው ከሐዋርያው ጳውሎስ፣ ወይም የእምነት አርበኞች ከሆኑት «የሚበልጠውን፣ በሰማይ ያለውን አገር ይናፍቃሉ» ከተባሉት የተለየ ነው (ዕብ 11፥16 ይመ፤ እንዲሁም በዘፍ 11፥15 ላይ በተገለጸው መሠረት ከሙሴ ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ኤልያስ ጥልቅ ከሆነ ተስፋ መቊረጥ ስሜት ውስጥ የገባባቸው አንዳንድ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፤ (ሀ) ስኬታማ ያለመሆን ስሜት፤ ኤልዛቤል እንኳ ሳትቀር እስራኤል ሁሉ ወደ ቀደመው እምነት ይመለሳሉ ብሎ ተስፋ አድርጎ ነበር፤ ሆኖም ያ ሳይሳካ በመቅረቱ በምትኩ ያተረፈው ነገር ቢኖር ሕይወቱን ለማዳን መሸሽ ብቻ ነበር። ዕድሜ ዘመኑን ተስፋ ያደረገው፣ የደከመለትና የወጣ የወረደለት ጉዳይ በስኬት አልባነት የተደመደመ መሰለው (ቊ 1-4)። (ለ) የብቸኝነት ስሜት፤ ለእግዚአብሔር እውነትና ጽድቅ ሲባል በሚደረገው ትግል ውስጥ ብቻውን የተጋፈጠ መሰለው (ቊ 10 ይመ፤ ከ2ጢሞ 4፥16 ጋር ያነጻጽሩ)። (ሐ) ረጅምና አድካሚ ጉዞ ከማድረጉ የተነሣ የደረሰበት መንገላታት (ቊ 3-4፤ 18፥46)።

ተቀምጦ፤ ይሞት ዘንድ "እግዚአብሔር ሆይ፤ በቅቶኛል፤ እኔ ከቀደሙት አባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰዳት" ብሎ ጸለየ። 5ዘዚያም ከዛፍ ሥር ተጋደመ፤ እንቅልፍም ወሰደው።

በድንገትም አንድ መልአክ ነካ አደረገውና፣ "ተነሥና ብላ" አለው። 6ዘወር ብሎ ሲመለከትም፣ እነሆ፣ በፍም የተጋገረ እንጎቻና አንድ ጎንቦ ውሃ ከራስጌው አገኘ፤ ከበላና ከጠጣም በኋላ ተመልሶ ተኛ።

7የእግዚአብሔርም መልአክ እንደ ገና መጥቶ ነካ አደረገውና፣ "ሩቅ መንገድ ስለምትሄድ ተነሥና ብላ" አለው። 8ስለዚህም ተነሥቶ በላ፤ ጠጣም፤ በምግቡም ብርታት አግኝቶ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ ኮሬብ እስኪደርስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ተጓዘ፤ 9በዚያም ወደ አንዲት ዋሻ ገብቶ ዐደረ።

እግዚአብሔር ለኤልያስ ተገለጠለት

የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እርሱ መጣ፤ "ኤልያስ ሆይ፤ እዚህ ምን ታደርጋለህ?" አለው።

10እርሱም፣ "እኔ ለሰራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ፤ እስራኤላውያን ኪዳንህን ትተዋል፤ መሠዊያዎችህን አፍርሰዋል፤ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና። የቀረሁት እኔ ብቻ ነኝ፤ አሁንም እኔን ለመግደል ይፈልጋሉ።"

11እግዚአብሔርም፣ "እግዚአብሔር በዚያ ያልፋልና ወደ ተራራው ወጥተህ በእግዚአብሔር ፊት ቁም" አለው።

ከዚያም ታላቅና ኀይለኛ ነፋስ ተራሮቹን ሰንጣጠቀ፤ አለቶችንም በእግዚአብሔር ፊት ብትንትናቸውን አወጣ፤ እግዚአብሔር ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም፤ ከነፋሱም ቀጥሎ የምድር መነዋወጥ ሆነ፤ እግዚ አብሔር ግን በምድር መነዋወጡ ውስጥ አልነበረም። 12ከምድር መነዋወጡም ቀጥሎ እሳት መጣ፤ እግዚአብሔር ግን በእሳቱ ውስጥ አልነበረም፤ ከእሳቱም ቀጥሎ ለስለስ ያለ ድምፅ ተሰማ። 13ኤልያስም ይህን ሲሰማ፣ ፊቱን በመጐናጸፊያው ሸፍኖ ወጣና በዋሻው ደጃፍ ቆመ።

ከዚያም፣ "ኤልያስ ሆይ፤ እዚህ ምን ታደርጋለህ?" የሚል ድምፅ ሰማ።

14እርሱም፣ "እኔ ሁሉን ለሚችል ጌታ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ፤ እስራኤላውያን ኪዳንህን ትተዋል፤ መሠዊያዎችህን አፍርሰዋል፤ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና። የቀረሁት እኔ ብቻ ነኝ፤ አሁንም እኔን ለመግደል ይፈልጋሉ" አለ።

15እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤ "በመጣህበት መንገድ ተመልሰህ ወደ ደማስቆ ምድረ በዳ ሂድ፤ እዚያ ስትደርስም አዛሄልን በሶርያ ላይ እንዲነግሥ ቅባው። 16እንዲሁም የናሜሲን ልጅ ኢዩን በእስራኤል ላይ እንዲነግሥ ቅባው፤ ደግሞም ነቢይ ሆኖ በእግርህ እንዲተካ የአቤል ምሖላን

19፥5 ዘፍ16፥7፣ 28፥11
19፥8 ዘፀ34፥1፣ 24፥18፣ ማቴ4፥2
19፥9 ዘፍ3፥9፣ ዘፀ33፥22
19፥10 ሥኖ25፥13፣ ዘጸ31፥16፣ 1ነገ18፥22፡30፣ ኤር5፥11፣ 9፥2፣ ሐሥ22፥3፣ ሮሜ11፥13፣ ገላ4፥18
19፥11 ዘፀ14፥21፣ 33፥19፣ 34፥2፣ 2ነገ2፥1፣ ናሆ1፥6፣ ማቴ17፥13
19፥12 ሶፎ11፥1፣ ዘፀ3፥2፣ 1ሳሙ14፥6፣ ኢዮ4፥16፣ ዘካ4፥6፣ 2ቆሮ12፥9
19፥13 ዘፀ3፥6
19፥14 1ነገ18፥22፣ ሮሜ11፥3
19፥15 2ነገ8፥7-15
19፥16 ሶፎ21፥1፣ መሳ7፥22፣ 2ነገ2፥1፣ 3፥11፣ 9፥6

19፥5 አንድ መልአክ ነካ አደረገውና፤ እግዚአብሔር ተስፋ የቁረጠውን ኤልያስን፣ ችግሩን በመረዳትና በመንከባከብ ቀረበው (ከዕብ 4፥14-15 ጋር ያነጻጽሩ)፥ (1) ኤልያስ እንዲተኛ ፈቀደለት (ቊ 5-6)፥ (2) ምግብ እንዲመገብ አደረገው (ቊ 5-7)፥ (3) አስፈሪ ኀይሉንና ሀልዎቱን በመግለጥ ጐበኘው (ቊ 11-13)፥ (4) ተጨማሪ ራእይና መመሪያ ሰጠው (ቊ 15-18)። (5) ቅን መንፈስ ያለው ታማኝ ተተኪውን ሰጠው (ቊ 16፥9-21)። ይህም የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ልጆች እግዚአብሔር ባስቀመጣቸው ስፍራ እያሉ ተስፋ በሚቈርጡበት ጊዜ፣ ላሉበት ሁኔታ ብቁ ሆነው ይገኙ ዘንድ ጥንካሬን፣ ጸጋንና ብርታትን እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ በክርስቶስ በኩል መጠየቅ ይችላሉ (ዕብ 2፥18፥ 3፥6፥ 7፥25 ይመ)።

19፥8 አርባ ቀንና አርባ ሌሊት፤ አንዳንዶች ይህን ሙሴ (ዘፀ 34፥28) እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ (ማቴ 4፥2) ካሳለፉት የጾም ወቅት ጋር አንድ በማድረግ የረኀሩም ጾም ምሳሌ አድርገው ያቀርቡታል፥ ይሁን እንጅ እነዚህ ሦስቱ የጾሙት ጾም የተለየ ነበር። ሙሴ በእግዚአብሔር ሀልዎት በደመናው ውስጥ ዲበ ተፈጥሮአዊ በሆነ ኀይል ተደግፎ ነበር፥ ኤልያስ ለአርባ ቀናት ሙሉ ብርታት የሚሰጡት፣ ዲበ ተፈጥሮአዊ መብሎች ተሰጥተውት ነበር (ቊ 6-8)። ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ወደ ምድረበዳ ተወስዶ ስለነበር፣ አርባው ቀናት እስከሚያበቁ ድረስ አፈተራበም (ማቴ 4፥2 ማብ፥ 6፥10 ማብ ይመ)።

19፥11 እግዚአብሔር በዚያ ያልፋልና፤ እግዚአብሔር የኤልያስን እምነት ለማጠንከርና ለማበረታታት በኮሬብ ተራራ ጐበኘው (ይህም የመገለጥ ተራራ የሆነው የሲና ተራራ ነው)። ይህም ጕብኝት በኀይለኛ ነፋስ፣ በምድር መነዋወጥና በእሳት የታጀበ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ግን በእነዚህ ከሥተቶች በአንዳቸውም ውስጥ አልነበረም፥ ይልቁንም የእግዚአብሔር መገለጥ እውን የሆነው፣ "ለስለስ ባለ ድምፅ" ውስጥ ነበር። የእግዚአብሔር ሥራ የሚጓዘውና የሚያድገው፣ "ዲበመንፈሴ እንጂ በኀይልና በብርታት አይደለምጂ ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት" (ከዘካ 4፥6 ጋር ያነጻጽሩ) በሚለው ቃል እንደሆነ ኤልያስ አስተዋለ። እግዚአብሔር ነቢዩንም ሆነ ታማኝ ሕዝቡን አልተወም፥ ነገር ግን በመንፈሱና በዘላለማዊ ቃሉ ቤዛነትን፣ ጽድቅንና የዘላለምን ድኅነትን ያመጣል።

19፥16 በእግርህ እንዲተካ ... ኤልሳዕን ቅባው፤ ኤልሳን ተተኪው ይሆን ዘንድ እንዲቀባው እግዚአብሔር ኤልያስን መራው። በየተመደበላቸው የሥራ ኀላፊነት የሚቀቡት ካህናትና ነገሥታት ብቻ ሳይሆኑ፣ ነቢያትም ጭምር እንደ ሆኑ እዚህ ላይ ማስተዋል ተገቢ ነው። ኤልሳዕም (1) ኤልያስን ማገልገል ነበረበት፥ (2) የሶርያን ንጉሥ አዛሄልንና የእስራኤልን ንጉሥ ኢዩን የእግዚአብሔርን ጠላቶች ያሸንፉ ዘንድ ማገዝ ነበረበት (ቊ 16-17)፥ (3) ታማኝ ለሆኑት ትሩፋን የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ ነበረበት (ቊ 18)። የኤልያስና የኤልሳዕ የአገልግሎት ዘመን 75 ዓመት ያህል ይሸፍናል (ከ875—800 ዓ.ክ.ል. ሲሆን፣ ይኸውም በአክዓብ፣ በአካዝያስ፣ በኢዮራም፣ በኢዩ፣ በኢዮአካዝና በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ማለት ነው)። በዕድሜ ለገፋው ነቢይ ኤልሳዕ ታማኝ አገልጋይ ነበር፥ "የኤልያስን እጅ ያስታጥብ የነበረው" በመባልም ይታወቅ ነበር (2ነገ 3፥11)።

ሰው የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ቅባው።
17ከአዛሄል ሰይፍ ያመለጠውን ኢዩ
ይገድለዋል፤ ከኢዩ ሰይፍ ያመለጠውን
ደግሞ ኤልሳዕ ይገድለዋል። 18እኔም
ጒልበታቸው ለበኣል ያልተንበረከከውንና
አፋቸው ምስሉን ያልሳመውን ሰባት ሺህ
ሰዎች በእስራኤል አስቀራለሁ።"


የኤልሳዕ መጠራት

19ስለዚህ ኤልያስ ከዚያ ተነሥቶ ሲሄድ
የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ፀሥራ ሁለት
ጥማድ በሬ አውጥቶ ራሱ በሁሥራ ሁለተኛው
ጥማድ ኽሬ ሲያርስ አገኘው። ኤልያስም
ወደ እርሱ መጥቶ መጕናጸፊያውን በላዩ
ጣለበት። 20ከዚያም ኤልሳዕ በሬዎቹን ትቶ
ኤልያስን ተከትሎ እየሮጠ፣ "አባቴንና
እናቴን ስሜ እንድሰናበታቸው ፍቀድልኝ፤
ከዚያም እከተልሃለሁ" አለው።
ኤልያስም መልሶ፣ "እኔ ምን ያደረግሁህ

19፥17
2ነገ8፥12;29፥
10፥32፤ 12፥17፤
13፥3;7;22፤
ኤር48፥44፤
አሞ1፥4
19፥18
ሆሴ13፥2፤
ሮሜ11፥4
19፥19
ዘፍ41፥42፤
2ነገ2፥8;14፤

19፥20 ሉቃ9፥61

19፥18 **ሰባት ሺህ ሰዎች በእስራኤል**፤ በእስራኤል ለባአል ያልተንበረከኩት ሰባቱ ሺህ ሰዎች፣ ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ክህደትን፣ ተመሳስሎ መኖርንና የዚህን ዓለም ምኞት አሸንፈው በፍቅር፣ በእምነት፣ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ በመታዘዝ ጸንተው የተገኙት ሁሉ ከእነዚሁ ጋር ናቸው። እነርሱ በዘሁ ዓለም ክፋት መጠመድን እንቢ ያሉ፣ ልብሳቸውን በበጉ ደም በማጠብ አንደ በረዶ ያነጹ ናቸው (ራእ 7፥14)። እነርሱ ስለ ጽድቅ ተሰደዋል (ማቴ 5፥10፣ እስከ ዘላቂታውም በቀጭኑ መንገድ ላይ ተገኝተዋል (ማቴ 7፥14 እንዲሁም በገጽ 1826 ላይ፣ «*የአማኞች መለያዎች*» በሚል ርእስና በገጽ 2022 ላይ፣ «*ክርስቲያን ክዓለም ጋር ያለው ግንኙነት*» በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ)። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በጌታ የሚታወቁት ታማኞችና አሸናፊ የሆኑት ትሩፋን ብቻ ናቸው (2ጢሞ 2፥19)። እግዚአብሔር በጎያል ክንዱ በእምነት እንደሚጠብቃቸው ቃል ገብቶላቸዋል (1ጴጥ 1፥5)፣ በጉም ወደ ሰማይ ቤታቸው ይመራቸዋል (ራእ 7፥17)።



© 1991 The Zondervan Corporation

ነገር አለ? ልትመለስ ትችላለህ" አለው።
[21]ስለዚህም ኤልሳዕ ትቶት ተመለሰ። ሁለቱን በሬዎቹን ወስዶ ዐረደ፤ የዕርሻ ዕቃውን እንድዶ ሥጋቸውን በመቀቀል ለሕዝቡ ሰጠ፤ እነርሱም በሉ። ከዚያም ኤልያስን ለመከተል ሄደ፤ ረዳቱም ሆነ።

ቤን ሀዳድ ሰማርያን ወጋ

20 በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ቤን ሀዳድ መላ ሰራዊቱን በእንድነት አሰባሰበ፤ ከእርሱም ጋር ሠላሳ ሁለት ነገሥታት ከነፈረሶቻቸውና ከነሠረገሎቻቸው አብረውት ነበሩ፤ ወጥቶም ሰማርያን ከቦ ወጋት። [2]ወደ ከተማዪቱም መልእክተኞች በመላክ የእስራኤልን ንጉሥ አክዓብን እንዲህ አለው፤ "ቤን ሀዳድ እንዲህ ይላል፤ [3]ብርና ወርቅህ የእኔ ነው፤ የሚያማምሩት ሚስቶችህና ልጆ ችህም የእኔ ናቸው።' "
[4]የእስራኤልም ንጉሥ "ንጉሥ ጌታዬ ሆይ፤ ልክ እንዳልኸው ነው እኔም ሆንሁ የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው" ሲል መለሰለት።
[5]መልክተኞቹም እንደ ገና መጥተው እንዲህ አሉት፤ "ቤን ሀዳድ የሚለው ይህ ነው፤ 'ብርህንና ወርቅህን፣ ሚስቶችህንና ልጆችህን እንድትሰጠኝ ልኬብህ ነበር፤ ዳሆም ነገ በዚሁ ጊዜ ቤተ መንግሥትህንና የሹማምትህን ቤቶች እንዲበረብሩ፣ ሹማ ምቴን እልካቸዋለሁ። እነርሱም ግናቸውንም ለአንተ ዋጋ ያለውን ሁሉ በእጃቸው በማስገባት ይወስዱታል።' "
[7]የእስራኤልም ንጉሥ የአገሩን ሽማግሌዎች ሁሉ ጠርቶ፣ "ይህ ሰው እንዴት ጠብ እንደሚፈልግ ታያላችሁ፤ ሚስቶቼንና ልጆቼን፣ ብሬንና ወርቄን እንዳስረክበው በጠየቀኝ ጊዜ አልከለከልሁትም" አላቸው።
[8]ሽማግሌዎቹና ሕዝቡም ሁሉ፣ "የሚልህን አትቀበለው፤ የጠየቀህንም እሺ አትበለው" አሉት።
[9]ስለዚህ ለቤን ሀዳድ መልእክተኞች፣ "ለጌታዬ ለንጉሡ፣ 'እኔ ባሪያህ በመጀመሪያ ያልኸኝን ሁሉ አደርጋለሁ፤ ያሁኑን ጥያቄህን ግን ልፈጽመው አልችልም' ብላችሁ ንገሩት" አላቸው። መልእክተኞቹም ይህንኑ ይዘው ተመለሱ።
[10]ከዚያም ቤን ሀዳድ፣ "ለሚከተለኝ ሰው ሁሉ የሰማርያ ዐፈር አንዳንድ ዕፍኝ የሚዳረስ ሳይሆን ቢቀር፣ አማልክት ይህን ያድርጉብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጡብኝ" ሲል ሌሎች መልክተኞችን ወደ አክዓብ ላከ።
[11]የእስራኤልም ንጉሥ፣ "'ታጥቆ ለጦርነት የሚወጣ ሰው የጦር ትጥቁን እንደፈታ ሰው መደንፋት የለበትም' ብላችሁ ንገሩት" አላቸው።
[12]ቤን ሀዳድ ይህን መልእክት የሰማው አብረውት የነበሩት ነገሥታት በድንኳኖቻቸው" ውስጥ ሆነው በሚጠጡበት ጊዜ ነበር፤ ቤን ሀዳድ ሰዎቹን፣ "በሉ ለጦርነት ተዘጋጁ" አላቸው፤ ስለዚህ ከተማዪቱን ለመውጋት ተዘጋጁ።

አክዓብ ቤን ሀዳድን ድል አደረገ

[13]በዚያን ጊዜ አንድ ነቢይ ወደ እስራኤል ንጉሥ ወደ አክዓብ መጥቶ፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ 'ይህን ብዙ ሰራዊት ታያለህን? ዛሬ በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁ፤ ከዚያም እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃለህ' " አለው።
[14]አክዓብም፣ "ይህን የሚያደርገው ማን ነው?" ሲል ጠየቀ።
ነቢዩም፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ 'ይህን የሚያደርጉት የየአውራጃው አዛዥ የሆኑ ወጣት መኰንኖች ናቸው' " አለው።
"ታዲያ ጦርነቱን የሚጀምረው ማን ነው?" ሲል ጠየቀ።
ነቢዩም፣ "አንተው ትጀምራለህ" ብሎ መለሰ።
[15]ስለዚህ አክዓብ የየአውራጃው አዛዥ የሆኑትን ሁለት መቶ ሠላሳ ሁለት ወጣት መኰንኖች ጠራ፤ ከዚያም የቀሩትን እስራኤላውያንን ሰበሰበ፤ እነዚህም በአጠቃላይ ሰባት ሺህ ነበሩ። [16]እነርሱም ቤን ሀዳድና ከእርሱ ጋር ተባብረው የነበሩት ሠላሳ ሁለቱ ነገሥታት በድንኳኖቻቸው ውስጥ ሰክረው ሳለ እኩለ ቀን ላይ መጡ። [17]በግንባር ቀደምትነት የወጡት ግን፣ የየአውራጃው አዛዥ የሆኑት ወጣት መኰንኖች ነበሩ።
በዚህ ጊዜ ቤን ሀዳድ ሰላዮች ልኮ ነበርና እነርሱም፣ "ሰዎች ከሰማርያ ወጥተው ወደዚህ በመምጣት ላይ ናቸው" ብለው ነገሩት።
[18]እርሱም፣ "አመጣጣቸው ለሰላምም ይሁን ለጦርነት ከነሕይወታቸው ይዛችሁ አምጧቸው" አለ።
[19]የየአውራጃው አዛዥ የሆኑ ወጣት መኰንኖችም ሰራዊቱን አስከትለው ከከተማዪቱ ወጡ፤ [20]እያንዳንዱም በፊቱ የገጠመውን ጠላት ገደለ፤ ሶርያውያን ሸሹ፤ እስራኤላውያንም ያሳድዷቸው ጀመር። የሶርያ ንጉሥ ቤን ሀዳድ ግን በፈረሱ ላይ ሆኖ ከጥቂት ፈረሰኞቹ ጋር አመለጠ። [21]የእስራኤል ንጉሥ አክዓብም ወደ ፊት በመግፋት ፈረሶችንና ሠረገሎችን ማረከ፤ በሶርያውያንም ላይ ከባድ ጉዳት አደረሰባቸው።

[20:12] ወይም ሱኮት ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፤ በቍ 16 ላይም እንደዚሁ

19፥21 ዘኍ16፥ 1ሳሙ6፥14
20፥1 1ነገ13፥32፤ 15፥18
20፥7 1ሳሙ11፥3፤ 2ነገ5፥7
20፥10 2ሳሙ22፥43
20፥11 ምሳ27፥1፤ ኤር9፥23፤ ኣሞ2፥14
20፥12 1ነገ16፥9
20፥13 ዘፀ6፥7፤ መሳ6፥8
20፥14 መሳ1፥1
20፥16 1ነገ16፥9

20፥13 ... **በእጅህ አሳልፌ ... እሰጥሃለሁ፤** አክዓብና የእስራኤል ሕዝብ ታማኞች ባይሆኑም እንኳ፣ እግዚአብሔር ምሕረት አሳያቸው፣ ሰማርያንም ከሶርያውያን ሰራዊት እጅ አዳናት (ቍ 20)። ከዓመትም በኋላ ዙሮዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ፣ ከአፌቅ ከተማ አጠገብ ባለው፣ እግዚአብሔር በሶርያውያን ላይ ለእስራኤላውያን ድልን ሰጣቸው (ቍ 22-29)፤ ይሁን እንጅ አክዓብ ለእውነተኛው የእስራኤል አምላክ ለመገዛትና እርሱንም ለማምለክ እሽ አላለም።

22ከዚያም በኋላ ነቢዩ ወደ እስራኤል ንጉሥ መጥቶ፣ "በሚመጣው የጸደይ ወራት የሶርያ ንጉሥ ተመልሶ ይመጣብሃልና በርታ፤ ምን ማድረግ እንዳለብህም ዕወቅ" አለው።

23በዚያኑ ጊዜም የሶርያ ንጉሥ ሹማምት እንዲህ ሲሉ መከሩት፤ "አማልክታቸው የኰረብታ አማልክት ናቸው፤ ያየሉብንም ከዚህ የተነሣ ነው። በሜዳ ላይ ብንገጥማቸው ግን እኛ እንደምናይልባቸው አያጠራጥርም። 24እንግዲህ እንዲህ አድርግ፤ ነገሥታቱን በሙሉ ከአዛዥነታቸው አስነሣ፤ በቦታቸውም ሌሎች ሹማምት አድርግ። 25ከእስራኤል ጋር በሜዳው ላይ እንዲጋጠም በፈረሱ ፈንታ ፈረስ፣ በሠረገላው ፈንታ ሠረገላ በመተካት፣ እንደ ተደመሰሰው ያለ ሰራዊት አቋቁም፤ ከዚያ በኋላ ከእነርሱ ይበልጥ እኛ እንደምንበረታ አያጠራጥርም።" ንጉሡም ባቀረቡት ሐሳብ ተስማማ፤ እንዳሉትም አደረገ።

26በተከታዩም የጸደይ ወራት ቤን ሀዳድ ሶርያውያንን አሰባስቦ እስራኤልን ለመውጋት ወደ አፌቅ ወጣ። 27እስራኤላውያንም እንደዚሁ ተሰብስበው ስንቅ ከተሰጣቸው በኋላ ሊገጥሟቸው ተሰልፈው ወጡ። ሶርያውያን አገር ምድሩን ሞልተውት ሳለ፣ እስራኤላውያን ግን እንደ ሁለት ትናንሽ የፍየል መንጋ ሆነው ከፊት ለፊታቸው ሰፈሩ።

28የእግዚአብሔርም ሰው ወጥቶ ለእስራኤል ንጉሥ፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ 'ሶር ያውያን እግዚአብሔር የኰረብታ እንጂ የሸለቆ አምላክ አይደለም ብለዋልና ይህን ስፍር ቊጥር የሌለው ሰራዊት በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁ፤ አንተም እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃለህ' " አለው።

29በየሰፈሩበትም ቦታ ሰባት ቀን ከተፋጠጡ በኋላ በሰባተኛው ቀን ጦርነት ገጠሙ። እስራኤላውያንም በአንዲት ጀምበር ከሶርያውያን ሰራዊት መቶ ሺህ እግረኛ ገደሉ። 30የቀሩት ወደ አፌቅ ከተማ ሸሹ፤ በዚያም በሃያ ሰባቱ ሺህ ላይ ቅጥሩ ተንዶ ወደቀባቸው። ቤን ሀዳድም ወደ ከተማዪቱ ሸሽቶ በመሄድ ወደ አንዲት እልፍኝ ገብቶ ተደበቀ።

31ሹማምቱም፣ "የእስራኤል ቤት ነገሥታት መሓሪዎች መሆናቸውን ሰምተናል፤ አሁንም እንኑሣና በወገባችን ላይ ማቅ ታጥቀን፣ በራሳችን ላይ ገመድ ጠምጥመን ወደ እስራኤል ንጉሥ እንሂድ፤ ምናልባትም ሕይወትህን ያተርፋት ይሆናል" አሉት።

32እነርሱም በወገባቸው ላይ ማቅ ታጥቀው፣ በራሳቸው ላይ ገመድ ጠምጥመው ወደ እስራኤል ንጉሥ በመሄድ፣ "አገልጋይህ ቤን ሀዳድ፣ 'እባክህ በሕይወት እንድኖር ፍቀድልኝ' ብሎ ይለምንሃል" አሉት።

ንጉሡም፣ "እስካሁን በሕይወት አለን? ወንድሜ እኮ ነው" አለ።

33ሰዎቹም ይህን በደግ በመተርጐም ቃሉን ከአፋ ቀበል አድርገው፤ "አዎን ቤን ሀዳድ ወንድምህ ነው" አሉት።

ንጉሡም፣ "በሉ ሂዱና አምጡት" አላቸው፤ ቤን ሀዳድም በመጣ ጊዜ፣ አክዓብ ሠረገላው ላይ እንዲወጣ አደረገው።

34ቤን ሀዳድም፣ "አባቴ ከአባትህ የወሰዳቸውን ከተሞች እመልሳለሁ፤ አባቴ በሰማርያ እንዳደረገው ሁሉ፣ አንተም በደማስቆ የራስህን ገበያ ማቋቋም ትችላለህ" አለው።

አክዓብም፣ "እንግዲያውስ ስምምነት አድርገን በነጻ እለቅሃለሁ" አለው፤ ስለዚህም ከእርሱ ጋር የውል ስምምነት አድርጎ ለቀቀው።

አንድ ነቢይ በአክዓብ ላይ ፈረደ

35ከነቢያት ልጆች አንዱ ጓደኛውን በእግዚአብሔር ቃል ታዞ፣ "ምታኝ" አለው፤ ሰውየው ግን ፈቃደኛ አልሆነም።

36ስለዚህም ነቢዩ፣ "ለእግዚአብሔር ባለ መታዘዝህ፣ ከእኔ ተለይተህ እንደ ሄድህ አንበሳ ይገድልሃል" አለው። ሰውየው ከሄደ በኋላ አንበሳ አግኝቶ ገደለው።

37ነቢዩም ሌላ ሰው እግኝቶ፣ "እባክህ ምታኝ" አለው። ስለዚህ ያ ሰው መትቶ አቁሰለው። 38ከዚያም ነቢዩ ሄዶ ከመንገድ ዳር በመቆም፣ ንጉሡን ይጠባበቅ ጀመር። የራሱን መጠምጠሚያ ወደ ታች አውርዶ ዐይኖቹን በመሸፈንም፣ ማንነቱ እንዳይታወቅ አደረገ። 39ንጉሡ በዚያ በሚያልፍበትም ጊዜ፣ ነቢዩ ጠርቶት እንዲህ አለው፤ "እኔ አገልጋይህ በተፋፋመው ጦርነት መካከል ገብቼ ሳለሁ፣ አንድ ሰው ምርኮኛ ይዞ መጥቶ 'ይህን ሰው ጠብቅ፤ ቢያመልጥ በገመዱ ትገባለህ ወይም አንድ መክሊት[ሸ] ብር ትከፍላለህ' አለኝ። 40ዐ ታዲያ እኔ አገልጋይህ ሥራ በዝቶብኝ ወዲያ ወዲህ ስል ሰውየው አመልጠ ሄደ።' "

የእስራኤልም ንጉሥ፣ "ራስህ ፈርደሃል፤ ይኸው ይፈጸምብሃል" አለው።

41ከዚያም ነቢዩ መጠምጠሚያውን በፍጥነት ከዐይኑ ላይ አነሣ፤ የእስራኤልም ንጉሥ ያ ሰው ከነቢያት አንዱ መሆኑን ዐወቀ። 42ነቢዩም ንጉሡን አለው፤ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ 'እኔ ፈጽሞ ይገደል[ሀ] ያልሁትን ሰው ለቀኸዋልና በገመዱ

20+22 መሳ6፥8፤ 2ሳሙ11፥1
20+23 ሞ28፥ ኢሳ36፥20፤ ሮሜ1፥21-23
20+26 ሞ30፥ 1ሳሙ4፥1፤ 2ሳሙ11፥1፤ 2ነገ13፥17
20+27 መሳ6፥6፤ 1ሳሙ13፥6
20+28 ሞ23፥ ዘፀ6፥7፤ ኤር16፥19-21
20+30 ሞ26፥ 1ነገ22፥25፤ መዝ62፥4፤ ኢሳ26፥21፤ 30፥13
20+31 ዘፍ37፥34፤ ኢዮ41፥3
20+34 ዘፍ10፥22፤ 14፥15፤ ዘፀ23፥32፤ 2ሳሙ8፥6፤ 1ነገ15፥20፤ ኤር49፥23-27
20+35 1ሳሙ10፥5፤ 1ነገ13፥21፤ አሞ7፥14
20+36 1ነገ13፥24
20+39 ኢሱ2፥14
20+40 2ሳሙ12፥5፤ 14፥13
20+42 ኢሱ2፥14፤ 2ሳሙ12፥7፤ ኤር48፥10

*20+39 34 ኪሎ ግራም ያህል ነው

[ሀ]20+42 የዕብራይስጡ ቃል ሰውን ወይም ሞስን ፈጽሞ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት የሚለውን ያመለክታል

20+35 ከነቢያት ልጆች አንዱ፤ እነዚህ እጅግ ዝና በነበራቸውና በዕድሜ በጉፋ እንደ ኤልሳዕ ባሉ ነቢያት ደቀ መዘመርት የሆኑ ተማሪዎች ናቸው (ከ1ነገ 2+3:5:7:15፥ 4+1:38፥ 5+22፥ 6+1፥ 9+1 ጋር ያነጻጽሩ)። መምህራን ከሆኑት ነቢያት ጋር ጥብቅ የሆነ ኅብረት በመመሥረትና የበላል አምልኮን በመቃወም ለእግዚአብሔር አምላክ መታዘዝን አራመዱ። በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ትንቢት በመናገራቸው ይታወቁ ነበር።

ትግ ባለህ፤ በሕዝቡም ፊንታ ያንተ ሕዝብ በገመዱ ይገባል።" 43የእስራኤልም ንጉሥ ተበሳጭቶና ተቈጥቶ ሰማርያ ወዳለው ቤተ መንግሥቱ ሄደ።

የናቡቴ የወይን ተክል ቦታ

21 ከጥቂት ጊዜ በኋላ በኢይዝራኤላዊው በናቡቴ የወይን ተክል ቦታ ላይ አንድ ነገር ደረሰ፤ ቦታውም በኢይዝራኤል ውስጥ ከሰማርያ ንጉሥ ከአክዓብ ቤተ መንግሥት አጠገብ ነበር። 2አክዓብም ናቡቴን፣ "የወይን ተክል ቦታህ ከቤተ መንግሥቴ አጠገብ ስለ ሆነ፣ የአትክልት ቦታ እንዳደርገው ልቀቅልኝ፤ በምትኩ ከዚህ የበለጠ የወይን ተክል ቦታ እሰጥሃለሁ፤ የተሻለ ሆኖ ከቦታህም የሚያወጣውን ገንዘብ እከልሃለሁ" አለው።

3ናቡቴ ግን፣ "ዐፅመ ርስቴን አለቅልህ ዘንድ እግዚአብሔር አይበለው" ሲል መለሰለት።

4ኢይዝራኤላዊው ናቡቴ፣ "ዐፅመ ርስቴን አልለቅልህም" ስላለው፣ አክዓብ ተበሳጭቶና ተቈጥቶ ወደ ቤቱ ገባ፤ እኮርፎም በዐልጋው ላይ ተኛ፤ ምግብም መብላት ተወ።

5ሚስቱ ኤልዛቤልም ወደ እርሱ ገብታ፣ "እስከዚህ የተበሳጨኸው፣ ምግብስ የማፐበላው ለምንድን ነው?" ብላ ጠየቀችው።

6እርሱም፣ "ኢይዝራኤላዊውን ናቡቴን፣ 'የወይን ተክል ቦታህን ሸጥልኝ፤ ከፈለግህም በምትኩ ሌላ የወይን ቦታ እሰጥሃለሁ' አልሁት፤ እርሱ ግን፣ 'የወይን ተክል ቦታዬን አልለቅልህም' ስላለኝ ነው" አላት።

7ሚስቱ ኤልዛቤልም፣ "አንተ አሁን የእስራኤል ንጉሥ ትባላለህ? በል ተነሥና እህል ቅመስ፤ ደስም ይበልህ፤ የኢይዝራኤላዊ ውን የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ እኔ እንድታገኝ አደርግሃለሁ" አለችው። 8ስለዚህ በአክዓብ ስም ደብዳቤዎች ጻፈች፤ በገዛ ማኅተሙም አትማ በናቡቴ ከተማ አብረውት ለሚኖሩ ሽማግሌዎችና መኳንንት ላከች። 9በደብዳቤዎቹም ላይ እንዲህ ስትል ጻፈች፤

"የአንድ ቀን ጾም ዐውጁ፤
ናቡቴንም በሕዝቡ መካከል ከፍ
ባለ ቦታ ላይ አስ ቀምጡት።
10እንዲሁም ሁለት የሐሰት
ምስክሮች ከፊት ለፊቱ
አስቀምጡና፣ 'ንግሥቲቱንም
ንጉሡንም ሰድቦአል' ብለው
ይመስክሩበት፤ ከዚያም
አውጥታችሁ በድንጋይ ወግራችሁ
ግደሉት።"

11ስለዚህ በናቡቴ ከተማ የሚኖሩ ሽማግሌዎችና መኳንንት በደብዳቤዎቹ ላይ እንደ ጻፈችላቸው አደረጉ። 12የአንድ ቀን ጾም ዐወጁ፤ ናቡቴንም በሕዝቡ መካከል ከፍ ባለ ቦታ ላይ አስቀመጡት። 13ከዚያም ሁለት የሐሰት ምስክሮች መጥተው ከፊት ለፊቱ ተቀመጡ፤ በሕዝቡም ፊት፣ "ናቡቴ ንግሥቲቱንና ንጉሡን ሰድቦአል" ብለው መሰከሩበት። ስለዚህ ከከተማዪቱ ውጭ ወስደው በድንጋይ ወግረው ገደሉት። 14"ከዚያም ለኤልዛቤል፣ "ናቡቴ በድንጋይ ተወግሮ ሞቶአል" ብለው ላኩባት።

15ኤልዛቤልም በድንጋይ ተወግሮ መሞቱን ወዲያው እንደ ሰማች አክዓብን፣ "ናቡቴ በድንጋይ ተወግሮ ሞቶአል፤ በል ተነሣና ኢይዝራኤላዊው ናቡቴ ሊሸጥልህ ያልፈለገውን የወይን ተክል ቦታ በርስትነት ውሰደው" አለችው። 16አክዓብ የናቡቴን ሞት ሲሰማ የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ በርስትነት ለመያዝ ተነሥቶ ወረደ።

17ከዚያም የእግዚአብሔር ቃል ወደ ቴስብያዊው ወደ ኤልያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ 18"ተነሣና በሰማርያ ሆኖ የሚገዛውን የእስራኤልን ንጉሥ አክዓብን ትግናኝ ዘንድ ውረድ፤ የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ በርስትነት ለመያዝ ሄዶ አሁን እዚያው ይገኛል። 19እንዲህም በለው፤ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ሰውየውን ገደልኸው፤ ደግሞ ርስቱን ልትወስድ? ከዚያም እንዲህ በለው፤ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ቦታ የአንተንም ደም ውሾች እንዲሁ ይልሱታል!' "

20አክዓብም ኤልያስን፣ "ጠላቴ ሆይ አገኘኸኝን?" አለው።

ኤልያስም መልሶ እንዲህ አለው፤ "በእግዚአብሔር ፊት የተጠላውን ነገር ለማድረግ ራስህን ሸጠሃልና አዎን አግኝቼሃለሁ። 21እነሆ ክፉ ነገር አመጣብሃለሁ፤ ዘርህን ፈጽሜ አጠፋለሁ፤ ባሪያም ይሁን ነጻ እያንዳንዱን የአክዓብን የመጨረሻ ወንድ ልጅ ከእስራኤል

20፡43 1ነገ21፡4
21፡1 1ሳሙ29፡1፡ 2ነገ9፡21፡ 10፡1
21፡3 ዘሌ25፡23
21፡4 1ሳሙ28፡23፡ 1ነገ20፡43
21፡7 1ሳሙ8፡14
21፡8 ዘፍ38፡18፡ 2ሳሙ11፡14
21፡10 ዘፀ22፡28፡ ዘሌ24፡1516፡ ዘዳ13፡13፡ ሐሥ6፡11
21፡12 ኢሳ58፡4
21፡13 ዘሌ24፡16
21፡15 1ሳሙ8፡14
21፡19 1ነገ22፡38፡ 2ነገ9፡26፡ ኢዮ24፡6፡ 31፡39፡ መዝ9፡12፡ 68፡23፡ ኢሳ14፡20፡ ኤር15፡3
21፡20 1ነገ18፡17፡ 2ነገ17፡17፡ ሮሜ7፡14
21፡21 ዘዳ32፡36፡ መሳ9፡5፡ 2ነገ10፡7

21፡17 የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤልያስ ... መጣ፤ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ያለውን ኢፍትሐዊነት ይጠላል። በደል በሌለበት በናቡቴ ላይ ባደረሱት ጥፋት አክዓብና ኤልዛቤል ሥቃይ እንደሚደርስባቸው ኤልያስ ትንቢት ተናገረ (ቊ 17-19)። የእግዚአብሔር መርሕ የሆኑት ሚለትም ሁሉም ባጠፋው መቀጣቱና ፍትሕን የማግኘቱ ጉዳይ በአዲስ ኪዳንም የተጠበቁ ናቸው። ለምሳሌም፣ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "ብደለኛውም የእጁን ያገኛል፤ አድልዎም የለም" ብሎአል (ቈላ 3፡25 እና ማቅ ይመ)። የእግዚአብሔር ሰዎች እርስ በርሳቸው በጽድቅ (በፍትሕ)፣ በእኩልነትና በምሕረት መተሳሰብ አለባቸው (ሚክ 6፡8፡ ቈላ 4፡1 ይመ፤ ከገላ 6፡7 ጋር ያነጻጽሩ)።

21፡19 የአንተንም ደም ውሾች እንዲሁ ይልሱታል፤ አክዓብ በጦርነት ሲሞት ይህ ትንቢት ተፈጸመ፤ ይኸውም ከነበረበት ሠረገላ ላይ ታጥቦ የወረደውን ደም ውሾች በላሱት ጊዜ ነበር (22፡35፡38)። የአክዓብ ወንድ ልጆችም የሞቱት ዘግናኝ ሞት ነበር፤ አካዝያስ ወድቆ ስለነበረ ታመመ፤ ከጊዜም በኋላ ሞተ (2ነገ 1፡2፡17)። ኢዮራም በኢዩ ከተገደለ በኋላ፣ ሬሳው በናቡቴ እርሻ ላይ እንዲወድቅ ተደረገ (2ነገ 9፡22-26)። የአክዓብ ሚስት ኤልዛቤልም የሞተችው ዘግናኝ ሞት ነበር (2ነገ 9፡30-37 ይመ)።

እጠርጋለሁ። 22ለቅጣ ስላነሣሣኸኝና እስራኤልንም ስላሳትሃቸው ቤትህን እንደ ናባጥ ልጅ እንደ ኢዮርብዓም ቤተ፣ እንደ አኪያም ልጅ እንደ ባኦስ ቤት አደርገዋለሁ።'

23"ስለ ኤልዛቤልም እግዚአብሔር፣ 'በኢይዝራኤል ቅጥር አጠገብ ውሾች ኤልዛቤልን ይበሏታል' ይላል።

24"ደግሞም ከአክዓብ ወገን ሆኖ በከተማ የሞተውን ውሾች ይበሉታል፤ በገጠር የሞተውንም የሰማይ አሞሮች ይበሉታል።"

25በሚስቱ በኤልዛቤል ተገፋፍቶ በእግዚአብሔር ፊት ክፋ ለማድረግ ራሱን የሸጠ እንደ አክዓብ ያለ ሰው ከቶ አልነበረም። 26እግዚአብሔር ከእስራኤል ፊት ያሳደዳቸው አሞራውያን እንዳደረጉት ሁሉ፣ እርሱም ጣዖታትን በማምለክ እጅግ የሚያስጸይፍ ርኩሰት ፈጸመ።

27አክዓብም ይህን ቃል ሲሰማ ልብሱን ቀደደ፤ ማቅ ለብሶ፤ ጾመ፤ በማቅ ላይ ተኛ በሐዘን ዝርምት ብሎም ይሄድ ነበር።

28ከዚያም እንዲህ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ ቴስብያዊው ወደ ኤልያስ መጣ፤ 29"አክዓብ ራሱን በፊቴ እንዴት እንዳዋረደ አየህን? ራሱን ስላዋረደ ይህን መከራ በዘመኑ አላመጣበትም፤ ነገር ግን ይህን በቤቱ ላይ የማመጣው በልጁ ዘመን ነው።"

ሚክያስ በአክዓብ ላይ ትንቢት ተናገረ

22፥1-28 ተጓ ምብ — 2ዜና 18፥1-27

22 በሶርያና በእስራኤል መካከል ለሦስት ዓመት ጦርነት አልነበረም። 2በሦስተኛው ዓመት ግን የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ የእስራኤልን ንጉሥ ለመጐብኘት ወረደ። 3የእስራኤልም ንጉሥ ሹማምቱን፣ "በገለዓድ የምትገኘው ራማት የእኛ ሆና ሳለች፣ ከሶርያው ንጉሥ እጅ ለመመለስ ምንም እንዳላደረግን አታውቁምን?" አላቸው።

4ስለዚህ ኢዮሣፍጥን፣ "በገለዓድ የምትገኘው ራማት ላይ ለመዝመት አብረኸኝ ለመሄድ ትፈቅዳለህን?" ሲል ጠየቀው።

ኢዮሣፍጥም፣ "እኔ ያው እንደ አንተው ነኝ፤ ሕዝቤ እንደ ሕዝብህ፣ ፈረሶቼም እንደ ፈረሶችህ ናቸው" አለ። 5ኢዮሣፍጥም የእስራኤልን ንጉሥ፣ "በመጀመሪያ ግን የእግዚአብሔርን ሐሳብ ጠይቅ" አለው።

6ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ አራት መቶ ነቢያትን በአንድነት ሰብስቦ፣ "በገለዓድ በምትዋጉት ራማት ላይ ልዝመት ወይስ ልተውኍ" ሲል ጠየቃቸው።

እነርሱም፣ "እግዚአብሔር በንጉሡ እጅ አሳልፎ ይሰጣታልና ዝመትባት" አሉት።

7ኢዮሣፍጥ ግን፣ "የምንጠይቀው የእግዚአብሔር ነቢይ እዚህ የለምን?" አለ።

8የእስራኤልም ንጉሥ ለኢዮሣፍጥ፣ "መኖሩንማ በእርሱ አማካይነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምንጠይቀው አንድ ሰው አሁንም አለ፤ ነገር ግን ምን ጊዜም ቢሆን ስለ እኔ ክፉ እንጂ አንዳችም መልካም ትንቢት ተናግሮ ስለማያውቅ እጠላዋለሁ፤ ይህም ሰው የይምላ ልጅ ሚክያስ ነው" አለ።

ኢዮሣፍጥም፣ "ንጉሡ እንዲህ ማለት አይገባውም" ሲል መለሰ።

9ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ ከሹማምቱ አንዱን ጠርቶ፣ "በል የይምላን ልጅ ሚክያስን በፍጥነት አምጣው" አለው።

10የእስራኤል ንጉሥና የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ እልባሰ መንግሥታቸውን ልብሰው፣ በሰማርያ ቅጥር በር አጠገብ ባለው አውድማ ላይ በየዙፋናቸው ተቀምጠው ሳለ፣ ነቢያቱ ሁሉ ፀፈታቸው ትንቢት ይናገሩ ነበር።

11በዚህ ጊዜ ሴዴቅያስ የተባለው የክንዓና ልጅ የብረት ቀንዶች አበጅቶ፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ 'ሶርያውያን እስኪጠፉ ድረስ የምትወጋቸው በእነዚህ ነው' " አለው።

12የቀሩትም ነቢያት ሁሉ፣ "እግዚአብሔር በንጉሡ እጅ አሳልፎ ይሰጣታልና በገለዓድ የምትገኘውን ራማትን ወግተህ ድል አድርግ" በማለት በአንድ ቃል ትንቢት ይናገሩ ነበር።

13ከዚያም ሚክያስን ሊጠራ የሄደው መልእክተኛ፣ "እነሆ፤ ሌሎቹ ነቢያት ንጉሡ ድል እንደሚያደርግ በአንድ ቃል ትንቢት እየተናገሩለት ነውና ያንተም ቃል ከእነርሱ ጋር አንድ እንዲሆን እባክህ መልካም ነገር ተናገር" አለው።

14ሚክያስ ግን፣ "ሕያው እግዚአብሔርን! ለእርሱ የምነግረው እግዚአብሔር የነገረኝን ብቻ ነው" አለ።

22፥6 መሳ18፥6፤ 1ነገ13፥18
22፥7 ዘጐሩ27፥21፤ ዘዳ18፥15፤ 1ነገ3፥11፤ 5፥8
22፥8 ሶ 13፤ ኢሳ5፥20፤ 30፥10፤ ኤር23፥17፤ አሞ5፥10
22፥11 ሶ 24፤ ዘኍ33፥17፤ ኤር27፥2፤ 28፥10፤ ዘካ1፥8-21
22፥13 ሶ 8
22፥14 ዘጐሩ22፥18፤ 1ሳሙ3፥17

ˢ21፥23 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፡ ነገር ግን አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ ቩልጌትና የሱርስቱ ትርጒም (2ነገ9፥26 ይመ) በዕርሻው ማሳ ላይ ይላሉ

21፥25 **ኤልዛቤል**፤ የክፉዋ የአክዓብ ሚስት ዓላማ በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን እምነት ከሥር መሠረቱ ነቅላ፣ በምትኩ የጢሮስን አምላክ በአልን ዋና የእስራኤል አምላክ በማድረግ መትከል ነበር፤ ሆኖም ሳይሳካላት ቀረ። ከዚህ የተነሣ ስሟ ከክፋት፣ ከጥንቆላ፣ ከክህደትና ከመንፈሳዊ መታለል ጋር ተመሳሳይ ትርጒም ያለው ቃል ሆነ። ሐዋርያው ዮሐንስ በትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን የነበሩትን የእግዚአብሔር ሰዎች ወደ ርኩሰትና ዓለማዊነት ስትመራ የነበረችውን ሐሰተኛ ነቢይ በኤልዛቤል ስም ጠርቶአታል (ራእ 2፥20 እና ማብ ይመ)።

22፥6 **አራት መቶ ነቢያትን**፤ እነዚህ አራት መቶ የአክዓብ ነቢያት (22-23 ይመ)፡ የእግዚአብሔር እውነተኛ ነቢያት ሳይሆኑ፣ ንጉሡ መስማት የሚፈልገውን ብቻ የሚናገሩ የሃይማኖት ሰዎች ነበሩ (ከሶ 8 ጋር ያነጻጽሩ፥ በገጽ 1009 ላይ፣ "ነቢይ በብሉይ ኪዳን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

15እዚያም እንደ ደረሰ ንጉሡ፣ "ሚክያስ
ሆይ፤ በገለዓድ በምትገኘው ሬማት ላይ
እንዝመትባት ወይስ እንተው?" ሲል ጠየ
ቀው።
እርሱም፣ "እግዚአብሔር በንጉሡ
እጅ አሳልፎ ይሰጣታልና ዘምተህ ድል
አድርጋት" ብሎ መለሰለት።
16ንጉሡም፣ "ከእውነት በቀር
በእግዚአብሔር ስም እንዳች ነገር
እንዳትነግረኝ የማምልህ ስንት ጊዜ ነው?"
አለው።
17ከዚያም ሚክያስ እንዲህ ሲል መለሰ፣
"እስራኤል ሁሉ ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች
በየተራራው ላይ ተበትነው አየሁ፣ እግዚአ
ብሔርም፣ 'ይህ ሕዝብ ጌታ የለውምና
እያንዳንዱ በሰላም ወደየቤቱ ይሂድ' አለ።"
18የእስራኤልም ንጉሥ ለኢዮሣፍጥ፣ "ስለ
እኔ ክፉ ብቻ እንጂ ከቶ መልካም ትንቢት
አይናገርም አላልሁህምን?" አለው።
19ከዚያም ሚክያስ እንዲህ አለ፤
"እንግዲህ የእግዚአብሔር ቃል የሚሉትን
ስማ፤ 'እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ
ቁቀምጠ፣ የሰማይ ሰራዊት ሁሉ በቀኙና
በግራው ቆመው አየሁ፤ 20እግዚአብሔርም፣
"በገለዓድ በምትገኘው ሬማት ላይ ዘምቶ
እዚያው እንዲሞት፣ አክዓብን ማን
ያስተው?" አለ።'
"ታዲያ አንዱ ይህን፣ ሌላውም ያን
አለ፤ 21በመጨረሻም፣ 'አንድ መንፈስ
ወጣ፤ ከዚያም በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ፣
"እኔ አስተዋለዋ" አለ።'
22እግዚአብሔርም፣ 'እንዴት አድርገህ?'
ሲል ጠየቀው።
"እርሱም፣ 'እኔ እወጣለሁ፤ በገዛ
ነቢያቱም አፍ ሁሉ የሐሰት መንፈስ
እሆናለሁ' አለ።
እግዚአብሔርም፣ "በል እንግዲያው
ውጣና አስተውሪ ይሳካልሃል" አለው።
23"ስለዚህ እነሆ እግዚአብሔር በእነዚህ
ሁሉ ነቢያትህ አፍ የሐሰት መንፈስ አኖረ፤
በአንተም ላይ መዓቱን እንደሚያመጣብህ
ተናገረ።"
24ከዚያም የከንዓና ልጅ ሴዴቅያስ ወጥቶ
ሚክያስን በጥፊ መታውና፣ "ለመሆኑ
የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኔ በየት በኩል
ዐልፎ ነው አንተን መጥቶ ያናገረህ?"
ሲል ጠየቀው።
25ሚክያስም፤ "ይህንማ ለመደበቅ ወደ
አንዲት እልፍኝ በገሄድህ ዕለት ታውቀዋለህ"
አለው።
26ከዚያም የእስራኤል ንጉሥ እንዲህ
ሲል አዘዘ፤ "በሉ ሚክያስን ይዛችሁ ወደ
ከተማዪቱ ገዢ ወደ አሞንና ወደ ንጉሡ
ልጅ ወደ ኢዮአስ መልሱት፤ 27'ከዚያም፣
"ንጉሡ፤ "በደኅና እስክመለስ ድረስ፤ ይህን
ሰው በእስር ቤት አቈይቱት፤ ከደረቅ እንጀራና
ከውሃ በስተቀር ሌላ እንዳትሰጡት" ብሎአል
በሉት' አለ።
28ሚክያስም፣ "አንተ በደኅና ከተመለስህ
እግዚአብሔር በእኔ አልተናገረማ!" አለ፤
ከዚያም በመቀጠል፣ "በዚህ ያለኸው ሕዝብ
ሁሉ ይህን ቃሌን ልብ ብለህ ይዘው፤"
አለ።

አክዓብ በገለዓድ በምትገኘው በሬማት ተገደለ

22፥29-36 ተጓ ምብ — 2ዜና 18፥28-34

29ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥና የይሁዳ
ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በገለዓድ ወደምትገኘው
ሬማት ወጡ። 30የእስራኤል ንጉሥ
ኢዮሣፍጥን፣ "እንዳልታወቅ እኔ ልብስ
ለውጬና ሌላ ሰው መስዬ እገባለሁ፤ አንተ
ግን ልብሰ መንግሥትህን ልበስ" አለው።
ስለዚህ የእ ስራኤል ንጉሥ ራሱን ደብቆ
ወደ ጦርነቱ ገባ።
31በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ሠላሳ ሁለቱን
የሠረገላ አዛዦች፣ "ከራሱ ከእስራኤል
ንጉሥ በቀር ትንሽም ይሁን ትልቅ ከማንም
ጋር እንዳትገጥሙ" ሲል አዞአቸው ነበር፤
32የሠረገላ አዛዦቹ ኢዮሣፍጥን ሲያዩት፣
"ያለ ጥርጥር ይህ የእስራኤል ንጉሥ ነው"
አሉ፤ ስለዚህ አደጋ ሊጥሉበት ከበቡት፤
ኢዮሣፍጥ ሲጮህ ግን 33የሠረገላ አዛዦቹ
እርሱ የእስራኤል ንጉሥ አለ መሆኑን አው
ቀው መከታተሉን ተዉት።
34ነገር ግን አንዱ ቀስቱን ሳያልም እን
ዲሁ ሲያስፈነጥር በጦር ልብሰ መጋጠሚያ
ላይ የእስራኤልን ንጉሥ ወጋው፤ ንጉሡም
ሠረገላ ነጂውን፣ "ቈስያለሁና ወደ ኋላ
አዙረህ ከጦሩ ሜዳ አውጣኝ" አለው።
35ጦርነቱም ቀኑን ሙሉ ተፋፍሞ ዋለ፤
በዚህ ጊዜም ንጉሡ በሶርያውያን ፊት
ለፊት ሠገላው ላይ ቀና ብሎ እንደ ተደገፈ
ነበር፤ የቍስሉ ደም በሠረገላው ወለል ላይ
ይወርድ ነበር፤ በዚያኑ ዕለት ማታም ንጉሡ

22፥17 ዘፍ11፥4፣ ዘኍ27፥17፣ ኢሳ13፥14፣ ናሆ3፥18፣ ማቴ9፥36
22፥19 ኢዮ1፥6፣ 15፥8፣ 38፥7፣ መዝ47፥8፣ 103፥20-21፣ 148፥2፣ ኢሳ6፥1፣ 63፥15፣ ኤር23፥18፣22፣ ሕዝ1፥26፣ ዳን7፥9፣ ሉቃ2፥13
22፥22 መሳ9፥23፣ 2ተሰ2፥11
22፥23 ዘዳ13፥3፣ 31፥29፣ ሕዝ14፥9
22፥24 ሶፎ11፣ ኢዮ26፥4፣ ሐሥ23፥2
22፥25 1ነገ20፥30
22፥27 2ዜና16፥10፣ ኤር20፥2፣ 26፥21፣ 37፥15፣ ዕብ11፥36
22፥28 ዘዳ18፥22
22፥30 1ሳሙ28፥8
22፥31 ዘፍ10፥22፣ 2ሳሙ10፥19፣ 17፥2
22፥34 2ነገ9፥24፣ 2ዜና35፥23

22፥15 **ዘምተህ ድል አድርጋት፤** አክዓብ እንኳን እየቀለደ መናገሩን እስኪያውቅበት ድረስ (ከሥ 16 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ሚክያስ የበአልን ነቢያት ትንቢያ አስተጋብ። ከዚያም ሚክያስ የተቀበለውን ትክክለኛ የነቢያዊ ራእይ (ቍ 17) ግልጽ ማድረግ ቀጠለ። ትርጉሙ ግልጽ ነበር፣ አክዓብ ይሞታል፣ የእስራኤልም ሕዝብ በማፈግፈግ ወደ ሰፈር ይመለሳል።

22፥23 **የሐሰት መንፈስ፤** ይህ የሐሰት መንፈስ የሰይጣን መልእክተኛ ነው ተብሎ ሊታሰብ ይችላል፤ ይኸውም አክዓብንና የሐሰት ነቢያትን በጎጠኢታቸው ይኮንን ዘንድ በእግዚአብሔር የተላከ ክፉ መንፈስ ሊሆን ይችላል። እውነትን ላለመቀበል ልባቸው በመደንደኑ፣ የጎጠኢታቸውን ዋጋ ያገኙ ዘንድ እግዚአብሔር በመጨረሻ ለሐሰት አሳልፎ ሰጣቸው (ከሮሜ 1፥21-27 ጋር ያነጻጽሩ)። በዘመኑ መጨረሻ፣ "እውነትን ባለመውደድ ... በክፋት ደስ ይላቸው የነበሩ" (2ተሰ 2፥10:12) "እግዚአብሔር ... የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል" (2ተሰ 2፥11) ስለሚል ተመሳሳይ ፍርድ ይደርስባቸዋል። ይህ መታለል የሚመጣው፣ "በሰይጣን አሠራር ... እውነትን ያላመኑት ነገር ግን በክፋት ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ እንዲፈረድባቸው ነው" (2ተሰ 2፥9:12፣ እንዲሁም 2ተሰ 2፥10-12 እና ማብ ይመ)።

ሞቱ። [36]፴ሓይ ስትጠልቅም በሰራዊቱ መካከል፣ "እያንዳንዱ ሰው ወደ ቤቱ፣ እያንዳንዱም ወደ ሀገሩ ይሂድ!" የሚል ጩኸት አስተጋባ።

[37]ንጉሡ ስለ ሞተም ወደ ሰማርያ አምጥተውት እዚያው ተቀበረ። [38]ሠረገላውንም አመንዝሮች በታጠቡበት በሰማርያ ኩሬ እጠቡት፤ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ቃል ደሙን ውሾች ላሱት።

[39]ሌላው በአክዓብ ዘመነ መንግሥት የተፈጸመውና ያደረገው ሁሉ፣ ቤተ መንግሥቱን መሥራቱና በዝሆን ጥርስ መለበጡ እንዲሁም የሠራቸው የምሽግ ከተሞች በእስራ ኤል ነገሥታት ታሪክ የተጻፈ አይደለምን? [40]አክዓብም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ ልጁ አካዝያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ

22፥41-50 ተጓ ምብ — 2ዜና 20፥31—21፥1

[41]የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ በነገሠ በአራተኛው ዓመት የአሳ ልጅ ኢዮሣፍጥ በይሁዳ ነገሠ። [42]ኢዮሣፍጥ ሲነግሥ ዕድሜው ሠላሳ አምስት ዓመት ነበር፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ሃያ አምስት ዓመት ገዛ። እናቱ ዓዙባ ትባላለች፤ እርዕም የሺልሒ ልጅ ነበረች። [43]በአካሄዱም ሁሉ የአባቱን የአሳን መንገድ ተከተለ፤ ከዚያች ፈቀቅ አላለም፤ በእግዚአብሔርም ፊት መልካም የሆነውን አደረገ፤ ይሁን እንጂ በየኰረብታው ላይ ያሉትን የማምለኪያ ቦታዎች አላጠፋም፤ ሕዝቡም በዚያ መሥዋዕት ይሠዋ፣ ዕጣንም ያጥን ነበር። [44]እንዲሁም ኢዮሣፍጥ ከእስራኤል ንጉሥ ጋር በሰላም ኖረ።

[45]ሌላውም ኢዮሣፍጥ በዘመነ መንግሥቱ የፈጸመው፣ ያከናወነውና ያደረገው ጦርነት ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ የተጻፈ አይደለምን? [46]ከአባቱ ከአሳ ዘመን በኋላ እንኳ ተርፈው በጣያት ማምለኪያ ቦታዎች የነበሩትን የወንዶች ቅሬታዎች ከምድሪቱ አስወገደ። [47]በዚያን ጊዜ ኤዶም ንጉሥ አልነበራትም፤ የሚገዛት እንደራሴ ነበር።

[48]ኢዮሣፍጥ ወርቅ ለማምጣት ወደ ኦፊር የሚሄዱ የንግድ መርከቦች አሠርቶ ነበር፤ ይሁን እንጂ በዔጽዮንጋብር ስለ ተሰበሩ ከቶ ወደዚያ መሄድ አልቻሉም ነበር። [49]በዚያን ጊዜም የአክዓብ ልጅ አካዝያስ ኢዮሣፍጥን "ሰዎቼ ከሰዎችህ ጋር በመርከብ ይሂዱ" ሲል ጠይቆት ነበር፤ ኢዮሣፍጥ ግን እሺ አላለውም።

[50]ኢዮሣፍጥ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ እነርሱ በተቀበሩበት በአባቱ በዳዊት ከተማ ተቀበረ። ልጁ ኢዮራምም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

የእስራኤል ንጉሥ አካዝያስ

[51]የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በነገሠ በዐሥራ ሰባተኛው ዓመት የአክዓብ ልጅ አካዝያስ የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ በሰማርያ ነገሠ፤ እስራኤልንም ሁለት ዓመት ገዛ። [52]እርሱም የእባቱንና የእናቱን፣ እንዲሁም እስራኤልን ያሳተውን የናባጥን ልጅ የኢዮርብዓምን መንገድ በመከተሉ፣ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ክፉ ሥራ ሠራ። [53]አባቱ እንዳደረገው ሁሉ፣ እርሱም በአልን አመለከ፤ ሰገደለትም። በዚህም የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ለቍጣ አንዲነሣሣ አደረገ።

ˣ22፥38 ወይም፣ የጦር መሣሪያ ሞሚታጠብበት በሰማርያ ተብሎ መተርጐምም ይችላል
ʸ22፥48 ዕብራይስጡ የተርሴስ መርከቦች ይላል

22፥41 **የአሳ ልጅ ኢዮሣፍጥ፤** ስለ ኢዮሣፍጥ ማብራሪያውን ይመልከቱ። ዘመነ መንግሥት በይበልጥ ለማወቅ 15፥24 እና

22፥36 2ነገ14፥12
22፥38 1ነገ21፥19
22፥39 2ዜና9፥17፤ መዝ45፥8፤ አሞ3፥15
22፥43 1ነገ3፥2፤ 8፥61፤ 2ዜና17፥3
22፥46 ዘዳ23፥17
22፥47 1ነገ11፥14-18፤ 2ነገ3፥9፤ 8፥20
22፥48 ዘኍ33፥35፤ 1ነገ9፥26
22፥52 1ነገ15፥26
22፥53 መሳ2፥11፤ 1ነገ21፥25